# የማይደገም ጉዞ



በቢሊ ግራሃም
ትርጉም:- ቁምላቸው ፋንታሁን

# የማይደገም ጉዞ

## በማያስተማምነው ዓለም ውስጥ እንዴት በእምነት እንደሚኖር

በቢሊ. ግራሃም
ትርጉም:- ቁምላቸው ፋንታሁን

አር·ት·ኦ·ት·
በሬ.ሠ.ሠ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2002 ዓ.ም.

# የማይደገም ጉዞ

## ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
## The Journey
## ከሚለው መጽሐፍ ነው፡፡

By Billy Graham

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

**ማስታወሻ**

*የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደው (ከኃይሥት 1954) እና ከ1980 ትርጉም ነው፡፡*

**ራዕይ አሳታሚ**
**የፖ. ሳ. ቁ 2332**
**አዲስ አበባ**

RPTR-32 3M



## ማውጫ

### ክፍል አንድ
### ጉዞው ተጀመረ

1) እንኳን ጉዞውን ለመጀመር በቃችሁ /8
2) ታላቁ ስቃይ/18
3) ታላቁ ሰቀድ /29
4) ነገሮች እንዴት ተፋለሱ? /38
5) እንዳዲስ መጀመር እንችላለን? /49
6) አዲስ ጅማሬ /59
7) እርግጠኛ መሆን ይቻላል? /69
8) በትክክለኛ አቅጣጫ መጓዝ /80

### ክፍል ሁለት
### ለጉዞአችን ስንቅ መያዝ

9) ለረዥሙ ጉዞ መዘጋጀት /90
10) የማያበቃው ተጋድሎ /99
11) ለስተማማኝ መፈያችን /109
12) የፀሎት አስፈላጊነት /119
13) በአንድነት መጓዝ /129
14) ዘወትር የማይለየን አጋዣችን /140
15) የሰለት ስንቅ /151

### ክፍል ሦስት
### በመንገድ ላይ የሚደቀኑብን ተግዳሮቶች

16) የመንቀዋለል (የመንከራተት) ዝንባሌ /164
17) የውስጥ ጠላቶቻችንን ፊት ለፊት መግጠም /176
18) የሚያንበረክኩን ስሜቶች /187
19) ለጥፋት የሚዳርጉን ነገሮች /199

በየትኛውም ዕድሜ ብትገኙ ወይም ኑሮአችሁ እንዲህና እንዲያ ቢሆን፣ ይህ ጉዞ ምን እንደሚመስል እንድትመረምሩ ጥሪ አቀርብላችኋለሁ። ንባባችሁን እግዚአብሔር ይባርክላችሁ፣ እናንተም፣ እርግጠኛነት በሌለው ዓለም እንዴት በእምነት መኖር እንድትችሉ ያስተምራችሁ።



## ክፍል አንድ

# ጉዞው ተጀመረ

## ምን ዓይነት ጉዞ?

### ሕይወት ጉዞ ነው - ለናንተ ምን ዓይነት ጉዞ ሆኖባችኋል?

ምናልባት ጉዞአችሁ የልብ ስብራት፣ ሀዘንና ጭንቀት ያጠሉበት ሆኖ ይሆናል። የተለየ ነገር፣ የተሻለ ሕይወት ስትናፍቁ፣ በተቃራኒው ዘላቂ ደስታና ሰላም እየሸሹና እየራቁአችሁ ይሆናል። ወይም ምናልባት በወጣትነት ዕድሜ ሕይወታችሁ በደስታ፣ በመዝናናት በዝና ወይም በስኬት የተሞላ እንዲሆን ወስናችሁ ይሆናል እኒህ ነገሮች ለተወሰነ ጊዜ እርካታ ሰጥተዋችሁ ይሆናል። ውሎ ሲያድር ግን (ሐቁን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆናችሁ)፣ እነዚህ መስላቸት፣ ባዶነት፣ ለዚህ ነበር እንዴ ወደ ሚያሰኝ ራስን ወደ ማጥፋት መንገድ እንደሚመሩ ተገንዝባችኋል።

ወይም ደግሞ ራሳችሁን የህመም፣ የገንዘብ ችግር፣ ከምትወዱት የመለየት፣ ፍርሃት፣ የበደለኝነት ስሜት፣ ብቸኝነትና ተስፋ መቁረጥና የመሳሰሉ ችግሮች እንደመርግ ተጭነውባችሁ አግኝታችሁ ይሆናል። ማለቂያ የሌለው ተስፋ ቢስ ሸክም ሆኖባችኋል። ወይም ምናልባት ጉዞአችሁ ትክክለኛ ዓላማ ወይም አቅጣጫ ሳይኖረው፣ ከሞላ ጎደል የተቃና ዳሩ ግን ዓላማቢስ እና ባዶ ሊሆን ይችላል። ምናልባትም በእግዚአብሔር የምታምኑ፣ ታማኝ ክርስቲያን እንደሆናችሁ የምታስቡ ሆናችሁ ልባችሁ የዛለና ግራ የተጋባችሁ፣ ምንነታቸውን በአግባቡ ባልተገነዘባችሁና ማምለጫውን በማታውቁት ሸክም ጉብጣችሁ ይሆናል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ፣ ይህ በጭራሽ የማይታገሱት ኑሮ እየሆነባቸው አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ እንገታቸውን ለገመድ ይሰጣሉ። ምናልባት እናንተም "ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል?" በሚል ይህንኑ አሳዛኝ መንገድ ለመከተል እየተፈተናችሁ ይሆናል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኢዮብ የተናገረው ቃል ዛሬም እውነትነቱ አልተቀየረም፤ "ፍንጣሪው ከእሳቱ ላይ ሽቅብ እንደሚወረወር፣ ሰውም ለመከራ ይወለዳል" (ኢዮ 5፥7)። ኢዮብ ይህን ያወቀው በግሉ ደርሶበት ካየው ነበር፤ ሁሉም ሰው ሲደርስበት ይህን መራር እውነት ያውቀዋል።





## የአሁኑ ሕይወቴ ሊለወጥ ይችላል?

ግን ጉዞአችን ሁልጊዜ በዚህ መቀጠል አለበት? በሕይወት ጐዳና ስንጓዝ ከአንድ ስርጓጉጥ ወደ ሌላ እያሉ መውገርገር የማናመልጠው ዕጣ ፈንታ ይሆን?

በውስጥ እኛነታችን ይህ ዓይነቱ ሕይወት ልንኖረው የታቀደልን እንዳልሆነ ስለሚታወቀን፣ ልባችን የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ይቃትታል። እስካሁን ያለትርፍና ምቾት ስናዘግምበት ከነበረው የተለየ መንገድ መኖር እንዳለበት አንዳች ጭልታ (የልብ ዕውቀት) ይነግረናል። ታዲያ ለምንድነው ይህን የበመረ ሕይወት ያገኙ የሚመስሉ ሰዎች በጣም ጥቂት የሆኑት? ለእኛ ለምን አልጨበጥ አለን? በሆነ መንገድ ሕይወቴን መለወጥ እችላለሁ?

ለመጨረሻው ጥያቄ መልሱ አዎን ነው! ማንነታችሁ ወይም የእስካሁኑ ሕይወታችሁ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ ከዚህ በኋላ ያለው ጉዞአችሁ የተለየ መሆን ይችላል። በእግዚአብሔር እርዳታ እንዳዲስ መጀመር ትችላላችሁ። እርሱን ተጠግታችሁ የተጋረጡ ችግሮቻችሁን በመጋፈጥ መፍትሔ ልታገኙላቸው ትችላላችሁ፣ ከእንግዲህ እግራችሁን ከሚከዱ ረግረጎችና ዙሪያ ጥምጥም መንገዶች መራቅና መሸሽ ትችላላችሁ። ከዚህም በላይ በዓለም ላይ አንዳች የለውጥ አሻራ ልታሳርፉ ትችላላችሁ። በሕይወቴ የሆነ ነገር ነው፤ ይህን ለውጥ ያዩና ያጣጣሙ ለፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች በሕይወት ዘመኔ ገጥመውኛል። የእናንተም ሕይወት እንዲህ ሊለወጥ ይችላል።

ሕይወት ጉዞ ናት፣ ግን መልካም ጉዞ ልትሆንልን የምትችለው እንዴት ነው? የምታረካና የግለጋሎ ግፊት ብቻ የማትሆነው፣ ከዚህም አልፎ የተፈጠርንበትን ዓላማም ማከናወን የምትችለው እንዴት ነው? ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ነው፣ በቀጣዮቹ ምዕራፎች ሕይወት ለተባለው ለዚህ አስደሳች ጉዞ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከኔ ጋር እንድትመረምሩ እጋብዛችኋለሁ።

ይህን ጉዞ ለማድረግ የተሰጣችሁ ዕድል አንዴ ብቻ ነው። ታዲያ የሚያስፈልገውን ሁሉ መሥዋዕት ከፍላችሁ ያማረ ለማድረግ መጣሩ የሚበጅ አይመስላችሁም?

## መስኮታዊው ቀጠር

ከመጀመራችን በፊት ግን የሕይወት ጉዞን አስመልክተን ሦስት ታላላቅ እውነቶችን መገንዘብ ያስፈልገናል፡፡ እነዚህ እውነቶች ልክ እንደ ትያትር መድረክ መሠረታዊ ትዕይንቱ የሚከወንባቸው ናቸው፡፡

*የመጀመሪያው እውነት በጣም ቀላል ነው - ግን ደግሞ ጥልቅ ነው፤ በሕይወት ጉዳና ላይ ያስቀመጣችሁ እግዚአብሔር ነው፡፡*

እዚህ ያላችሁት በአጋጣሚ አይደለም፣ እዚህ ያላችሁት እግዚአብሔር አስቦ ስላስቀመጣችሁ ነው፡፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፣ እግዚአብሔር ስለእናንተ ያውቅ ነበር፤ ወደምድር ሲያመጣችሁ ዕቅድ ነበረው፡፡ *ከዘላለም ዓለም ጀምሮ የርሱ እቅድ አካል ነበራችሁ ወደ ምድር መምጣታችሁ የእናንተ ምርጫ አልነበረም፤ ይህን ወስኖ ወደምድር ያመጣችሁ እግዚአብሔር ነው፡፡* ሁሉን ነገር እናንተን ጨምሮ የፈጠረ እርሱ ነው፡፡ ተጓዦቹ እናንተ ብትሆኑም ይህን ያዘጋጀላችሁ ግን እግዚአብሔር ነው፡፡ ከቶም ቢሆን ልትዘነጉ የማይገባው በጉዞ ላይ ያደረጋችሁ እግዚአብሔር መሆኑን ነው፡፡

በመላው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ይህ እውነት የሰዎችን ሕይወት እንደለወጠ ሁሉ የናንተንም ሕይወት ይለውጣል፡፡ እግዚአብሔር ኤርምያስን፣ "በማህጸን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ" (ኤር 1፥5) ሲለው ኤርምያስ ነቢይ እንዲሆንለት ያቀረበለትን ጥሪ ተቀበለ፡፡ ብላቴናው እረኛ ዳዊትም ይህን እውነት ተገንዝቧል፣ "ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣ ገና አንዳቸው ወደመኖር ሳይመጡ፣ በመጽሐፍ ተመዝገቡ" (መዝ 139፥6)፡፡ ዳዊት በትረ ሥልጣን ሲረከብ፣ የአይሁድን ሕዝብ እጅግ ከፍ ላለ ክብር አቀዳጃቸው፡፡

እኔና እናንተ በዚህ የተገኘነው በአጋጣሚ አይደለም፤ እግዚአብሔር ሕይወት በሚባል መንገድ ላይ አስቀመጠን፡፡ የተገኘ ነው ከእርሱ ነው፤ የላቀ ደስታ የምናገኘው ራሳችንን ለርሱ በመስጠትና ወደርሱ እስክንመለስ በየዕለቱ ከእርሱ ጋር በመመላለስ ነው፡፡

## ብቻችንን አይደለንም

*ሁለተኛውንም እውነት መገንዘብ ይኖርብናል፣ እግዚአብሔር በዚህ ጉዞ ላይ ከኛ ጋር ሊሆን ይወዳል፡፡*





እስቲ ለአፍታ ያህል ስለዚህ ነገር እናስብ፡፡ እግዚአብሔር እኛን ፈጥሮ ካበቃ በኋላ ሊተወንና ዞር ብሎ ሳያየን ይችል ነበር፡፡ እንዲያውም ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ማድረግ እንደነበረበት ያምናሉ፣ ወይም ቢያንስ አካሄዳቸው የዚህ ዓይነት እምነት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ለእነርሱ ጉዳይ ቁብ ስለማይሰጥ ለምን እርሱን ጉዳዬ ይላሉ? በማለት ያስባሉ፡፡ ለነርሱ እግዚአብሔር ሩቅ፣ የማይደረስበትና በየዕለቱ ለሚገጥሙአቸው ችግሮችና ውሳኔዎች ደንታ የሌለው ሆኖባቸዋል፡፡

*ይህ ግን እውነት አይደለም!* እግዚአብሔር እኛን በዚህ ጉዳና ላይ ከማኖሩም ባሻገር ብንፈቅድለት የጉዞአችን አጋር ለመሆን ይሻል፡፡ እርሱ ከእኛ ጋር ስለሆነ ብቻችንን አይደለንም፡፡ መዝሙረኛው፣ "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፤ አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ" (መዝ 139፥7-8) በማለት ጠይቋል፡፡

ይህን እውነት ብንረዳ ተስፋን ይሰጠናል፤ ይህም ተስፋ እግዚአብሔር ለእኛ ግድ ስለሚለውና ሊረዳን ስለሚወድ ሕይወታችን ሊለወጥ እንደሚችል የሚያበስር ነው፡፡ እምነታችንን በርሱ ብናኖር፣ በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እርሱ አይተወንም፡፡ ሙሴ እንዲህ ሲል ያውጃል፡፡ "እግዚአብሔር ራሱ በፊትህ ይሄዳል፣ ከአንተም ጋር ይሆናል፤ ፈጽሞ አይለይህም፤ አይተውህም፤" (ዘዳ 31፥8)፡፡ "እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ 28፥20)፡፡ በዘመናት ሁሉ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የእነዚህን ቃላት እውነትነት በሕይወታቸው ተገንዝበዋል፤ ይህ በእናንተም ሕይወት ሊሆን ይችላል፡፡

## አዲስ ጉዳና

*የሕይወት ጉዞን በተመለከተ ልንገነዘበው የሚያሻን ሦስተኛ እውነት አለ፡፡ እግዚአብሔር እኛን በሕይወት ጉዳና ከማኖሩ፣ የጉዞአችን አጋር ከመሆኑ ባሻገርም፣ የአዲስ ጉዞ ጥሪ ያቀርብልናል፡፡* በሌላ አባባል፣ *እግዚአብሔር አዲስ ማለትም የእምነትና በእርሱ የመታመን መንገድ እንድንጀምር እየጠራን ነው፡፡*

እስቲ እንዲህ ብለን እናስብ፡፡ ከዚህ ቀደም ሄዳችሁ ወደማታውቁበት ስፍራ ለመሄድ በማቀድ፣ በጫካ ውስጥ

እየተራመዳችሁ ነው ፤ ከአንድ ወይም ከሁለት ሰዓት በኋላም መንታ መንገድ ላይ ደረሳችሁ እንበል:: በዚህ ወቅት አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት መንገዶች ከፊታችሁ ተዘርግተዋል:: ትክክለኛው መንገድ የትኛው ይሆን? ሁለቱም ወደሆነ መድረሻ ማምራታቸው ግልጽ ነው፤ ግን የት? ወዳሰባችሁት ግብ የሚያደርሳችሁ የትኛው ነው?

ቀረብ ብላችሁ ስትመለከቱ፣ አንደኛው መንገድ ሰፊና አመቺ ሲሆን በዛ ያሉ ሰዎች ሲሄዱበት ይታያል:: ይህን ስታዩ በዚህ መንገድ ለመጓዝ ልባችሁ ተፈተነ፤ በርግጥም በርካታ ሰዎች የሚጓዙበት ከሆነ፤ ትክክለኛው መንገድ ሳይሆን አይቀርም ብላችሁ አሰባችሁ::

ሌላ ተጓዥ በድንገት ከኋላችሁ መጣ እንበል:: ምን ታደርጋላችሁ? እንደባለአእምሮ ሰው የምታደርጉት ካሰባችሁበት የሚያደርሳችሁ የትኛው መንገድ እንደሆነ መጠየቅ ነው:: እርሱም ያለምንም ማመንታት መተላለፊያው ጠባብ ቢሆንና ጥቂቶች ብቻ የሚጓዙበት ቢሆንም፣ ሁለተኛውን መንገድ ይዛችሁ እንድትሄዱ ይገልጽላችኋል:: ካሰባችሁበት የሚያደርሳችሁ ይኸኛው መንገድ ብቻ እንደሆነ ይነግራችኋል:: እናንተም እውነት አልመሰል ብሏችሁ እርግጠኛ ነህ? ስትሉ ትጠይቁታላችሁ:: እርሱም እንዴታ መንገዱን ያበጀሁት እኔው ራሴ ነኝ ይላችኋል:: እኔ ራሴ በዚህ መንገድ እየተጓዝኩ ነውና አቅጣጫ እንዳትስቱም አብሬአችሁ እጓዛለሁ ይላችኋል::

በዚህ ጊዜ የትኛውን መንገድ ትመርጣላችሁ? ሁለተኛውን እንደምትሉ ጥርጥር የለውም:: ጉዞአችሁን አላቋረጣችሁም፤ አሁን ግን በተለየ ማለትም በትክክለኛ መንገድ ላይ ናችሁ::

እግዚአብሔር እንድታደርጉ፣ እየነገራችሁ ያለውም ይህንኑ ነው:: *ትራመዱበት የነበረውን ትታችሁ አዲስ ጐዳና እንድትመርጡ ነው::* ይህ መንገድ እርሱ ያዘጋጀላችሁ ነው፤ ወደ እውነተኛ ሕይወት የሚመራን ይኸው መንገድ እንደሆነ ያረጋግጥልናል:: አሁንም መንገድ ላይ ነን፤ ብዙ ሰዎች ባይራመዱበትም ትክክለኛውን መንገድ ይዘን እየተጓዝን ነው:: ኢየሱስ እንዲህ ሲል ይነግረናል:: "በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ በሩም ሰፊ ነውና፣ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ:: ወደሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፤ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው" (ማቴ 7፥13-14)::





## ይኸኛውን መንገድ መከተል ያለብን ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር የቀድሞውን መንገድ ትታችሁ ከእርሱ ጋር በአዲስ መንገድ እንድትጓዙ ጥሪ እያቀረበላችሁ ነው:: እንደእውነቱ ከሆነ መጋበዝ ብቻ አይደለም፣ እየገፋፋችሁም ነው! ግን ይህን ማድረግ የሚኖርብን ለምን ይሆን? የለመድነው መንገድ የፈለግነውን ሰላምና እረፍት ባያስገኝልንም ለምን እንቀጥልበትም? አዲሱ መንገድ የት እንደሚያደርሰን ምን አውቀን ነው የምንከተለው? ልትሉ ትችላላችሁ::

የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ደፍራችሁ ውሳኔ መውሰድ ለምን እንደሚሻል ሦስት ምክንያቶች ልስጣችሁ::

*በመጀመሪያ፣ መንገዳችሁ (አሮጌው) የምትጠብቋቸውንና ተስፋ የምታደርጉአቸውን ነገሮች አይሰጣችሁም*

እስኪ ለአፍታ ቆም በሉና በዙሪያችሁ ካሉ ሰዎች ምን ያህሎች በርግጥ ደስተኞች እንደሆኑ ተመልከቱ፤ ላይ ላዩን ሲታዩ እርካታና እረፍት የሰፈነባቸው ይመስላሉ፤ ግን እውነት ልባቸው ተደላድሎ አርፏል? ይህ ደስታቸው ዘላቂ ነውን? እዱኛ ስትሸሻቸው ደስታው አብሮአቸው ይቆያል?

አሮጌው መንገዳችሁ ሰላምና ዋስትና በዚህ አለ እያለ ያባብላችኋል፤ ፍጻሜው ግን ሽብር፣ ፍርሃት፣ ራስምታት፣ መሰላቸትና ሐዘን ነው:: አሮጌው መንገድ እርካታን ያውጅላችኋል እንደ እውነቱ ግን በሥጋ ምኞት፣ በስስት፣ በንዴትና በመራርነት እስራት ተብትቦ ያስቀራችኋል:: ኢየሱስ በምሳሌ እንደነገረን እንደ ራስ ወዳዱ ባለጠጋ፣ አሮጌው መንገድ፣ "ለነፍሳችን፣ ዕረፊ፣ ብዪ ጠጪ፣ ደስም ይበልሽ" እያለ ያታልላታል:: እግዚአብሔር ግን "አንተ ሞኝ! ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሲወስዱ ይፈልጓታል" (ሉቃ 12፥19-20) ይለናል:: ያ ሰው የመረጠው የተሳሳተ መንገድ ነበርና ፍጻሜውም አላማረም::

አሮጌው መንገድ የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን በመንገር ያባብላችኋል፤ እውነታው ግን ሌላ ነው፣ ሲከፍቱት ተልባ የሚያሰኝ:: ታዲያ መንገዱን መለወጡ አይሻልም?

## የተገባ ቃል ተፈፀመ

*ለቀሪው ጉዞአችሁ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመምረጥ የሚያበቃ ሁለተኛ ምክንያት አለ፤ የእግዚአብሔር መንገድ ሁልጊዜ የገባልንን ቃል ይፈጽምልናል።*

ምናልባት በዚሁ "የእግዚአብሔር መንገድ" ባልነው ላይ እየተራመዱ ያሉ ሰዎችን ታውቁ ይሆናል (እናንተም ራሳችሁ በዚሁ መንገድ እየተጓዛችሁ ይሆናል)። እነዚህ ሰዎች ፍጹማን ሆነው አላገኛችኋቸውም፤ እንዲያውም የማትወዱት ክፉኛ የሚጐረብጥ ባህርይ ይኖራቸው ይሆናል። እንዲህም ሆኖ ግን ለየት የሚያደርግ ነገር እንዳላቸውና እነርሱ ኖሮአቸው እናንተ የጐደላችሁ ነገር እንዳለ እንዲሰማችሁ አድርገዋል። ነገሮች ሲመሳቀሱባቸው እንኳን ለመግለጽ የሚያዳግት የውስጥ ሰላም በላያቸው ሲሰፍን ተመልክታችኋል። ሌሎች ሰዎች ጉዳትና ችግር ላይ ሲሆኑ፣ እነዚህ ለራሳቸው ሳይሳሱ በርህራሄ የሚቻላቸውን አድርገዋል። ለምን ይሆን? ምክንያቱ ሌላ አይደለም፤ በእግዚአብሔር መንገድ የመጓዝን ምስጢር ተገንዝበዋል።

እዚህ ላይ በትክክል እንድትረዱኝ እፈልጋለሁ፤ መንገዱ ሁልጊዜ ቀናና እልጋ ባልጋ ነው አላልኩም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ በጤናና በብልፅግና እንደሚባርከን የሚሰብኩ ሰዎች የኢየሱስን ቃል ዘንግተዋል፡- "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ" (ዮሐ 16፥33)። ክርስቲያን መሆናችን መከራና ሐዘንን አያስቀርልንም። ግን በምንም ሁኔታ ውስጥ "ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን ያሳርፈናል" (ፊሊጵ 4፥7)።

## ከቤት የሚያደርሰን መንገድ

*የእግዚአብሔርን መንገድ መምረጥን የአስተዋይ ውሳኔ የሚያደርገው ሌላው ሦስተኛ ምክንያት ቤታችን የሚያደርሰን መንገድ መሆኑ ነው*

በጉዞ ላይ በሆንኩ ጊዜ ሁሉ፣ ሁልጊዜ የሚታሰበኝ ቤት የምደርስበት ጊዜ ነው። በሥራ ብጠመድም እንኳን ከምኔው ቤት በደረስኩና ከቤተሰቤ ጋር መሆንን እናፍቃለሁ። ቤት የሰላም፣ የዋስትናና የእረፍት ቦታ ነው፤ ቤቴ የእኔ የምለው መጠለያዬ ነው። እኔና የአገልግሎት አጋሮቼ ለስድስት ወራት አውስትራሊያ በቆየን ጊዜ ሁላችንም ቤተሰባችንን ጥለን ነበር የሄድነው። ጊዜው ሲገባደድና የቤተሰቦቻችን ናፍቆት ሲበረታብን፣ ወሬያችን ሁሉ አገር





ቤት ስለተውናቸው ቤተሰቦች ሆነ። ጌታን እያገለገልን እንደሆነ እውቀናል፣ የወንጌል መልእክተኞችና ወታደሮች ከዚህ ለረዘመ ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ርቀው መቆየት ግድ እንደሚሆንባቸውም እናውቃለን። ነገር ግን ይህ በናፍቆት ሲቃ ከመናወዝ አላዳነንም።

ምድራዊ ቤት እንዲህ ካደረገ፣ የሰማያዊ ቤታችን ናፍቆት ምንኛ የላቀ ይሆን! እኔና እናንተ በዚህ ምድር ሰተወሰኑ አሥርታት ዓመታት ልንኖር የተፈጥርን ሰዎች አይደለንም፤ *የተፈጠርነው ለዘላለም ልንኖር ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ዓለም በእፎይታ የምንደላደልበት የመጨረሻ ቤት እንዳይደለ ይነግረናል፤ ይልቁንም፣ በዚህ ምድር ስንኖር መጻተኞችና እንግዶች ነን (ዕብ 11፥13)። እውነተኛ ቤታችን መንግሥተ ሰማያት ነው፤ የእግዚአብሔር መንገድም የሚያደርሰን ወደዚሁ ነው።

## ስለዚህ የቱን መንገድ ልከተል?

እኔና እናንተ መንገደኞች ነን፤ መንገድ የጀመርነው ገና ከማህጸን እንደወጣን ነው፤ ጉዞው የሚያበቃው የምድር ኑሮአችን ሲያበቃ ነው። ታዲያ ጉዞው ለእናንተ ምን መልክ ይኖረው ይሆን?

የዚህ ጥያቄ መልስ በእጃችሁ ነው። ያለፈውን መለወጥ አትችሉም፣ መጻኢውን (መጪውን) ጊዜ ግን በእግዚአብሔር እርዳታ መለወጥ ትችላላችሁ። እርሱ ስለእናንተ ያውቃል፤ ብርታታችሁን ቢሆን ድካማችሁን፣ ውድቀታችሁና የልብ ስብራታችሁ ሁሉ በፊቱ የታወቀ ነው። ነገር ግን እርሱ ያለፈው ሁኔታችሁ ተብትቦ እንዲያስቀራችሁ አይፈልግም። ይልቁንም፣ *ከአሮጌው መንገድ እሥራት አርነት አውጥቶ አግራችሁን በአዲሱ በርሱ ጐዳና ላይ ሊያቀና ይሻል።*

ኢየሱስ፣ "እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጣሁ" (ዮሐ 10፥10) ይላል። ሕይወታችሁን ለጌታ አደራ በመስጠትና በየዕለቱ ከርሱ ጋር በመራመድ የሕይወትን ጉዞ እንዳዲስ መጀመር ትችላላችሁ። ይህ መጽሐፍ የሚናገረው ይኸንኑ ነው፤ እኔም የምጋብዛችሁ ይህንኑ እንድታደርጉ ነው።

## እንግዲህ ጉዞው ይጀመር!

ነው:: ከእኛ እጅጉን ይልቃል:: እርሱ ወሰን አልባ፣ እኛ ግን ውሱን ነን:: በምልዐት ልናየው የምንችለው በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው::

ልጅ ሳለሁ አንዳንድ ጊዜ አባቴ ከከተማችን አቅራቢያ ወዳሉ የብሉይ ሪጅ ተራሮች በመኪና ይወስደኝ ነበር:: ተራሮቹን በጭጋግ ተሸፍነው ከሩቅ ስመለከታቸው ትንሽ ሲመስሉ፣ እኛ መኪና ውስጥ ያለነው ተመልካቾች ግዙፍ መስለን እንታይ ነበር:: ወደ ተራሮቹ እየቀረብን ስንመጣ ግን፣ እነርሱ እየገዘፉ እኛ እየኮሰስን መጣን::

ይህ ስለእግዚአብሔር ከምናስበው ጋር ይመሳሰላል:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከኛ ትንሽ ከፍ ቢል እንጂ ያው እንደኛው የሆነ ይመስለናል:: እውነታው ግን ይህ አይደለም:: እርሱ አምላክ እኛ ግን ሰዎች ነን:: እግዚአብሔር የቀድሞ እስራኤላውያንን፣ "እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና፣ በመካከልህም ቅዱሱ ነኝና" (ሆሴ 11፥9) በማለት አሳስቦአቸዋል::

ትንሽነታችንን የምንረዳው የእርሱን ግዙፍነት ስንገነዘብ ነው::

ይህ ማለት ግን ስለእግዚአብሔር ምንም ልንረዳ አንችልም ማለት አይደለም:: እራሱ ራሱን ስለገለጠልን ምን እንደሚመስል መረዳት እንችላለን:: እኛ እንድንረዳቸው የሚፈልጋቸውን ዐራት አስፈላጊ እውነቶች ጠቅለል አድርጌ ለማቅረብ ልሞክር::

## እግዚአብሔር መንፈስ ነው

*እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድንገነዘብ የሚሻው የመጀመሪያው እውነት እርሱ መንፈስ መሆኑን ነው::* ኢየሱስ ሲካር ከተባለው መንደር ውጪ ላገኛት ሰማርያዊት ሴት "እግዚአብሔር መንፈስ" እንደሆነ ነግሯታል (ዮሐ 4፥24):: እግዚአብሔር የአቶሞችና የሞሎኪዩሎች ውሁድ አይደለም፤ የፍጥረት አካልም አይደለም:: በፍጹም ልዩ በሆነ ክልል ማለትም በመንፈስ ክልል የሚኖር ህላዌ ነው::

መንፈስ የሚለውን ቃል ስትሰሙ ምን ይታሰባችኋል? እንደ ጉም የሚንቀሳቀስ አንድ ዓይነት የማይጨበጥ ነገር ይመስላችኋል? ወይስ በአስፈሪ ፊልሞች እንደምታዩት አይነት ሽብር እንደ ሚነዙ ምስሎች ይቀረጽባችኋል? መንፈስ የቁሳዊ አካል ተቃራኒ ስለሆነ





እንደዚያ ካለባችሁ ተሳስታችኋል፤:: ኢየሱስ እንደተናገረው "መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና" (ሉቃ 24፥39)::

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፣ በጊዜና በቦታ አይወሰንም:: በአንድ ጊዜ በየስፍራው ሊገኝ ይችላል:: በትልቁ ጋላክሲ (የከዋክብት ክምችት) እንደዚሁም በጥቃቅን አቶሞች መካከል ሊገኝ ይችላል:: ከቁሳዊው ዓለም በእጅጉ የላቀ ነው (ለዚህም ነው እኛ ጣዖታትን ወይም ተፈጥሮን ማምለክ የሌለብን):: እርሱ መንፈስ ስለሆነ፣ በምንም መንገድ ሊገደብ አይችልም:: እግዚአብሔርን ለመወሰን እየሞከራችሁ ካላችሁ፣ የምነግራችሁ ይህን እንዳታደርጉ ነው! በአንድ ቦታ ልትወስኑት ወይም በአእምሮአችሁ ስለ እርሱ ምናባዊ ስዕል ለመሳል አትሞክሩ:: በኀይሉ ወይም በታላቅነቱ ወይም በፍቅሩ ወይም በጥበቡ ላይ ወሰን አታኑሩ:: እግዚአብሔርን መወሰን ማለት ትንሽ ኩሬን ከውቂያኖስ እኩል ማድረግ ማለት ነው::

## እግዚአብሔር ሰብእና አለው

*እግዚአብሔር መንፈስ ብቻ አይደለም፣ ሰብእናም አለው፣ ይህም ማለት እንደ እኛ ሰብአዊነት አለው ማለትነው::* እንደ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርም ስሜት፣ ሀሳብ፣ ምኞትና ውሳኔ አለው:: ሰው ከመሰሎቹ ጋር ግንኙነት እንደሚመሠርት ሁሉ፣ እግዚአብሔርም እንደዚሁ ግንኙነት ያደርጋል:: እንደሰው ሁሉ፣ እግዚአብሔርም እስቦ አንድ ነገር ያደርጋል:: እግዚአብሔር ስሜት አለው፤ እግዚአብሔር ያስባል፤ የሌሎች ስቃይ ይሰማዋል፤ እግዚአብሔር ይቅር ይላል፤ እግዚአብሔር ተስፋ ያደርጋል፤ እግዚአብሔር ይወስናል፣ እግዚአብሔር ያከናውናል፤ እግዚአብሔር ይፈርዳል:: ይህን ሁሉ የሚያደርገው ሰብእና ስላለው ነው:: ባይሆን ኖሮ፣ ለምን ወደ እርሱ እንጸልያለን ወይም እናመልከዋለን? እግዚአብሔር ሰብእና የሌለው ኀይል አይደለም፣ እርሱ ሰብዕና ያለው ያውም በምናብ ሊታይ የማይችል እጅግ ፍጹም ሰብእ ነው::

በእርግጥ በእኛና በእግዚአብሔር ሰብእና መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፤ እርሱ ፍጹም ሲሆን እኛ ግን አይደለንም:: እንደ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ ጥላቻ፣ ቅናትና ትዕቢት የመሳሰሉ ስሜቶች እኛን ይገዙናል:: ከዚያም አልፎ የኛ ሰብዕና የታወከ ወይም የገዛ ራሱን ጥፋት የሚያፈጥን ሰብእና ሊሆን ይችላል::

ካልፈሩ በስተቀር፣ ይህንኑ የሚሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች መኖራቸው የማይጠረጠር ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ይህ የጉደሎነት ስሜት በአጋጣሚ የመጣ አይደለም፤ *ያለ እግዚአብሔር ጉደሎ ነን፡* እርሱን ከሕይወታችን ስናስወጣው፣ በነፍሳችን ባዶነትና እግዚአብሔር ብቻ ሊሞላው የሚችል የውስጥ ረሃብ ይነግሳል፡፡ እግዚአብሔርን ችላ እስካልን ድረስ፣ ይህ ባዶነት እኛው ዘንድ መሰንበቱ ግድ ነው፡፡ ዘላቂ ሰላምና ደስታ ለማግኘት የምናደርገው ጥረትም ፍሬቢስ ሆኖ ይቀራል፡፡ ከበርካታ ምዕተዓመታት በፊት ቅዱስ አውግስጦስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡፡ "አቤቱ ጌታ ሆይ፤ አንተ ለራስህ ፈጥረኸናልና ልባችን በአንተ እረፍት እስኪያገኝ ድረስ እንደተቅበዘበዘ ይኖራል፡፡"

ነገሩ ከጥንት እንደዚህ አልነበረም፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሲፈጥር፣ ይህ የውስጥ መቅበዝበዝና ባዶነት አልነበረም፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ ሰፋ ባለ መንገድ እንደ ምንመለከተው፣ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር ሲፈጥራቸው ሙሉ በሙሉ ደስተኞች ነበሩ፣ ከራሳቸው፣ ከዓለምና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ነበሩ፡፡ እርስ በርስ የነበራቸው ግንኙነት ፍጹም ነበር፤ ግንኙነታቸው ቅንጣት የራስ ወዳድነት ወይም የጠብ አዝማሚያ አልነበረውም፡፡ በዙሪያቸው ካለው ዓለም ጋር የነበራቸው ግንኙነትም ፍጹምና ሰላም የማጣት፣ የፍርሃት ወይም የሞት ስጋት የማይደርስበት ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነትም እንደዚሁ በጥፋተኝነት ወይም ባለማመን ያልተበከለ ፍጹም ነበር፡፡

የዚህ ዓይነቱ ዓለም ምንኛ ውብ እንደሆነ ሊታሰባችሁ ይችላል? ኃጢአት፣ ሐዘን፣ ቅያሜ፣ ደንታቢስነት፣ የራሱ ጉዳይ የሚባሉ ነገሮች የሌለበት ዓለም ነበር፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራላቸው ዓለም አንዳችም ህፀፅ አልነበረውም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ "እነሆም እጅግ መልካም ነበር" (ዘፍ 1፥31)፡፡

አዳምና ሔዋን ከእርስ በርሳቸውና ከእግዚአብሔር ጋር በፍጹም መስማማት የሚኖሩ ነበሩ፡፡ በመግቦቱ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላላቸው ነበር፤ እነርሱም ሙሉ በሙሉና ያለማመንታት ይወዱት ነበር፡፡ ዛሬ ዓለምና የኛም ሕይወት የሚገኙበት ሁኔታ ከዚህ በጣም የራቀ ስለሆነ በምን ዓይነት ዓለም እንደነበረ እንኳን በምናብ መሳል አይቻለንም፡፡





## በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ

ሕይወታቸው ፍጹም ሊሆን የቻለው እንዴት ነበር? ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ *እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን አስቦ የፈጠራቸው ለዘላለም ወዳጆቹ እንዲሆኑት ነበር፡፡* ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ኅብረት ለአፍታም የማይቋረጥ እውነታ ነበር፡፡

አዳምና ሔዋን እንዲሁ ሥጋ፤ ነፍስ ፍጥረታት ወይም ላቅ ያለ ደረጃ ያላቸው እንስሳት አልነበሩም፡፡ እጅግ የላቁ ፍጡራን ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርን እንዲያውቁና ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ ከሚያስችላቸው መንፈስ ወይም ነፍስ ጋር የተፈጠሩ መንፈሳውያን ህልዋን ነበሩ፡፡ እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ ይነግረናል፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር የራሱን ባህርይ አካፈላቸው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ "እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" (ዘፍ 1፥27)፡፡ እግዚአብሔር የተለየ መንፈሳዊ ባህርይ ሰጣቸው፡፡

የኛ ጉዳይም እንዲህ ነው፡፡ እንደ አዳምና ሔዋን፣ ሥጋና አእምሮ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ወይም ነፍስ ብሎ የሚጠራው ጭምር አለን፡፡ ይህን የሰጣችሁ፣ የራሱን ባህሪይ በእናንተ ያኖረ፣ እግዚአብሔር ነው፡፡ ነፍስ ያለን በመሆናችን ከሌሎች ሕይወት ካላቸው ፍጡራን ሁሉ የተለየን ነን፤ ምሉዕ ሰው የሚያደርገን ይህ ነው፡፡

## የነፍስ ዋጋ

ነፍሳችሁ ምን ያህል ክቡር እንደሆነች ታውቃላችሁ? ኢየሱስ ነፍሳችን በዓለም ካለ ከማንኛውም ነገር የላቀ ዋጋ እንዳላት ነግሮናል፡፡ ሥጋችሁ ይሞታል፤ ነፍሳችሁ ግን ለዘላለም ኗሪ ናት፡፡ ኢየሱስ ለእኛ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ነፍሳችን በፊቱ የከበረች በመሆኗ ነው፡፡ ነፍስ ዋጋ እንደማይተመንላት፣ በሚከተለው መንገድ ይነግረናል፤ "ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ለነፍሱ ምትክ ሊከፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድነው?" (ማቴ 16፥26)፡፡

መንፈሳዊ ባህርይ እንዳለን በመዘንጋት ራሳችንን ከፍ ያሉ እንስሳት አድርገን ከቆጠርን፣ እንደነሱ መሆን እንጀምራለን፡፡ በተቃራኒ በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠርንና እርሱ የሰጠን

ነፍስ እንዳለን ከተገነዘብን ግብራችን እንደ እንስሶች አይሆንም:: ከሌሎች ፍጥረታት ለይቶ ሰው የሚያደርገን ነፍስ ያለን መሆኑ ነው፤ ለሰው ክብርና ዋጋ የሚያላብሰው ነፍሱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- "ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርንና የምገስን ዘውድ አቀዳጀኸው" (መዝ 8÷5)::

የሰው ሕይወት በፍፁም መንቋሸሽ፣ ወይም መረገጥ፣ ወይም እንዲሁ እንደዋዛ መጥፋት የሌለበት ለዚህ ነው፤ ሰው ትልቅ ይሁን ትንሽ በሥላሴ አምሳል ስለተፈጠረ ክቡር ነው::

ከሁሉም በላይ ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ የሚችለው የእኛነታችን አካል ነው:: ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔርን የማወቅና ከእርሱ ጋር ለዘላለም ወዳጅነት የመመሥረት ችሎታ አለን:: እግዚአብሔር ሲፈጥረን በምድር እንድንኖር ብቻ ሳይሆን በሰማይ ንፍቅም መኖር እንድንችል አድርጐ ነው:: ታላቁ አቃጅ ያበጀው ታላቅ የእጅ ሥራ ይህ ነው::

## በፍቅሩ ፈጠረን

አዳምና ሔዋን፣ በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠራቸው፣ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ልዩ ነበሩ:: ይሁንና የፈጠራቸው ለምን ነበር? በመጀመሪያ ደረጃ የሰውን ዘር እንዲፈጥር ያነሣሣው ምን ነበር? እናም አንተን የፈጠረህ ለምን ነበር? መልሱ በአንድ ቃል ሊጠቃለል ይችላል:- "በፍቅር":: እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳልና መልክ ፈጥሮ በተዋበ ገነት ውስጥ እንዲያስቀምጠው ያደረገው ፍቅር ነው::

ቀደም ሲል እንደ ተመለከትነው፣ እግዚአብሔር በወጉ ሊታወቅ የማይችል ስብዕና የሌለው ኃይል ሳይሆን ሰብዕ ነው፤ ስብዕና አለው:: ምናልባትም ከስብዕናው ባህርያት ልዩ የሚያደርገው ፍቅሩ ነው:: እርሱ ፍጹም ስለሆነ፣ ፍቅሩም ፍጹም ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ "የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው" (መዝ 18÷30):: ሰዋዊ ፍቅር ኢ-ፍጹምና ተለዋዋጭ ነው፤ የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ፍጹም በመሆኑ የሚለወጥ ወይም የሚቀንስ አይደለም::

በዚህ ምድር እያለን፣ ስለእግዚአብሔር ፍቅር ሙሉ በሙሉ ልንረዳው የማንችል መሆኑ እሙን ነው:: ለምሳሌ ሰውን የሚወድ አምላክ እንዴት ክፉን ነገር ሊፈጥር ቻለ? ይህ አስቸጋሪ ጥያቄ ኋላ ላይ እንመለስበታለን፤ ይሁንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ሙሉ





በሙሉ አልተገነዘብንም ማለት በተወሰነ ደረጃ ልንገነዘብ አንችልም ማለት አይደለም::

በዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፍቅር ዐቢይ ትኩረት ሊሰጠው የሚያስፈልገው ለምንድነው? እርሱ ለምን እንደፈጠረን ስለሚነግረን ነው:: የፈጠረን ስለሚወደን ነው::

በሰዋዊ ወሰን (መለኪያ) ፍቅር መገለጫ እንደሚፈልግ፣ ራሱን ለመግለጥና የሚወደውን ለመንካት እንደሚናፍቅ እናውቃለን:: ከዚህ በተለቀ ደረጃ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ራሱን ለመግለጥና ወደሚወደው አጁን ለመዘርጋት ይፈልጋል:: እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን መውደድ እንዲችሉ አድርጐ በመልኩ የፈጠራቸው ለዚህ ነው:: እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ይህንን አስደናቂ ባህርዩን ለአዳምና ለሔዋንም አካፈላቸው:: ምንኛ ትልቅ ስጦታ ነው! እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በፍቅሩ አበጅቶ በምላሽ ደግሞ እንዲወዱት (እርስ በርሳቸውም እንዲዋደዱ) አድርጐ ፈጠራቸው::

ይህንን ነጥብ በትክክል መገንዘብ ይኖርብናል:: እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን የፈጠራቸው ብቸኝነት ተሰምቶት ወይም በምላሽ የሚወደው ሰው አስፈልጎት አልነበረም:: ይህ ለሰው እንጂ ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የሚመሳሰል አይደለም:: እግዚአብሔር በራሱ ምሉዕ በመሆኑ አንዳች አይጐድለውም:: ግን ፍቅሩ እነዚህን ሰዎች እንዲፈጥር አስገደደው:: ፍቅሩ በአንድ መንገድ መገለጹ አንድ ሠዓሊ የሚያምር ስዕል ለመንደፍ፣ የእንጨት ቀራጭም በጥበብ የተቀረጸ ዕቃ ለማበጀት ውስጡ እንደሚገፋፋው፣ አፍቃሪ አምላካችንም እንዲሁ ሰውን እንዲፈጥር አንዳች ነገር አስገደደው:: ፍቅሩን የገለጸው የሰውን ዘር በመፍጠር ነበር::

## የእግዚአብሔር ወዳጆች እንድንሆን ተፈጠርን

አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት ለምን ነበር? እኛስ ለምን ተፈጠርን? የሥነ ሕይወት አጥኚዎች የአሁኑ መልካችንን እንዴት እንዳገኘን የተለያዩ መላ ምቶች ይሰነዝራሉ፤ ቁምነገሩ ግን ለምን ተፈጥርን ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ የሚሰጠውን መልስ ልብ እንበል፤ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን ከእርሱ ጋር በግል ኅብረት ማድረግ እንድንችል ነው:: በሌላ መንገድ ሲገለጽ፣ ወዳጆቹ እንድንሆን ፈጠረን፣ መለኮታዊው ዕቅዱ ገና ከመጀመሪያው እንዲህ ነበር:: ይህ የተጠነሰሰውም በእግዚአብሔር ፍቅር ነበር::

አልታወቃቸው ይሆናል፤ ሆኖም ደስታን ፍለጋ ያልሞከሩት ነገር የለም፡- ወሲብ፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ አልኮል፣ ዝና፣ ገንዘብ፣ ንብረት ሥልጣን፣ እና ስኬትን ያሳድዳሉ።

መንገዶቹ ሁሉ ወደ እርካታና ሰላም እንደሚያደርሱን ተስፋ ቢሰጡም፣ እዚያ ስንደርስ ግን ሁሉም ነገር (ሁሌም እንደሆነው) እንደጉም ይተናል። ሕይወታቸው አሁንም ባዶ እንደሆነ ነው፤ ደስታና ሰላም ፍለጋ በሚያደርጉት መራወጥ ሕይወታቸው አንዳንዴ አደጋ አፋፍ የሚደርስበት ጊዜም አለ። በዚህም በዚያም ቢባል ሕይወት የምንፈልገውን አትሰጠንም።

ከሚደርሱን ደብዳቤዎች አንዳንዶቹ ከባዶነት ባሻገር፣ ክርስቶስ ሕይወታቸውን እንዴት እንደለወጠና ጥልቅ መሻታቸውን እንደሞላላቸው የሚተርኩም አሉ። እነዚህ ሰዎች ፍለጋቸው ድምዳሜ አግኝቷል፤ የነፍሳቸው ባዶነትም ተሞልቷል። እግዚአብሔርን ለማወቅና ለዘላለም ወዳጆቹ ለመሆን እንደተፈጠሩም ተገንዝበዋል። ይህ እውነት ለእናንተም ነው።

ከላይ የተጠቀሰውን ባለጠጋ ሰው ከጐበኘን በኋላ፣ እኔና ባለቤቴ በአቅራቢያ ባለች አነስተኛ ቤተክርስቲያን ሰባኪ የሆነ ሰው ጋር ተገናኘን። ይህ ሰው በደስታ የተሞላና ገፀ የሚያበራ ነበር፤ "ሰባራ ሳንቲም የለኝም፤ ሆኖም በዓለም ላይ የኔን ያህል ደስተኛ ሰው የለም" ሲል ተናገረ።

## የተፈጠርነው እግዚአብሔርን ለማወቅ ነው

እግዚአብሔር እንድናውቀው ይፈልጋል - ይህም ስለእርሱ ማወቅ ሳይሆን እርሱን በግል ማወቅ ማለት ነው።

ልዩነቱ ይታያችኋል? ስለ እናንተ ሳውቅ፣ ስማችሁን ልሰማ፣ ፎቶአችሁን ልመለከት ከዚያም አልፎ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ላገኛችሁ እችላለሁ። ይሁንና በአካል ተገናኝተን በሚገባ እስክንተዋወቅ ድረስ ወዳጆች ነን ወይም የግል ግንኙነት አለን ማለት አያስችለኝም። ተዋውቀናል ሊባል የሚቻለው በእንደዚህ ሁኔታ ብቻ ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነትም እንዲሁ ነው። በቅርብ ጊዜ የተደረገ የሕዝብ አስተያየት ቅኝቶች እንደሚያመለክቱት፣ ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ያምናሉ። እንዳለ ያምናሉ፣ ስለእርሱም የተወሰነ እውቀት ሊኖራቸው ይችላል። ለብዙዎች ግን





እግዚአብሔር ሩቅና ደብዛዛ ነው ምክንያቱም ስለእርሱ እንጂ እርሱን ስለማያውቁት ነው። በሕይወታቸው በግል ስለማያውቁት በእውነት ወዳጄ ሆኗል ሊሉ የሚያስችል እውቀት የላቸውም። ይሁንና እርሱ የሚፈልገው ይህን ነው፤ እንድናውቀው ይፈልጋል። ይህ አእምሮአችን ሊያስተናግደው የሚሳነው እውነት ነው። እስቲ አስቡት፤ ወሰንአልባው፣ ሁሉን ቻይ፣ ቅዱስና የፍጥረተዓለም ፈጣሪ የእናንተ ወዳጅ መሆን ይሻል! በግል እንድታውቁትና በየዕለቱ ከእርሱ ጋር የመሪመድን ደስታ እንድታጣጥሙ ይናፍቃል። እርሱ ከእናንተ ጋር እንዳለ እንድታውቁ፣ በቃሉና በጸሎት ሀሳቡን ሊገልጥላችሁ ይሻል። ጭንቀት ወይም ፈተና ሲገጥማችሁ ሊያፅናናችሁ፣ ልባችሁ ሊሰበር ወይም ስትዝሉ ከፍ ሊያደርጋችሁ ይፈልጋል። አስቸጋሪ ፈተናዎች ሲገጥሙአችሁ ሊመራችሁ፣ የተሳሳተ ወይም የሞኝነት ሥራ ልታደርጉ ስትሉም ሊያርማችሁ ይሻል።

ሰዋዊ ወዳጆች ሊተውንና ሊከዱን ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን መቼም አይጥለንም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ወዳጅ የሚያበዛ ሰው ራሱን ለጥፋት ይዳርጋል፤ ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚቀርብ ጓደኛም አለ" (ምሳ 18፥24)። የዚህ ዓይነቱ ጓደኛ እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ለተከታዮቹ፣ "ከእንግዲህ አገልጋዮች አልላችሁም ወዳጆች ብያችኋለሁ" (ዮሐ 15፥15) ብሏቸዋል።

እግዚአብሔር ወዳጃችን ሊሆን ይሻል። ግን ይህ እንዳይሆን ያደረገው ምንድነው? የተፋለሰው ነገርስ ሊቃና ይችል ይሆን?

መንፈሳዊ ደዌ ነው። ከፈርጣማ እጆቹ ሊያላቅቀን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

### ታዲያ ምን ተሻለን?

አስታውስ፣ ዛሬ ዓለምም ሆነ እኛ ያለንበት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቀዳማይ ዕቅድ እጅግ የራቀ ነው። ይህ የሆነው ኀጢአት የሚባል አውዳሚ ሁነት ወደዓለም በመግባቱ ነበር።

እና የነገሩ መጨረሻ እንዲህ ነው? ነገሩ እንዲህ ቢሆን ሕይወት ምንኛ አስከፊ ምንኛ ተስፋ ቢስ ትሆን ነበር! ግን አይደለም! ሕይወታችን የተለየ መስመር ሊይዝ ይችላል። እግዚአብሔር ፊውስን ስላዘጋጀልን በኃጢአት ደዌ ሽባ ሆነን መቅረት ግዴታ መሆኑ ቀርቷል።





# አምስት

## እንዳዲስ መጀመር እንችላለን?

*"የሕይወትን መንገድ ለባየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን ለጠገብኸኝ፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ ለለ።"*

*መዝ 16፥11*

ከምንም ነገር በላይ የሚያስፈልገን፣ ትክክለኛውን መንገድ ማግኘት ነው።

የሚያሳዝነው ግን ብዙዎች ወደቀናው መንገድ ሳይመለሱ ዘመናቸውን ይፈጽማሉ። እየተጓዙ ያሉበት መንገድ አስቸጋሪና የሚያስመርር ቢሆንም ሌላ መንገድ ያለ አይመስላቸውም። ሌሎች ደግሞ አማራጭ መንገዶች ቢኖሩም እንኳን እሁን ካሉበት ብዙም ያልተለየ እንደሆነ ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ስለዚህ ጉዳይ በማሰብ ራሳቸውን ማስጨነቅ አይፈልጉም። ይሁንና ሁሉም በውስጥ ማንነታቸው የሆነ የተፋለሰ ነገር እንዳለ በማሰብ የተሻለ ነገር ይናፍቃሉ። ምናልባት እናንተም እንደዚህ እየተሰማችሁ ይሆናል።

### ለመሆኑ ትክክለኛ መንገድ አለ?

በእርግጥም መንገዳችን የተቃና ይሆን ዘንድ፣ ትክክለኛውን መንገድ ማግኘት ያስፈልገናል፤ ግን ይህ የሚቻል ነው? መንገዱስ አለ?

ሰዎች ለነዚህ ጥያቄዎች በተለያዩ መንገዶች በትምህርት፣ በገንዘብ፣ በስኬት፣ በማኅበረዊ ደረጃ መልስ ሊያገኙላቸው ይሞክራሉ፤ ወደትክክለኛው መንገድ እንደሚያደርሷቸው በማሰብ ሌሎች ደግሞ በመዝናናት፣ ራስን የማሻሻያ የሥነ ልቡናና የተለያዩ መንፈሳዊ የሚመስሉ ዘዴዎችን ይከታተላሉ። ሌሎች ደግሞ የሚሆናቸውና የልካቸውን ሰው ቢያገኙ ችግሮቻቸው ሁሉ

ስማያት የሚወስደንና በዚህ ሕይወት ስንኖር ዓላማና ሰላም የሚሰጠን ሌላ መንገድ አዘጋጅቶናል፡፡ መንገዱም ኢየሱስ ነው፤ እንዲህ ብሎ መናገር የሚችለው እርሱ ብቻ ነው፡- "መንገዱ እኔ ነኝ፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደአብ የሚመጣ የለም፡፡" (ዮሐ 14፥6)፡፡

ኃጢአት በተሳሳተ መንገድ እንድንዘፈቅ አድርጐናል፡፡ መልካሙ የምሥራች ይህ ነው በኢየሱስ ቤዛነት ወደትክክለኛው መንገድ ልንመለስ እንችላለን፣ የሚያስፈልገንም ይኸው ነው፡፡

## ኢየሱስ ማን ነው?

የክርስትና እምነት ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሲሆን፣ ኢየሱስ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ብዙም በማትታወቅ የሮማ ግዛት ውስጥ የሚኖር ሰው ነበር፡፡ የታሪክ ሲቃውንትና ሃይማኖታዊ የሆኑ አይሁድ የሚስማሙበት ነገር በዓለም ታሪክ ዘላቂ ሰውጥ በማምጣት እርሱን የሚስተካከል ሰው እንዳልነበረ ነው፡፡ የክርስትና እምነት የማዕዘን ድንጋይና ማዕከል ነው፤ ለዘለዓለምም ነው፡፡ ክርስቲያኖች ትምህርቱን ሲዘነጉ፣ ጌታቸውን በመካድ ስሙን አስነቅፈዋል፡፡ ሲያከብሩትና ሲከተሉት ግን ሕይወታቸው ተለውጦ ዓለምን መለወጥ ችለዋል፡፡

ታዲያ ይህ ሰው ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላም የሚተካከለው የሌለ ሰው የሆነው ለምንድነው? ታላቅ ሰው ብቻ ነው? ወይስ ከዚያም ይልቃል?

ስለኢየሱስ ያለን መረጃ ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለእርሱ የሚነግረን ነገር በምናባችን ልናስበው ያዳግተናል፡፡ ኢየሱስ በእኛ ዘንድ የኖረ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ሰው ነበር፤ ግን ከዚያም በላይ ነበር፤ እግዚአብሔርም ነበር፡፡ እንዲህ ጻድቅ ሰው ብቻ ሳይሆን፤ በሰው ሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ" (ዮሐ 1፥1፤14)፡፡

ይህ አባባል ሊያንገዳግደን ይችላል፤ ሆኖም ኢየሱስ በአደባባይ አገልግሎቱ ደጋግሞ የተናገረው ነው፤ "እኔና አብ አንድ ነን" (ዮሐ 10፥30)፣ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" (ዮሐ 14፥9)፡፡





በአንድ ወቅት ደቀመዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር ሳሉ ገፁ በደማቅ ብርሃን ሲያበራ፣ በቅፅበት ያህል ሰማያዊ ክብሩ ተገለጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሰማይ አንድ ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማ፤ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" (ማቴ 17፥5)፡፡

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችም ሳያቋርጡ የመሰከሩት ይህን ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ "እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ ... እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲሆን ወዶአልና" (ቆላ 1፥15፤19)፡፡ ኢየሱስ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ነው፡፡

በየዓመቱ ገናን ስናከብር፣ ይህን ማመልከታችን ነው፡፡ መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ተገልጦ እንዲህ አላት፡- "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱስ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃ 1፥35)፡፡

ኋላ ላይ መልአክ ለባሏ ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፣ "ስሙንም ኢየሱስ (ትርጉሙ ጌታ ያድናል ማለት ነው) ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና"፡፡ ይህ፣ የወንጌል ጸሐፊው በማከል፤ የሚሆነው "ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤ ትርጉሙም፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው (ማቴ 1፥21፤23) ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ እንደሆነ ነገረው፡፡ ይህንን መዘንጋት የለብንም፤ በፊት በቤተልሔም የተወለደው ሕፃን ከኀጢአታችን ያድነን ዘንድ አብ የላከልን አንድያ ልጁ ነው፡፡ እርሱ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ነው፡፡

ይህን መግለጽ የሚያስፈልገን ለምንድነው? ምክንያቱም ከኀጢአታችን ሊታደገን የሚችለው መለኮታዊ አዳኝ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ሰው ብቻ ከሆነ ሊያድነን አይችልም ምክንያቱም እንደእኛው ሰው በመሆኑ ራሱ የኃጢአት ይቅርታ የሚያሻው ኃጢአተኛ ስለሚሆን ነው፡፡ ኢየሱስ ግን ሰውም አምላክም ስለሆነ፣ ያለ ኃጢአት ነበር፤ ስለዚህም እርሱ ብቻ ኀጢአታችንን ሊሸከም ይችላል፡፡

## ኢየሱስ ምን አደረገ?

ኢየሱስ ሰማያዊ ክብሩን ትቶ በእድፈትና በብክለት ወደተሞላው ዓለም እንዲመጣ ያደረገው ምን ነበር? የመጣው

ከዚህ ቀደም ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ሰጥታችሁ የማታውቁ ከሆነ ወይም ይህን ውሳኔ መወሰናችሁን እርግጠኛ ካልሆናችሁ፣ አሁኑኑ ወደእርሱ እንድትመለሱ ጥሪ እቀርብላችኋለሁ። የሚከተለውን አጭር ጸሎት በመጸለይ ዛሬውኑ ሕይወታችሁን ለእርሱ መስጠት ትችላላችሁ።

*እግዚአብሔር ሆይ! ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ። ስለሠራሁት ኃጢአት በመጸጸት ከዚህ መንገድ መመለስ እፈልጋለሁ። ክርስቶስን ብቻ እንደ አዳኝ እቀበላለሁ! ጌታ ብዬም በሕይወቴ እሾመዋለሁ። ከዚህ ቅጽበት ጀምሮ፣ በአማኞች ህብረት እርሱን ለማገልገልና ለመከተል እፈልጋለሁ። በክርስቶስ ስም እጸልያለሁ። አሜን!*

ይህን ጸሎት ከልባችሁ ከጸለያችሁ፣ እግዚአብሔር ሰምቷችኋል። ለዘላለም የእርሱ ልጅ ሆናችኋል።





# ስድስት

## አዲስ ጅማሬ

*"በዙፋንም ላይ የተቀመጠው፦ እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ"*

(ራእ 21፥5)

ማንነታችንን እስካላወቅን ድረስ እንዴት መኖር እንዳለብን ከቶም ልናውቅ አንችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርጌ የተቀበልኩበትን ቀን ዛሬም ድረስ አስታውሰዋለሁ። ጊዜው የዐሥራ ሰባተኛ የልደት በዓሌን የማከብርበት ወቅት ነው፤ ከሌላ አካባቢ የመጣ ወንጌላዊ በከተማችን በአንድ ትልቅ መጠለያ ይሰብክ ነበር። መጀመሪያ ላይ የዚህ ዓይነቱን ስብሰባ መካፈል በጭራሽ አልመሰለኝም፤ በኋላ ላይ ግን በአንድ ጓደኛዬ ውትወታ ሄድኩ። ቁጭ ብዬ ወንጌላዊውን ስሰማ ግን መልእክቱ (እና መስህብ ያለው አቀራረቡ) ሁለተናዬን ተቆጣጠረኝ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም እኔን በቀጥታ የሚያናግረኝ ነበር የሚመስለኝ - ከፊት ለፊቴ ያለች አንዲት ሴት ያደረገችው ትልቅ ኮፍያ ከእርሱ እይታ ቢሰውረኝም እንኳ። አሁን ተመልሼ ስለዚያ ጊዜ ሳስብ፣ መንፈስ ቅዱስ በልቤ ሆኖ ስለኃጢአቴ በመውቀስ ክርስቶስ እንደሚያስፈልገኝ እየገለጸልኝ ነበር።

በአንድ ምሽት ሰባኪው ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ ጥሪ ሲያቀርብ፣ እስከዚያ ድረስ ጥሪውን እምቢ እያልኩ መቆየቴን በመገንዘብ፣ ወደመድረኩ ሄድኩ (ያም ሆኖ የመጨረሻው መዝሙር እስኪያልቅ ድረስ አልወጣሁም)። አንድ መልካም የሆነ ሰው ክርስቶስን ወደሕይወቴ እንዴት መቀበል እንደምችል አብራራልኝ፤ በርሱ ምሪት መሠረት አጭር ጌታን የመቀበል ጸሎት ጸለይኩ።

ቤት ስደርስ ፎቅ ላይ ወዳለው ክፍሌ ደረጃውን ስወጣ ይህ ነው ብዬ ልገልጸው ባልችልም፤ በሕይወቴ አንድ ትልቅ ነገር እንደተከሰተ ይሰማኝ ነበር። ጠንካራ ስሜት ወይም ምትሓታዊ ለውጥ አልተሰማኝም፤ ሆኖም ከበረንዳ ሆኜ በጨረቃዋ ብርሃን የአባቴን የእርሻ ማሣዎች ስመለከት ስለወሰድኩት እርምጃ አሰላስል ነበር። ከዚያም በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በጉልበቴ ተንበርክኬ እንዲህ ስል ጸለይኩ፣ ጌታ ሆይ፤ ዛሬ ምሽት በሕይወቴ የተከሰተውን በውል አላውቀውም፤ አንተ ግን ታውቃለህ። ያ ውሳኔ ምን ማለት እንደሆነና ምን እንደሚጠይቀኝ የተገነዘብኩት ቆይቼ ነበር። ዐሥርቶች ቢያልፉም፣ የክርስትና ሕይወት ሁልጊዜ የሚታደግበት እንጂ ደርሻለሁ የሚባልበት እንዳልሆነ ተረድቼአለሁ።

## መንገዶቹ ቢለያዩም እውነታው አንድ ነው

ሰዎች ክርስቶስን የሚቀበሉት በተለያየ መንገድ ነው፤ እናንተ የምታልፉበት መንገድ የግድ ከእኔ ጋር ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቹ ድንገተኛና አስደናቂ በሆነ መንገድ ሥርነቀል የሕይወት ለውጥ ያደርጋሉ። የጠርሴሱ ሳውል የኢየሱስን ተከታዮች ለማሰር ወደ ደማስቆ በሚጓዝበት ወቅት፣ በድንገት ደማቅ ብርሃን ዓይኑን አሳወረው። ኋላ ላይ ተመልሶ የሆነውን ሲያስታውስ፣ "በምድርም ላይ ወድቄ፤ ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ? የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ።" (ሥራ 22፥7)። ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ሳውል ከዚያ ቀደም ይቃወመው የነበረውን ኢየሱስን ማገልገል ጀመረ፤ በኋላ ላይም (በአዲስ ስም ሐዋርያው ጳውሎስ ተብሎ) ወንጌልን በመላው የሮማ ግዛት ለማስፋፋት እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል።

ሌሎች ደግሞ ወደክርስቶስ የሚመጡት ቀስ በቀስ፣ ምናልባትም ካለማመን ወደማመን ድንበር ያቋረጡበትን ጊዜ እንኳን በትክክል ሳያውቁት ነው። የሐዋርያው ጴጥሮስ መለወጥ የዚህ ዓይነቱ ይመስላል። በመጀመሪያ ፈራ ተባ እያለና እየዋለለ፣ በኋላ ግን ጽኑና ቁርጠኛ ሆኖ ለኢየሱስ የወሰነ ይመስላል። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ፣ ያ የለውጥ ቅፅበት መቼ እንደተከናወነ አይነግረንም፤ ጴጥሮስ ራሱ ላያውቀው ይችላል። ባለቤቴ ሩት ያደገችው በጠንካራ ክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ነው (ወላጆቿ በቻይና ወንጌል የሰበኩ አገልጋዮች ነበሩ)። ስለዚህም ልጅ ሆና እንኳን የኢየሱስን አዳኝነት ያላመነችበት ጊዜ ትዝ አይላትም።





ቁም ነገሩ ወደ ክርስቶስ እንዴት መጣን ሳይሆን መምጣታችንና እንደዚሁም ለድነታችን በዚህ ሰዓት በእርሱ ላይ መተማመናችን ነው። ሕይወታችሁን ለእርሱ ስለመስጠታችሁ እርግጠኞች ናችሁ? ካልሆናችሁ ይህን ውሳኔ ሳትወስኑ ይህ ቅፅበት አይለፍ። መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ሰፍራ ከሞት በኋላ ሁለተኛ ዕድል እንደሚሰጠን አይናገርም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እነሆ፤ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ የመዳን ቀን አሁን ነው" (2ቆሮ 6፥2) ይላል።

## የተለየ ነገር ይከሰታል?

የመለወጣችሁ አኳኋን የትኛውም ዓይነት ቢሆን፣ ሕይወቴን ለክርስቶስ ስሰጥ የተሰማኝን ዓይነት ስሜት ሊሰማችሁ ይችላል፤ እኔ "ጌታ ሆይ፤ በሕይወቴ የተከናወነውን ነገር አላውቅም ነበር ያልኩት። ሌላው ቀርቶ ለውጥ ስለመከሰቱም እንኳን እርግጠኞች ላትሆኑ ትችላላችሁ። ወይም ደግሞ መጀመሪያ በክርስቶስ ባመናችሁ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ መሆን ስሜት የነበራችሁና ያ ስሜት አሁን ደብዝዞባችሁ እምነታችሁ በእርግጥ እውን እንደነበር እየተጠራጠራችሁ ሊሆን ይችላል። እምነታቸው እንዴ ከፍ እንዴ ዝቅ እያለ እንደሚዋዥቅባቸው በደብዳቤ የሚገልጹልኝ ሰዎች አሉ። እነዚህ ነገሮች የሚከሰቱበት አንዱ ምክንያት ሕይወታችንን ለክርስቶስ ስንሰጥ ሰይጣን እግዚአብሔርን እንድንጠራጠር ለማድረግ ስለማይተኛልን ነው።

ግን ይህን ልብ በሉ፤ ሕይወታችንን ለክርስቶስ ስንሰጥ የሚከሰቱ ነገሮች አሉ፤ እነዚህን በውል ስንገነዘብ፣ ሰይጣን በእኛ ላይ የሚዘራውን ጥርጣሬ ለማምከን ጽኑ መሠረት ይሆኑናል። እግዚአብሔር እንዲህ ሲል የገባልን ቃል እውነት ነው፤ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ አዲስ ሆኗል" (2ቆሮ 5፥17)። ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ከሰጣችሁ፤ አዲስ ፍጥረት ናችሁ፤ ምንም ይሰማችሁ ምን እውነታው ይህ ነው።

ይህ ምን ማለት ነው? በክርስቶስ ስናምን ምን ይከሰታል? ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ስትሰጡ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ሰባት ስጦታዎች እንመልከት።

የላባችሁም:: በንስሐና በእምነት ወደክርስቶስ ስትመለሱ እግዚአብሔር የሚያደርግላችሁን ከቶም እንደዋዛ መውሰድ የለባችሁም:: በዚህ ሰዓት ለአፍታ ቆም ብላችሁ ስለሰጣችሁ ስጦታ ለምን አታመሰግኑትም?

*ይሁንና የእግዚአብሔር ልግስና በዚህ አይደመደምም፤ እግዚአብሔር ተጨማሪ ስጦታም ሰጥቶናል፤ መንግሥተ ሰማይ እስክንደርስ ድረስ የምንጓዝበት አዲስ ጉዞም ሰጥቶናል::*

በሌላ አባባል፣ ክርስቶስን ለመከተል መወሰናችሁ ፍጻሜ ሳይሆን ጅማሬ ነው - የአዲስ ሕይወት ጅማሬ ነው:: በስም ክርስቲያኖች ወደመሆን ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ክርስቲያን ለመሆንም ነው የተጠራነው:: በክርስቶስ ያለ እምነት እንደ "መንፈሳዊ ሕይወት መድን" ተደርጐ ሊታሰብ አይገባውም:: በቃ አንዴ ተቀብለናልና መንግሥተ ሰማይ እስክንገባ ድረስ ምን ያስፈልጋል የምንለው አይደለም:: የክርስትና ሕይወት በቀሪ ዘመናችን ሁሉ የምንጓዝበት አዲስ ጉዞ ነው::

የሚያስደስተው ነገር ደግሞ ይህ ነው፤ ክርስቶስ አብሮን ስላለ ክቶም ቢሆን ብቻችንን አንጓዝም::





# ሰባት

## እርግጠኛ መሆን ይቻላል?

*"የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ::"*

(2ጢ.ሞ 1፥12)

ሕይወት የምትሰጠን ብቸኛ እርግጠኝነት እርግወኛ *ያለመሆንን ብቻ ይሆን?*

በየጋዜጣው የምናየው ዜና አምብዛም ተስፋ የሚሰጥ አይደለም:: መገናኛ ብዙሃን የሚያወሩት ጦርነት፣ ረሃብ፣ ነውጠኝነት፣ የዘርና የጐሳ ግጭት፣ የምጣኔ ሀብት መዛባት፣ የጭካኔ ድርጊትን ነው፤ ዝርዝሩ ማብቂያ የለውም:: በዕለትተለት ኑሮአችን የሚያጋጥሙን ሁኔታዎችም ለምሳሌ የጋብቻና የቤተሰብ መፍረስ፣ ህመም፣ ሱስና አደጋዎች የተስፋ እብነት አይሰጡንም፤ ዋስትና ማጣትና ያለመደላደል የዘመናችን መለዮ የሆኑ ይመስላል:: ብዙዎች በዚህ ውሉ በማይታወቅ ዓለም እርግጠኝነት መጠበቅ የሕልም ሩጫ መሆኑን ደምድመዋል::

### የመንፈሳዊ እርግጠኝነት ዕጦት

ስለመንፈሳዊ ሕይወታችንም እርግጠኝነት ማግኘት አንችልም ይሆን? ወይስ እግዚአብሔር ለእኛ ግድ እንደሚለው እኛም በእርግጠኝነት በእጆቹ እንዳለን ማወቅ በእውነት ማወቅ እንችላለን?

አባቴ ለበርካታ ዓመታት በዚህ ረገድ በጥርጣሬ ይታወክ ነበር:: በወጣትነት ጊዜው፣ ብርቱ ከሆነ ከመንፈሳዊ ውጊያና ከራስ ጋር ሙግት በኋላ፣ ሕይወቱን ለክርስቶስ ሰጠ:: ሆኖም ቀስ በቀስ የእግዚአብሔር ቅርብነት ስሜት እየደበዘዘበት መጣና ስለድነቱም ጥርጥር ይገባው ጀመር:: ከዚያም አልፎ ይቅርታ የሌለውን ኃጢአት ፈጽሚ ይሆን ብሎም መታወክ ጀመረ (ይህ የተሰማው

ብዙዎች እግዚአብሔርን የሚያስቡት እንደዚህ ነው፤ ድነትን ይሰጠንና ፍጹም ካልሆንን ከኛ ይወስደዋል! ይህ ግን እውነት አይደለም።

## የሚያሳስቱ ስሜቶች

*ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ በስሜታቸው ላይ ብቻ ስለሚደገፉ ስለድነታቸው እርግጠኝነት አይኖራቸውም።* ምናልባት ወደክርስቶስ ሲመጡ፣ ጥልቅ የደስታና የሰላም ስሜት ተሰምቷቸው ውሎ ሲያድር ግን እነዚህ ስሜቶች ሲደበዝዙ ድነታቸውን ጥርጣሬ ውስጥ ያስገባሉ። እነኚህ ሰዎች ስሜቶች እንደሚያሳስቱ አልተገነዘቡም፤ ስሜቶቻችን አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ የሚሉ በመሆናቸው፣ እምነታችንን በስሜቶች ላይ መመሥረት አስተዋይነት አይደለም።

ስሜቶች በሌሎች መንገዶችም ያሳስቱናል፤ በቅርቡ አባቱ የአልኮል ሱሰኛ ስለሆነ ሰው ሰምቼ ነበር። በልጅነቱ ከዕለት ዕለት የአባቱ ሁኔታ ምን ሊሆን እንደሚችል በጭራሽ ማወቅ አይችልም ነበር። አንዳንዴ ርኅሩኅና ደግ ሲሆን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጨካኝና አንገላች ነበር። ይህ ሰው በኋላ ላይ ክርስቲያን ሲሆን፤ እግዚአብሔር እንደ አባቱ - ሲለው ደግ፣ ሲለው አንገላች - ላለመሆኑ ዋስትና ማግኘት እጅግ ተቸግሮ ነበር። ስለእግዚአብሔር እንደዚህ የሚያስብብትን ምክንያት ለመገንዘብ በርካታ ዓመታት (እና የአንድ አስተዋይ ክርስቲያን አማካሪ እርዳታ) ወስዶበታል። ስሜቶቹ እውነታውን አደበዘዙበት እስተያየቱን ለማስተካከልም ዘለግ ያለ ጊዜ ፈጀበት።

የሕይወት ፈተና ሲጠናብን ወይም ተስፋ መቁረጥና ኑሮ ሲጫጫነን ስሜቶች ሊያሳስቱን ይችላሉ። "እግዚአብሔር ተቆጥቶኛል፤ ምናልባትም አይወደኝም፤ እስከናካቴውም የተጣለኩ አድርጎኛል" እንላለን። በቀጣይ ምእራፎች እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ፈተናን በሕይወታችን የሚፈቅድበት ጊዜ አለ፤ ሆኖም ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን እውነት ፀሐይ እንዲጋርዱብን መፍቀድ የለብንም። የምናልፍባቸው መከራዎች እጅግ ፈታኝ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁንና ክርስቶስ ለእኛ ያየው ስቃይ ከዚህ የገዘፈ ነበር፤ የእግዚአብሔር ፍቅር በማያዳግም ሁኔታ የተገለጠልን በእርሱ ነው።





## ትምክህት ሳይሆን የልብ እርግጠኝነት

*ክርስቲያኖች ስለመዳናቸው እርግጠኛ የማይሆኑበት ሌላው ምክንያት ፈር የሳተ ትህትና ሊሆን ይችላል።* አንድ ሰው እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፣ "ወደ መንግሥተ ሰማይት መሄድ እንደምንችል ማወቅ የምንችል አይመስለኝም። ለዚህ የሚያበቃ ጽድቅ አለኝ የሚል ሰው ትዕቢተኛ ብቻ ነው፤ ትዕቢት ደግሞ ኃጢአት ነው። ለእኔ እንደሚመስለኝ አንጽደቅ እንኳን የምናውቀው ከሞት በኋላ ነው።"

ይህ ሰው ስለአንድ ነገር አልተሳሳተም፤ ትዕቢት በርግጥም ኀጢአት ነው፤ ክርስቲያን ትዕቢተኛ ሊሆን ከቶም አይገባውም። እግዚአብሔር የሚያድነን በማንነታችን ወይም መልካም በመሆናችን ወይም ከሌሎች የተሻልን እንደሆንን በመናገራችን አይደለም። እግዚአብሔር የሚያድነን በምሕረቱና በጸጋው ብቻ ነው፤ ስለዚህም የኛ በጎ ምግባርና ትሩፋት ከቶም ቢሆን ድነትን አያስገኝልንም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌ. 2፥8-9)። የመዳናችን አብነት - የእግዚአብሔር ጸጋ - ኃጢአተኞች ብንሆንም እንኳን እኛን መውደዱና በጎ መሆኑ ነው።

በራሳችን ጽድቅ የምንመካ ከሆንን በርግጥም ትዕቢተኞች ነን። ሆኖም መታመናችን በክርስቶስና በእርሱ ብቻ ሊሆን ይገባል። እንደ እውነቱ ከሆነ መዳኔን የማውቀው ስሞት ነው የሚል ሰው መንግሥተ ሰማይት ለመግባት የሚያበቃ ጽድቅ አለኝ እያለ ይሆናል። በክርስቶስ ሳይሆን በራሱ ስለሚመካ በትክክለኛ መሠረት ላይ አልቆመም።

## ጽኑ መሠረታችን

እግዚአብሔር ለእኛ እንደሚጠነቀቅልንና አንድ ቀንም ወደ መንግሥተ ሰማይት እንደሚወስደን በእውነት ማወቅ እንችላለን? በምንም ዓይነት ሁኔታ ለእኛ ግድ እንደሚለውና እስከመጨረሻው ከእኛ ጋር እንደሚሆን ማወቅ እንችላለን?

አዎን ማወቅ እንችላለን፤ በዚህ ምዕራፍ፡ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ይህ ለምን እውነት እንደሆነ ለማሳየት እሞክራለሁ። ጠንቃቃ የግንባታ ሠራተኛ ሕንፃ የማቆም ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣ በመጀመሪያ የተደላደለ መሠረት እንደሚጥል ሁሉ፣ የእግዚአብሔር

# ስምንት

## በትክክለኛው አቅጣጫ መጓዝ

*"በሕይወትም ያሉት ስለነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለሁሉ ሞተ"*

(2ቆሮ 5፥15)

ሕፃን ልጅ ሁልጊዜ ሕፃን እንደሆነ እንዲቆይ እንደማይጠበቅ ሁሉ፣ አዲስ ክርስቲያንም ባለበት መቆየቱ የሚወደድ ነገር አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ "አዲስ የተወለዱ ሕፃናት" የሚለን ያለምክንያት አይደለም፤ በመጀመሪያ ወደክርስቶስ ስንመጣ እንዲሁ ማለትም መንፈሳዊ ሕፃናት ነንና (1ጴጥ 2፥2)። እግዚአብሔር በመንፈሱ በውስጣችን በመሥራትና ልባችንን በመለወጥ የቤተሰቡ አባላት አድርጎናል፤ ይሁንና አዲስ እንደተወለደ ሕፃን፣ ገና ደካሞችና ለጉዳት የተጋለጥን በመሆናችን፣ ከጨቅላነት አልፈን ወደመንፈሳዊ ብስለት እንሸጋገር ዘንድ እርዳታና እገዛ ያስፈልገናል። ለመሆኑ መንፈሳዊ ብስለት ምንድነው?

### ልደትና እድገት

የአምስቱ ልጆቻችን ልደት ለእኛ የተለየና ውብ ሁነት ነበር፤ በተለይም የመጨረሻ ልጃችን የኤድ ልደት ሁልጊዜ የማስታውሰው ነው። ለዚህ ምክንያቱ አዋላጅ ዶክተሩ፣ ሩት ስትገላገል አብሬአት እንድሆን ስለፈቀደልኝ ነበር፤ ከልጆቻችን የአንዱን ልደት በቦታው ተገኝቼ ለማየት ዕድል ሳገኝ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። በልጅነቴ በአባቴ እርሻ ላይ እንስሳት ሲወለዱ አይቻለሁ፤ ይህ ግን ልዩ ነበር። ባለ በሊሉ ጉልበቱ ያጮህ የነበረው ይህ ጨቅላ ሰው እንጂ እንስሳ አልነበረም። ከዚያም በላይ የእኔው ልጅ ነበር! የሕፃን ልጅን መወለድ "ተዓምር" ብለው የሚገልጹ ሰዎች ከእውነት እንዳልራቁ





የተገነዘብኩት ያኔ ነበር። የኤድ ልደት መቼም የማልረሳው ልዩና እንዳች ሆድ የሚያባባ ሁነት ነበር።

ሩት ተቀብላ ስታቅፈው፣ እግዚአብሔር ለእኛ በዐደራ ለሰጠን ለዚህ ልጅ በጸጥታ መጸለይ ጀመርኩ። መልካምና አፍቃሪ ወላጆች መሆን እንድንችልና ዕድሜው ሲደርስም ወደ ክርስቶስ እንድንመራው እንድንችል ጸለይኩ። በተጨማሪም እግዚአብሔር እንዲጠብቀውና እንዲከልለው፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ እንዲያድግ የጸጥታ ጸሎት አደረስኩ። ሩትና እኔ ለሌሎች ልጆቻችን እንዳደረግነው በየቀኑ ይህን ጸሎት ለሚያድገው ልጃችን እናደርስ ነበር።

ተመልሼ ስለዚህ ጉዳይ ሳሰላስል፣ ለልጄ ለኤድ ካደረስኩት ጸሎት በስተጀርባ (ሁሉም ወላጅ ለልጁ ከሚያደርሰው ጸሎት በስተጀርባ) የተሰወረ ፍርሃት እንደነበር ተረድቻለሁ። ይህ ፍርሃት ማደግ መመንደጉን የሚያግድ እንዳች ነገር ቢከሰትስ የሚል ነበር። አይበለውና ያልተጠበቀ በሽታ፣ በዘር የተወረሰ እንዳች እክል፣ በአጭር የሚቀጭ አደጋ እነሆና የመሳሰሉ በርካታ ችግሮች ተከስተው በጤና እንዳያድግ ቢያደርጉና እስከናካቴውም ሕይወቱን ቢቀጩትስ? በዘመዶቻችንና በቅርብ ወዳጆቻችን ይህ ሲከሰት ስናይ፣ ልባችን በጥልቅ ሀዘን ይመታል።

ቁም ነገሩ ይህ ነው፤ ሕፃን ልጅ ምንም ውብና ለዓይን የሚያሳሳ ቢሆን፣ *ለዘላለም ሕፃን ሆኖ እንዲኖር አንፈልግም።* እንደዚሁ ብላቴና ወይም አዳጊ ልጅ በነበረበት ሁኔታ እንዲኖር አንፈልግም። ልጅ ማደጉን ትቶ በነበረበት ቢኖር አንድ ችግር እንዳለ እንረዳለን፤ ምክንያቱም የምናውቀውና የምናስበው ልጆች አድገው ወደብስለት እንደሚደርሱ እንጂ የዚህን ተቃራኒ አይደለም። ጨቅላ ሕጻን ልጅ እንዲሆን ልጅ ደግሞ እንዲጎረምስ፣ ጎረምሳም ጎልማሣ ሆኖ እንዲያድግ እንጠብቃለን።

### መንፈሳዊ ልደትና ዕድገት

ሕፃን ልጅ በአካልና በአእምሮ ማደጉ ቀርቶ ሲቀጫጭ ማየቱ እጅግ አሳዛኝ ከመሆኑ በላይ፣ ክርስቲያን በመንፈስ ማደግ ሲሳነው ማየት የበለጠ አሳዛኝ ነው። ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ *መንፈሳዊ ህጻናት ሆነን እንድንከርም የእግዚአብሔር ሀሳብ አይደለም።* ይልቁንም እግዚአብሔር ለእኛ ያቀደልን *መንፈሳዊ ብስለት ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ "ስለዚህ ወደ ብስለት እንሂድ" (ዕብ

ክርስቲያኖች እንዲህ ናቸው፤ ይበልጡኑ የሚታወቁት በማያደርጓቸው ወይም በሚታቀቡባቸው ነገሮች ነው፤ ስለዚህም ሰዎች እነርሱን ተመልክተው በክርስቶስ አይማረኩም።

ኢየሱስ ግን እንዲህ አልነበረም። ሰዎች በእርሱ ይማረኩ የነበረው ይህን ወይም ያን ከማድረግ ራሱን ስላቀበ ሳይሆን በሚያደርገው ነገር ነበር። ከዚያ ቀደም ያላዩትን የሕይወት ውበት ተመልክተው፣ ይህን በራሳቸውም ማግኘት ፈለጉ። በክርስቶስ ደስታ፣ ሰላምና ርህራሄ ከሁሉም በላይ የእግዚአብሔር ፍቅር ተገልጦ ተመለከቱ።

እግዚአብሔር ይህንኑ ኢየሱስ የገለጠውን ውብ የሆነ ሕይወት ሊሰጠን ይፈልጋል። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸዋል፤ "ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ" (ዮሐ 15፥11)። የክርስትና ሕይወት ጨፍጋጋ፣ አሰልቺና ፈዛዛ እንደሆነ የምታስቡ ከሆነ ይህን እነግራችኋለሁ፣ ተሳስታችኋል! ልብ በሉ፤ *እግዚአብሔር የተሻለ ምትክ ሳያደርግ፣ ከሕይወታችን የሚያስወግደው ነገር የለም።*

ይህ ለጊዜው እውነትነቱ ላይገለጥልን ቢችልም ውሎ አድሮ ግን እናስተውለዋለን። እውነቱ ሲገባንም በእግዚአብሔር ጥበብና መልካምነት እንደነቃለን። እግዚአብሔር ባሪያ ያደረጋችሁን ክፉ ልማድ ሲነቅልላችሁ የተሻለ የአኗኗር መንገድ ይሰጣችኋል። ሐሜትን፣ መራገምን፣ አሉባልታን ከእናንተ ሲያስወግድ የፍቅርና ሰዎችን የሚደግፍ እንደዚሁም የምስጋና ቃልን በአንደበታችሁ ያኖራል። ራስን ማዕከል ማድረግን ከእናንተ ሲያርቅ የእርሱን ፈቃድ የማድረግን፣ ደስታና ሐሴትን በምትኩ ይሰጣችኋል። እግዚአብሔር እጉል ነገሮችን ከሕይወታችሁ ሲያስወግድ ሥራውን እንዳጠናቀቀ አይቆጥርም፤ ከዚህም ባሻገር በመልካም ነገሮች ሲተካላችሁ ይሻል። *የእርሱ ሀሳብ በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን አዲስ ሰው አድርጎ ሊለውጠን ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" (ሮሜ 12፥2)።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ነው፤ *መልካም፣ ደስ የሚያሰኝ እና ፍጹም።* ታዲያ ወርቅ እያሰልን፣ ዓይናችን መዳብ ይቀላውጣልን?



# ክፍል ሁለት

---

# ለጉዞአችን ስንቅ መያዝ

ያምናሉ:: ሌሎች ደግሞ ክፋው የሚባለው የሥነ አዕምሮ ወይም የማህበራዊ ቀውስ ሌላው ስም ነው ይላሉ:: ይሁን እንጂ፣ በክፋው የጭክና ድርጊት ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ምንም መልስ አይኖራቸውም፣ ምክንያቱም መኖሩንም ሆነ በሰው ዘር ላይ የሚያስከትለውን አስቃቂ ተጽዕኖውን መቀበል ስለማይችሉ ነው:: የክፋውን የተራቀቀ እውነት ብንክድ፣ ለመዋጋት ከቶ የተዘጋጀን አንሆንም:: አንድ ወዳጄ አንድ ጊዜ በአባቱ ተንከል በተሞላና ስግብግብ ብቻ ሳይሆን ፍጹም ክፉ በሆነ ባሕርይ ምክንያት እንደተጐዳ አጫውቶኛል:: ይህ ወዳጄ ክርስቶስ ከዚህ ሥቃይ ነፃ ስላወጣው ያለው አክብሮትና ምስጋና ወሰን የለውም::

*ሁለተኛው ስህተት ደግሞ ከመጀመሪያው ተቃራኒ ነው፣ ክፉ አለ፣ እናም እኛ ከቶ ልናሸንፈው አንችልም የሚል* ነው:: አንዳንዶች እግዚአብሔርና ሰይጣን እኩል ናቸው፣ ሁለቱ ሳይሸናነፉ ማለቂያ በሌለው ትግል ውስጥ ናቸው ብለው ያምናሉ:: ምንም በጐ ነገር የለውምና ክፉን መዋጋትስ ለምን አስፈለገ? ይላሉ:: እነኚህ ሰዎች ማየት የተሳናቸው ነገር ቢኖር፣ ሰይጣን ኃያል ሲሆን እግዚአብሔር ግን ሁሉን ቻይ መሆኑን ነው:: ከዚህም በላይ ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል እንደነሣቸው (ቆላ 2፥15) ዘንግተዋል:: በምዕራፍ ዐራት እንደተመለከትነው፣ ሰይጣን አለ (እውን ነው) - ሆኖም የተሸነፈ ጠላት ነው! ሰይጣን አሁንም በሥራ ላይ ነው - የመጨረሻውም ፍርድ አጠራጣሪ አይደለም:: ሕይወት ጀርባዋን ብታዞርባችሁ ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም፤ ክርስቶስን ካወቃችሁ በርግጥ ታሸንፋላችሁ!

*ሦስተኛው ስህተት ደግሞ ምናልባት በጣም አደገኛው ነው፣ ከግንዛቤ ማነስ የተነሣ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ በዚህ ስህተት ውስጥ ሲገቡ ይስተዋላል*:: እንዲህ ይላሉ፣ ክፋው እውን ነው፣ ግን እራሴ እዋገዋለሁ:: እንዲረዳን በእግዚአብሔር በመደገፍ ፋንታ፣ በራሳችን እንመካለን:: ከኃጢአት አኳያ ፍጹም ተስፋቢስነታችንንና የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንደሚያስፈልገን በመገንዘብ ፋንታ በራሳችን ጥንካሬ ድል ለመቀዳጀት መሞከር እንዳለብን እናስባለን:: እግዚአብሔር ለድል የሚያስፈልገንን ብቃት ሁሉ እንደሰጠን ከመገንዘብ እንስታለን::

እግዚአብሔር ከፊታችን በዘረጋልን በዚህ የሕይወት ጉዞ ላይ የሚያጋጥሙንን አደጋዎች አሳንሰን እንመልከታቸው:: ክፋው እየሠራ ያለው በተለያየ መንገድ ነው - አንዳንዴ በገሃድ፣ ብዙውን ጊዜ ግን በድብቅ እየሠራ ነው:: የክፋው ዓላማ ግን ሁሌም አንድ





ነው፣ እኛን ከእግዚአብሔር ለመለየት ይሠራል:: ሰይጣን እኛን ማደናገር ከቻለ፣ ወይም ከመንገዳችን ካዘነፈን፣ ወይም ተስፋ ካስቆረጠን፣ ወይም በፈተና ውስጥ ከከተተን - ያኔ ተሳክቶለታል::

ነገር ግን እግዚአብሔር ሲረዳን መፈለጉን ዝቅ አድርገን ልንመለከት አይገባም! እርሱ ይወዳናል፣ ሲረዳንም ይፈልጋል:: የነቢዩ ሶፎንያስ መልዕክት፣ "አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃያል ነው፣ በደስታ በአንቺ ደስ ይለዋል፣ በፍቅሩም ያርፋል፣ በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል" (ሶፎ 3፥17) የሚለው፣ በነቢዩ ዘመን ለኖሩ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለኛ እውን ነው::

## ለተጋድሎ ጥንካሬ

በቅርቡ አንድ ሰው፣ "ስህተቴ ምንድነው? ከሁለት ዓመት በፊት ሕይወቴን ለኢየሱስ ሰጥቼ ነበር፣ ነገር ግን ትክክል የሆነውን ነገር ለመሥራት የቻልኩ አልመሰለኝም" ብሎ ጻፈልኝ:: ምናልባት እናንተም እንዲሁ ተሰምቷችሁ ይሆናል::

ለተጋድሎው ጥንካሬ የምናገኘው እንዴት ነው? በጉዞስ ላይ ፀንተን የምንቀጥለው እንዴት ነው? ስለዚህ ጉዳይ ሁልጊዜ አስባለሁ፣ የማስበው የራሴን መንፈሳዊ ትግል እያስላሰልኩ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ጭምር ነው:: በየቀኑ በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ትግል ውስጥ እያለፍን ድል የምንቀዳጀውስ እንዴት ነው?

እኔ እንደማምነው፣ መልሱ ቀላል ነው፣ *ለመንፈሳዊ ድል ቁልፉ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣብቆ መኖር ወይም እግዚአብሔርን መቅረብ ነው*:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተመለከተ፣ "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ፣ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል" (ያዕቆብ 4፥7-8) በማለት ይገልጻል:: *ተገዙ . . . ተቃወሙ . . . ቅረቡ* - መንፈሳዊ ድል ለመቀዳጀት እነዚህን ማድረግ አለብን::

ለእግዚአብሔር መገዛት ምን ማለት እንደሆነ አስቀድመን ተመልክተናል:: መገዛት ማለት ሁለተናችንን ለክርስቶስ ማስረከብ ማለት ነው:: መገዛት ማለት ፈቃዳችንን መተውና ራሳችንን ለርሱ ሥልጣን አሳልፎ መስጠት ማለት ነው:: ሁለተናችሁን ለክርስቶስ ጌትነት አስገዝታችኋል? ይህ መሆን ያለበት ቀዳሚ ርምጃችሁ ነው::

በማናገረን ጊዜ ሙሉ ለሙሉ የሆነ መሰጠታችንን (ትኩረታችንን) ይፈልጋል።

ፀሎትና ማሰላሰል አስፈላጊ ናቸው። በምንፀልይበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር እንናገራለን - እናም በልባችን ያለውን ደስታና ሸክም እንገልጽለታለን። በምናሰላስልት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል እናመነዥካለን፣ በሕይወታችንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳን እንጠይቀዋለን። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንዳስተማራቸው በማስታወሻቸው መዝግበው ይይዛሉ። ብዙዎች ደግሞ ለማንና ለምን እንደፀለዩ የፀሎት ዝርዝር ይይዛሉ (የእግዚአብሔርን መልስ ደግሞ ይመዘግባሉ)።

*በመጨረሻም፣ በየዕለቱ በሞላ ጊዜአችሁ የእግዚአብሔርን መገኘት ልትለማመዱ ይገባል።* መዝሙረኛው እንዲህ አለ፣ "አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው" (መዝ 119፥97)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ያለማቋረጥ ፀልዩ (1ተሰ 5፥17) ይለናል። ሁልጊዜ ከአንድ ሰው ጋር በምንጋገርበት ጊዜ እንኳን፣ በፀጥታ ለሌሎች ስፀልይ ራሴን አገኘዋለሁ። በዕለቱ ማለዳ ያነበብኩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በአእምሮዬ አሰላስለዋለሁ። ያልተጠበቀ ነገር በሚከሰትበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር እነግረዋለሁ፣ የርሱንም ጥበብ እሻለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ በእውነት ለሚጠሩት ቅርብ ነው" (መዝ 145፥18) ይላልና። በየቀኑ በያንዳንዱ ሰዓት የእግዚአብሔርን መገኘት ተለማመዱ።

### ሰላም በወጀብ ውስጥ

ከቶ አትዘንጉ፤ ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ብቻ የሚያከትሙ በጣም ብዙ የማይታዩ መንፈሳዊ ትግሎች (ግጭቶች) በጉዞአችን ያጋጥሙናል። ነገር ግን ከቁጥጥራችን በላይ በሆኑ ኃይላት ፍላጎት ተሰፋ በሌለን ሁኔታ ተጠፍረን የተያዝን አይደለንም። ይልቅስ ምርጫ ያለን ነን፣ በየዕለቱ ምርጫ አለን - ምርጫው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ወይም ከእርሱ መራቅ ነው።

ለሰይጣን ዕድል ፋንታ አትስጡት፣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ራሳችሁን አስገዙ። እርሱ ብቻ ዋስትናችሁ ነው።





# ዐሥራ አንድ

## አስተማማኝ መሪያችን

*ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው።*

*(መዝ 119፥105)*

እምነት እንደ ለምለም አፈር በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሲተከል ያድጋል።

የዳንነው ብቻ ሳይሆን የምንኖረውም በእምነት ነው፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ መታጠፊያ ላይ የእግዚአብሔር ጸጋና እርዳታ ያሻናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ "የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" (2ቆሮ 5፥7)።

ታዲያ እምነታችን የሚያድገው እንዴት ነው?

### እምነታችን ሊያድግ ይችላል?

አንድ ሰው በቅርቡ እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፣ "እምነቴ ደካማ ነው፤ በእምነት መጠንከር እፈልጋለሁ፤ ግን ይህን ማድረግ የምችለው እንዴት ነው? ይህ የዚህ ሰው ብቻ ሳይሆን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ክርስቲያኖች ጥያቄ ነው። እምነት ለተለዩ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነገር ነው? እምነት ማለት ጥርጣሬን ማዳፈንና የሌለ ማስመሰል ማለት ነው? እምነት ሊያድግና ሊጠነክር ይችላል?

ለመጨረሻው ጥያቄ መልሱ አዎን ሊያድግ ይችላል ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እምነታችንን እንዲያድግ ስለሚፈልግ ነው። በተጨማሪም ለእምነታችን ማደግ የሚያስፈልገንን ሁሉ አቅርቦልናል። እነዚህ ጸጋዎች የተካነ የእንጨት አናጺ እንደሚጠቀማቸው መሣሪያዎች፣ የጐረበጡና ቅርጽ የለሽ እንጨቶችንም ያማሩ አድርገው መቅረጽ የሚችሉ ናቸው።

## የእግዚአብሔር ቃል

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህም በበለጠ ምክንያት ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፤ *መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው::* እርግጥ ነው የተደረሰው በተለያዩ ሰዎች ነው፤ *ይሁን እንጂ ከሰዎቹ በስተጀርባ ሌላ ደራሲ ማለትም የእግዚአብሔር መንፈስ አለ::* እነኚህ ሰዎች ለራሳቸው ሳይታወቃቸውም እንኳን እግዚአብሔር ይመራቸው ስለነበር የሚጽፉት የራሳቸውን ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ነበር:: ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል:- "ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጉመው አይደለም፤ ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም" (2ጴጥ 1፥20-21):: እግዚአብሔር እኛ በምንረዳው ቃል ተናግሮናል፤ እነዚህም ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ተካትተዋል::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያሏቸው አስተሳሰቦች ጥርቅም ወይም ሰዎች በየዘመናቱ ለኑሮ መርህነት የቀረጹት መመሪያ አይደለም:: ይልቁንም *የእግዚአብሔር ቃል ነው፤* ልዩነቱም በዚህ ነው:: ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያነሳቸው ጉዳዮች ሁሉ ለኛ ባለሥልጣን ነው ማለት ነው:: ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳየን መመሪያ ነው ማለት ነው:: ከሁሉም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔርና እግዚአብሔር በክርስቶስ ስላዘጋጀልን መዳን የሚያስተምረን መመሪያችን ነው:: ብሉይ ኪዳን ስለክርስቶስ መምጣት ይጠቁመናል፤ አዲስ ኪዳንም ስለመምጣቱ ይነግረናል:: ከዘፍጥረት እስከ ራእይ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ልጅ ወደራሱ የመመለስ ታላቅ ዕቅዱን ይተርክልናል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ርዕስ - ጉዳይ ድነት ሲሆን፣ ማዕከላዊ ሰብእ ደግሞ ክርስቶስ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ለኛ የቀረበልን የእግዚአብሔር ገፀበረከት ነው:: ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑ፣ የሚያመለክተውም ወደ እግዚአብሔር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ እንዲህ ይላል:- "ቅዱሳት መጻሕፍት፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናትና በጽድቅ መንገድ ለመምከር፣ ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር





ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው" (2ጢሞ 3፥16-17)::

## ልንተማመንበት እንችላለን?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ፣ ሰይጣን የዚህን ተቃራኒ እንድናምን ሊያደርገን ቢሞክር መደነቅ የለብንም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሰይጣን የተናገረው የመጀመሪያው ቃል እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የተናገራቸውን ቃል ጥርጣሬ ላይ መጣል ነበር (ዘፍ 3፥1):: በመቀጠልም ከዚህ በበለጠ ድፍረት እግዚአብሔር የተናገረውን በግልጽ ሲቃረን እናያለን (ዘፍ 3፥4):: ከዚያ የዕልመት ቀን ጀምሮ፣ ሰይጣን ያስመታከት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛነትና ሥልጣን እንድንጠራጠር ማድረግ ነው:: በ1949 የበጋ ወራት እኔና የአገልግሎት አጋሮቼ፣ በአገልግሎታችን በስፋቱ ትልቁ የሆነውን የወንጌል ስብከት በሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ ለማካሄድ እየተዘጋጀን ነበር:: ይህ ዝግጅት በመገናኛ ብዙሃን ብዙ ትኩረት ባይሰጠውም፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያናት ለታቀደው የሦስት ሳምንት አገልግሎት ለመዘጋጀትና ለመጸለይ በአንድ ላይ ተሰባስበው ነበር:: እግዚአብሔር ይህን ስብከት እንድናካሄድ እንደመራን አመንን:: ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ይህን አገልግሎት ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንዲጠቀምበት በትጋት ይጸልዩ ነበር::

አገልግሎቱ ከመጀመሩ ከጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ፣ ግን በሕይወቴ ከዚያ ቀደም ገጥሞኝ የማያውቅ ብርቱና ፈታኝ የእምነት ቀውስ ገጠመኝ፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት እጅግ የማከብረው እብሮኝ በወንጌል የሚያገለግል ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ጥርጣሬ ገልጾልኝ፣ እኔም ሀሳቡን በጊዜ ብቀበል እንደሚያዋጣኝ በመንገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብዬ ማመኔን እንድተው ይወተውተኝ ጀመር:: "ቢሊ"፣ አለኝና፣ "ከዘመኑ በሃምሳ ዓመት ያህል ወደኋላ እንደቀረህ ታውቃለህ? አንተ እንደምታምነው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው ማመናቸው ዘመን ያለፈበት እየሆነ ነው:: እንደ የዋህ ነው የምታምነው" አለኝ:: ዘመናዊ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ይህን የመሰለ አቋሙን እንደሚያቀነቅኑለት እኔም በቅርብ አነብቤአለሁ::

ለወራት ያህል መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ ጥርጣሬ በአእምሮዬ ይጉላላ ጀመር፤ በሎስ እንጀለስ አገልግሎት በምሰብክበት ወቅት ጥርጣሬው ልቋቋመው ከምችለው በላይ ሆነብኝ:: አንድ

ውሎ አድሮ ለህልፈት መዳረጋችን አይቀርም:: ታዋቂ የሆነ ክርስቲያናዊ የርዳታ ድርጅት አስተዳዳሪ የሆነው ልጂ ፍራንክሊን፣ የረሃብ ሰለባ ሆኖ ለማልቀስ እንኳን የጉልበት እንጥፍጣፊ ያልቀረው ህፃን ልጅ በዕቅፍ መያዝ ምንኛ ልብ እንደሚሰብር ነግሮኛል::

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ያቀረበላቸውን መንፈሳዊ ምግብ ችላ ብለው በመንፈሳዊ ረሃብ ደክመዋል:: *መጽሐፍ ቅዱስ የአማራጭ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ነው::* ያለ ቃሉ በመንፈስ ልትበረቱ አትችሉም:: ኢዮብ እንዲህ ብሏል፡- "የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ደገፍሁ" (ኢዮ 23፥12):: እናንተስ ለመጽሐፍ ቅዱስ ይህን ያህል ዋጋ ሰጥታችሁታል?

## ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ትውውቅ ማድረግ

የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ልትረዱ የምትችሉት እንዴት ነው? የሕይወታችሁ ድርና ማግ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

*በቅድሚያ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ተማሩ::* እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳትና ለሌሎች የማስተማር ልዩ ብቃት ሰጥቷቸዋል:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይናገራል፡- "እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶቹን፣ አስቀድሞ ሐዋርያትን … ሦስተኛም አስተማሪዎችን … መድቦአል" (1ቆሮ 12፥28):: የቤተክርስቲያናችሁ መጋቢ መጽሐፍ ቅዱስን ሲሰብክ በጥንቃቄ አድምጡት፤ በተጨማሪም በቤተክርስቲያናችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሲዘጋጅ ተሳተፉ:: በሬዲዮ የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመከታተል ሞክሩ (እንደ ፊባ ሬድዮ ዓይነት):: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥበት ኮንፍራንስ ተሳታፊ ሁኑ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ የየዕለት የጥሞና መጻሕፍትንም ብዙዎች ጠቃሚ ሆነው አግኝተዋቸዋል:: እነዚህ የጥሞና መጻሕፍት ለየዕለቱ አንድ ወይም ሁለት ጥቅስ ብቻ በማብራራት ቢወስኑም እግዚአብሔር እናንተን ለማነጽ ሊጠቀማቸው ይችላል::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየታዩ ካሉ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡ በመላው ዓለም ክርስቲያኖች እየተሰባሰቡ መጽሐፍ ቅዱስን በአንድነት ማጥናታቸውና ሀሳቦች መለዋወጣቸው የተለመደ እየሆነ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የክርስቶስ





ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ" (ቆላ 3፥16):: ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተስፋ ሰጥቶናል፣ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" (ማቴ 18፥20)::

*ሁለተኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችሁ አንብቡ::* መጽሐፍ ቅዱስን አንብባችሁ የማታውቁ ከሆነ ወይም ጀምራችሁ አልዘለቅ ብሏችሁ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችሁ እንድታጠኑ አበረታታችኋለሁ::

ይህን ልታደርጉ የምትችሉት እንዴት ነው?

*በመጀመሪያ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በደስታ ቅረቡት::* መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ደስታ እንጂ ሸክም መሆን የለበትም! ለዛሬዋ ባለቤቴ ሩት በመጀመሪያ ያቀረብኩላትን የጋብቻ ጥያቄ መቀበሏን በደብዳቤ ስትገልጽልኝ የተሰማኝ ደስታ አሁን ድረስ በግልጽ ይታወሰኛል:: ያን ደብዳቤ በዚያ ቀን ብዙ ጊዜ አንብቤዋለሁ:: እግዚአብሔርም በቃሉ ሊናገረን ይፈልጋል እንዲያውም ቃሉ ለእኛ የተላከልን የፍቅር ደብዳቤ ነው:: ታዲያ ለምን በደስታ አናነበውም?

*ቀጥሎም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በጸሎትና በመጠባበቅ ልብ ቅረቡት::* እግዚአብሔር በቃሉ እንዲናገራችሁ ጠይቁት፣ ይህን እንደሚያደርግ እመኑ:: ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን በከፈታችሁ ቁጥር አዲስ ነገር ታገኛላችሁ ማለት አይደለም:: አዲስ እውነትን መግለጥ ብቻ ሳይሆን የተማርነውንም እውነት ያጸናልናል:: የመዝሙረኛው ጸሎት የእናንተም ጸሎት ይሁን፤ "ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ ዐይኖቼን ክፈት" (መዝ 119፥18)::

*በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሥርዓት ባለው መንገድ አጥኑት::* አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲህ በነሲብ ገልጠው ማንበብ ወይም የሚያውቋቸውን ክፍሎች መደጋገም ይቀናቸዋል:: እግዚአብሔር በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሊናገረን ችግር ባይሆንበትም መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ ብቻ እንድንወሰን እንዳልተጻፈ ማስታወስ አለብን:: መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መንገድ ዘወትር የማንበብ ልማድ አዳብሩ፤ ይህም በአንድ ጊዜ አንድ መጽሐፍ በማንበብ ማለት ነው:: ለሰዎች የምመክረው ከወንጌላቱ የአንዱን (ለምሳሌ የዮሐንስ ወንጌል) ጥቂት አንቀጾች በአንድ ጊዜ በማንበብ ቢጀምሩ መልካም እንደሆነ ነው:: በመቀጠልም የሐዋርያት ሥራን (ስለ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች

*አምስተኛ፣ ስለ ውጤቱ በእግዚአብሔር ተማመኑ፡፡* ሰዎች በተደጋጋሚ ከሚጠይቁኝ ጥያቄዎች አንዱ ስለማይመለሱ ፀሎቶች ነው፡፡ አንድ ሰው ፍርጥ አድርጐ "እግዚአብሔር ደንቆሮ መሆን አለበት" በማለት ጽፎልኛል፡፡ ሌላው ሰው ደግሞ "የኔ ፀሎቶች ከቶ ከጣሪያ በላይ የማይወጡ ናቸው" ብሏል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለኛ የተሻለው (የሚሻለው) ምን እንደሆነ ያውቃል፣ እናም ስለ ጸሎታችን ውጤት በርሱ መተማመናችንን ልንለማመድ ይገባናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለአንድ ለሆነ ነገር በምንጠይቀው ጊዜ "አዎን" ይላል (ይፈቅዳል)፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ "ቆይ" ይሆናል መልሱ፣ ወይም "አይሆንም" የሚል ይሆናል፡፡ አንዳንዴም ደግሞ መልሱ "ባትረዳኝም እንኳን በኔ ታመን" የሚል ይሆናል፡፡

የባለቤቴ የሩት አባት፣ ዶ/ር ቤል፣ ሁልጊዜ የሚጸልይላቸውን ሰዎች ዝርዝር ይይዛል፡፡ ዶ/ር ቤል ከሞተ በኋላ ባለቤቴ ሩት ከአባቷ ከፀሎት ዝርዝሮቹ አንዱን አግኝታ ነበር (በፍፁም የማይነበብ ነው፣ ዶክተሮች እንዴት እንደሚጽፉ ታውቃለህ ብላ ነበር)፡፡ ነገር ግን በዝርዝሩ ውስጥ ስለልጆቻችን የነበረውን የፀሎት ሸክም ጽፎ ነበር፡፡ ዶ/ር ቤል ለልጆቻችን ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ የነበረው ፀሎት መልስ የመጣው እርሱ ከሞተ ከአምስት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ ይህ እግዚአብሔር ጸሎትን በታማኝነት እንደሚመልስና በኛ ጊዜ ሳይሆን በራሱ ጊዜ እንደሚሠራ ግልጽ የሆነ ቀስቃሽ ማስረጃ ነው፡፡

*በመጨረሻ፣ ማድመጥን ተለማመዱ፡፡* መፀለይ ማለት ለእግዚአብሔር መንገር ነው፣ ነገር ግን አንዳንዴ በፀሎት ጊዜአችን በፀጥታ ሆነን እርሱ ይናገረናል፡፡ ስለርሱ መገኘት (ህልውት) ውስጣዊ ማረጋገጫ ሊሰጠን ይችላል፣ ወይም በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ ይመራናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በትዕግሥትህ ጸንተህ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለማየት ተጠባበቅ" (መዝ 37፥7) ይላል፡፡

ዛሬ፣ ፀሎትን የሕይወታችሁ ማዕከላዊ በማድረግ ጀምሩ፡፡ የኢየሱስን ምሳሌነት በመገንዘብ ፀልዩ፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነ ፀልዩ፡፡ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አባት እንድንደርስ ስለሞተ ጸልዩ፡፡ እግዚአብሔር ምስጋናና ውዳሴአችሁን ስለሚፈልገው ጸልዩ፡፡ የርሱ ምህረት፣ ማንፃት፣ ምሪትና ጥበቃ ስለሚያስፈልጋችሁ ፀልዩ፡፡ ሌሎች ሰዎች ጸሎታችሁን ስለሚፈልጉ ፀልዩ፡፡ ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር በዘረጋላችሁ በዚህ የሕይወት ጉዞ እርሱ የእናንተን ህብረት ስለሚፈልግ፣ እናንተም የርሱ ህብረት ስለሚያስፈልጋችሁ ፀልዩ፡፡





# ዐሥራ ሦስት

## በአንድነት መጓዝ

***ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡***

**(ማቴ 18፥20)**

የእኛ አባልነት ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለእርስ በርሳችንም ነው፡፡

እግዚአብሔር በሰጠን በዚህ የሕይወት ጉዞ የምንጓዘው ብቻችንን አይደለም፤ ሌሎችም ከኛ ጋር እየተጓዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን ባንድ ውድድር ወይም በማራቶን ሩጫ እንደሚሆነው ለማሸነፍ እርስ በርሳችን እየተወዳደርን አይደለም፣ ወይም ደግሞ ከሌሎች ቀድሞ ለመግባት እየሞከርን አይደለም፡፡ በዚህ ጉዞ ደስታዎቻችንን እየተከፋፈልን፣ ሸክሞቻችንንና የልብ ስብራቶቻችንን እየተሸካከምን ባንድነት እየተጓዝን ነው፡፡ አንዳንዶች ቢደናቀፉ፣ በእግሮቻቸው እንዲቆሙ እናግዛለን፤ አንዳንዶች አቅጣጫ ቢለውጡ፣ እንዲመለሱ እንጐተጉታለን፡፡ በዚህ ጉዞ ላይ ያለን ሁላችን ባንድ ቤተሰብ - የእግዚአብሔር ቤተሰብ - ውስጥ ያለን ወንድሞችና እህቶች ነን፡፡

ይህ ቤተሰብ አዲስ ኪዳን "ቤተክርስቲያን" ብሎ የሚጠራው ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ሲባል በጭራሽ አንድ የተወሰነ ሕንፃ ወይም ማኅበረ-ምዕመናን ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑ ሁሉ መንፈሳዊ ህብረት ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ስንሆን፣ የርስ በርሳችንም እንሆናለን፤ ለክርስቶስ ሕይወታችንን ከሰጠን ለርስ በርሳችንም የተሰጠን ነን፡፡ ምክንያቱ ቀላል ነው፣ አንዳችን ለሌላው እናስፈልጋለን፡፡ "ቤተክርስቲያን" ብለን የምንለው

## ለምን እችገራለሁ?

የሴትዮዋ ጥያቄ ብዙዎች፣ ክክርስቶስ ጋር ጠንካራ ቃል ኪዳን ያደረጉ እንኳን ሳይቀሩ፣ የሚጠይቁት ዋና ጥያቄ ነው። በአጥቢያ (በአንድ አካባቢ) ማህበረ-ምዕመናን አባላት ሆነን ባንድነት የተሰባሰብነው ለምንድነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢያንስ አራት ምክንያቶችን አቀርባለሁ።

*አንደኛ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ አንድነት ያስፈልገናል።* እግዚአብሔር ለምሥጋናችን ዋጋ ይሰጠዋል፣ በመሆኑም ስናመልከው እናከብረዋለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎች፣ "ወደ ደጆቹ በመገዛት ወደ አደባባዮቹም በምሥጋና ግቡ፣ አመስግኑት፣ ስሙንም ባርኩ" (መዝ 100፥4) ተብለው ታዘው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በህብረት የምንሆነው፣ "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ" (ቆላ 3፥16) ስለተባልን እንደሆነ ይነግረናል።

የተለያዩ ቤተክርስቲያናትን ጎብኝታችሁ ከሆነ፣ የአምልኮአቸው ሥርዓት (መንገድ) አንድ ዓይነት እንዳልሆነ ታውቃላችሁ። አንዳንዶች በአገልግሎታቸው በጣም ግልጽ አይደሉም፤ የአንዳንዶች በጣም የታወቀ ሲሆን የብዙዎች ደግሞ ከሁለቱም ያልሆነ ነው። አንዳንድ ቤተክርስቲያናት (የጌታ እራት አገልግሎትን በተመለከተ) ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ ለቅዱስ ቁርባን ሥነ ሥርዓት ትኩረት ይሰጣሉ።

አምልኮን በተመለከተ ካንድ መንገድ በስተቀር ሌሎች ሁሉ ስህተት ናቸው ማለት ነው? በርግጥ አይደለም። የእናንተ የአምልኮአችሁ መንገድ ከሌሎች ይልቅ ለናንተ ምቹ ሲሆን ይችላል፤ ዋናው ነገር በአምልኮና በምስጋና ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ላይ ነው። (ይሁን እንጂ፣ ከናንተ በተለየ መንገድ የሚያመልኩትን አትናቁ። እግዚአብሔር አምልኮአችንን ከምናቀርብበት መንገድ ይልቅ ልባችንን ይመለከታል።) አምልኮ እንደ መዝናኛ ሲታሰብ አይገባም፤ በህብረት የምንሆነው እግዚአብሔርን ለማምለክ እንጂ ራሳችንን ለማዝናናት አይደለም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም ሆኖአል፣ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና" (ዮሐ





4፥23)። ይህን አስተውሉ፤ እግዚአብሔር በእውነት የሚሰግዱለትን (የሚያመልኩትን) ይሻል።

*ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በአንድነት ለመስማት ህብረት ያስፈልገናል።* እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በግል በምናጠናበት ጊዜ ይናገረናል፤ ነገር ግን ደግሞ ሌሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲያስተምሩና እንዲቀሰቅሱ ወይም እንዲሰብኩን ልዩ ስጦታ ሰጥቷቸዋል፣ በህብረት የምንሆንበትም አንዱ ምክንያት ከነርሱ ለመማር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፤ እግዚአብሔር፤ "አንዳንዶቹ . . . እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" (ኤፌ 4፥11) ይላል። ጳውሎስ፣ "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥፁ" (ቆላ 3፥16) በማለት ጽፏል።

የተለያዩ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲህ እያሉ ይጽፉልኛል፣ "ከቤተክርስቲያን የማገኘው ነገር የለም"። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች በሳምንት አንድ ቀን የሚሄዱ እንደሆኑና ቤተክርስቲያን በምትሰጣቸው በሌሎች ዕድሎች - በክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል መማር፣ በቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ ልዩ ድርጊቶች፣ በመንፈሳዊ ሽርሽሮችና በመሳሰሉ - ስለማይካፈሉ እንደሆነ ደርሼበታለሁ። አንዳንድ ጊዜ የመጋቢያቸውን ስብከት በማስታወሻ እንዲይዙ እመክራቸዋለሁ። ይህ ዓይነቱ ልምምድ ዋና ነጥቦችን እንዲያስታውሱ የሚያግዛቸው ከመሆኑም በላይ መጋቢያቸው ይህን ሲያውቅ በበለጠ በጥንቃቄ እንዲዘጋጅበት ያበረታተዋል።

*ሶስተኛ፣ እርስ በርስ ለመተናነጽ ህብረት ያስፈልገናል።* በሕይወቱ ምንም ዓይነት ችግር እጋጥሞት የማያውቅ ሰው ገጥሞኝ አላውቅም። እንደዚሁም ከፈተናዎች ወይም ከተፅዕኖዎች ነፃ የሆነ አማኝ ገጥሞኝ አያውቅም፣ አንዳንድ አማኞች ክርስቲያን የመሆን ፋይዳው ምኑ ላይ ነው እስኪሉ ድረስ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። የእርስ በርስ ማበረታቻና (ምክር) ጥበብ የሚያስፈልገንም ለዚሁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ "አንዳንዶች ማድረጉን እንደተውት መሰባሰባችንን አንተው፣ ይልቁንም ቀኑ (ክርስቶስ የሚመለስበት) እየተቃረበ መምጣቱን ስታዩ እርስ በርሳችን እንበረታታ" (ዕብ 10፥25)።

(ከመካከላቸው አንዱ ከነጭራሹ እውነተኛ ደቀመዝሙር አልነበረም) ሆኖም ሕይወቱን በእነርሱ ላይ በማፍሰሱ ዓለምን የሚለውጥ ሥራ ሰርተዋል። ምናልባትም እግዚአብሔር አንድ ወይም ሁለት ክርስቲያኖችን ጓደኛ በማድረግ በእምነት እንዲያድጉ እንድትረዷቸው ጥሪ እያቀረበላችሁ ይሆናል። ጳውሎስ ለወጣት የአገልግሎት አጋሩ ለሆነው ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ይመክረዋል "ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" (2 ጢሞ 2፡2)።

ይሁንና በግለሰብ ደረጃ የምናደርገው ኅብረት ለማኅበረ ምዕመናን ኅብረት ምትክ አይደለም። ክርስቶስ በሚሰበክባትና መጽሐፍ ቅዱስን የምታስተምር ቤተክርስቲያን አባላት ከሆናችሁ ስለዚህ ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ መንፈሳዊ መታነጽ ሊሰጧችሁ የሚችሉ ማንኛቸውንም አጋጣሚዎች ተጠቀሙ። የቤተክርስቲያን አባላት ካልሆናችሁ (ወይም አሁን ባላችሁበት ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወት እያደጋችሁ ካልሆነ) እግዚአብሔር ለናንተ ወዳዘጋጀላችሁ ቤተክርስቲያን እንዲመራችሁ ጠይቁት። አዲስ አማኝ ከሆናችሁ ወይም ለቤተክርስቲያን አዲስ ከሆናችሁ መጀመሪያ ላይ ሁሉም ነገር ላይገባችሁ ቢችልም፤ ሐፍረት አይያዛችሁ። መቆም ሲገባችሁ ባትቆሙ ወይም ከመዝሙር መጽሐፍ ላይ የሚዘመረውን መዝሙር ገጹን መለየት ካልቻላችሁ፤ ክርስቶስን የሚወዱ ሰዎች አይንቁአችሁም፤ ይልቁንም ለናንተ ስለሚጠነቀቁ ሊረዷችሁ ይችላሉ።

ለናንተ የሚሆናችሁን "ትክክለኛ" ቤተክርስቲያን የምታገኙት እንዴት ነው? በአካባቢያችሁ ያሉ የሌሎች ክርስቲያኖችን ምክር ጠይቁ፤ ስለተለያዩ ቤተክርስቲያናት ለማወቅ ሞክሩ፤ የቻላችሁትን ያህል የተለያዩ ቤተክርስቲያናትን በመጎብኘት የሚስማማችሁን ለመምረጥ ወስኑ። በተጨማሪም ይህን ምርጫ ስታደርጉ ያላችሁበትን ሁኔታ ከግምት አስገቡ። ለምሳሌ፡- ልጆች ካሉአችሁ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ የተነቃቃ የወጣቶች ፕሮግራም ያለው ቤተክርስቲያን አባል መሆኑ መልካም ነው። ሳምንታዊ የአምልኮ ፕሮግራም አስፈላጊ ቢሆንም ሌሎች ፕሮግራሞች ለምሳሌ፡-





የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የተሃድሶ ፕሮግራም፣ በተለያዩ ዕድሜ ላሉ ሰዎች የሚሆኑ ፕሮግራሞች እንዳሉ ማየቱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ የመዘምራን፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የወንጌል ስብከቶች አገልግሎቶች፣ እና የመሳሰሉትን ልትሳተፉ የምትችሉባቸውን ዕድሎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ጥምቀት ወስዳችሁ የማታውቁ ከሆነም፣ ቤተክርስቲያንን ስትቀላቀሉ ይህን ይፋዊ ውሳኔ የአዲስ ሕይወታችሁ አካል አድርጉት።

ከሁሉም በላይ ግን፣ እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ጸልዩ። ምክንያቱም እርሱ ለእናንተ የሚሆናችሁን ቤተክርስቲያን ያውቃል። ፍፁም ቤተክርስቲያን የለም፤ ሆኖም በዚህ ሳቢያ ልባችሁ ሊዝል አይገባም። አንድ ሰው እንደተናገረው "ፍፁም የሆነች ቤተክርስቲያን ካገኛችሁ እናንተ በተቀላቀላችኋት ቅጽበት ፍጽምናዋ ያበቃል" ሲል ተናግሯል።

እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁ ይህ ጉዞ ብቻችሁን የምትጓዙት አይደለም። እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ነው፣ እንደዚሁም የእርሱ ሕዝብ አብሯችሁ ነው። ለናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ሁሉ፣ እናንተም ለነርሱ ታስፈልጓላችሁ።

# ዐሥራ ዐራት

## ዘወትር የማይለየን አጋዣችን

*ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ::*

(የሐዋ.ሥራ 1፥8)

በዓለም ውስጥ ክርስቲያንን ከሌላ ሰው የሚለየው ምንድነው?

በርግጥ፣ ይህን ጥያቄ በተለያዩ መንገዶች ልንመልሰው እንችላለን:: አንድ ክርስቲያን፣ ከሌሎች ክርስቲያን ካልሆኑ ጓደኞች የሚለየው የቤተክርስቲያን አባል ስለሆንኩ ነው ሲል ይችላል:: ሌላዋ ደግሞ ከሌሎች የሚለየኝ ኃጢአቴ ይቅር ስለተባለና ወደመንግሥተ ሰማያት ስለምሔድ ነው ልትል ትችላለች:: ሌላ ሰው ደግሞ ክርስቲያኖችን ከሌሎች የሚለያቸው የሚያምኑት ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን፣ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን የሞተ አምላክ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሌሎችንም ሲል ይችላል:: ሌላ ሰው ደግሞ ክርስቲያኖች የሚለዩት በአኗኗራቸው ነው ሲል ይችላል (ታዛቢ ተመልካች የሚያውቃቸውን ክርስቲያኖች ግን ይህ ነው የሚባል ልዩነት እንደሌላቸው ሲናገር ይችላል)::

### በውስጣችን ያለው መንፈስ

እነዚህ አስተያየቶች ሁሉ እውነት የሆነ ነገር ቢኖራቸውም ምሉዕ ስዕል ግን አይሰጡም:: እንዲያውም፣ እግዚአብሔር በተሰመልን በዚህ መንገድ ላይ ስንጓዝ ልናስተውለው የሚገባንን





አንድ ወሳኝ እውነት ይዘላሉ:: ይህም ክርስቲያንን ከሌላ ከማንኛውም ሰው የሚለየው እግዚአብሔር ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጡ የሚያድር መሆኑ ነው:: ወደ ክርስቶስ ስንመጣና ሕይወታችንን ለእርሱ ስንሰጥ፣ እግዚአብሔር በልባችን ማደር ይጀምራል:: ሁልጊዜ የተለየ ስሜት ሳይሰማን ወይም ህልዎቱ (መገኘቱ) ላይታወቀን ይችላል:: ይሁንና ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ተፈጽሟል፤ "እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው" (ዮሐ 14፥16 - 17)::

በወንጌል ስብከት ፕሮግራም ላይ ክርስቶስን በተቀበልኩበት ምሽት የተለየ ኃይለኛ ስሜት አልተሰማኝም፤ ከአጠገቤ የነበረችው ሴት ስታለቅስ ሳያት፣ እኔ የማላለቅሰው አንድ ችግር ቢኖርብኝ ይሆናል ብዬ ማሰቤን አስታውሳለሁ::

ይሁንና በውስጤ አንድ የተለየ ነገር እንደተከሰተ አውቄ ነበር፤ በኋላ ላይ የዚህ ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ለማደር ስለመጣ እንደሆነ አወቅኩ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም" (ሮሜ 8፥9):: ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ከሰጣችሁ እግዚአብሔር አሁን በመንፈሱ በውስጣችሁ ይኖራል:: ክርስቲያን ከሆናችሁ ወደሕይወታችሁ እንዲመጣ ልትለምኑት አያስፈልጋችሁም:: አሁንም በውስጣችሁ ነው፤ በውስጣችሁ መኖሩን በመቀበል በእምነት ለእርሱ ኃይል መገዛት ብቻ ነው የሚያስፈልጋችሁ::

### የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልገናል

ሰው እንደ መሆናችን ሁለት ታላላቅ መንፈሳዊ መሻቶች አሉን:: የመጀመሪያው፣ የኃጢአት ይቅርታ ሲሆን፣ ይህን እግዚአብሔር ልጁን ወደዓለም በመላክ አሟልቶልናል:: ሁለተኛው፣ የሚያስፈልገን በጎነት ሲሆን፣ ይህንን እንድናገኝም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን እንዲያድር ልኮልናል::

## መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

ሰዎች ስለመንፈስ ቅዱስ ብዙ ዓይነት አስተሳሰቦች አሏቸው - ከነዚህ አንዳንዶቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን አይደሉም። አንዳንዶቹ መንፈስ ቅዱስን ሰብዕና (አካል) እንደሌለው ኃይል ይመለከታሉ፣ ለምሳሌ እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ወይም የስበት ኃይል ያስቡታል። ሌሎች ደግሞ መንፈስን የሚያስቡት ከስሜት ጋር በተያያዘ ብቻ ነው፤ የእግዚአብሔር መገኘት በውስጣቸው እንደሚሰማ ቢያስቡ፣ ይህን ስሜት ‹‹መንፈስ ቅዱስ›› ብለው ይሰይሙታል። ሌሎች ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ስለሚሰጣቸው ስጦታዎች ያስባሉ። እነዚህ ግን ዋናውን ቁምነገር ይስታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፈስ ቅዱስ *ሶስት ዓቢይ እውነቶችን* ይነግረናል።

*አንደኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰብእ ነው።* ሰብዕና ያለው አካል ያሉት ባህርያትና መገለጫዎች ሁሉ አሉት። ይናገረናል፣ ያዘናል፣ ለእኛ ይማልዳል፣ ይሰማናል፣ ይመራናል፣ ወዘተ። በተጨማሪም ልናሳዝነው ወይም ልንዋሸው እንችላለን፤ ከዚያም ባሻገር ልንሰድበው ወይም ልናስከፋው እንችላለን። እነዚህ ነገሮች በግዑዝ ኃይል ላይ ልናደርጋቸው የምንችል ነገሮች አይደሉም፤ ይልቁንም እነዚህን ማድረግ የሚችለው እርሱ ሰብእ ስለሆነ ነው። "የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል" (ሮሜ 8፥16)።

*ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።* መንፈስ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ኃይሉን በዚህ ምድር ላይ ለመግለጥና ፈቃዱን ለማከናወን የሚሠራበት የማይታይ አስተሳሳፊ ነው። ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት "የእግዚአብሔር መንፈስ በውሆች ላይ ይሰፍፍ ነበር" (ዘፍ 1፥2)። ኢዮብ እንዲህ ሲል ያውጃል፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጥሮኛል" (ኢዮብ 33፤4)። ሳምሶን "የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል እንደ ወረደበት" እና ካሠሩት ሰዎች ራሱን ነጻ ማውጣት እንደ ቻለ እናነባለን (መሳ 15፥14)። እግዚአብሔር ባስልኤልን ለምች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበትን የመገናኛ ድንኳን እንዲገነባ ኃላፊነት ሲሰጠው እንዲህ ብሎታል፣ "በሁሉም ዓይነት የእጅ ጥበብ ሥራ፣ ብልሃት፣ ችሎታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞልቼዋለሁ" (ዘፀ 31፥3)

ከዚህም በላቀ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ስለኃጢአታችን በመውቀስ አዲስ ልደትን ይሰጠናል። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በየምሽቱ ወንጌልን ከሰበኩትና ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ ጥሪ ካቀረብኩላቸው በኋላ፣ በውስጤ ለእነርሱ ጥልቅ ሸክም ይሰማኛል። አንዳንድ ጊዜ እቅመቢስነትና ብቁ ያለመሆን ስሜት ይጫነኛል፤ ወንጌሉን ግልፅ አድርጌ ለማቅረብ የሚገባኝን ያህል አድርጌ ይሆን? ስል ራሴን እጠይቃለሁ። ይሁንና ሰዎቹ እውነቱን ማየት እንዲችሉ ዓይናቸውን ሊከፍት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደሆነም አውቃለሁ፤ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደዚያው ስፍራ ስንመለስ መንፈሳዊ ጉዞአቸውን በዚያች ቅዕበት የጀመሩ ሰዎች ይገጥሙኛል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ቃሌ በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም፤ ነገር ግን የምሻውን ያከናውናል፣ የተላከበትንም ዓላማ ይፈጽማል" (ኢሳ 55፥11)። ኢየሱስም እንደዚህ ብሏል፣ "ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው" (ዮሐ 3፥6)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ እንደዚህ ይላል፣ "ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው" (ጴጥ 1፥23)። በመንፈስ ዳግም ስንወለድ፣ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነታችን በማቆየት ሕይወታችንን ይለውጣል። እርሱ "የእርሱ ለመሆናችን ማኅተሙን ያተመብን ደግሞም ወደፊት ለምናገኘው ነገር የመንፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ እርሱ ነው" (2ቆሮ 1፥22)።

*ሶስተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።* ኢየሱስ ፍጹም እምላክ እንደሆነ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እርሱ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅና ሁሉን የሚችል እንደሆነም መጽሐፍ

ቅዱስ ይነግረናል፤ እነዚህ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑ መለያ ባህርያት ናቸው። (ሰይጣን እንደዚህ አይደለም፤ ኃያል ቢሆንም ሁሉን ቻይ ግን አይደለም።)

በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስ በማያሻማ መንገድ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ያውጃል "ጌታ መንፈስ ነው" (2ቆሮ 3፥17)። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን "የክርስቶስ መንፈስ" ወይም "የእግዚአብሔር መንፈስ" ብሎ የሚጠራበትም ጊዜ አለ፤ ይህም መለኮታዊ ባህርዩን ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአብሔር ለብእ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ለብእ ነው፤ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንደሆነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔር ባህርይ የሆነ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስም ነው፤ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው።

## ምስጢረ ሥላሴ

እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆኖ ከእግዚአብሔር እንዴት ሊለይ ይችላል? የሚል ጥያቄ ልታ ነሱ ትች ላላችሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ፤ ኢየሱስ ከሰማያዊ አባቱ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዴት ፍፁም አምላክ ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ እውነቶች አንዱ በሌላ በኩል ለማስተዋል እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑት ውስጥ የነገረ መለኮት ሊቃውንት *"የሥላሴ ምስጢር"* የሚሉት ነው። እግዚአብሔር ወደእኛ የሚመጣው በሶስት የተለያዩ መንገዶች እንደ አብ፣ እንደ ወልድና እንደ መንፈስ ቅዱስ - ሆኖ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምረናል። ጳውሎስ ከመልዕክቶቹ አንዱን እንዲህ ሲል ይደመድማል፦ "የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን" (2ቆሮ 13፥14)። ሶስቱ አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በአካል የተለያዩ ቢሆኑም እንደ አንድ ተዋህደዋል። ራሱን በሶስት አካላት የገለጠልንን አንድ አምላክ እንጂ፤ ሶስት አማልክት አናመልክም።





ይህንን እውነት በምናባችን እንዴት ልንቀርጽ እንችላለን? በመጀመሪያ ክርስትናን ወደ አየርላንድ ያመጣው ቅዱስ ፓትሪክ የተባለ ሰው፣ ምስጢረ ሥላሴን ለአዲስ ክርስቲያኖች ለማብራራት የሣር ዓይነት በምሳሌነት ተጠቅሟል፤ ቅጠሎቹ ሶስት ለየብቻ የሆኑ ቢሆኑም በአንድ ተክል ውስጥ ተዋህደዋል። ሌሎች ደግሞ ምሥጢረ ሥላሴን ለማብራራት የፀሐይን ምሳሌ ይጠቀማሉ፤ ፀሐይ ቦታ የምትይዝ ነገር ሆና ብርሃንና ሙቀትን ትሰጣለች - ሆኖም አንድ ናት። ውሃንም ምሳሌ የሚያደርጉ አሉ፤ ውሃ፣ ጠጣር ወይም ፈሳሽ ወይም ጋዝ ቢሆንም፣ ያው ውሃ ነው።

የአንድ ባልንጀራዬ ወጣት ልጅ አባቱን፣ እንዴት እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር፣ እንዲሁ ደግሞ ወልድ የሆነው ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊባሉ ቻሉ ብሎ ጠየቀው። ይህ ማለት ኢየሱስ የራሱ አባት ነው ማለት አይደለም እንዴ? ብሎ ግራ መጋባቱን ገለጸ (ሕፃናት እንደዚህ ዓይነት የተወሳሰቡ ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት ይችሉበታል)። በወቅቱ መኪና ውስጥ ተቀምጠው ስለነበር አባትዬው ድንገት በመጣለት ሀሳብ እንዲህ ሲል መለሰለት፣ "ይኸውልህ ልጄ የመኪናው ሞተር ውስጥ አንድ ባትሪ አለ፤ ይህን ባትሪ መብራት ለማብራት፣ ክላክ ስ ለመንፋት ወይም መኪናውን ለማንቀሳቀስ ልጠቀምበት እችላለሁ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለኔ ምስጢር ነው። ግን ይሆናል" ሲል መለሰለት።

እነዚህ ሥዕላዊ መግለጫዎች የሥላሴን እውነት እንድናስተውል ሊረዱን ይችላሉ፤ ሆኖም አንዳቸውም ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ ሊያብራሩት አይችሉም። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ በምድር እስካለን ሙሉ በሙሉ ልንረዳው የማንችል ምስጢር ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ የሚመጣልኝ ጳውሎስ እንዲህ ሲል የተናገረው ቃል ነው፤ "አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን" (1 ቆሮ 13፥12)። ሙሉ በሙሉ አናስተውለውም ማለት ግን እውነትነቱን ይቀንሰዋል ማለት አይደለም። ቅድስት ሥላሴ ስለሆነ

እግዚአብሔርን እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እናመልክዋለን።

## ወደ ምድር የመጣው ለምንድነው?

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ገና ከማለዳው (ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ) የሠራው መንፈስ ቅዱስ በመላው የብሉይ ኪዳን ዘመንም ሥራው ቀጥሏል። በአዲስ ኪዳን ጅማሬ ላይም ሲገለጥ እናያለን። መልአኩ ለድንግል ማርያም እንዲህ ሲል ያበስራታል:- "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱስ ሕጻን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃ 1፥35)።

ይሁን እንጂ፣ ይህ እስከ ጴንጤቆስጤ ቀን ድረስ ባይፈፀምም፣ መንፈስ ቅዱስ በልዩ መንገድ በደቀመዛሙርቱ ላይ የወረደው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ነበር (የሐዋ. ሥራ 2)። ኢየሱስ በአካል ከእነርሱ ጋር ሳለ አልመጣም ነበር፤ ዳሩ ግን ተለይቷቸው ሲሄድ መንፈሱን እንደሚልክላቸው የተስፋ ቃል ሰጥቷቸዋል። (መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ኢየሱስ በምድር ላይ አገልግሎቱ ወቅት፣ "ኢየሱስ ገና ስላልከበረ፣ መንፈስ አልተሰጠም ነበር" (ዮሐ 7፥39) የሚለው ለዚህ ነው።) ኢየሱስ ከነርሱ ጋር መሆኑ እውን የነበረውን ያህል መንፈስ ቅዱስም ከነርሱ ጋር መሆኑ እውን ሆኗል።

ኢየሱስ የመንፈስቅዱስን ሥራ ለመግለፅ የተጠቀማቸውን ቃላት ልብ ልንል ይገባል። ለምሳሌ መንፈስ ስለ ኀጢአታችን እንደሚወቅሰን ነግሮናል። "በሚመጣበትም ጊዜ ዓለምን ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል›› (ዮሐ 16፥8)። ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን በፊት መንፈስ ቅዱስ በቅድሚያ ስለ ኀጢአታችን በመውቀስ ዓይናችንን ለወንጌል እውነት ሊገልጥ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ አስተማሪያችንና መሪያችን ይሆናል። "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ 16፥13)። መጽሐፍ ቅዱስ በጣም አስፈላጊ





የሆነው ለዚህ ነው፤ ቃሉን እንድናስተውል የሚረዳን መጀመሪያውኑ በሐዋርያት አድሮ ያስጻፋቸው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው - ያለ እርሱ ትርጉሙን ሙሉ በሙሉ ልናስተውል አንችልም። በተጨማሪም በየዕለቱ ለሕይወታችን በሚያስፈልገን ምሪት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጥልናል።

እንደገናም ኢየሱስ ለሰዎች ስለክርስቶስ እንድንናገር ይረዳናል፤ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤. . . እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (የሐዋ. ሥራ 1፥8)። ስክርስቶስ ስንመሰክር መንፈስ ቅዱስ ጥርጊያ በመክፈት፣ ትክክለኛ ቃላት በመስጠትና ልባችንን በድፍረት በመሙላት ከፊታችን ቀድሞ ይወጣል።

በሕይወቱ ከማልረሳቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ከሶብየት ጂዮርጂያ ወደ አሜሪካ ስደተኛ ሆኖ የመጣ አስተማሪ ነው። ሶስት የዶክትሬት ዲግሪዎች ቢኖሩትም፣ በታወቀ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበረው ምሁር ቢሆንም ድብርት የሚጫነውና ደስታ የሸሸው ሰው ነበር። አንድ ቀን፣ ጫማውን እያስጠረገ ሳለ፣ ጫማ ጠራጊውን ሁልጊዜ ፊቱ በደስታ ብሩህ የሆነበትን ምክንያት ጠየቀው። ጫማ ጠራጊው በትህትና ግን በልበሙሉነት ደስታው የመነጨው ኢየሱስ እንደሚወደው በማወቁ፣ በኢየሱስ ምክንያት እንደሆነ ገለጸለት። ፕሮፌሰሩ ጫማ ጠራጊው የተናገረውን ቃል ሊያጣጥለው ቢሞክርም፣ በቀላሉ ከጭንቅላቱ ሊያስወጣው አልቻለም። በዚህ ሰው ቀላል ምስክርነት ሳቢያ፣ እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ - ይህም ፍለጋ ሕይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሰጥ አደረገው። በኋላ ላይ ያስተምርበት የነበረውን ትልቅ ዩኒቨርስቲ ተሰናብቶ፣ እኔና ባለቤቴ ሩት በተማርንበት ክርስቲያናዊ ኮሌጅ ማስተማር ጀመረ፤ በአስተማሪነቱም በሕይወቱ ላይ ትልቅ አሻራ ከተዉ ሰዎች አንዱ ነው። ይህ ለውጥ የተከሰተው መንፈስ ቅዱስ ያን ያልተማረ ጫማ ጠራጊ ሰው ለዚህ ልሒቅ አእምሮ ላለው ሰው እንዲመሰክር በማድረጉ ነው፣ ልሂቁ ሰው የተራቆተ ልብ (በርግጥ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ያዘጋጀው ልብ) ስለነበረውና

ሰመስካሪውም የመመስከር ድፍረትን ስለሰጠው ነበር። መንፈስ ቅዱስ በርግጥ እንድንመሰክር ይረዳናል።

### ክርስቶስን በመምሰል ማደግ

መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠበትን ሌሎች በርካታ ምክንያቶችን መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ያቀርብልናል። ከነዚህ አንዳንዶቹን በኋላ ዘርዘር አድርገን እንመለከታችዋለን። *መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ክርስቶስን በመምሰል ማደግ እንድንችል ለመርዳት ነው።* በራሳችን ጥረት ክርስቶስን መምሰል ስለማንችል የእግዚአብሔር እርዳታ ያሻናል። እርሱም መንፈስ ቅዱሱን በመስጠት እርዳታን ለግሶናል።

የክርስትና ሕይወትን በገዛ ራሳችሁ ጥረት ለመኖር እየሞከራችሁ ነው ወይስ በየቀኑ የሚያስፈልጋችሁን እርዳታ ይሰጣችሁ ዘንድ ወደ እርሱ እየተመለከታችሁ ነው? እዚህ ላይ ቆም ብላችሁ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ሊያድር ስለመጣ አመስግኑት። እርሱ ከእናንተ ጋር ስላለ፣ ከቶም ቢሆን ብቻችሁን አይደላችሁም።





# ዐሥራ አምስት

## የዕለት ስንቅ

*ነገር ግን በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ*

***(2ጴጥ 3፥18)***

ክርስቲያን መሆን የቅጽበት ውሳኔ ሲሆን በክርስትና መቆየት ግን የሕይወት ዘመን ሥራ ነው።

ከበርካታ ዓመታት በፊት፣ (ታሪኩ እንዲህ እያለ ይቀጥላል) መሐንዲሶች በገደልማ የወንዝ ሸለቆ ላይ ተንጠልጣይ ድልድይ ለመገንባት ይወስናሉ። እዚህ ላይ ትልቁ ችግራቸው የነበረው በጣም ከባድ የሆኑትን የብረት ኬብሎች ከአንድ የሸለቆ ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ መዘርጋት ነበር። በወቅቱ ሔሊኮፕተሮች አልተሠሩም ነበርና ኬብሎቹን በጀልባ ሆነው እንዳይዘረጉ ደግሞ በዐለቶች ላይ የሚጋልበው ፈረሰኛ ውሃ አደገኛ ነበርና አላሰቻላቸውም።

ጥያቄአቸው የመፍትሔ ያለህ? ሆነ። ለችግሩ መላ እየፈለጉ ሳለ፣ አንድ ቀን መሐንዲሶቹ በገደልማ ወንዝ ሸለቆ ላይ ወላንዶ (በገመድ ታስሮ በአየር የሚለቀቅ መጫወቻ) ለማብረር ሃሳብ መጣላቸው። ወላንዶዋ በወዲያኛው ጫፍ ላይ ስትደርስ፣ ሆን ብለው መሬት ላይ አሳረፉአትና ሁለቱ የወንዝ ዳርቻዎች በቀጭን የወላንዶ ገመድ ተገናኙ። በመቀጠልም በአንደኛው የወላንዶ ገመድ ጫፍ ላይ ወፈር ያለ ገመድ በማሰር በጥንቃቄ ወደ ሌላኛው ጫፍ አጓጓዙት። ይህንን በርካታ ጊዜ በመደጋገም ቀጭን ገመድ ከዚያም ወፍራም ገመድ በመደራረብ ከባድ የብረት ኬብሎችን በገደልማ ወንዝ ሸለቆ ላይ በማድረግ ድልድዩን ገነቡ።

የወላንዶ ገመድ ብቻ አሻግረው ቢቀሩ ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? ወይም ደግሞ የወላንዶዋን ስኬታማ በረራ ብቻ ምክንያት ስማድረግ ድላቸውን ለማክበር የወር እረፍት ቢወስዱ ኖሮስ? ድልድዩ ሳይሰራ ይቀር ነበር፤ ይህ ብቻ ሳይሆን የወላንዶዋ ገመድ በንፋስና በፀሐይ ተጎድቶ ይበጠስ ነበር።

## ወደ ብስለት ማደግ

መንፈሳዊ ዕድገት ከዚህ ድልድይ ግንባታ ጋር ተመሳሳይ ነው። በመጀመሪያ እምነታችን ትንሽና በቀላሉ የሚጎዳ ስለሚሆን፣ በብርቱ ማዕበሎችና ፈተናዎች የሚናወጥ ሊሆን ይችላል። ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም! ሁለቱ የወንዙ ዳርቻዎች ቀስ በቀስ እንደተጋጠሙ ሁሉ፤ እግዚአብሔርም እምነታችን ዕለት ዕለት እንዲጠነከር ይሻል። የእግዚአብሔር ሀሳብ መለወጣችን ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ብስለት ማደጋችንም ነው።

አዲስ ክርስቲያን በእምነቱ (በእምነቷ) ከቶ ዕድገት ባይኖርና ሁልጊዜ መንፈሳዊ "ሕጻን" ሆኖ (ሆና) ማየት የሚያሳዝን ነገር ነው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ልክ እንደ ወላንዶዋ ገመድ፣ የመጀመሪያውን ወሳኝ እርምጃ ወስደው ከዚያ በኋላ ግን ባሉበት ቀርተዋል። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን ከተቀበልን በኋላ፣ በጭንጫና በእሾሃማ መሬት ላይ እንደተዘራ ዘር በዚህ ዓለም ሀሳብ ጠውልገና ታንቆ እንዳይቀር አስጠንቅቆናል (ሉቃ 8፥1-15)። ይልቁንም ‹‹ቃሉን ቅንና በጎ በሆነ ልብ ሰምተው የሚጠብቁ፣ ታግሰውም በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ›› (ሉቃ 8፥15) እንድንሆን ነግሮናል።

ሰብል በአንድ ጀንበር በቅሎ አይደርስም። ለማሸት ጊዜ ያስፈልገዋል፤ ገበሬውም ብርቱ ትጋት ይጠበቅበታል። በተወለድኩበት ዕለት እናቴ ለበርካታ ሰዓታት ያህል ከእርሻ መሬታችን ላይ የባቄላ እህል እየለቀመች ለእሸጋት (እንዲታሸግ) ታዘጋጀው ነበር። ሥራውን ማከናወን እንዳለባት በማመን፣ ለራሷ ፋታ መስጠት አልፈለገችም። ገበሬዎች እርሻቸውን ችላ ቢሉ፣ ወይም ማሳቸውን ማጨድ ቢተው፣ ዓለማችን ምን ትመስል ነበር? ታዲያ በመንፈስ ደካማና ልፍስፍስ ስንሆን፣ ነፍሳችን ይኸው





ዓይነት ዕጣ እንዲገጥማትና እንድትጠወልግ እየፈቀድን ነው። እንግዲያውስ ምን ይበጀናል?

## ግባችን ላይ ማነጣጠር

እንደ "ደቀመዛሙርነት" እና "መንፈሳዊ ብስለት" ያሉ ቃላት ለጆሮአችን የሆነ ክብደት አላቸው፤ ግን በትክክል ምን ማለት እንደሆኑ ለአፍታ ቆም ብለን አስበን እናውቃለን?

ሁሉም ቀደም ብለን በተመለከትነው አንኳር እውነት ላይ ያተኩራሉ፣ *እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማ ክርስቶስን በመምሰል እንድናድግ ነው።* ጳውሎስ ከተለወጡ ብዙም ሳልቆዩት የገላትያ ክርስቲያኖች እንዲህ ሲል የልቡን ናፍቆት ይገልጥላቸዋል፡- "የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደገና ምጥ ይዞኛል" (ገላ 4፥19)። ለሌሎች ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፡- "እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" (2 ቆሮ 3፥18)። ልጆች የወላጆቻቸውን መልክ ይዘው እንደሚወጡ ሁሉ እኛም የክርስቶስ ቤተሰብ አባላት እንደመሆናችን የእርሱን መልክ እንድንመስል ይጠበቅብናል።

በዚህ ምድር እስካለን ድረስ፣ ሙሉ በሙሉ እርሱን ወደመምሰል ልንደርስ አንችልም። በመንግስተ ሰማያት ግን በምልአት እርሱን እንመስለዋለን "እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን" (1ዮሐ 3፥2)። ይሁንና ያ ቀን እስኪደርስ ድረስ ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ተሰጥቶናል፤ ይኸውም "በጠማማና በክፉ ትውልድ መካከል ንፁሓንና ያለነቀፋ፣ ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሆናችሁ፣ እንደከዋክብት ታበሩ ዘንድ ነው" ሲል ጳውሎስ ያስታውሰናል (ፊሊ.ጵ 2፥15)። ይህ በሕይወታችሁ እየሆነ ነው?

## ክርስቶስን መምሰል

በወጣትነቴ፣ በአንድ ስፍራ ከታወቀ ክርስቲያናዊ መሪ ጋር ተገናኝቼ ነበር። ይህ ሰው ለእውነት ያለው ቅንአትና ለእምነት ተቃዋሚዎች መልስ ለመስጠት የነበረው ትጋት የሚያስደንቅ ነበር። ይሁንና ትንሽ ቆይቼ ይህ ሰው አንድ የሚጎድለው ነገር እንዳለ ተገነዘብኩ፤ ይህም ሌሎችን መውደድ ለእርሱ ቀላል አልነበረም (በተለይም ከእርሱ ጋር የማይስማሙትን ሰዎች)። ከሰውዬው ሁኔታ የተነሣ ኢየሱስ በእንዲህ ዓይነት ነበር የሚታወቀው? ብዬ ራሴን እንድጠይቅ አደረገኝ። የሰውዬውን ጉድለት ካስተዋልኩ በኋላ በእግዚአብሔር እርዳታ ፍቅር አልባ ቅንአትን አስወግጄ፣ በክርስቶስ ፍቅር ለመሞላት እንድጨክን አደረገኝ።

ክርስቶስን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው? ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ክርስቶስ በሁሉም የሕይወታችን ክልል ጌታ እንዲሆን መፍቀድ ማለት ነው። ለዚህ አብነት የሚሆኑ (ብዙ ሌሎች መዘርዘር ብችልም) ሦስት ምሳሌዎችን ልጥቀስ።

*አንደኛ፣ ክርስቶስ በባህርያችን ላይ እንዲገዛ መፍቀድ ማለት ነው።* አንድ ሰው በሰፈሩ ከሚያውቀው ከአንድ ነጋዴ ጋር አንዳችም ግንኙነት ሊኖረው እንደማይፈልግ ገለጸልኝ። ምክንያቱንም ስገልጽልኝ፣ "ነጋዴው ክርስቲያን ነኝ ቢልም፣ ሁልጊዜ በአቋራጭ መንገድ ማሳበር የሚቀናው፣ ቃል ገብቶ ቃሉን የሚያጥፍና ባገኘትም አጋጣሚ ሁሉ የራሱን ጥቅም የሚያስቀድም ሰው ስለሆነ ነው" አለኝ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ባህርዩ ክርስቶስን የሚያንፀባርቅ አልነበረም።

*ሁለተኛ፣ ክርስቶስን መምሰል ማለት ክርስቶስ በምግባራችን ላይ እንዲገዛ መፍቀድ ማለት ነው።* አንድ የኮሌጅ ተማሪ በቅርቡ ክርስትና እምብዛም እንደማይማርከው ጻፈልኝ። እንዲህም ሲል ምክንያቱን ገለጸ፦ "ክርስቲያን መሆን ከማልፈልግባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ እውነተኛ ክርስቲያን እስካሁን ስላልገጠመኝ ነው"። ይህ ምንኛ ብርቱ ነቀፌታ ነው! እኔም በምላሽ በጻፍኩለት ደብዳቤ፣ ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን እንዲመለከት (ክርስቶስ ብቻ ፍጹም ስለሆነና እርሱ ብቻ ሊያድን ስለሚችል) አበክሬ ብገልጽለትም፣ ክርስቲያኖች የሰጡት ስዕል ከክርስቶስ ባሕርይ የራቀ መሆኑ ግን ሳያስከፋኝ አልቀረም። ሕይወታችን ክርስቶስን የማይመሰክር ከሆነ፣ ሰዎች ለስብከታችን ጆሮ እንዲሰጡ መጠበቅ የዋህነት አይሆንምን? ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "ከዚህ ሁሉ (ከክፉው) ሽሽ፣ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግስትንና ገርነትን ተከታተል" (1ጢሞ 6፥11) ሲል ይመክረዋል።

*ሶስተኛ፣ ክርስቶስን በመምሰል ማደግ ማለት የልባችን ዝንባሌዎች ላይ ሁሉ እንዲገዛ እንፈቅዳለን ማለት ነው።* የልባችን ዝንባሌና ሁኔታ ውጫዊ ምግባራችንን ይወስናል - የሚያሳዝነው ግን ምናልባት ክርስቶስን ማንፀባረቅ ሳይችሉ ሲቀሩ ነው። ክርስቲያኖች አሉታዊና አቃቂር አውጪ መሆን የሚቀናቸው ለምን ይሆን? ሌሎቹስ ነጭናጫ፣ ዕቡይና ትዕግስት አልባ ለምን ይሆናሉ? አንዳንዶቹስ ልባቸው የታወከ፣ የሚጨነቁ ወይም ደግሞ ዳተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ እምነት የማይጣልባቸውና ኃላፊነት የጎደላቸው የሆኑት ለምን ይሆን? ሌሎቹስ በሰዎች ላይ የሚሰለጥኑና የማይመቹ የሚሆኑት ምን ነክቷቸው ይሆን? እግዚአብሔር የልባችን ሁኔታ ክርስቶስን የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ጥሪ እያቀረበልን ነው።

## የክርስቶስ ትህትና

በትውስታዬ ተቀርጸው ከሚኖሩ ገጠመኞች ውስጥ አንዱ ናጋላንድ የሚባል በህንድ አገር ራቅ ብሎ የሚገኝ ተራራማ አካባቢ መጎብኘቴ ነው። ይህ ቦታ በህንድ ውስጥ ክርስቲያኖች በብዛት ከሚገኙባቸው ስፍራዎች አንዱ ሲሆን፣ የተገኘሁት የወንጌል ለባኪያን ወደዚያ ስፍራ የመጡበት መቶኛ ዓመት በሚከበርበት ጊዜ ነበር። በዐሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለክብረ በዓሉ መጥተዋል- አንዳንዶቹ እዚህ ለመምጣት ለአራት ቀን በጫካ መንገዶች ተጉዘዋል። ሰዎቹ እንደነገሩን፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ

ለምች በየማለዳው ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ በየምሽቱ ደግሞ ለወንጌል ስብከት ይሰበሰቡ ነበር።

ለማደሪያ ወደተዘጋጀልን የመንግሥት ቤት ስንደርስ፣ አንድ ሰው ጓዛችንን ከመኪና ካወረደ በኋላ፣ ጫማችን ላይ የነበረው ጭቃ ይጠረግላችኋል አለን። የሰም ራሳችን እንጠርገዋለን ብንለውም እሺ ሊለኝ አልቻለም። ይህ ሰው በማግስቱ የሚካሔደውን የማለዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚመራ ሰው እንደሆነ የተገነዘብኩት ኋላ ላይ ነበር። የዚህ ሰው ትህትናና ሌሎችን ለማገልገል ያሳየው ፈቃደኝነት፣ በእውነት ክርስቶስን የሚገልጥ ነበር። የዚህ ሰው አርአያ ከቶም ተዘንግቶን አያውቅም።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው፡ ፡" (ገላ 5፥22-23)። ይህ ዝርዝር ዘጠኝ ባህርያትን ያቀፈ ሲሆን፣ የክርስቶስ የሆነ ሰው ሕይወቱ በነዚህ መለያዎች ሊያጌጥ ይገባል- ምክንያቱም የክርስቶስ ሕይወት መለያ ጌጦች ስለሆኑ ነው። ክርስቶስን መምሰል ማለት ምን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋላችሁ? እግዚአብሔር እነኚህን ዘጠኝ ባህርያት ተገንዝባችሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሕይወታችሁ አካል ማድረግ እንድትችሉ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

ይሁን እንጂ ይህ ማለት እግዚአብሔር ማንነታችንን ሊሰርዝ ያስባል ማለት አይደለም - በርግጥ ሻካራና ጎርባጣ ጎናችንን ሊያስተካክል ይፈልጋል! ሁላችንም የተለያየን ነን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደዚያ አደረገን። የጠርሴሱ ሳውል ቁርጠኛ፣ የጨከነ፣ ወሰም ዘለም የማያውቅና የክርስትና እምነትን ከምድረ ገፅ ማጥፋትን ሥራዬ ብሎ በእልህ የያዘ ሰው ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ለክርስቶስ የነበረውን ጥላቻ ወደፍቅር ለወጠለት። መሠረታዊ ማንነቱ አልተለወጠም፤ ይልቅስ እግዚአብሔር የብርታቱን አቅጣጫ በማስለወጥ (እንደሐዋርያ ጳውሎስ ሆኖ) የወንጌልን ብርሃን ይዞ የሚገሰግስ ሰው አደረገው። በአንጻሩ የጳውሎስ ረዳት ወጣት ጢሞቴዎስ የተለየ ስብዕና የነበረው ሰው ነበር - ዓይናፋር፣ እዛኝ፣ ከሰው የማይደባለቅ ሰው





ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ዓይናፋርነቱን አስወግዶ ሌሎችን የሚደርስና የሚያገለግል ሰው አደረገው፤ አዛኝ ባህርዩንም ውጤታማና ለመንጋው የሚራራ፣ መጋቢ እንዲሆን አድርጎ ለወጠው።

## የመለወጥ ጎዳና

ክርስቶስን በመምሰል ማደግ እንድንችል ከእኛ ምን ይጠበቃል? ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ የራሳችን ጥንካሬ የትም አያደርሰንም፤ *ሊለውጠን የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው።*

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ" (ኤፌ 5፥18) ብሎ የሚያዘን ለዚህ ነው። አንድ ሰው ሲሰክር፣ በአልኮል ተፅዕኖ ስር ነው እንላለን (በዜና እንደምንሰማው፣ ይህ ብዙ ጊዜ ለነገር ጠንቅ ነው)። በሌላ አባባል፣ አልኮል ሰውዬውን እየተቆጣጠረው ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በመንፈስ የተሞላ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ወይም ተፅዕኖ ሥር ነው። ይህ በሕይወታችን እውን የሚሆነው እንዴት ነው? መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን ይለውጥ ዘንድ በውስጣችን መሥራት የሚጀምረው እንዴት ነው?

*አንደኛ፣ ንስሐ መግባት ይጠበቅብናል።* ይህ ማለት ኃጢአት እስካሁን እየገዛው ያለና የክርስቶስን ጌትነት ያልሾምንበትን የሕይወታችንን ክፍል እግዚአብሔር እንዲያመለክተን መጠየቅ ማለት ነው - ከዚያም በጨከነ ልብ ልባችንን ከነዚህ ኃጢአቶች እንመልሳለን ማለት ነው።

በሰሜን ካሮላይና በሚገኘው ቤታችን የምንጠቀምበት ውሃ የሚመጣው ከፍ ካለ ተራራ ከሚፈልቅ ምንጭ ነው። በዚህ ቤታችን መኖር ስንጀምር የአካባቢው ነባር ነዋሪዎች ይህ ምንጭ በድርቅ ወራት ሳይቀር ሳያቋርጥ እንደሚፈስ ነገሩን - በርግጥም ልክ ነበሩ። ይሁንና በአንድ ወቅት ለዓመት ያህል ያልተለመደ ቀዝቃዛ ክረምት ስለነበረ፣ አንድ ቀን ውሃው ተቋረጠ። ክምንጩ በሚያስተላልፈው የውሃ ቧንቧ ላይ ውሃው በረዶ ሠራ፣ በቁር

የተጋገረውን መሬት ቆፍረን መፀየጃ በመጠቀም በረዶውን ማቅለጥ ነበረብን። ያኔ ውሃው እንደገና መፍሰስ ጀመረ።

ይህ ምንጭ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያስታውሰኛል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ልክ እንደ ምንጩ ለኛ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው። ሆኖም ኃጢአት እንደተጋገረው በረዶ ቧንቧችንን ዘግቷል። የተቃዋሚው ዓለም መንፈሳዊ ቅዝቃዜ ነፍሳችንን እንዲያቀዘቅዝ ስንፈቅድ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወት ሰጪ ውሃ ያቋርጣል።

ማነቆውን በማስወገድ ፍሰቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ ንስሓ ነው። መንፈሳዊ ሕይወታችን ድርቀት የነገሠበትና ምድረበዳ (የመከነ) ከሆነ፣ የመዝሙረኛውን ጸሎት በመጸለይ ጀምሩ፣ "እግዚአብሔር ሆይ፣ መርምረኝ፤ ልቤንም ዕወቅ . . . የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ።" (መዝ 139፥23-24)። ኃጢአት የሰለጠነበት የሕይወታችሁ ክፍል እንዳለ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት፤ ከዚያም ንስሓ ግቡ።

## በየዕለቱ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት

*ሁለተኛ፣ ክርስቶስን በመምሰል ለማደግ ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ይጠበቅብናል።* በየዕለቱ በልባችን ውስጥ በኛ ፈቃድና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል የከረረ ትንንቅ ይካሔዳል። እግዚአብሔር አሁን በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ይኖራል፤ ሆኖም አሮጌ ባህርያችን አሁንም ሕያው ስለሆነ፣ አሁንም የበላይነት ለማግኘትና እኛን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ይታገላል። በሕይወታችን ክርስቶስን በማንፀባረቅ ፈንታ የማያምነውን ዓለም ባህርይ እናንጸባርቃለን።

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ያላቸው ለዚህ ነው፣ "በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ" (ሉቃ 9፥23)። ይህ ቃል ደቀመዛሙርቱን እንደሚያስደነግጣቸው ዕሙን ነው። በዚያ ዘመን መስቀል የሐፍረትና የሞት ትእምርት (ምልክት) ስለነበረ መስቀል የሚሸከም ሰው ሞት የተፈረደበት ሰው ብቻ ነበር (ኢየሱስ





በመጨረሻ ላይ እንደተሸከመው)። በርግጥም ኢየሱስ ያለው ይህንኑ ነበር። አሮጌ ባህርያችን - ራስ ወዳድነታችን፣ ክፉ መሻታችን፣ አሮጌ ዝንባሌዎቻችንና አኗኗራችን በአንድነት መሞት አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ "ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ" (ቆላ 3፥5)። ጳውሎስ ከግል ተሞክሮው ይህ ምን ማለት እንደሆነ ያውቅ ነበር:- "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል" (ገላ 2፥20)።

ራስን ለክርስቶስ ማስገዛት ማለት እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍል ከእርሱ ሥልጣን በታች ማኖር ማለት ነው፣ እንደዚሁም እንደፈቃዱ እንዲለውጠን እርሱን መጠየቅ ማለት ነው። ከተሳሳተ መንገድ ተመልሰን፣ መልካምና ንጹሕ በሆነው እንዲሞላን እርሱን መጠየቅ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልብስ ከመለወጥ ጋር ያመሳስለዋል- አሮጌና እድፋም ልብስን አውልቆ አዲስና ንጹህ ልብስ እንደ መልበስ:- "ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ . . . ስእውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" (ኤፌ 4፥22፤ 24)።

በሕይወታችሁ ክርስቶስ የተተወበት የት ጋ ነው? በባህርያችሁ? በዝንባሌያችሁ? በድርጊታችሁ ነው? ወይስ በሌላ እንደ ጊዜያችሁ ወይም ገንዘባችሁ ወይም ከሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት ነው? በሥልጣኑ ሥር ያልተገዛ አለ? ለራሳችሁም ለእግዚአብሔርም እውነተኞች ሁኑ። አስታውሱ፤ እግዚአብሔርን ማታለል አትችሉም። መዝሙረኛው እንዲህ ሲል ጸልዮአል፦ "ከተሰወረ በደል አንጻኝ" (መዝ 19፥12)። ይህን ጸሎት የናንተ አድርጉት።

ከዚያም የሕይወታችሁን ሁለንተና ለክርስቶስ ሥልጣን አስገዙ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:- "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ ዲያብሎስን ተቃወሙት፣ ከእናንተም ይሸሻል። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል" (ያዕ 4፥7-8)።

## መታመንና መታዘዝ

*በመጨረሻ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ለዋጭ ኃይል በውስጣችሁ ሊለቀቅ የሚችለው በንስሓና በመገዛት ብቻ ሳይሆን፣ በመታዘዝና በመታመን ነው።*

አንድ ወታደር ለአዛዡ መኮንን ራሱን በሚያስገዛበት ጊዜ አዛዡ የሚያዝዘውን ለማድረግ ፈቃደኛ ይሆናል። ታማሚ ሰው ወደ ሐኪም ለመታከም ሲሄድ ሐኪሙ እንደሚለው ያደርጋል። የእግር ኳስ ተጫዋች ለአሰልጣኙ አመራር ራሱን ከሰጠ፣ አሰልጣኙ ያዘዘውን ያደርጋል። እናም እኛ ራሳችንን ለነገሥታት ንጉሥና ለጌቶች ጌታ በምንሰጥበት ጊዜ እርሱ እንድናደርግ የሚነግረንን እናደርጋለን፤ ምክንያቱም የርሱ መንገድ ትክክል እንደሆነ እናውቃለን።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ እግዚአብሔር ከሁሉ በፊት ፈቃዱን የሚገልጥልን በቃሉ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ አማካይነት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ብናውቅና ብንታዘዘው ከስንት ችግሮች እናመልጥ ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ ለሚገጥመን ሁኔታ ሁሉ መመሪያ ባይሰጠንም እኛ ከምንገምተው በላይ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ምሪትን ይሰጠናል። በተጨማሪም ሕይወታችንን ልንመራ የምንችልባቸውን መርሆች ያመላክተናል። የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠን እንድንተነትነው ወይም እንድንሚገትበት ሳይሆን እንድንተገብረው ነው። መዝሙረኛው እንዲህ ይላል። "ቃልህን እጠብቅ ዘንድ፣ እግሬን ከክፉ መንገድ ሁሉ ከለከልኩ" (መዝ 119፥101)

እግዚአብሔር በመንፈሱ ደግሞ ይመራናል፣ በተለይም አጣብቂኝ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ስንገባ፣ እርሱ በዚህ መንገድ ሲመራን፣ ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለን፣ ልንታዘዘው ይገባል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በተደጋጋሚ ገጥሞኛል። አንዳንድ ጊዜ ያለ ብዙ ትግል እታዘዛለሁ፤ በሌሎች ጊዜያት ግን ትክክለኛው ውሳኔ የቱ እንደሆነ ማወቁ ራሱ አስቸጋሪ ይሆንብኛል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አገልግሎታችን በአንዳንድ መንገዶች ለምሳሌ





በፊልሞችና በቴሌቭዥን በመጠቀም ለማስፋት ስናስብ ወይም ደግሞ ከሚደርሱኝ የወንጌል ስብከት ጥሪዎች የትኞቹን መቀበል እንዳለብኝ ለመወሰን ተስኖኝ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ከአጋሮቼ ጋር ለመወሰን የምከርንባቸውን ጊዜያት አስታውሳለሁ። በአእምሮ ማገናዘብ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ትክክለኛውን ውሳኔ ለማወቅ የቻልነው ስ ንጸልይ፣ ቃሉን ስናጠና ና የሌሎች በሳል የእግዚአብሔር ሰዎችን ምክር ስንጠይቅ ብቻ ነው፤ ውሳኔው ትክክለኛ እንደሆነ እግዚአብሔር በውስጣችን ያጸናልናል። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ፤ "መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሒድ" (ኢሳ 30፥21) እያለ ያረጋግጥልናል።

### በየዕለቱ እንዳዲስ መጀመር

ንስሓ . . . መገዛት . . . መታዘዝ . . . እነዚህ ክርስቶስን በመምሰል ለማደግ እግዚአብሔር በመንፈሱ ይሞላን ዘንድ ልንወስዳቸው የሚገቡን ሶስት እርምጃዎች ናቸው። እነዚህንም እርምጃዎች በየዕለቱ ልንወስዳቸው ይገባናል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እርዳታ በየቀኑ ያሻናል። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አንዴ ሆኖ የሚያበቃ ሁነት ሳይሆን፣ በሕይወታችን በየዕለቱ መቀጠል ያለበት እውነታ ነው።

በግሌ በየዕለቱ ቀኑን በጸጥታ ለእግዚአብሔር በማስረከብ፣ የእርሱ ወገን ስላደረገኝ በማመስገንና በዕለቱ ምን እንደሚጠብቀኝ ስለማያውቅ በማመስገን እጀምረዋለሁ። በመቀጠልም በዚህ ቀን ለክብሩ እንዲጠቀምብኝና ይህ እንዳይሆን ከሚከለክል ኃጢአት ሁሉ እንዲያነጻኝ እጠይቀዋለሁ።

ከዚያም በእምነት፣ ቃሉን ስታዘዝና በእርሱ ስተማመን፣ መንፈሱን እንደሚሞላኝ በማመን እራመዳለሁ። ሁልጊዜ ህልውኑ (መገኘቱ) ባይታወቀኝም፣ በዕለቱ ፍጻሜ ላይ ግን ውስጡን ተመልሼ ሳስብ ከእኔ ጋር ሆኖ ስለመራኝ አመሰግነዋለሁ። በዚያን ዕለት ከእኔ ጋር እንደሚሆን በሰጠኝ ተስፋ መሰረት፣ በርግጥም ቃሉን አክብሯል።

ይህ የእናንተም ልምምድ ሊሆን ይችላል፣ በየዕለቱ ሕይወታችሁን ለክርስቶስ ጌትነት ስታስገዙ፣ በእናንተም ሕይወት የሚሆን ነገር ነው። ውሎእችሁን ተመልሳችሁ ስታስቡት ተስፋ እንደሰጠው ከናንተ ጋር ስለነበር ልታመሰግኑት እንድትችሉ፣ ቀኖቻችሁን ሁሉ ለእርሱ አስረክቡ።



# ክፍል ሦስት

# በመንገድ ላይ የሚደቀኑብን ተግዳሮቶች

ተጋላጮች እንሆናለን። ልክ በኃይለኛው ውሃ እንደተሸረሸረው ግድብ ጥገና፣ ዳግመኛ መጠገኑ ከፍ ያለ ወጪ የሚጠይቀን ሊሆን ይችላል።

## ችግሮቻችንን መጋፈጥ

ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላም እንኳን፣ በርካታ ችግሮች የሚገጥሙን ለምንድነው? አንዱ ምክንያት (እንደተመለከትነው)፣ በዘመን ፍጻሜ ሰይጣን ለመጨረሻ ጊዜ እስከሚሸነፍ ድረስ፣ በማያባራ ሰፊ መንፈሳዊ ተጋድሎ ውስጥ ተካፋዮች በመሆናችን ነው። በተጨማሪም፣ አሮጌው የኃጢአት ባህርያችን አሁንም ገና ስላልሞተ፣ እግዚአብሔር ከሰጠን አዲስ ባህርይ ጋር ትግል ላይ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ አሁን በውስጣችን ቢያድርም፣ ይህ ማለት ከችግሮች ነፃ እንወጣለን ወይም ዳግመኛ ኃጢአት አንሠራም ማለት እይደለም። እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠበት ምክንያት እግዚአብሔር ምን ያህል ደካሞች እንደሆንን ስለሚያውቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እንዲሁም መንፈስ በድካማችን ያግዘናል" (ሮሜ 8፥26)

ይሁን እንጂ፣ ዋናው አከራካሪ ጉዳይ ችግሮችና ፈተናዎች ለምን ይገጥሙናል ሳይሆን በእንዴት ያለ አኳኋን ምላሽ እንሰጣለን ነው። በቀጣዮቹ ጥቂት ምዕራፎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚናገር እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ተግባራዊ መጽሐፍ ሲሆን እግዚአብሔር በዚህ መልኩ የሚናገረን ለሕይወት ፈተናዎችና ችግሮች የበለጠ የተዘጋጀን እንሆን ዘንድ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን፣ ብዙ ጊዜ ፈተና ሲገጥመን የምንሰጠው ምላሽ ክርስቶስን በማያሳይ መንገድ ነው፣ አደራረጋችን ለእኛም ላይታወቀን ይችላል። ይህን ዓይነት ምላሽ ስንሰጥ፣ ሰይጣን ባለድል ይሆንና የክርስቶስ ስም ይነቀፋል።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ርዕሰ ጉዳይ ስለፈተና ይሆናል። ፈተና በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ የሚገጥማቸው ነገር ስለሆነ፣ የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች በመንገዳችን ይጋረጣሉ። ግን ፈተና የሚመጣው ከየት ነው? ለመቋቋም የሚያስቸግረንስ





ለምንድነው? ፈተናን መቋቋም ያለብን እንዴት ነው? እጅ ስንሰጥስ ምን ማድረግ አለብን? ለቀጣይስ ከመውደቅ ልንጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

## ፈተና ምንድነው?

የፈተናን ፍቺ ለመስጠት ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? በቀላል አነጋገር፣ መፈተን ማለት ልክ ያልሆነን ነገር ለማድረግ መገፋፋት ወይም መማለል ማለት ነው።

ፈተና ማለት ኃጢአት ማለት እይደለም፣ መፈተንም ኃጢአት ማለት አይደለም። መፈተን ማለት ልክ ያልሆነን ነገር ለማድረግ መማለል (መሳብ) ማለት ነው፤ ኃጢአት ግን ለፈተና ተሸንፎ ልክ ያልሆነን ነገር ማድረግ ማለት ነው። መፈተን ኃጢአት አይደለም፣ ለፈተና እጅ መስጠት ግን ኃጢአት ነው። በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረበዳ ወሰደው" (ማቴ 4፥1)። ኢየሱስ ግን ለሰይጣን ፈተናዎች (ፈተናዎቹና ማባባያዎቹ እጅግ ማራኪና አጓጊ ቢሆኑም) እጅ አልሰጠም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ኢየሱስ "ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው" (ዕብ 4፥15)።

ልክ ያልሆነን ነገር ለማድረግ በምንፈተንበት ጊዜ፣ የኢየሱስን ምሳሌ በማየት ብርታት አገኛለሁ። በነገር ሁሉ ስለተፈተነ፣ እርሱ ሊረዳው የማይችል ፈተና፣ እናንተንና እኔን ሊገጥመን አይችልም። እርሱ ራሱ በዚህ መንገድ ስላለፈ፣ ስንፈተን የምናልፍበትን መንገድ ያውቀዋል። እንደዚሁም እርሱ ፈተናን ተቋቁሞ ስላሸነፈ፣ የድልን ጎዳና ያመለክተናል። እኛም እናሸንፋለን።

## ዓለም፣ ሥጋና ሰይጣን

ፈተና የሚመጣው ከየት ነው? የክፋት ሁሉ ሥረ - መሠረት (የፈተናም ጭምር) ባለጋራችን የሆነው ሰይጣን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ ይዞራል" (1 ጴጥ 5፥8)። አንበሳ ከእንስሳት መንጋ ውስጥ

ደካማውንና ስማጥቃት የሚያመችውን ፊልጎ እንደሚዞር ሁሉ፣ ሰይጣንም እንደዚሁ ደካማ የምንሆንበትን አጋጣሚ እየፈለገ ያደባል።

ይሁንና ሰይጣን በጣም የረቀቀ ስልት ስለሚጠቀም፣ በቀጥታ ወይም በገሃድ አያጠቃንም። "መጣሁብህ እኔ ባስጋራህ፣ ላጠፋህ ነው" የሚል ጽሑፍ ያለበት ምልክት አንግቦ አይመጣም። ከበርካታ ዓመታት በፊት በአውስትራሊያ አደላይድ በተባለ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በምናገርበት ወቅት፣ የተወሰኑ ተማሪዎች "እኔ ሰይጣን ነኝ! እኔ ሰይጣን ነኝ" የሚል ጽሑፍ አንግበው ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ በመምጣት መረበሻቸው ትዝ ይለኛል። ሰይጣን ራሱን በይፋ እየገለጸ አይመጣም፤ በጣም የረቀቀ በመሆኑ ራሱን ይሰውራል፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ሰይጣን "የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋወጣል" (2ቆሮ 11፥14)። ብዙ ጊዜ ራሱን ሰውሮ፣ ከመጋረጃ በስተጀርባ ይሠራል።

ሰይጣን የሚ ፈትነን እንዴ ት ነው ? ይህን የ ሚያደርገው በሁለት መንገድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። *አንደኛ፣ ውጫዊ ግፊት ያበረታብናል፤* ይህም ማለት በዙሪያችን ካለው ዓለም ማለት ነው። ቀደም ሲል የገለጽኩት ግድብ፣ የዘነበው ዝናብ በቶሎ ቢያበራ ኖሮ፣ የመፍረስ (የመለነጣጠቅ) አደጋ አይገጥመውም ነበር። ይሁን እንጂ በዝናቡ የተባበሰው ምንጭ ወደ ግድቡ እየገባ ግፊቱን አጠነከረበት - በእኛም ሕይወት የሚሆነው እንደዚሁ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ግፊት "ዓለም" ይለዋል። ዓለም ሲባል በዙሪያችን የምናየው አካላዊ ዓለም ሳይሆን፣ የማያምነው ዓለም ራሱን የሚያስተዳድርበት የእሴት ሥርዓት - የአስተሳሰብና የድርጊት ዘይቤ ማለት ነው። ይህ ከእግዚአብሔር የተለየውን፣ በፈጣሪው ላይ እያመጸ ያለውን ዓለም መስኪያዎችና ባሕርያትን ያመለክታል።

ይህን ከቶ አትዘንጉ፤ የምንኖረው ምስቅልቅል ባለ ዓለም ውስጥ ነው፣ ሰዎች ሲወዱ የሚገባቸውን ሲጠሉ፣ ሲጠሉ





የሚገባቸውን ሲወዱ በሚገኙበት ዓለም ውስጥ ነው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት የሚያስጠነቅቀን፣ "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውም ነገር አትውደዱ"። ይህን ካለ በኋላም ዓለማዊ ዝንባሌን የሚገልጡ ባህርያትን ይዞ ረዝራል፤ "በዓለም ያለው ሁሉ፣ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም" (1 ዮሐ 2፥15-18)።

ዓለማዊነት እግዚአብሔርን ሳይሆን እኔነትን ማዕከል የሚያደርግ ውስጣዊ ዝንባሌ ነው። ትኩረቱ በአሁን ጊዜ ላይ የታሰረ ሲሆን፣ የእሴቶቹ መነሻዎችም የትዕቢትና የራስ ወዳድነት መሻቶች ናቸው። ጳውሎስ የቆሮንቶስን አማኞች በክርስቶስ ቢያምኑም መንፈሳዊ ብስለት ስላልነበራቸውና እንደ ኢ-አማንያን ይመላለሱ ስለነበር እንዲህ ሲል ይገስፃቸዋል "በመካከላችሁ ቅናትና ክርክር አለ፤ ታዲያ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን?" (1ቆሮ 3፥3)።

## የሥጋ ፈተና

*ሰይጣን እኛን የሚፈትንበት ሁለተኛው መንገድ ከራሳችን ውስጥ ነው* - በመጽ ሐፍ ቅዱስ አጠራር "*ሥጋ*" የተባለውን በመጠቀም ነው። እዚህ ላይ "*ሥጋ*" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አካላዊ *ሥጋችንን* ብቻ ሳይሆን፣ እኛን ሊገዙን የሚሞክሩ ምኞቶቻችንና ፍላጎቶቻችንን ጥምር ነው። *ሥጋ* ማለት ከ*ሥጋ* ፍትወት ምኞት (እርሱን ቢጨምርም) የገዘፈ ነው። *ሥጋ* ማለት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ከመፈለግ ይልቅ የራሳችንን ምኞቶችና ፍላጎቶች ማርካትን ዋነኛ ዓላማ ማድረግ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፦ "እንደ *ሥጋ* የሚኖሩ ልባቸውን በ*ሥጋ* ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ" (ሮሜ 8፥5)። ያዕቆብም እንዲህ ይላል፦ "ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው" (ያዕ1፥4)።

አካላችንን የሰጠን እግዚአብሔር እንደ መሆኑ፣ ተገቢ እንክብካቤ ልናደርግለትና ለክብሩ ልናውለው ይገባል። ብዙ ጊዜ ግን ሰውነታችንን ከመግዛት ይልቅ፣ እንዲገዛን እንፈቅድለታለን።

# ዐሥራ ሰባት

## የውስጥ ጠላቶቻችንን ፊት ለፊት መግጠም

*ለምባሌ ሆይ፤ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ ቀና የሆነውን መንፈስ በውስጤ አድስ*

(መዝ 51፥10)

ከሼክስፒር ገጸባህርያት አንዱ ትክክለኛ የሆነ ነገር አለው፤ "ጥፋቱ እኛው ዘንድ ነው" የሚል፡፡

በቅርቡ በክርስቲያናዊ ባሕርይዋ ፍጹም አርአያ ልትባል ስለምትችል አንዲት ሴት ሰማሁ፤ ይህች ሴት በቤተክርስቲያኗ በትጋት የምትሳተፍ፣ በጎረቤቶቿ የተከበረች፣ በግል ሕይወቷ የማትነቀፍ፣ ችግር ላይ ላሉ የእርዳታ እጅ ለመስገስ ወደኋላ የማትል ናት፡፡

ይሁንና አንድ ቀን ሐኪሟ፣ በሕይወት ለመኖር የቀራት የተወሰነ ወራት እንደሆነ ሲያረዳት፣ ይህች ሴት ከመቅጽበት ሌላ ሰው ሆነች፡፡ ሥራዋን ተወች፣ ከወዳጆቿ ጋር ግንኙነቷን አቆመች፤ ለቤተክርስቲያኗም ጀርባዋን ሰጠች፡፡ በጎ ሰው ለመሆን ያደረግኩት ሙከራ በቂ ስለሆነ ያመለጠኝን ደስታና ፈንጠዝያ ማሳደድን ዓላማዬ አድርጌአለሁ ስትል አወጀች፡፡ የጭፈራ ቤቶች የዘወትር መመላለሻዎቿ ሆኑ፣ ግብረገብና መልካምነትን ደህና ሰንብቱ ያሉ አዳዲስ ባልንጀሮችን አፍርታ ውሎዋና አዳርዋ ከእነርሱ ጋር ሆነ፡፡ እስከምትሞት ቀን ድረስ፤ ከዚያ ቀደም ትኖረው የነበረውን ሕይወት አሽቀንጥራ ጣለች፡፡ በመጨረሻዎቹ ወራት ቤተክርስቲያን የመጣችው ለቀብሯ ቀን በሬሳ ሳጥን ውስጥ ሆና ነበር፡፡





### ይህ ለምን ሆነ?

ዘመኗን ሁሉ ራሷን በሥርዓት፣ ከብሯን ጠብቃ የኖረች ሴት እንዲህ በድንገት አቅጣጫዋን እንድትቀይር ያደረጋት ምን ይሆን? ክርስቲያናዊ ሕይወቷን በይፋ የገለጠች ሴት ሳይታሰብ መሐል ላይ ግብረገብነትንና ጨዋነትን አሽንቀጥራ እንድትጥልና ከዚያም አልፎ የተፈጥሮ ዕውቀቷን እንኳን እንዳትጠቀም ያደረጋት ምን ይሆን?

በርግጥ፣ ልቧንና የውስጥ ሀሳቧን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ በዚያ የማምሻ ዕድሜዋ ላይ ለምን እንደዚህ እንዳደረገች የሚያውቅ እርሱ ነው፡፡ በክርስቶስ የነበራት እምነት እውነት ይሁን ወይም ሌሎችን ለማስደነቅ ብቻ የታቀደ የሐሰት እምነት ይሁን የሚያውቅም እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ራሳችንን በማንም ሰው ሕይወት ላይ የመጨረሻውን ብይን ሰጪ አድርገን ልናስቀምጥ ከቶም አይገባንም፡፡

አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፤ የዚህች ሴት እምነት የውስጥ ማንነቷን የለወጠ አልነበረም፡፡ እስከመጨረሻዎቹ ወራት ድረስ ውጫዊ ባህርይዋ የማይነቀፍ ነበር፤ ልክ ያልሆነውን አስወግዳ ትክክለኛውን አድርጋለች፡፡ በውስጧ ግን - ማንም ሊያየው በማይችለው ጥልቅ ልቧ - ራሳቸውን ብቻ ለማስደሰት በሚኖሩት ላይ በስውር ትቀና ስለነበር ቅናቷ በመጨረሻ ላይ ለውድቀት ዳረጋት፡፡

በሌላ አባባል፣ ለእርሷ ክርስቲያናዊ ሕይወት ማለት ውጫዊ (አፍአዊ) የአኗኗር ዘይቤ ብቻ ነበር፡፡ ምናልባትም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንኳር ትምህርቶች ውስጥ አንዱ የሆነውን፣ "እግዚአብሔር ምግባራችንን ብቻ ሳይሆን ልባችንንም መለወጥ ይፈልጋል" የሚለውን እውነት አልተገነዘበችም፡፡ በሌላ አባባል፣ *እግዚአብሔር ከውስጥም ከውጪም" ሊለውጠን ይፈልጋል፡፡* ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "ብልቶቻችሁን የክፋት *መሣሪያ* አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፤ . . . ይልቁንም . . . ብልቶቻችሁን የጽድቅ *መሣሪያ* አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ" (ሮሜ 6፥13)፡፡

በተጨማሪም እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ" (ሮሜ 12፥2)። ሰውነታችንና አእምሮአችን ለክርስቶስ ሲቀርቡ ያስፈልጋቸዋል፤ እርሱ የሚፈልገን ዓይነት ሰዎች አድርጎ ሊለውጠን የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

## ምን ዓይነት ለውጥ ያመጣል?

የልባችን ሁኔታ እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ለምንድነው? መኖር እንዳለብን እየኖርን እስከሆነ ድረስ ይህ ምን ለውጥ ያመጣል?

መልሱ ቀላል ነው፡- *የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ነው።* ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዕለት ወደ ዕለት ክርስቶስን ወደ መምሰል እንድናድግ ነው። የኃጢአት ሃሳቦችና ስሜቶች እንዲለሰጥኑብን ስንፈቅድ፤ ከእርሱ ፈቃድ እየጎደልን ነው። ክርስቶስ ውስጡም ውጪውም ንጹሕ ነበር። ይህ የእኛም ግብ መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና" (1ኛተሰ 4፥3)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ "ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ" (2 ቆሮ 7፥1)። ኢየሱስ ጠንካራ የተግሳጽ ቃል የተናገረው በውጫዊ ሁኔታቸው ሲታዩ ግብረገብ ያሳቸው የሚመስሉ፣ ውስጣቸው ግን በክፉ ሃሳቦችና ምኞቶች የተሞሉ ሰዎች ላይ ነበር፣ "እናንተ ግብዞች ውጫቸውን በኖራ ተለስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኩሰት የተሞላ መቃብሮች ስለምትመስሉ ወዮላችሁ" (ማቴ 23፥27)።

## የውስጥ አደጋ

የልባችን ሁኔታ ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምን ይሆን? *አንዱ ምክንያት ሀሳባችን ምግባራችንን ስለሚገልጥ ነው።* አንዳንድ ጊዜ እንዲህ፣ "ይህን ያደረግኩት ሳላመዛዝን ነው" እንላለን፤ ይህ እውነት የሚመስልበት ጊዜ አለ። ሥረ - መሠረቱን ጠልቀን ስንመረምር ግን፣ ግብራችን ሁልጊዜም የውስጥ ሀሳባችን ነጸብራቅ ነው። እንዲያውም ሀሳባችንን ከምግባራችን መለየት የማይቻል





የሚሆንበት ጊዜ አለ። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- "ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጉደፍ ከልብ ይመነጫሉና" (ማቴ 15፥19)። ልባችንንና አእምሮአችንን መለወጥ የሚችል እርሱ ብቻ ስለሆነ፣ በየዕለቱ ሕይወታችንን ለክርስቶስ መስጠት ያለብንም ለዚህ ነው።

*ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ስለልባችንና ውስጣችን ሁኔታ የሚያተኩርበት ሌላው ምክንያት እርሱ ስለሚወደንና የተሳሳቱ ሀሳቦችና ስሜቶች ምን ያህል አውዳሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ስለሚያውቅ ነው።* እንደዚህ ዓይነት ሀሳቦች ነፍሳችንን በመመረዝ፣ አካላችንንም ይጎዳሉ። የሥነ ልቡና ሊቃውንት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከበርካታ ዘመናት በፊት ያስተማረውን እውነት እየተገነዘቡ ነው፤ ይኸውም አእምሮአችንና አካላችን በጥብቅ የተሳሰሩ መሆናቸውን ነው። ሁልጊዜ የሚናደድ ሰው ለልብ በሽታ ወይም ለደም ብዛት ወይም ለሌላ አካላዊ በሽታ የመጋለጥ ዕድሉ የሰፋ ነው። ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ያደረገውን ዝሙት ለመናዘዝ እምቢ ሲልና የበደለኝነት ስሜቱን ለማፈን ሲሞክር፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ዋጋ አስከፍሎታል፣ "ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሳ፣ ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ. . . . በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለችና" (መዝ 32፥3-4) ጤናው የተመለሰለት ኃጢአቱን ፊት ለፊት በመጋፈጥ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሲጠይቅ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ደስ ያላት ልብ መልካም መድኃኒት ናት፤ ያዘነች ነፍስ ግን አጥንትን ታደርቃለች" (ምሳ 17፥22)።

ኃጢአት፣ እንደ ገዳይ ካንሠር፣ ወደ ሁሉም አቅጣጫ በሰውነታችን፣ በአእምሮአችን፣ በስሜቶቻችን፣ በፈቃዳችን፣ በሁሉም ነገራችን በመሰራጨት ይበክለናል። ኃጢአት እንደ ዋዛ የሚታይ ነገር አይደለም! ይሁንና ኢየሱስ ኃጢአትን ድል ለመንሣት መጥቷል። የመጣው ይቅር ሊለን ብቻ ሳይሆን፣ ከኃጢአት ኃይል አርነት አውጥቶ በመንፈሱ ሊለውጠንም ጭምር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፣ "ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ ነበራችሁ። . . . አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ

ቅዱሳን አድርጐ በእርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ" (ቆሮ 1፥21-22)።

ቅዱሳን . . . ያለ ነቀፋ . . . ነውር የሌለብን . . . እግዚአብሔር በየዕለቱ ለእኛ ያቀደልን ይህን ነው። ይህ ግን እንዴት ይከናወናል?

## የውስጥ ጠላት፤ ትዕቢት

ከበርካታ ዓመታት በፊት የኖሩት የካቶሊክ ጳጳስ ጎርጎርዮስ፣ ኃጢአትን በሰባት ክፍሎች መድበው ነበር፣ እነዚህም ትዕቢት፣ ቁጣ፣ ቅናት፣ ርኩሰት፣ ሆዳምነት፣ ዳተኝነትና ስግብግብነት ናቸው። ለብዙ ጊዜ እነዚህ "ሰባት ገዳይ ኃጢአቶች" ተብለው ተጠርተዋል፤ ነገር ግን ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛው ሥፍራ በዚህ መልክ ባይዘረዝራቸውም፣ እያንዳንዳቸው ተደጋግመው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል።

ትዕቢት አውራ ሆኖ መጠቀሱ ያለምክንያት አይደለም፤ ምክንያቱም ራስን የሚያስታብይ ትዕቢት የሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ሥር ነው። ሰይጣንን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፅ ያደረገው ትዕቢት ነው። ኢሳይያስ የባቢሎንን ንጉሥ ትዕቢት የገለጸበት መንገድ ሰይጣንንም የሚወክል ነው፡- "በልብህም እንዲህ አልክ ‹‹ወደሰማይ ዐርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ አደርጋለሁ ... ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ" (ኢሳ 14፥13-14)። (እዚህ ላይ "እኔ" እና "የኔ" የሚለው ቃል በተለያዩ መልኮች እንዴት እንደተገለጠ ልብ በሉ፤ ትዕቢት ማለት "እኔነት" ማለት ነው።) ሰይጣን የአዳምንና የሔዋንን ክፍ የማለት ፍላጎታቸውን በማነሳሳት፣ እርሱን (ሰይጣንን) ቢከተሉት፣ "እንደ እግዚእብሔር እንደሚሆኑ" (ዘፍ 3፥5) ነገራቸው። እንደ እግዚአብሔር መሆን - እንዴት ያለ ማባበያ ነው! ከዚያች የሰውን ሕይወት ካበላሸበት ቀን ጀምሮ፣ የሰው ዘር በትዕቢት ትብታብ ተጠመደ - በውጤቱም አሳዛኝ ዋጋ ከፈለ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስጠንቅቃል፣ "ትዕቢት ጥፋትን፣ የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድማለች" (ምሳ 16፥18)።





## የሚያጠፋ ትዕቢት

ትዕቢት አውዳሚ የሆነው ለምንድነው? *ዋነኛው ምክንያት፣ ትዕቢት የራሳችንን ስህተት እንዳናይ የሚያሳውረን መሆኑ ነው።* ትዕቢት ከሆንነው ይልቅ የተሻልን በመሆናችን ከኃጢአታችን ንስሓ መግባትና መንገዳችንን ማስተካከል እንደማያስፈልገን ሊነግረን ይሞክራል። ኢየሱስ በተናገረው አንድ ምሳሌ፣ በትምክህት የተሞላና በጽድቅ የሚታበይ አንድ ሰው፣ "እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደ ሌሎች ሰዎች ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ" እያለ ይፀልይ ነበር፣ እየፀለየ እያለም ከእርሱ ብዙም ሳይርቅ የሚጸልየው ሌላ ቀረጥ ሰብሳቢ የሆነ ሰው ግን "እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ" በማለት ይጸልይ ነበር (ሉቃስ 18፥11፣13)። እግዚአብሔር የዚህኛውን ሰው ጸሎት ሰማ፤ የራሱ ኃጢአት የተሰወረበትን ትዕቢተኛ ሰው ቃል ግን ሊሰማ አልወደደም።

*በተጨማሪም፣ ትዕቢት ከሌሎች ሰዎች ይነጥለናል።* በተለያዩ ምክንያቶች ልንታበይ እንችላለን፣ ለምሳሌ ሃብታችን፣ ቁመናችን፣ ችሎታዎቻችን፣ ማኅበራዊ ደረጃችን፣ ያገኘናቸው ስኬቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ትዕቢት ከሌሎች ሰዎች ለይቶ ስለሚሰቅለን - ከነርሱ ይነጥለናል። ትዕቢተኛና ትምክህተኛ ሰውን ማንም አይወድም።

እብሪት ደግሞ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሊገመት የማይችል መከራና ጭካኔን ያስከተሉ የጥላቻና የዘረኝነት ሥር ነው። ጥላቻና ዘረኝነት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት በመሆናቸው እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ በሆነ ሰው ልብ ውስጥ እንዳችም ስፍራ ሊኖራቸው አይገባም። የሰውን ዘር ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ስለሆነ፣ በፊቱ ይህ ዘር ወይም ከዚያ ብሔር ይበልጣል ወይም ያንሳል ማለት ተገቢ አይደለም። "ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር በመዋጀቱ" (ራዕ 5፥9)፣ በመስቀሉ ግርጌ ያለው መሬት ደልዳላ ነው። ክርስቶስ የሞተለትን (ዋጋ - የከፈለለትን) ሰው ለመናቅ ምን ምክንያት ይኖረናል?

*ከሁሉም በላይ፣ ትዕቢት ከእግዚአብሔር ይነጥለናል።* ንጉሥ ዖዝያን ይሁዳን ካስተዳደሩት ምርጥ መሪዎች አንዱ ነበር፤ ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን "ዓዝያን ከበረታ በኋላ ዕብሪቱ ለውድቀት ዳረገው። አምላኩንም እግዚአብሔርን በደለ (2 ዜና 26፥16)። የባረከው እግዚአብሔር ነው፤ ሆኖም ክብሩን ለእግዚአብሔር እንደ መስጠት፤ ልቡን ከእርሱ መለሰ። ትዕቢት ሲገዛን ሲጀምር፣ እግዚአብሔር እንደማያስፈልገን በማሰብ፣ ለራሳችን ክብር መፈለግ እንጀምራለን። እግዚአብሔር፣ "ክብሬን ለማንም አልሰጥም" (ኢሳ 48፥11) እንዳለ እንዘነጋለን።

ክርስቲያኖችም ሳይቀር በረቀቀ መልክ በሚገለጥ ትዕቢት ሊሸነፉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ መመልከትና (ሌሎች አማኞችን ጨምሮ) በሌሎች ኪሳራ ራሳቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይችላሉ። "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል" (1 ጴጥ 5፥5) ተብሎ የተጻፈውን ቃል ይዘነጋሉ። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ ከአምላክህም ጋር በትህትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?" (ሚክ 6፥8) ያለውን ይረሳሉ።

*ይህ ማለት ትዕቢት ሁልጊዜም ስህተት ነው ማለት ነው? በትክክል ከተገነዘብነው አይደለም።* ለምሳሌ፣ ማስፈያ በሆን ሁኔታ በሠራነው ሥራ መኩራት ስህተት አይደለም፤ ችሎታውን የሰጠን እግዚአብሔር እንደሆነና እርሱ ብቻ ክብር እንደሚገባው እስከተገነዘብን ድረስ እኛም ሆንን የምንወዳቸው ሰዎች በተቀዳጁት ስኬት መኩራት ስህተት አይደለም። ሚዛናዊና ትክክለኛ የሆነ የማንነት ግምትና በራስ መተማመንም የተሳሳተ አይደለም። ራሳችንን ስንጥል ወይም ዝቅ አድርገን ስናስብ፣ ራሳችንን እግዚአብሔር እንደ ፈጠረን አድርገን ስመቀበል አሻፈረን እያልን ነው። እዚህ ላይ ቁልፉ ሚዛናዊነት ነው፣ ሚዛናዊነት ስንል በራስ ወዳድነትና እኔነት ላይ ያተኮረ ትዕቢትንና ልክ ባልሆነ ሁኔታ ራስን ዝቅ ማድረግን ማስወገድ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ራሳችሁን





በአግባቡ መገዘኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ አታስቡ" (ሮሜ 12፥3) ይለናል።

## ትዕቢትን ከልባችን ማራቅ

ኃጢአተኛ ትዕቢትን ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው? *አንደኛ፣ ትዕቢት በልባችሁ እንዳለ በመቀበል በእግዚአብሔር ፊት ተናዘዙ፤ በትሕትናም ይቅርታውን እሹ።* እኔነትን ማዕከል ያደረገ ትዕቢት ኃጢአት ነው፣ ስለዚህም በእውነተኛነት ልንጋፈጠውና ዝቅ ባለ ልብም የእግዚአብሔርን ይቅርታ ልንለምን ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ" (1 ጴጥ 5፥6)።

*በተጨማሪ፣ በየዕለቱ በእግዚአብሔር ህልውት (መገኘት) መመላለስን ልመዱ።* እግዚአብሔርን ምንኛ ታላቅ እንደሆነ ስትገነዘቡ፣ የጉራና የትዕቢት ዝንባሌአችሁ መደብዘዝ ይጀምራል። ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ስናነጻጽር ትዕቢት ከደጃችን ይርቃል።

## በውስጥ ያለ ጠላት፤ ቅናትና ስግብግብነት

ይህን በምጽፍበት ወቅት፣ የዜና ማሰራጫዎች በየዕለቱ የሒሳብ ስሌት ማጭበርበሮችን ይዘግባሉ፤ አንዳንዴ በቢልዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ይመዘበራል። እነዚህ ዜናዎች የሚያስደነግጡን ቢሆኑም፣ አዲስ አይደሉም።

አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት ከተባረሩበት ጊዜ ጀምሮ - ምናልባትም ከዚያም ጊዜ በፊት - ቅናትና ስግብግብነት የሰውን ልጅ ተጣብቀዋል። ሰይጣን እነርሱን የፈተነው ከፍ የማለት ፍላጎታቸውን በማነሣሣት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ከሰጣቸው በላይ እንዲሹ ለማድረግ ቅናትና ስግብግብነትንም በልባቸው በማስነሣት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ የቅናትና የስግብግነት ብዙ ታሪኮች ያቀርብልናል። ዮሴፍን ከሁሉም ወንድሞቹ በላይ አባቱ ይወደው ስለነበር፣ ወንድሞቹ ቀኑበትና፣ በስስት ተነሳስተው ሸጡት። ንጉሥ አክአብ የናቡቴን የወይን ተክል የግሉ ለማድረግ

ስለጎመጀ፣ ንግሥት ኤልዛቤል በሴራ ናቡቴን እንድታስገድል በማድረግ መሬቱን የራሱ አደረገ። ይሁዳም በገንዘብ ፍቅር ተነሳስቶ ኢየሱስን ለሰላሳ ብር ሸጠው። ሃናንያና ሰጲራም እንደዚሁ ለገንዘብ በመሳሳት፣ ከመሬታቸው ሽያጭ ለእግዚአብሔር መስጠት የሚገባቸውን ገንዘብ አስቀሩ።

ይሁንና፣ በተጠቀሱት ምሳሌዎች፣ ቅናትና ስስት ለማናቸውም እንዳልበጁና እውዳሚ እንደሆኑ እንመለከታለን። አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት ተባረሩ፤ የዮሴፍ ወንድሞች እርሱን አሳልፈው መስጠታቸው ከተጋለጠ በኋላ በፍርሃት ነበር የኖሩት። ንጉሥ አክአብ በውጊያ ተገድሎ ውሾች ደሙን ላሱት፤ ይሁዳ ራሱን ሰቀለ፤ ሃናንያና ሰጲራ ሞት ቀጠፋቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል፣ "ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት ይሰጣል፤ ቅናት ግን ዐጥንትን ያነቅዛል" (ምሳ 14፥30)። ቅናትና የንዋይ ስስት ሁልጊዜ በጣም ከባድ ዋጋ ያስከፍሉናል። ቅናትና ስግብግብነት በልቡ ሰልጥኖበት፣ በእረፍት የሚኖር ሰው ገጥሞኝ አያውቅም።

ቅናትና ስግብግብነት አንድ ባይሆኑም፣ በቅርብ የተሳሰሩ ናቸው። በሌላ ሰው ስንቀና፣ የነርሱ የሆነን ሁሉ ለኛ የማድረግ ምኞት አቅል ያሳጣናል። ስስትና ቅናት የሚያተኩሩት በገንዘብ ላይ ነው ነገር ግን ስሌሎች ነገሮችም እንስገበገባለን፤ ለምሳሌ፦ ውበት፣ ክብር፣ ንብረት፣ ዝናና ሥልጣንም ሊያስጎመጁን ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ መጎምጀትን ጣዖት ከማምለክ ጋር ያስተካክለዋል፤ ምክንያቱም ስስታም ሰው በእግዚአብሔር ፈንታ ቁሳቁስን ስለሚያመልክ ነው። ስስትና ቅናት ሥረመሠረታቸው ራስ ወዳድነት ሲሆን፣ ጤና በመንሳት የሌለንን ነገር እንድናሳድድ ያደርጉናል። ቅናትና ስስት በውጫቸው የሚጎዱ ባይመስሉም፣ በቀላሉ ሰውን ወደ ማሰቃየት፣ ጭካኔና ብሎም ወደ ጦርነት ያድጋሉ። ያዕቆብ በዚህ መልክ ይህን ሽግግር ይገልጸዋል፣ "በእናንተ መካከል ያለ ው ጦርነትና ጠብ ከ የት የመጣ ነው ? በውስጣችሁ ከሚኖረው ምኞታችሁ አይደለምን? ትመኛላችሁ፣ ግን አታገኙም፤ ትጣላላችሁ፤ ትዋጋላችሁም" (ያዕ 4፥1-2)።





ስስትና ቅናት ማኅበረሰብን ብቻ ሳይሆን በግለሰብ ደረጃም ጉዳት ያደርሱብናል። ቢያንስ ከአንድ ሰው በየሳምንቱ፣ በስስት ላይ የተመሠረተ የቁማር ሱስ ቤተሰቡን እንዴት እንዳናጋ የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሰኛል። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቤተሰቦች በስስትና በቅናት በመነዳት እስከ አንገታቸው ድረስ በዕዳ በመነከር ለክስረት ተዳርገዋል። የጋብቻ አማካሪዎች እንደሚነግሩን፣ ጋብቻን ሰብጥብጥ የሚዳርገው ቀንደኛ ምክንያት ገንዘብ ነው። ወህኒ ቤቶች የተጨናነቁት በስስት ሕይወታቸው በተመሳቃቀለ ወንዶችና ሴቶች ነው።

ቅናትና ስስት የሀብታሞች በሽታ ብቻ አይደሉም፤ ድሃ የሆነ ሰውም ባልተናነሰ ሁኔታ በነዚህ ደዌዎች ሊያዝ ይችላል። የበለጠ የሚያሳዝነው ግን፣ ክርስቲያኖችም ከቅናትና ስስት ተፅዕኖ ነፃ ያለመሆናቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው" (1 ጢሞ 6፥10)።

## ቅናትና ስስትን ፊት ለፊት መቋቋም

ቤተሰባችን በመልካም ሁኔታ እንዲኖር መመኘት በእርግጠኝነት ስህተት አይደለም፤ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ያውቃል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ትጉሆችና በገንዘብ ጠንቃቆች (እንደዚሁም ለጋሶች) እንድንሆን ያበረታታናል። ስኬታማ ለመሆን መፈለግም የግድ የተሳሳተ አይደለም፤ እግዚአብሔር ያደለንን ተሰጥኦዎች ሙሉ በሙሉ ስንጠቀም እርሱን ማክበራችን ነው። ሆኖም ቅናትና ስስት በቀላሉ ወደ ልባችን ሰርገው በመግባት፣ በጎ ሀሳባችንን ያጨናግፉብናል። ይህ በሕይወታችሁ እንዲከሰት አትፍቀዱ!

አንደኛ፣ ቅናት ወይም ስስት ልባችሁን ገዝቶት እንደሆነ እንዲገልጥላችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት - ተግሎም ኃጢአታችሁን ተናዝዛችሁ ንስሃ ግቡ። ተሳሎች አትሁኑ፣ ቅናትና ስስት ኃጢአት ናቸው፤ ለጥፋት አሳልፈው ይሰጧችኋል። ከዐሥርቱ ትእዛዛት ብዙዎቹ ከግብር ጋር የተገናኙ ናቸው - አትስረቅ፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ ወዘተ። የመጨረሻው ትእዛዝ

ግን የውስጥ መሻቶችን በተለይም ቅናትና ስስትን የሚመለከት ነው፡- "አትመኝ . . . የባልንጀራህ የሆነውን ማናቸውም ነገር" (ዘጸ 20፥17)። ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ዐሥርቱ ትዕዛዛትን በአዲስ መልክ ሲያቀርብ፣ ያተኮረው በውጫዊ ግብር ላይ ሳይሆን በውስጠኛ ችግር ላይ ነበር። ለምሳሌ ያህል፣ አንድን ሰው ስንጠላ ወይም በቁጣ ስንናገር በልባችን እየገደልነው እንደሆነ፣ የፍትወት ምኞት ሀሳብን በልባችን ስናስተናግድ እያመነዘርን እንደሆነ ተናግሯል።

*በመቀጠል፣ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን እውነተኛ ምስጢር እንዲያስተምራችሁ እርሱን ጠይቁት።* ይህን የምታደርጉት እንዴት ነው? አንዱ መንገድ ምስጋና ማቅረብን የዕለት ሕይወታችሁ ወሳኝ አካል በማድረግ ነው። በየዕለቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ስታደርሱ፣ ቅናትና ስስት ይቀጭጫሉ! መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና" (1 ተሰ 5፥18)።

*በመጨረሻም፣ በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ተማመኑ።* መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፡- "ራሳችሁን ከፍቅረ - ነዋይ ጠብቁ፤ ባላችሁ ነገር ረክታችሁ ኑሩ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ ከቶ አልተውህም፣ በፍጹም አልጥልህም ብሎአል" (ዕብ 13፥5)። የሚያስፈልገንን ነገር እርሱ እንደሚያሟላልን በእርሱ ስንተማመን፣ እኛም እንደ ጳውሎስ፣ "በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ" (ፊሊጵ 4፥11) እንላለን።

እግዚአብሔር ልባችሁንና አእምሮአችሁን ጠልቆ ሲመለከት የሚያየው ምንድነው? ርኅራኄና መርካትን - ወይስ ትዕቢት፣ ቅናትና ስስትን? የውስጣችሁን ሀሳቦች ከሰዎች መሰወር ትችላላችሁ፤ ከ እግዚአብሔር ግን ልትሰውሩአ ቸው አትችሉም። እዚህ ላይ ቆም በሉና መላ ሕይወታችሁን ዳግመኛ ለክርስቶስ ስጡ - የውስጥ ሃሳቦቻችሁንና ምኞታችሁን ጭምር። እግዚአብሔር በመንፈሱ ኀይል ውስጣችሁን እንዲለውጥ ጠይቁት።





# ዐሥሩ ስምንት

## የሚያንበረክኩን ስሜቶች

*ከሁሉ በላይ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት ምንጭ ነውና*

(ምሳ 4፥23)

የብረት ሰንሰለት ጥንካሬው፣ መገጣጠሚያው (ማያያዣው) ጥብቅ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው። ባህርያችንም እንደዚሁ ነው።

ባለቤቴ ሩት ተወልዳ ያደገችው፣ ወላጆቿ በህክምና የሚያገለግሉ የወንጌል መልእክተኞች ሆነው ይሠሩ በነበረበት በቻይና ነው። ከተጋባን ዕለት አንስቶ የትውልድ አገሯ ወደሆነችውና ሕዝቡንና ጥንታዊ ባህ ሏን ወ ደምትወዳት ቻይና ልትወስደኝ ሁልጊዜ ትመኛለች። የማኦን ኮምዩኒዝም ተከትሎ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መነሳት ወደዚያ መሔድን የማይታሰብ አደረገው። ሆኖም መጸለይና ተስፋ ማድረጋችንን አልተውንም - ውሎ አድሮም ቢሆን ከግማሽ ምዓተ ዓመት በኋላ፤ በሩ በመጨረሻ ተከፍቶ ቻይናን የመጎብኘትና አዳዲስ በተከፈቱት ቤተክርስቲያናት የመስበክ ዕድል አገኘን።

በቻይና ጉዞአችን ከማይረሱን ትዝታዎች ውስጥ ታላቁ የቻይና ግንብ መጎብኘታችን ነበር። ግንቡ ላይ ቁጭ ብዬ፣ ምናልባት ከዚያ ቀደም አሜሪካዊ አይተው በማያውቁ ህፃናት መከበባችን ትዝ ይለኛል። ከኛ ጋር ይጓዝ የነበረ ቻይናዊ አሜሪካዊ ጓደኛችን ቀርቦ ሲያነጋግራቸው፣ ፍርሃታቸው ለቀቃቸውና መዝሙሮች ይዘምሩልን ጀመር። እኛም "ኢየሱስ ይወደኛል"

ያደፈርሳል። ባለቤቴ፣ መራራና ከምጣጣ የሆነ ክርስቲያን ከሰይጣን የድል ማሳያና መፎከሪያዎች እንዱ ነው ስትል ተናግራለች - በርግጥም ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "መራራ ሥር በቅሎ ችግር እንዳያስከትልና ብዙዎችን እንዳይበክል ተጠንቀቁ" ይለናል (ዕብ 12፥15)። ንዴትና መራራነት፣ እግዚአብሔር እንድትሆኑ የሚፈልጋችሁን ዓይነት ሰው ከመሆን እየከለከላችሁ ነው?

## ንዴትን ማሸነፍ

በየጊዜው በንዴት ከመግዛት ይልቅ ልናሸንፈው እንችላለን? አዎን በእግዚአብሔር እርዳታ እንችላለን። ጴጥሮስ ንዴቱን በማሸነፉ ለክርስቶስ ደፋር ወደመሆን ለወጠው። ጳውሎስ በክርስቲያኖች ላይ የነበረው ቁጣ ወንጌልን የመስበክ ቅንአት ሆኖ ተለወጠለት። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያዘናል፦ "በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው" (ኤፌ 4፥23-24)። የእናንተስ ግብ ይህ ነው?

ንዴትን መቋቋም ያለብን እንዴት ነው? መልሱ ቁርጠኛ በመሆን ነው። *ያልተገራ ቁጣን ለማሸነፍ የመጀመሪያው እርምጃ አልፈልገውም ብሎ በመጨከን ነው - ይህን ለማድረግ ቁልፉ ቁጣ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት መሆኑን በመገንዘብ ነው።* ኢየሱስ እንዲህ ሲል አስጠንቅቆናል፦ "ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል" (ማቴ 5፥22)።

ይህ ማለት ለቁጣችን ወይም ለንዴታችን ሰበብ አስባብ መፈለግ - ለምሳሌ በወላጆቼ ምክንያት የመጣ ነው፣ በሕይወቴ ይህና ያ ስለደረሰብኝ የመቆጣት መብት አለኝ ማለትን ማቆም አለብን ማለት ነው። በተጨማሪም፣ ንዴትና መራራነት በሕይወታችን የሚያስከትሉትን ጉዳት ያለ ማድበስበስ መቀበል ይኖርብናል። ጠላቶቻችን ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ቁጡ ሰው ጠብን፤ ግልፍተኛም ብዙ ኃጢአት ይሠራል" (ምሳ 29፥22)። በተጨማሪም እንደዚሁ ይላል፦ "ከንዴት ተቆጠብ፤ ቁጣንም ተወው፤ ወደ እኩይ ተግባር እንዳይመራህ አትከፋ" (መዝ





37፥8)። ቁጣ የሚያስከትለውን ጉዳት ከቶም ቢሆን በቀላሉ አትመልከቱት።

*ሁለተኛው ደረጃ - በሌሎች ኃጢአቶች እንደምናደርገው ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ይቅርታና እርዳታውን እሹ።* ኢየሱስ በመስቀል ላይ እናንተ የፈጸማችኋቸው በደሎች ሁሉ፣ ንዴትን ጨምሮ በራሱ ላይ ተሸክሞታል። እግዚአብሔር በፍቅሩና በምህረቱ ቁጣችንን ይቅር ሲል ብቻ ሳይሆን፣ ብንፈቅድለት ከሕይወታችን ሊያስወግደውም የተስፋ ቃል ሰጥቶናል። መንስኤው ምንም ይሁን ምን፣ ቁጣችሁን እግዚአብሔር ሆይ አንተ ተረከበው በማለት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፣ "ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፤ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነትና ራስን መግዛት" እንዲተካላችሁ ጠይቁት (ገላ 5፥22-23)። አስተውሉ፤ ቁጣ፤ የነዚህ ሁሉ ተቃራኒ ነው። የመንፈስ ፍሬ ልባችንን ሲሞላ፣ ቁጣ ይሸሻል።

*በመቀጠል፣ ቁጣን ለማሸነፍ ተግባራዊ እርምጃዎች ውሰዱ።* በቁጣ ለመገንፈል የምትፈተኑባቸው አጋጣሚዎች የትኞቹ ናቸው? በተቻላችሁ መጠን ከነዚህ አጋጣሚዎች ሽሹ - ካልተቻላችሁ ደግሞ አስቀድማችሁ በመጸለይ፣ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት። ራሳችሁን መግዛት ተስኗችሁ ቁጣ ሲሰለጥንባችሁ፣ ፈጥናችሁ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ብቻ ሳይሆን የጎዳችኋቸውን ሰዎች ይቅርታ ጠይቁ። ለአንድ ሰው ለምሳሌ ለወላጅ ወይም ለቀድሞ ፍቅረኛችሁ ወይም ለአለቃችሁ፣ ቁጣ፣ መራራነትና የቅናት ስሜት የሚሰማችሁ ከሆነ፣ ይህን ለክርስቶስ በማስረከብ፣ ከናንተ እንዲያርቀው ጠይቁት።

*በተጨማሪም፣ ሌሎችን ይቅር በማለት የሚገኘውን ሕይወትን የመለወጥ ኃይል ተገንዘቡ።* ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ "የሚረግሙአችሁን መርቁ፣ ለሚበድሉአችሁ ጸልዩ" (ሉቃ 6፥28)። ይህን ትዕዛዝ ስትታዘዙ ቁጣ ውስጥ ልትቆዩ አትችሉም። እምቢ ቢሉችሁና ቢያስቸግራችሁ እንኳን፣ ራሳችሁን በመግዛት መመላለስ እንዳለባችሁ ተመላለሱ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

"እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ አርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ" (ኤፌ 4፥32)።

## ጥፋት የሚያስከትሉ ስሜቶች፡- ጭንቀትና ፍርሃት

ፍርሃትና ጭንቀት የዘመናችን መለያዎች ቢሆኑ ያስገርማል? በቅርቡ ወንጀል በበረከተባቸው ከተሞች በአንዷ ከምትኖር አንዲት ሴት እንዲህ የሚል ደብዳቤ ተቀበልኩ። "የቤቴን በር የምቆልፈው በአምስት ቁልፎች ቢሆንም፣ በጣም ስለምፈራ መተኛት እንኳን አልችልም"።

ፍርሃት በሕይወታችን ሚና እንዳለው አይካድም፤ አደጋን መፍራት ብናቆም፣ ሕይወታችን የማያልቅ ችግር ውስጥ ይገባል። ትንሽ ልጅ መኪኖች የሚያዘወትሩበትን የመኪና መንገድ ወይም ያልተዘጋ የመድሐኒት ብልቃጥ መፍራትን መማር ይኖርበታል። ወታደር ወይም ፖሊስ ለቅጽበት ያህል እንኳን ከትኩረት መናጠብ አደገኛ እንደሆነ ያውቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ ይሻል፤ ብስለት የጎደለው ግን በዚያው ይቀጥላል፤ መከራም ያገኘዋል" (ምሳ 22፥3)። ይሁንና መፍራት ያለብን አካላዊ አደጋን ብቻ ሳይሆን፣ አንዲያውም ከዚያ በላይ ግብረገባዊና መንፈሳዊ አደጋን ጭምር መፍራት አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ ይዞራል" (1 ጴጥ 5፥8)።

ፍርሃት ጠቃሚ ሊሆን ቢችልም፣ ከምንቆጣጠረው በላይ ሊሆንብን ይችላል፣ በዚህ ጊዜ ኃጢአት ይሆናል። ለምን? ምክንያቱም ፍርሃት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እንድንጠራጠር በማድረግ፣ በፍቅሩ እንዳናምን ስለሚያደርገን ነው። ፍርሃት ሽባ ሊያደርገንና በእግዚአብሔር አምነን በእምነት ከመለማራት ሊያቅበን ይችላል። ሰይጣን ፈሪ ክርስቲያን ይወዳል! እግዚአብሔር ለቀደሙት እስራኤላውያን ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና የተስፋይቱን ምድር ለማስገበር እንደሚረዳቸው ነግሯቸዋል። በዚህም ምክንያት፣ በሲና ምድረበዳ ለአርባ ዓመት ለመንከራተት ተገደዱ





(ዘኁ 14)። ፍርሃት ሽባ እንዲያደርጋቸው ስለፈቀዱ፣ ጠቅላላው ትውልድ ከእግዚአብሔር በረከት ጋር ተላለፉ። ይህ በእናንተም ሕይወት ሊከሰት ይችላል።

ብዙ ሰዎች ከሌላ ከማንኛውም ነገር ይልቅ የውስጥ ሰላምን አጥብቀው ይናፍቃሉ፡ ያለ ሰላም ዘላቂ ደስታ ወይም የመደላደል ስሜት ማግኘት አይቻልም። ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች እየፈለጉት የሚያጡት ነገር ሰላም ነው - ዋናው ምክንያትም ጭንቀትና ፍርሃት ነው።

## ፍርሃቶቻችንን ማሸነፍ

ጭንቀቶቻችንንና ፍርሃቶቻችንን ልናሸንፍ እንችላለን? ወይስ ዘመናችንን ሁሉ በጭንቀት ተውጠን መኖር አለብን?

ሌላ ጥያቄ በማንሳት መልስ ልስጥ፤ የፍርሃት ተቃራኒ ምንድነው? ለክርስቲያን መልሱ አንድ ብቻ ነው፣ የፍርሃት ተቃራኒ እምነት ነው - በእግዚአብሔርና በማይለወጠው ፍቅሩ መተማመን ነው።

በሁሉም ላይ ስልጣን ያለውና በፍቅር እጆቹ የሚይዘን እግዚአብሔር እንደሆነ ስንረዳ፣ በሕይወት የሚገጥሙንን አደጋዎችና ችግሮች በልበሙሉነት መጋፈጥ እንችላለን። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የዘላለም ድነት ይሰጠናል ብለን ካመንን፣ ለአሁኑ ኑሮ ልንተማመንበት እንዴት ይሳነናል? መዝሙረኛው እንዲህ ሲል ያውጃል፡- "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፤ አልፈራም" (መዝ 118፥6)።

ግን እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፣ አደጋ ከፊት ለፊት ሲጋረጥብንና ዙሪያው ገደል ሲሆንብን፣ በእግዚአብሔር መተማመን ቀላል ነገር አይሆንም። በዚህ ጊዜ በፍጥነት የሚመጣብን ፍርሃት እንጂ እምነት አይደለም። ግን ይህን አትርሱ፤ ፍርሃት እምነትን እንዲያባርር፤ እምነትም ፍርሃትን ያባርራል። እምነት ማለት ችግሮቻችን በነው እንደሚጠፉ በማመን ራሳችንን መደለል ወይም በጭፍን ሁሉም ብሩህ ነው ብሎ ማመን አይደለም። እምነት

እግዚአብሔር እንደ ፊቃዱ ጣልቃ በመግባት ያላችሁበትን ሁኔታ እንዲለውጥላችሁ ጸልዩ። እኛ የምንፈልገውን ሁልጊዜ ላያደርግልን ይችላል፤ ሆኖም ለእኛ የሚበጀንን ስለሚያውቅልን ሁልጊዜ ልንተማመንበት እንችላለን። እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንደ መሆኑ፣ ምንም ዓይነት ሁኔታ ከእርሱ ሥልጣን በላይ ሊሆን አይችልም። ባለቤቴ በምትጠቀምበት ጠረጴዛዋ ላይ እነዚህን ቃላት ጽፋለች፤ "ነገ ምን ይሆናል ብዬ አልፈራም፤ እግዚአብሔር እዚያም አለ።"

ስሜቶች ሕይወታችንን ያበለጽጋሉ፤ ነገር ግን አንዳንዴ ከአቅማችን በላይ ሆነው ፊር ሊያስቱን ይችላሉ። ይሁንና በእግዚአብሔር እርዳታ ሚዛን ጠብቀን መኖር እንችላለን።





# ሀምሳ ዘጠኝ

## ስጥፋት የሚዳርጉን ነገሮች

*እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውም ነገር ስታደርጉ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፡፡*

(1 ቆሮ 10፥31)

ሰይጣን አዳዲስ ፈተናዎች መፍጠር አያስፈልገውም፤ ጥንት የነበሩት ፈተናዎች ዛሬም ቢሆን ደህና ያገለግሉታል።

ከቶ የምንማር አይመስልም፤ የምንሸነፍባቸው ፈተናዎች የቀድሞ ትውልድን የጣሉት ፈተናዎች ሲሆኑ፣ የሚከተለን መዘዝም ከእነርሱ የተለየ አይደለም። የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ እንዲህ ሲል የተናገረው ይህን በማሰብ ይመስላል፦ "የተደረገው ነገር መልሶ ይደረጋል፤ ከጸሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም" (መክ 1፥9)።

### የቁልቁለት መንገድ

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አንድ ሰው ራሱንና ቤተሰቡን ሊያጠፋ ሲል ተመልክቼአለሁ። ይህ ሰው ቤተክርስቲያን የሚያዘወትር፣ በሥራው የተሳካለት፣ በሚኖርበት አካባቢም እንቱ የተባለ ሰው ነበር። ከእኔ ጋር የምንገናኘው አልፎ አልፎ ቢሆንም፣ የሚያውቁት ሰዎች ከልቡ የእምነት ሰው እንደሆነ ነበር የሚያውቁት።

ይሁን እንጂ ይህ ሰው በስውር የሸሸገው ኃጢአት እንደነበረ እነኚህ ሰዎች አያውቁም ነበር፤ ይህን ኃጢአቱን ሆን ብሎ

መሆኑን ባለማስተዋል ዘወትር እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይጥራሉ። እምነታችን ከሕግጋትና ከደንቦች ዝርዝር ያልዘለለ ሲሆን፣ ደስታ ያሸሽና ለክርስቶስ ያለን ፍቅር ይኮስምናል። ሕግጋት የራሳቸው ፋይዳ እንዳላቸው ባይካድም፣ ጤናማ የሆነ ጋብቻ ከሕግጋት በላይ እንደሆነ ሁሉ፣ ከክርስቶስ ጋር ጤናማ ግንኙነት መመስረትም፣ ከሕግጋት በላይ ይጠይቃል።

እዚህ ላይ ባህርያችንም የማይናቅ ሚና አለው። ለምን ቢባል፣ ለሌሎች ሰዎች የምናሳየው ሁኔታ ስለእነርሱ ያለንን ስሜት ስለሚያንጸባርቅ ነው። አንድን ሰው በእውነት ስትወዱት፣ ልታስደስቱትና በምታደርጉት ሁሉ ልታከብሩት ትሻላችሁ። በሌላ አባባል፣ ለሌሎች የምታሳዩት ሁኔታ ለነርሱ ያገዳችሁ አይገዳችሁ እንደሆነ ያመለክታል። ሌላውን ሰው ባለማክበር ወይም ፍላጎቱን ችላ በማለት የምታደርጉት፣ በእንደቡት የምትገልጡት ምንም ይሁን ምን፣ እንደማትወዱት ነው የሚያሳየው።

ከዚህ በለፋ ሁኔታ፣ ከክርስቶስ ጋር ባላችሁ ግንኙነትም ይህ እውነት ነው። ክርስቶስን በእውነት የምንወደው ከሆነ፣ እርሱን ደስ ልናሰኘውና በአኗኗራችን ልናከብረው እንሻለን። እርሱን የመጉዳት ወይም ስሙን የማስነቀፍ ሀሳቡን እንኳን በጣም የምንጠየፈው ነገር ይሆናል። ኢየሱስ እንዲህ ሲል የተናገረው ቃል፣ በእያንዳንዱ አማኝ ልብ መከተብ ይኖርበታል፡- "ብትወዱኝ ትዕዛዜን ትጠብቃላችሁ" (ዮሐ 14፥15)።

## የዲያብሎስ ማባበያዎች

ሁሉም ዓይነት ኃጢአት ከባድ ነው፤ በእግዚአብሔር ዓይን ጥቃቅን ወይም ጉዳት የማያመጡ የሚባሉ ኃጢአቶች የሉም። በእርግጥ አንዳንድ ኃጢአቶች ከሌሎች የበለጠ ክብደት አላቸው፤ ለዚህ ምክንያቱ የሚያስከትሉትም መዘዝ የበለጠ ከባድ ስለሆነ ነው። ለዚህም ነው እኛን ለመከታተል የማይታክተው ባላጋራችን ዲያብሎስ እነዚህን ከባድ ኃጢአቶች እንድንፈጽም ለማባባል የሚችለውን ያህል የሚያደርገው። ይህን አትዘንጉ፣ የሰይጣን ግብ እኛን ከእግዚአብሔር ለማራቅ ሲሆን፣ ይህን ለማድረግ ደግሞ





እጅግ ቀላሉ መንገድ እኛን ወደ ገሃድ ኃጢአት መጎተት እንደሆነ ያውቃል።

ልጅ እያለሁ፣ በአባቴ እርሻ ላይ ሰብል በመፍጀት ያስቸግሩን የነበሩ ጥንቸሎችን ለመያዝ ወጥመድ አስቀምጥ ነበር። አባቴ እነኚህን ጥንቸሎች ለመያዝ ምን ዓይነት ማራኪ ምግብ ማስቀመጥ እንዳለበት ያውቅ ነበር - አደጋውን ረስተው ወጥመድ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጋቸው ዓይነት ምግብ ነበር። ሰይጣንም እንደዚህ ነው የሚያደርገው። ወደ ወጥመዱ ውስጥ ሊያስገባን ሲፈልግ፣ ምን ዓይነት ‹ማጥመጃ› ቢጠቀም እኛን መሳብ እንደሚችል ያውቃል። ማንነታችንን ስለሚያውቅ ደካማ የሆንንበትን ስፍራ አይቶ ያጠቃናል።

ይህንን በአእምሮአችን ይዘን፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሲተክላቸው የሚሻቸውን አራት ባህርያት ወይም መሰያዎችን እንመልከት፤ በመቀጠልም ሰይጣን በተቃራኒው እነዚህን ባህርያት እንዴት ሊሸረሽር እንደሚፈልግ እናያለን።

## ክርስቲያናዊ ባህርይ፡- ሐቀኝነት

ሩትና እኔ ወደቻይና ባደረግነው የመጀመሪያ ጉዞአችን፣ ቤጂንግ ውስጥ ያስተናገደን ሰው ልባዊና የሞቀ አቀባበሉ ቤተኝነት እንዲሰማን አደረገን። ይህ ሰው ጡረታ የወጣ ታዋቂ ዲፕሎማት ሲሆን፣ በአሜሪካ የቻይና አምባሳደር ነበር፤ ለውዬው በመላው ቻይና "ሐቀኛው" ተብሎ ይታወቅ ነበር፤ ምክንያቱን ስንጠይቅ፤ ባህርይው ከነቀፋ በላይ መሆኑ ስለሚታወቅ እንደሆነ ተነገረን።

እኛ ክርስቲያኖች በሐቀኝነት እጅግ እጅግ የምንታወቅ መሆን በተገባን! ሐቀኝነት ማለት የምንለውና የምናደርገው ይጣጣማል ማለት ነው። *ሐቀኝነት* ማለት ታማኝ ወይም እምነት የሚጣልብን ሰዎች ማለት ነው፣ ባህርያችንም ከነቀፋ በላይ ነው ማለት ነው። ሐቀኝነት ማለት የጓዳ ሕይወታችን (ማንነታችን) በድንገት ለአደባባይ ቢጋለጥ፣ የምናፍርበት ወይም የምንሸማቀቅበት ነገር አይሆንም ማለት ነው። ውጫዊ ሕይወታችን ከውስጥ እምነታችን ጋር የተስማማ ነው ማለት ነው። ሐቀኛ ሰው ማለት

እንደ ዳንኤል ጠላቶቹ ድክመት ሊያገኙበት ምንም ያህል ቢተጉም አይሳካላቸውም ማለት ነው፤ "ዳንኤል ታማኝ፣ ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለበት ስለነበር፤ በእርሱ ላይ ስህተት ሊያገኙ አልቻሉም" (ዳን 6፥4)። ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ሲል ጸልዮአል፤ "አምላኬ ሆይ፣ ልብን እንደምትመረምርና ቅንነትን እንደምትወድ አውቃለሁ" (1 ዜና 29፥17)።

ሌሎች ሰዎች ሕይወታችሁን ሲመለከቱ ምን ያያሉ? ቀርበው የሚያውቁህ ሰዎች ባለቤትህ፣ ልጆችህ፣ ባልንጀሮችህ፣ የሥራ ባልደረቦችህ - ስለአንተ ቢናገሩ ምን ይላሉ? በእንዱ በማንኛ ውም የሕይወታችሁ ክፍል - በገንዘብ፣ ከሰው ጋር ባላችሁ ግንኙነት፣ በንግግራችሁ፣ በንብረት አያያዛችሁ ወይም በሌሎች በመቶዎች ሁኔታዎቻችሁ የሚቃረን ወይም የሚጣረስ ነገር ያያሉን? ሀሳበ ጽኑ ሳንሆን ስንቀር ሰይጣን ደስ ይለዋል፤ ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ ክርስቲያን ውጤታማነት የሚጎድለው ብቻ ሳይሆን የባሰም እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። በየሳምንቱ እንደዚህ የሚል መልእክት ያዘሉ ደብዳቤዎች ከተለያዩ ሰዎች ይደርሱኛል፦ "ክርስቲያኖች ሲባሉ ግብዞች ናቸው"፤ በማለት ከክርስቶስ ጋር ጉዳይ እንደማይኖራቸው ይጽፉልኛል። አንዳንድ ጊዜ የሚሰነዝሩት አስተያየት ጥቅልና ድፍን ነው - ብዙ ጊዜ ግን እነዚህ ሰዎች ክርስቲያን ነኝ የሚል፣ ግን ሕይወቱ ይህን ስም የማይመጥን ሰው ያውቃሉ ብዬ እገምታለሁ። ሁልጊዜም የምሰጣቸው መልስ ክርስቶስ ብቻ ፍጹም ስለሆነ እርሱን ብቻ ልንከተለው እንደሚገባ፣ ሰዎችን ሳይሆን ክርስቶስን እንዲመለከቱ ነው። ሆኖም ትችታቸው እኛን ጠልቆ ይወጋናል፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ሰዎች ከክርስቶስ የሚርቁት በክርስቲያኖች ግብዝነት ወይም የተቃረነ አኗኗር ነው። ይህን ሲያደርጉ፣ ሰይጣን ተጨማሪ ድል ያስቆጥራል።

እግዚአብሔር በተናገራችሁት የምትኖሩ ሐቀኛ ሰዎች እንድትሆኑ እንዲያደርጋችሁ ጠይቁት፤ ሕይወታችሁ በሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ ይሁን። ሌሎች ሰዎች እንዴትም ይኑሩ፣ እናንተ ግን በጽናት ለክርስቶስ መኖርን ዓላማ አድርጉት።





የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ሳይቀሩ፤ "መምህር ሆይ፣ አንተ ትክክለኛ ሰው እንደሆንህ እናውቃለን" (ማር 12፥14) ሲሉ መስክረውለታል።

## ክርስቲያናዊ ባህርይ፣ ታማኝነት

*ታማኝነት* ማለት በማንኛውም ሁኔታ ዕምነት የሚጣልብንና ለአደራ የምንበቃ ሰዎች ነን ማለት ነው። ሐሰት ለመናገርና እውነትን ለማድበስበስ የማንፈቅድ ስለሆንን (ጠቃሚ ሆኖ ብናገኘውም እንኳን) ሰዎች ቃላችንን ይተማመናሉ ማለት ነው። በተጨማሪም፣ የራሳችንን ጥቅም ለማስጠበቅ ስንል ከፊል እውነቶችን እንደማንጠቀምና እንደማናታልል ያውቃሉ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ክብርን ይጎናጸፋሉ፤ ምክንያቱም፣ "በአፋቸው ምንም ዓይነት ውሸት አልተገኘም፤ ነቀፋም የለባቸውም" ይላል (ራእ 14፥5)። በብሉይ ኪዳንም እንዲህ፣ "አትዋሹ፣ ከእናንተ አንዱ ሌላውን አያታልል" (ዘሌ 19፥11) የሚል ትዕዛዝ አለ።

*ታማኝነትን* አጉድሎ ከመገኘት የበለጠ በፍጥነት እምኔታ የሚያሳጣን ነገር የለም። ልንታመን እንደማንችል ሰዎች አንዴ ከደመደሙ ሀሳባቸውን ለማስለወጥ የማይቻል ይሆንብናል። ለዚህም ነው ሰይጣን እውነት ብንናገር ባንናገር ለውጥ እንደሌለው (ከነጭራሹም እውነት የሚባል ነገር እንደሌለ) ሊያሳምነን ላይ ታች የሚለው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን የሚከተለውን ቢል ልንደነቅ አይገባም፣ "በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልቆመም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰት ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው" (ዮሐ 8፥44)።

ይሁን እንጂ፣ ታማኝነትን ማጉደል ዓይኔን ግንባር ያድርገው ብሎ በመዋሸት የተወሰነ አይደለም። የሐሜት መልክ ሊወስድ ይችላል - ይህም ማለት በከፊል እውነቶችና ባልተረጋገጡ አሉባልታዎች የሌሎችን ኑሮ ማፍረስ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ሐሜተኛ ምስጢር ያባክናል፤ ስለዚህ ለፍላፊን ሰው አርቀው" (ምሳ 20፥19)። ጳውሎስ በቆሮንቶስ የነበሩትን ብስለት የጎደላቸውን ክርስቲያኖች በመካከላቸው ስለነበረው "ስም

ማጥፋት፣ ሐሜት፣ እብሪትና ሁከት" (2 ቆሮ 12፥20) ምክንያት ይገስጻቸዋል።

ታማኝነት የጎደለው ምላስ በእግዚአብሔር ፊት አስፀያፊ የሆነው ለምንድነው? የእግዚአብሔር ፈቃድ "በአፉ ተንኮል አልተገኘበትም" (1 ጴጥ 2፥22) የተባለውን ክርስቶስን በመምሰል እንድናድግ ስለሆነ ነው። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ፣ "እውነት እውነት እላችኋለሁ" ብሎ ተናግሯል። ታማኝነት ማጉደልን እግዚአብሔር የሚንቅበት ሌላው ምክንያት፣ ኃጢአተኛ በሆነ ዓላማ የተገፋፋ ስለሆነ ነው። ብዙ ጊዜ ውሸት የምንናገረው በሌሎች ፊት ራሳችንን መልካም አድርገን ለማቅረብ አይደለምን? ብዙ ጊዜ የምናማው "ውስጠ አዋቂ" መስለን ለመታየት ወይም ራሳችንን ከሌሎች የተሻልን አድርገን ለማቅረብ አይደለምን?

ታማኝነትን ማጉደል ሌሎችም መገለጫዎች አሉት። ተማሪ ፈተና ላይ ሲያጭበረብር ወይም ሰው ከመሥሪያ ቤቱ ዕቃ ሲሰርቅ ወይም ቢሮ የገቡበትን ጊዜ አሳስተው ሲጽፉ፣ ወይም መክፈል ያለባቸውን ግብር ሲያጎድሉ፣ ታማኝነት እያጎደሉ ነው። የንግድ ባለቤቶች የሒሳብ ስሌት ሲያጭበረብሩ ወይም ሰራተኞቻቸውን ሲበዘብዙ ወይም በማታለል የሰው ገንዘብ ሲወስዱ፣ ታማኝነት አያጎደሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል በግልጽ ያዘናል፡- "በሰው ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ" (ሮሜ 12፥17)።

## የክርስቲያን ባህርይ፡- ንጽህና

የምንኖረው ወሲብ ያለ ልክ የትኩረት ማዕከል በሆነበት ዓለም እንደሆነ ታውቃላችሁ። ተፅዕኖው የማይደርስበት ሰው የለም፤ የማስታወቂያና የመዝናኛ ኢንዱስትሪዎች ሆን ብለው የወሲብ ስሜቶቻችንን የሚቀሰቅሱ መልዕክቶችን ከየአቅጣጫው ይለቁብናል። የግብረገብ ልጓማችንን ሰብረን፣ ለምኞት፣ ለሥጋዊነትና ለጠማማ ግብሮች ሳይቀር በራችንን እንድንከፍት በተደጋጋሚ ሁኔታ እንወተወታለን። ትውልዳችን በኤርምያስ ዘመን





እንደነበረው ሆኗል፤ "ጨርሶ ዕፍረት የላቸውም፤ ዕፍረት ምን እንደሆነ እንኳን አያውቁም" (ኤር 6፥15)።

ይሁንና፣ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን ዓለም ከዛሬው ከኛ ዘመን ብዙም የተለየ አልነበረም። ምግባረ ብልሹነትና ጠማማ ግብሮች በየሥፍራው ነበሩ፤ አንዳንድ የዘመኑ አረማዊ ኃይማኖቶችም እነዚህን ግብሮች በይፋ ያጸድቁ ነበር። የግብረገብና የወሲብ ንጽህና አቋም መውሰድ፣ ራስን ከማኅበረሰብ መገለልን፣ ከዘመኑ ወ ግ ጋር ራስን ማቃረ ንና ብሎም ራስን ለመናቅና ለመገፋት ደጋልጥ ነበር።ይሁንና የእግዚአብሔር የግብረገብ ልኮች ግልጽ ናቸው፤ ዛሬም አልተለወጡም። ክርስቶስን ስንቀበል፣ እግዚአብሔር የንጽህና ሕይወት እንድንኖር ጥሪ ያቀርብልናል። ጳውሎስ በምግባረ ብልሹነቷ ታዋቂ በነበረችው በቆሮንቶስ የነበሩትን ክርስቲያኖችን እንዲህ ሲል መክሯቸዋል፡- "ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚሠራው ኃጢአት ሁሉ ከአካሉ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚፈጽም ግን በገዛ አካሉ ላይ ኃጢአትን ይሠራል" (1 ቆሮ 6፥18)።

እግዚአብሔር ወሲብን በተመስከተ ስላለው እቅድ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 25 በስፋት እንመለከታለን። ነገር ግን በዚህ ክፍል ማስታወስ ያለብን አስፈላጊ ነገር፣ ወሲብን የሰጠን እግዚአብሔር መሆኑን፣ ይህንን ኃይለኛና አስደናቂ የሆነውን ስጦታ እርሱ እንዳቀደልን መጠቀም የምንችለው ትዕዛዛቱን በመከተል መሆኑን ነው። ምናልባት ከዚህ የበለጠ ደስታ ሊሰጠን የሚችል ነገር የለም ማለት እንችላለን - በተቃራኒው ግን አግባብ በሌለው ሁኔታ ስንፈጽመው ከሌላ ከምንም ነገር ይልቅ ለሀዘን ይዳርገናል። ሁኔታ ስንፈጽመው ከሌላ ከምንም ነገር ይልቅ ለሀዘን ይዳርገናል። የፈጸሙት ልክ ያልሆነ (ያልተገባ) የወሲብ ግብር ሕይወታቸውን እንዳመሳቀለው ከሚነግሩኝ ሰዎች በየዕለቱ ደብዳቤ እቀበላለሁ። መጀመሪያ ላይ እዚህ ደረጃ የሚያደርሳቸው አልመስላቸውም ነበር፤ አሁን ግን ውድመቱ ከደረሰ በኋላ፤ ምንኛ እንደተሳሳቱ እያሰቡ በጸጸት ይቆዝማሉ።

በዚህ ወሳኝ የሆነ የሕይወታችሁ ክፍል ላይ ለሰይጣን የእግር ጣት መርገጫ የሚሆን ቦታ እንኳን አትስጡት፤ ደካማ

ጎናችሁን ስለሚያውቅ፣ እናንተን ለመጣል የሚችለውን ሁሉ ይሞክራል። ከሌላ ከማንኛውም የሕይወታችሁ ክፍል ይልቅ ይኼኛው ለጥቃት የተጋለጠ ነው። ወንዶች፣ ደግማችሁ ማማተርን አስወግዱ፤ "ከእህትነት የወጣ"፣ ግብዣን፣ የአጋጣሚ ያልሆነ ንኪኪን አስወግዱ! ሴቶች፣ ቀስቃሽ አለባበስን፣ ዋዘኛ ጨዋታን፣ የመሽኮርመም ፈገግታን አስወግዱ። አንዲት ሴት እንዲህ ስትል ጻፈችልኝ፣ "ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው እንደሚባለው ሳናስበው ነበር የጀመርነው፣ ድንገት ሳይታወቀን፣ ከቁጥጥራችን ውጭ ሆነ። ይህን ያለፈውን ሕይወቴን ጠባሳ ሊለውጥልኝ የሚችል ቢኖር፣ ያለኝን ሁሉ እሰጠው ነበር"።

የወሲብ ፈተናን ለመቋቋም ጊዜው አሁን ነው፤ ቅጥራችሁን ሰብሮ በኃይል በናንተ ላይ ሲመጣ አይደለም። አካላችሁንና አሳባችሁን ለእግዚአብሔር የመስጠት ጊዜው አሁን ነው፤ የንፅህና አቋም የመውሰድ ጊዜው አሁን ነው፤ አስቀድሞ የማቀድና የወሲብ ፈተና ሲገጥማችሁ ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባችሁ በትክክል የምታውቁበት ጊዜ አሁን ነው። ቀደም ሲል ፈተናን ስለ መቋቋም የተነጋገርነውን አስታውሱ፤ ፈተናን ለይታችሁ ስታውቁት፣ ወዲያውኑና ያለማወላወል ተቃወሙት።

## የክርስቲያን ባህርይ፡- አርነት

"አርነት" የሚለውን ቃል ስንሰማ ብዙ ጊዜ የሚታሰበን ፖለቲካዊ አርነት ወይም ያለገደብ የመኖርን አርነት ነው። ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ግን "አርነት" ሚለው ቃል የሚከስትላቸው ምስል ከዚህ የተለየ ነበር። የታሪክ አዋቂዎች እንደሚገምቱት የሮማ ግዛት ቢያንስ ግማሽ ያህሉ ባሮች ስለነበሩ፣ "አርነት" የሚለው ቃል ለነርሱ ከባርነት ቀንበር መላቀቅን የሚያመለክት ነበር።

ባርነት አስከፊ ሥርዓት ነው፣ በልጅነቴ አፍሪካዊ አሜሪካውያን ጓደኞቼ በደቡብ አሜሪካ በአያት ቅድመ አያቶቻቸው ላይ የተዋለባቸውን ግፍ ሲገልጹ እሰማ ነበር። ኢየሱስ እንደሚነግረን ግን ከዚህ የከፋ ባርነትም አለ፣ "እውነት





እላችኋለሁ፤ ኃጢአት የሚያደርግ የኃጢአት ባሪያ ነው።" ይሁንና እንዲህ ሲል አክሏል፡- "እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትወጣላችሁ" (ዮሐ 8+34፣36)።

ይህን አስቡ፣ በክርስቶስ አርነትን አግኝተናል - ከኃጢአት ባርነት፣ ኃጢአት ከሚያስከትለው በደለኝነትና ፍርሃት፣ ከኃጢአት መዘዝ፣ ከኃጢአት ኃይል ሳይቀር ነጻ ወጥተናል። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ከኃጢአት አርነት የመውጣት ልዩ ክብር ተሰጥቶታል፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ነጻ አውጥቶናል! ይህ ማለት እንደምንፈልገው ለመሆን መረን እንለቀቃለን ሳይሆን (እንደዚህ ቢሆን፣ ዳግመኛ የኃጢአት ባሮች እንሆናለን)፣ ክርስቶስን ለማገልገል አርነት አለን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሆነው ወደ ክብረው ነጻነት የሚደርስበት ጊዜ እንዳለ" ይነግረናል (ሮሜ 8+21)።

ይሁንና ሰይጣን እኛን ዳግመኛ ወደ ባርነት ለመጎተት የቻለውን ሁሉ ያደርጋል! - ሁልጊዜ ወደ አንድ ወደ ተለየ የኃጢአት ባርነት። ከሚደርሱኝ ልብን በሐዘን ከሚሰብሩ ደብዳቤዎች ውስጥ ሰዎች በመጠጥና በዕፆች ሱስ ሕይወታቸው እንደጠፋና ቤተ ሰባቸው እንደ ፈረሰ የሚገልጹ በት ነው። ሌሎች ደግሞ የዕዳ ወይም የምግብ ወይም የጎጂ ልማድ ወይም የአንድ ዓይነት ሥነ ልቦናዊ ቀውስ ባሮች ይሆናሉ። እንደማይጎዳ እንደ ጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተጀመረ ነገር መጨረሻው እስፈሪ፣ ሊቋቋሙት የማይቻል ሱስ ወይም በገዛ ራስ ጉልበት ሊላቀቁት የሚያስቸግር ልክፍት ይሆናል።

እናንተስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ናችሁ? ልትቋቋሙት እስቸጋሪ የሆነባችሁና በሕይወታችሁ ተጣብቆ አልላቀቅ ያለ አንዳች ኃጢአት አለ? እንደዚህ ከሆነ ኃጢአታችሁን በእውነተኝነት ተጋፈጡ፣ እናም ይታ ደጋችሁ ዘንድ የእግዚአብሔ ርን እርዳታ እሹ። መላ ሕይወታችሁን - ይህንን ችግር ጨምሮ - ለክርስቶስ አስረክቡ፣ የሚያስፈልጋችሁን እርዳታ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። ከዚህ ችግር ውስጥ የገባችሁበት ምክንያት ጥልቅና የተወሳሰበ

ሊሆን ይችላል። (ምናልባት መነሻው ከልጅነታችሁ ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይችላል)። መጋቢያችሁ ወይም ሐኪ.ማችሁ፣ ይህን ችግር እንድትረዱና በማሸነፍ ረገድ ሊያገለግሏችሁ የሚችሉ የሠለጠኑ የማማከር ባለሙያዎች ወይም በአካባቢ. የሚገኝ ጣቢያ ሊያመላክታችሁ ይችላል። እግዚአብሔር አርነት እንድትወጡ ይፈልጋል፤ ከተጫናችሁ ከዚህ ቀንበር ተላቃችሁ በሙሉ ልባችሁ ክርስቶስን መውደድና ማገልገል የሚያስችላችሁ ነፃነት ሊሠጣችሁ ይሻል።

ከእንግዲህ የኃጢአት ባሮች አትሁኑ፣ በእምነት ልባችሁንና ሕይወታችሁን ለክርስቶስ በማስረከብ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁለንተናችሁን እንዲገዛ ፍቀዱለት። ክርስቶስን የምታዉቁ ከሆነም፣ ሠይጣን ከእናንተ ምንም እንዳያተርፍ (እንዳያገኝ) በንቃት ተከላከሉት፣ "እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ ዳግመኛ በባርነት ቀንበር አትጠመዱ" (ገላ 5፥1)።





# ሃያ

## ሕይወት ሲጣመምብን

*የመከራ ማዕበል ሲያንገላታን ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንሸነፍም፣ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቆርጥም*

(2 ቆሮ 4፥-8)

"ለምን?" የሚለው ጥያቄ በዓለም እጅግ ተዘውትሮ የሚነሳ ነው። ክፋት እንደዚህ የተንሰራፋው ለምንድነው? ምንም ያልበደሉ ሕፃናት በካንሰር፣ በስቃይና በረሃብ ለምን ይሞታሉ? ዓለም በተፈጥሮአዊ አደጋዎች፣ በጦርነትና በበሽታ የምትታመሰው ለምንድነው? ብዙ የልብ መሰበር ያለው ለምንድነው? መልካም ሰዎች እንደ ክፉዎች እንዲያውም የበለጠ የሚሰቃዩት ለምንድነው? እግዚአብሔር እንደሚባለው አፍቃሪና ርህሩህ ከሆነ፣ ይህን ሁሉ እያየ አንድ ነገር የማያደርገው ለምንድነው? ለምን?

### ቀውስ ውስጥ የገባች አገር

እ.ኤ.አ. መስከረም 11 ቀን 2001 በአሜሪካ ላይ የደረሰውን ጥቃት ማንኛችንም አንዘነጋውም። በደቂቃዎች ውስጥ ሁለት የተጠለፉ አውሮፕላኖች፣ በአሜሪካ ረዥሙ የሆነውን የትዊን ታወርስ ሕንጻ፣ በኒውዮርክ ከተማ የሚገኘውን የዓለም የንግድ ማዕከልና በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የሚገኘውን ፔንታጎንን ሲመቱ ዓለማችን ተቀየረች፣ እንደ ቀድሞም ልትሆን አልቻለችም። በዚያ ምሕረት የለሽ የሽብርተኞች ጥቃት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የእሳት አደጋ ሠራተኞች፣ የፖሊስና የድንገተኛ አደጋ ሠራተኞች ሞቱ። በአራተኛው የተጠለፈ

በአንድ ምክንያት እንደሆነ እናውቃለን፤ ይህም ክርስቶስ ለእኛ ሞቶ በመነሳቱ ነው፡፡ መጥፎ ሁኔታዎች ለምን እንደሚከሰቱ ባይገባንም እንኳን፣ መስቀሉ የሚያበስርልን የምስራች እግዚአብሔር እንደሚወደንና እንደሚጠነቀቅልን ነው፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ወደር የሌለውና እጅግ ታላቁ መከራ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ የተቀበለው መከራ ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ወታደሮች ሊይዙት ከመምጣታቸው ከአንድ ሰዓት በፊት እንዲህ ሲል ጸልዮአል፡- “አባቴ ሆይ፣ ቢቻልህ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ” (ማቴ 26፥39)፡፡ “ጽዋ” የሚለው ቃል ሊቀበለው ያለውን መከራ ሁሉ የሚወክል ነው፡፡ “ጽዋው” የሰውን ዘር ኃጢአት ሁሉ የያዘ ሲሆን፣ መስቀል ላይ ሆኖ ጠጥቶታል፡፡ በዚህ “ጽዋ” ስላለው ነገር ለአፍታ እናስብ - በሰዎች የተፈጸሙ ግድያዎች፣ አመንዝራነት፣ ስርቆት፣ ፍትህ ማዛባት፣ ክፉ ሀሳብና ድርጊት ሁሉ - ሰው የሠራው ኃጢአት ሁሉ በዚያ “ጽዋ” ውስጥ ነበር፡፡ የሰው ልጅ ድነት የሚፈጸምበት ሌላ መንገድ እንዳለ አባቱን ቢጠይቅ የሚያስገርም አይሆንም! ይሁን እንጂ ሌላ መንገድ አልነበረም፡፡ ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ኃጢአቶቻችንን ሁሉ ይሸከማል፤ ስለዚህም የእግዚአብሔር ፍርድ በእኛ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ ይወርዳል፡፡ የኢየሱስ መከራ እንዲያው በጭካኔና በስቃይ እንደተገደለ ሰው መከራ ብቻ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ በጣም የሚደስጋም ነበር፡፡ ከተቀበለው መከራ ሁሉ ትልቁ እኔና እናንተ የሚገባንን ሞትና ሲኦል በራሱ ላይ በማኖር የተቀበለው መንፈሳዊ ስቃይ ነበር፡፡

ሆኖም እግዚአብሔር እኛን ምን ያህል እንደሚወደን ያሳየን ልጁን በሞትና በገሃነም መውጊያ እንዲቀሰፍ በማድረግ ነው፡፡ እኛን ባይወደን ኖሮ፣ ልጁ የመንግስተ ሰማያትን ክብር ትቶ ለእኛ እንዲሞት ባልፈቀደ ነበር፡፡

## የኛ ምላሽ እንዴት ነው?

በቅርቡ አንዲት ሴት በቁጣ፣ “የእግዚአብሔርን ነገር በቃኝ ብያለሁ፡፡ ባለፈው ወር ሕጻን ልጃችን በድንገት በበሽታ ተቀጨ፤ በእግዚአብሔር ላይ ተመርሬአለሁ፡፡ ምንም ነገር ሊያጽናናኝ ወይም ይሀን ሊያካክስ አይችልም” ስትል ጻፈችልኝ፡፡ የዚህች ሴት ቃል





ልብን በሀዘን የሚያውክ ነበር፤ ልጅን በሞት እንደ መነጠቅ ያህል የሚያሳምም ነገር የለም፤ እግዚአብሔር ስሜትን እንደሚረዳ ሁሉ እኔም በተወሰነ መንገድ ምንኛ በጠለቀ የልብ ስብራት እንደምትመታ ማሰብ እችላለሁ፡፡ ይሁንና ህዘኗ ልቤን የነካው በሌላም ምክንያት ነበር፤ ይሀን መሪር እጣ ተቋቁማ ማለፍ የምትችልበት መፅናናትና ጥንካሬ ያሻት ነበር፡፡ ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ስትካረፍ ይሀን ሊሰጣት ከሚችለው ብቸኛ አለኝታ ራሷን እያራቀች ነበር፡፡ መዝሙረኛው የተናገረው ቃል እውነት ነው፡- “አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፣ በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ ረዳታችን ነው” (መዝ 46፥1)፡፡

ለእኛ ቢታወቀንም ባይታወቀንም፣ አዱኛ ሲርቀንና ሕይወት ጎርባጣ ስትሆንብን፣ በወሳኝ መንታ መንገድ ላይ ነን፡፡ ሀዘን ወይም መከራ ወይም አንዳች ዱብዳ ሲገጥመን “ከእግዚአብሔር እንርቃለን? ወይስ ወደ እርሱ እንቀርባለን” ከሚለው ጥያቄ ጋር እንጋፈጣለን፡፡

የእርሱን ድጋፍና እርዳታ እንገፋለን ወይስ እንሻለን? የሚያስፈልገንን ብርታት ለማግኘት በራሳችን ላይ ወይስ በእርሱ ላይ እንደገፋለን? የትኛውን መንገድ እንወስዳለን? አንደኛው መንገድ ወደ ጥርጥር፣ ንዴት፣ መራርነት፣ ፍርሃትና፣ ተስፋ መቁረጥ ይመራል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ወደ ተስፋ፣ መጽናናት፣ ሰላም፣ ብርታትና ደስታ ይወስደናል፡፡ የትኛውን መከተል ትመርጣላችሁ?

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የሕይወት ጉዞአችን መቼም ቢሆን አልጋ ባልጋና ከችግር የተላቀቀ ሊሆን አይችልም፡፡ ሕይወት ሁልጊዜ ይገባናል የምንለውን አትከፍለንም፣ እንዲሆንልን እንደምንመኘውም ሁሌ ቀና ሆኖልን አያዘልቀንም፡፡ ሀዘን፣ ዱብዳ፣ የልብ ስብራት፣ ውድቀት፣ የአካል መጉደል፣ በሽታ፣ የፍትሕ መጓደል፣ መገፋት፣ መከራ - እነዚህ ሁሉ ፣ አንዳንድ ጊዜ በፍጹም ባልጠበቅናቸው ጊዜያትና ባልተጠበቁ መምጣታቸው አይቀርም፡፡

እነኢህ ነገሮች ሲገጥሙን፣ "ጌታ ሆይ ለምን? ይህ ለምን ይሆንብኛል?" ብሎ መጠየቁ ተፈጥሮአዊ ነው። ይህን ጥያቄ ማንሳቱ ስህተት አይደለም፤ እንዲያውም እግዚአብሔር ጩኸታችንን ሊመልስልን ይችላል (ቢያንስ ፍንጭ ይሰጠናል)፤ ምክንያቱም እኛን በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በማሳለፍ ሊያስተምረን የሚሻው ትምህርት ስላለ ነው።

ሆኖም ሕይወት ጨለማ ስትሆንብን ልንጠይቀው የሚገባን ዋናኛ ጥያቄ "ለምን?" ሳይሆን "ምን?" መሆን አለበት። "ጌታ ሆይ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ? ለዚህ ሁኔታ ምን ምላሽ ልሰጥ ይገባኛል? እንዴት ባለ ሁኔታ እንድመልስ ትሻለህ?" ማለት ይገባል።

ይህንን ጥያቄ ሳንጠይቅ ስንቀር፣ ምላሻችን የመራርነት፣ የቁጣ፣ የቅናት ወይም የብስጭት ብሎም የተስፋ መቁረጥ ስለሚሆን የተሳሳተውን መንገድ ልንከተል እንችላለን። ይህን ስናደርግም፣ ሁልጊዜ ከባድ ዋጋ እንከፍላለን። መንፈሳዊ ባልሆነ፣ እግዚአብሔርን መምሰል በጎደለው መንገድ ምላሽ መስጠት ምንም መፍትሔ አያስገኝልንም፤ ሁልጊዜም ሁኔታውን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል። ነፍሳችን ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ሰዎችና ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ይመረዛል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ዓይነት ሰው እንዲህ ይላል፡- "በብዙ ጭንቀት፣ በመከራ፣ በብስጭት፣ በደዌና ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ውስጥ ይበላል" (መክ 5፥17)። ከዚህ ዓይነቱ ሰው አጠገብ ለመድረስ የሚፈልግ ማነው? እውነቱን ለመናገር፣ የዚህ ዓይነት ሰው ለመሆንስ የሚፈልግ ማን ነው?

## ለክፉ ቀን መዘጋጀት

ይሁንና ስንከፋ ሁልጊዜ በትክክለኛ መንገድ ምላሽ መስጠት ቀላል አይደለም። ለእኛ ሳይታወቀን፣ ስሜቶቻችን ሚዛን በማሳጣት ስለሚያናጉን፣ በንዴት፣ በእልህና ወይም በተስፋ መቁረጥ ወጀብ መላጋት እንጀምራለን። የምንሰጠውን ምላሽ ለአፍታ ቆም ብለን ለመመርመር ብንሞክር እንኳን፣ በዚያች ቅጽበት ሚዛን በማጣት





የተናገርነውን ክፉ ቃል መመለስ ወይም ያደረስነውን ጥፋት መቀልበስ መሞከሩ "የፈሰሰ ውሃን እንደማፈስ" ይሆንብናል።

ለዚህም ነው ሊመጡ ላሉት ሀዘኖችና የልብ ስብራቶች መዘጋጀት ያለብን አስቀድሞ ሳይከሰቱ በፊት መሆን ያለበት፡፡ የሁኔታዎች ጭንቀትና ግፊት የማያናውጠውን መንፈሳዊ መሠረት የመገንባት ጊዜው አሁን ነው፤ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና መከራ ሲመጣ የእርሱን መንገድ ለመከተል የመወሰን ጊዜው አሁን ነው፤ ያልታሰበ አደጋ ድንገት ሲደርስብን እምነታችን እንዳይከዳን፣ በርትቶ የመገኘት ጊዜው አሁን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የጭንቀት ጊዜ ሳይመጣ፣ ደስ አያሰኙም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፣ በወጣትነትህ ጊዜ ፈጣሪህን አስብ" (መክ 12፥1)።

በሐኪም ቤት በሽተኞችን የሚያገለግል ሰው በአንድ ወቅት እንዲህ አለኝ፣ ‹‹አዲስ የምንቀበላቸው በሽተኞች ምን ያህል የጠነከረ እምነት እንዳላቸው የማውቅበት መንገድ አለኝ። ጠንካራ እምነት ካላቸው፣ ብርታት ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር መዞርን ከልምዳቸው ያውቃሉ፣ የሚያደርጉትም ይህንኑ ነው። ደካማ እምነት ያለው ሰው ግን ይህን ሊያደርግ አይችልም። መከራቸውን ማለፍ የሚችሉበት መንፈሳዊ አቅም አይኖራቸውም፣ አሁን ይህ እምነት ይኑረኝ ቢሉም አይሆንላቸውም"። ኢየሱስ በነገረን ታሪክ፣ ቤቱን አሸዋ ላይ እንደሠራው ሰው ማዕበል ሲያናውጣቸው መከታ አይኖራቸውም። ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል ጨምሮ ይናገራል፡- "እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል፣ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራው ብልህ ሰው ይመስላል። ዶፍ ወረደ፣ ጎርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንን ቤት መታው፣ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም" (ማቴ 7፥24- 25)። ከጥቂት ወራት በፊት ኃይለኛ የንፋስ ማዕበል በቤታችን ዙሪያ የነበሩ በርካታ ዛፎችን ነቃቅሎ፣ የመሬት መናድ አስከተለ። ቤቱ ራሱ ግን ምንም አልሆነም፣ ምክንያቱም ቤቱ ሲሰራ፣ እንደ አርኪቴክት ወዳጃችን መሰረቱን በጠጣር ዐለት ላይ የብረት ርብራብ አድርገን እንድንሰራው በነገረን መሠረት ስለሰራነው ነው።

የእናንተስ የሕይወት መሠረት ምን ያህል የተደላደለ ነው? ጥንካሬውን የበለጠ የተደላደለ ለማድረግ ምን እያደረጋችሁ ነው? የቤት መሠረት በአንድ ጀምበር አይሠራም፤ መንፈሳዊ መሠረትም እንደዚሁ። ለሕይወታችሁ የማይናወጥ መሠረት መጣልን ዓላማችሁ አድርጉ፤ ይህም በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል የተገነባ መሰረት ነው። የጥንት ዝማሬ ይህን ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል፣ “የጌታ ቅዱሳን መሠረቱ ምንኛ ጽኑ ነው፣ ወደር በሌለው ቃሉ በማመናችሁ የተዘጋጀላችሁ ነው!”

## ብስጭትና ውድቀት

ሕይወት በበርካታ መንገዶች ፈታኝ ታዞርብናለች፤ በሁላችንም ሕይወት የሚገጥመን የተለመደ ክስተት ግን ብስጭት ነው። አንዳንዴ ምክንያቱ ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ በድንገተኛ ማዕበል ምክንያት የሽርሽር መሰረዝ ሊሆን ይችላል። ሩትና እኔ በተዋወቅንበት ጊዜ በየጊዜው ደብዳቤ እንለዋወጥ ነበር፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በደብዳቤ የጋብቻ ጥያቄ አነሳሁባት። በየቀኑ በፖስታ ሳጥን ውስጥ ከርሷ የመልስ ደብዳቤ እንደሌለ ሳውቅ ምን ያህል የመከፋት ስሜት ያድርብኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። (በርግጥ በመጨረሻ ላይ ይሁንታዋን የሚገልጽ ደብዳቤ ስትጽፍልኝ መከፋቴ ወደ ደስታ ተለውጧል!)

ሌሎች መከፋቶች ግን ከዚህ በበለጠ ይጐረብጣሉ። ለምሳሌ እርካታ የማይሰጥ ሥራ፣ ልጅ ዐመሉ ተበላሽቶ በቤተሰብ ላይ ሲያምፅና እሬት እሬት የሚል ጋብቻ ናቸው።

ብስጭቶች በተደጋጋሚ ሲገጥሙን ሌሎች ተመሳሳይ ስሜቶችን ያጭራሉ፣ የልብ መዛል፣ ቁጣ፣ እልህ፣ መራርነት፣ ኩርፊያና ከዚህም አልፎ ድብርት (ብርቱ ጭንቀት) ይገጥሙናል። ለዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በጊዜ መፍትሔ ካላገኘንላቸው፣ ደስታችንን በማጥፋት ነፍሳችንን ይመርዛሉ። “እኔን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም” (ኢሳ 49፥23) ተብሎ የተነገረንን የተስፋ ቃል በመዘንጋት እግዚአብሔርን መወንጀል እንጀምራለን።





ለብስጭት በቅርበት የተዛመደው ሌላው የሕይወት እውነታ ውድቀት ነው። ብስጭት በሁላችን ላይ የሚደርስ ዕጣ እንደሆነ ሁሉ፣ ውድቀትም ሁላችንን የሚገጥመን ነገር ነው። ልክ እንደ ብስጭት፣ ውድቀት ከመለስተኛ ጀምሮ ከመሰረታችን የሚያናጋንና ሌሎች እሉታዎች፣ ስሜቶች፣ ጭንቀት፣ ሽብርና ብሎም ተስፋ መቁረጥ የሚያስከትል ገጠመኝ ሊሆን ይችላል። በሥራ ወይም በግንኙነት ያቀድናቸው ግቦችን ማሳካት አለመቻል ሊሆን ይችላል። ወይም እግዚአብሔር ከእኛ ከሚጠብቀው ጉድለን መገኘት፣ ማለትም ግብረገባዊ ወይም መንፈሳዊ ውድቀት ሊሆን ይችላል።

ብስጭትና ውድቀት አንድ ባይሆኑም፣ በአንድ ጊዜ ሲከሰቱና እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ሀሳብ ሲያጎድሉን ይችላሉ። በተወሰነ መልኩ ግን ውድቀት የበለጠ አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም በተደጋጋሚ የሚወድቅ ሰው የውድቀቶቹ ምርኮኛ ስለሚሆን ነው። በሌላ አባባል እነኚህ ሰዎች አንዴ ስለወደቁ፣ ሁልጊዜ እንደሚወድቁ ደምድመው ይቀመጣሉ። አንድ ወጣት እንዲህ ሲል ጻፈልኝ፡- “ከማደርገው ነገር የትኛውም ልክ የሚባል የለም፤ አሁንማ መሞከርም አቁሜአለሁ።” ቀጥሎም ውድቀቱን ለመርሳት ሲሞክር የአልኮል ሱሰኛ ወደ መሆን እንደተቃረበ ተናገረ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ወድቄአለሁ ብሎ ማመኑ ወደ ባሰ የውድቀት ሽክርክሪት ውስጥ ከተተው። የዚህ ሰው ችግር ውድቀቱ ድል እንዲነሳው መፍቀዱ እንጂ መውደቁ ብቻ አልነበረም። እኔም ይህንን አጉል ዑደት መስበር የሚችለው በእግዚአብሔር እርዳታ ብቻ እንደሆነ ነገርኩት።

## ውድቀትንና ቅይማትን (መከፋትን) ማሸነፍ

ውድቀትና ቅይማት ሁልጊዜ ስህተት አይደሉም፣ ሁላችንንም በሕይወት መንገዳችን ያጋጥሙናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- “ሁላችንም በብዙ ነገር እንሰናከላለን (ያዕ 3፥2)። የሚገጥመን ማንኛውም ውድቀት ወይም ቅይማት የእኛ ኀላፊነት አይደለም፤ ለምሳሌ የሚሠራበት ኩባንያ ሠራተኞችን በመቀነሱ ምክንያት ሥራውን ያጣ ሰው ለዚህ ተጠያቂ አይደለም።

አንዳንድ ጊዜ ለውድቀቶቻችን ተጠያቂ የምንሆንበት ሁኔታ አለ፤ ስለዚህም የእኛ ጥፋት እንዳለበት ለማየት በታማኝነትና በጸሎት ልባችንን መመርመር አለብን። አንዳንድ ጊዜ ውድቀት የገጠመን ምናልባት በነፍሳችን ሥር እንዲሰድ በፈቀድንለትና መንገዳችንን ባበላሸ በአንድ በተወሰነ ኃጢአት ሳቢያ ሊሆን ይችላል። ውድቀትና ቅይማት ወደኋላ እንዲጎትቱን እና እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ዓላማ እንዲገቱ ስንፈቅድ ኃጢአት ይሆናሉ። ያስታውሱ፤ እግዚአብሔር ለኛ ያለው መሻት ክርስቶስን እንድንመስል ነው፣ ነገር ግን ከቅይማትና ከውድቀት ባለመላቀቅ ከፈቀድን ይህ ሊሆን አይችልም።

*ታዲያ ውድቀት ወይም ቅይማት ሲገጥመን ምን ማድረግ ይኖርብናል?*

*አንደኛ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ ያለው ፍቅር እንዳልተለወጠ አስታውሱ።* ሁሉም ነገር ያማረና ቀና ሲሆን እግዚአብሔር እንደሚወደን ማመን ቀላል ነው፤ መንገዳችን በጋሬጣና በመሰናክል ሲከበብ ግን እንደሚወደን ማመን ቀላል አይሆንም። ሆኖም ቅይማት ወይም ውድቀት፣ እግዚአብሔር እንደተዋችሁ ወይም እናንተን መውደዱን እንዳቋረጠ አያመለክቱም። ስትወድቁ ሰይጣን በቃ እግዚአብሔር አይወድህም በማለት ሊያሳምናችሁ ይፈልጋል፤ ግን ይህ እውነት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር ደምቆ የሚታየን በጨለማ ስንከበብ ነው።

ይህ ማለት እግዚአብሔር ኃጢአትን አድበስብሶ ይተዋል ወይም በአለመታዘዛችን ደስ ይለኛል ማለት አይደለም - በጭራሽ። እኛ ለርሱ ያለንን ታማኝነት ብናጓድል እንኳን፣ እግዚአብሔር ፍቅሩን አያጓድልብንም፤ እርሱ ሁልጊዜም ይቅር ሊለንና ወደራሱ ሊመልሰን ዝግጁ ነው። ነቢዩ ኤርምያስ በኖረበት ዘመን እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ ራሳቸውን ለጽኑ ቁጣ አጋለጡ። ግን ይህም ሆኖ እንኳን፣ እግዚአብሔር ፍቅሩ እንዳልተለወጠ ዋስትና ሰጣቸው። "ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር





ታላቅ ፍቅር የተነሳ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና፣ ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህም ብዙ ነው" (ሰቆ 3፥22-23)።

*ሁለተኛ፣ ውድቀትና ቅይማትን በሚዛናዊ አይታ መመልከትን ተለማመዱ።* ውሃ ቀጠነ ብለው የሚበሳጩ ወይም የሚነጫነጩ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን፤ እናንተም የዚህ ዓይነት ሰዎች ልትሆኑ ትችላላችሁ። ሆኖም በጥቃቅን ችግሮች ያለልክ መበሳጨት፣ ችግሮች የሉም ብሎ ራስን የመደለልን ያህል ስህተት ነው። የሚያበሳጭ ነገር ያጋጥማል፤ ሁኔታዎች ሁልጊዜ እኛ እንደፈለግናቸው አይሆኑም፤ ስለዚህ ትኩረት ሊሰጠው የሚያስፈልገውን ነገር እንዲሁ ከሚያበሳጨን ነገር ለመለየት መማር አለብን። በሆነው ባልሆነው (ወይም ሊለወጥ በማይችል ነገር) መበሳጨት ፋይዳቢስ ነው። ውድቀትና ቅይማት ፊጽመው የሚወገዱት በመንግስተ ሰማያት ብቻ ነው። አንድ ጓደኛዬ እዚህ ግባ የማይባል ነገር ሲረብሸው፣ ራሱን እንዲህ ሲል ያረጋጋል፦ "ይህ ጉዳይ የዛሬ መቶ ዓመትም የሚያመጣው ለውጥ የለም።"

ከፋቱ ግን ሁሉም ውድቀትና ቅይማት አናሳ ነው የሚባል ላይሆን ይችላል፤ መጸዓ. ጉዞአችን ላይ የገዘፈ አንድምታ ሊኖረው ይችላል። በተጨማሪም በባህርያችን ወይም በሁኔታዎች አንዳች መፍትሔ የሚያሻው ክፍተትን አመላካች ሊሆን ይችላል። ይህ ሲከሰት፣ ቆም ብለን ልብ ማለት ይኖርብናል።

## ከተሞክሮአችን መማር

*ውድቀትንና ቅይማትን የማስተናገድ ሶስተኛው መርህ፣ ይህ ነው፤ ከገጠማችሁ ውድቀት ወይም ቅይማት ያለመሳካት በመማር፣ በእግዚአብሔር ረድኤት፣ ልትቋቋሟቸው ትጉ።*

ምን ባደርግ ከዚህ ላመልጥ እችል ነበር? ተስፋዎቼና ህልሞቼ እውነታን ያላገናዘቡ ነበሩ? መሻቴስ የተሳሳተ ነበር? ልናዘዘው የሚገባኝ ኃጢአት ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር እንድከተለው የሚፈልገው መንገድ አለ? መከሰቱ ባይቀርም እንኳ ከዚህ ተሞክሮ የምማረው ነገር አለ? እግዚአብሔር ሊያስተምረኝ እየፈለገ ያለ ነገር አለ?

ለምን ይሆን?"፤ እርሱም ጥቂት አሰብ ካደረገ በኋላ ባንድ ቃል "ሰዎች" ይሳታል። በርግጥ ሰዎች መልካምና ለሌሎች መስዋዕትነት የሚከፍሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግን በዚያው ልክ ደግሞ እዋኪዎች፣ ግትሮች፣ በእኔነት የሚነዱ፣ ይሉኝታ ቢሶች፣ ከፉዎች ራስ ወዳዶችና ሌሎችን የሚሸከረከሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ችግሩ ሰዎች ብቻም አይደሉም፣ እኛም ራሳችን ነን።

## ግጭት ለምን ይነሳል?

ተስማምተን መኖር የሚያቅተን ለምን ይሆን? አንዳንዶቹ ምክንያቶች ግልጽ ናቸው (ቢያንስ ላይ ላዩን ስንመለከታቸው)። ለምሳሌ ያህል፣ ከተለያዩ ባህሎች ወይም አኗኗሮች የመጡ ሰዎች፣ ሌሎችም የራሳቸውን መንገድ ብቻ እንዲከተሉ ስለሚፈልጉ ነው። የተቃረነ ስብዕና ያሉአቸው ሰዎች እርስ በርስ መስማማት ይቸግራቸዋል። የኛ ጎሣ ወይም ዘር የበላይ ነው ባዮች ከሌሎች ጋር ሰላም መመሥረት ቀላል አይሆንላቸውም።

ዋናው ግን ከነዚህ በስተጀርባ ያለው ጠለቅ ያለ ችግር ነው፤ እኛ እያንዳንዳችን ያልነው ይሁን ባዮች ወይም የራሳችንን ፈላጊዎች ስለሆንን ነው። "ይሄ ሰውዬ ምናለ የምለውን ቢሰማኝ ኖሮ" "ቢሰማኝ እንስማማ ነበር" እንላለን። ችግሩ ሌላኛውም ሰው ልክ እንደዚሁ ነው የሚያስበው - ይህም ግጭት ያስከትላል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚዋጉት ምኞቶቻችሁ አይደለምን? (ያዕ 4፥1)

ለዚህ ነው አፍአዊ ሁኔታዎችን መለወጥ ብቻውን መፍትሔ የማይሆነን። አንዲት ሴት እንዲህ ስትል ጻፈችልኝ፣ "በአገራችን ወደተሻለ አካባቢ ተዛውረን የሚያምር ቤት መሥራት ብንችል ደስተኞች የምንሆን መስሎን ነበር። ግን አልሆነም። ችግሮቻችን እዚያው ተከትለውን መጡ። ስለዚህ ቀጣዩ መድረሻችን (አማራጫችን) ፍርድ ቤት ቆሞ ፍቺ መጠየቅ ይመስለኛል።" ጥልቅ ችግሮቻችን ያሉት እኛው ዘንድ ነው። ያሉት በልባችንና በአእምሮአችን ነው። ስለዚህም እነኚህን ችግሮች ፊት ለፊት እስክንጋፈጥና ለመለወጥ የእግዚአብሔርን እርዳታ እስካልፈለግን





ድረስ፣ ሙሉ በሙሉ ልንፈታቸው አንችልም። ኢየሱስ በማቴ 15፥19፣ "ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጉደፍ ከልብ ይመነጫልና" ብሏል። እነዚህ ኃጢአቶች ሁሉ ሌላውን ሰው እንድንጐዳ የሚያደርጉ ናቸው።

ክርስቲያኖችም ከነዚህ ግጭቶች ነፃ አይደሉም። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የቀደመው አዳማዊ ባሕርያችን አብሮን (በውስጣችን) ይኖራል፣ ባለማቋረጥም ራሱን (መኖሩን) ሊያረጋግጥ ይሞክራል። በተጨማሪም፣ ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለመለያየትና ምስክርነታችንን ለማጥፋት የማያደርገው ነገር የለም። እርጌ ባሕርያችንን በእግዚአብሔር ፍቅር ሊያሸንፍና ሊጫነው የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

## የእግዚአብሔር ቀዳሚው ፍላጎት:- በፍቅር ውስጥ መኖር

በየዓመቱ ቁጥራቸው የበዛ ጉባኤዎች ይደረጋሉ። መንግስታት፣ ዘሮችና ባሕሎች እርስ በርሳቸው እንዴት ሊስማሙ እንደሚችሉ የሚመለከቱ ሲሆኑ ያለውጤት ይጠናቀቃሉ። የዓለምን ችግር ለማቃለል ምን መደረግ እንዳለበት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች ወስዳችሁ ብትመለከቱአቸው፣ እርግጠኛ ነኝ በአንድ አረፍተ ነገር መጠቃለል የሚችሉ ናቸው፤ መልሱ እርስ በርስ መዋደድ ከተማርን ብዙ ችግሮች አይኖሩብንም የሚል ነው። የተበላሹ ነገሮች በሙሉ መስመር ይይዛሉ፣ ምክንያቱም በአንድ ጊዜ አንድን ነገር እኩል ለመውደድና ለመጥላት አንችልምና። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ፍቅር ብዙ ኃጢአትን ስለሚደመስስ ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ" (1 ጴጥ 4፥8)።

ነገር ግን ምላሹ እንዲህ ቀላል ሆኖ ሳለ፣ ለምን ይህ ሊፈፀም አልቻለም? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል እንመልከት።

አስቀድመን ምን እንደተነጋገርን አስታውሱ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እኛ የበለጠ ክርስቶስን እንድንመስል ነው - *ይህም ማለት በባህርያችን የበለጠ እርሱን እንድንመስል ማለት ነው።* መጽሐፍ

ቅዱስ ሲያዝዘን፦ "ስለዚህ አታልሎ ወደ ኃጢአት በሚመራ ምኞት የተበላሸውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ፤ . . . በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል የተፈጠረውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ" (ኤፌ. 4፥22፤24)::

"በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል›› ሲል ምን ማለቱ ነው? እንኖርበት የነበረውንና ስህተት እንደነበር የምናውቀውን የተለያዩ ልማዶችና ክፉ መንገዳችንን ማለት ነው? ወይስ ከዚህ የበለጠ ጥልቅ የሆነ ነገር ነው? ይህ ያለን ልማድ በሌሎች ሰዎች ላይ ሊፈጥር የሚችለው የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል?

ጉዳዩ በቀላሉ ይህ ነው፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እኛ የኢየሱስን ባህርይ እንድናንፀባርቅ ነው - የኢየሱስ ባህርይ መሰረቱ ፍቅር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃለን፤ እናምናለንም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል" (1ዮሐ 4፥16):: ኢየሱስ ሲናገር፤ "እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ። እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ከተዋደዳችሁ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሰው ሁሉ ያውቃል" (ዮሐ 13፥34-35)::

ፍቅር ምንድን ነው? በአማርኛ አንድ ቃል ነው ያለን - "*ፍቅር*":: ፍቅር የሚለው ቃል ብዙ የተለያዩ ፍቺዎች አሉት:: *የሥነ መለኮት ምሁራን የግሪክን ቋንቋ* (የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የተፃፈበት ቋንቋ) በመጠቀም ያቀረቡትን ከአራት ፍቺዎች የማያንሱ የፍቅር አይነቶችን እንመልከት። አንደኛው የፍቅር አይነት *ኢሮስ* ነው፤ ይህም አካላዊ የሆነ ውበትንና (ቁንጅናን) በወሲብ ስሜት በመነሳሳት የሚገለጽን የፍቅር ዓይነት የሚያሳይ ነው። ሁለተኛው የፍቅር አይነት ደግሞ "*ስትሮጅ*" ሲሆን የቤተሰብን ፍቅር የሚመለከት ነው፤ ይህ አይነቱ ፍቅር በወላጆችና በልጆች መካከል የሚታየውን ፍቅርና መዋደድ የሚያሳይ ነው። ሶስተኛው የፍቅር ዓይነት ደግሞ "*ፊሊዮ*" የሚባል ሲሆን በጓደኞሞች መካከል





የሚፈጠረውን ወንድማዊ የሆነ ባልንጀርነትን የሚያሳይ የፍቅር ዓይነት ነው:: (ፊላደልፊያ "የወንድማማቾች የፍቅር ከተማ" ተብላ የተሰየመችው ከዚህ በመነሳት ነው።)

የመጨረሻው የፍቅር ዓይነት፤ "*አጋፔ*" ፍቅር ነው:: ይህ ዓይነቱ ፍቅር የሰፋና ጥልቀት ያለውን ትርጉም የያዘ ሲሆን በተለይ በአዲስ ኪዳን የፍቅርን ትርጉም ለማስተማር በቋሚነት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው። "አጋፔ" ፍቅር የማይወደዱትን ከዚያም አልፎ ጠላቱን የሚወድ የፍቅር ዓይነት ነው። እግዚአብሔር ለእኛ እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እኛም እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ለሌሎች እንዲኖረንና እንድናሳይ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

ይህ ዓይነቱ ፍቅር - "አጋፔ" ፍቅር - ጋል ካለ ስሜት ወይም በስሜት ከሚገፋፋ ደግነት የበለጠና በጣም የተለየ ነው። እግዚአብሔር እኛ እንዲኖረን የሚፈልገው ፍቅር ከፍ ዝቅ የሚል ስሜታዊ አይደለም፤ የህሳባችንና የፈቃዳችን ድርጊት ነው - ከራሳችን ይልቅ ሌሎችን ለመውደድና ለማስቀደም ሆን ብለን የምናደርገው ውሳኔ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፤ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ" (ፊልጵ 2፥4):: እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር ጥልቅ የሆነ፤ ክርስቶስ ሰማያዊ ክብሩን ትቶ ለኛ ኃጢአት በመስቀል ላይ እስኪሞትልን ድረስ የተገለጠ ፍቅር ነው። የአጋፔ ፍቅር ተቃራኒው ራስ ወዳድነት ነው፤ ነገር ግን የኢየሱስ ፍቅር ልባችንን ሲሞላው ራስ ወዳድነት ከውስጣችን ውልቅ ብሎ ይወጣል፡ ለእናንተ የእግዚአብሔር ቀዳሚ ፍላጐት ምንድነው? *የእግዚአብሔር ቀዳሚ ፍላጐት ዘላለማዊ ፍቅሩ መለዮአችሁ እንዲሆን ነው፤ ምክንያቱም የክርስቶስም ሕይወት መለዮ ስለነበር ነው።*

## በፍቅር ማደግ

ይህ በሕይወታችን እንዴት እውን ሊሆን ይችላል? ይህ እውን ሊሆን የሚችለው በድንገት ወይም ጥርሳችንን በመንከስና ሌሎችን ለመውደድ ተሰፋ በማድረግ ስለተመኘን አይደለም። እውን ሊሆን የሚችለው ክርስቶስን ወደ መምሰል ስናድግና ሕይወታችንን

ስርሱ ስናስረክብ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲያድስንና እንዲለውጠን ስንፈቅድለት ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ግን ፍቅር ነው።" (ገላ 5፥22)

ይህ በሕይወታችን እውን የሚሆነው ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ እንደሆነ እውቃለሁ። በአሁኑ ሰዓት ዕድሜዬን እያገባደድኩ ባለሁበት ጊዜ እንኳን፣ እግዚአብሔር በወደደበት መንገድ ሌሎችን መውደድ ማለት እንዴት እንደሆነ እያስተማረኝ ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ ለኛ ሰላም መስጠት ነው፤ ሰላም በልባችን ውስጥ፣ ሰላም ከሌሎች ጋር፣ ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ማለት ነው። ወደ ክርስቶስ ስንመጣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ሰላም ወዲያውኑ ይፈፀማል፤ ወደ ኢየሱስ ስንመጣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ጦርነት ያበቃል። ሰላምም በልባችን ውስጥ ማደግ ይጀምራል። ዕድገቱ አንዳንድ ጊዜ በፍጥነት፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዝግታ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሦስተኛው ዓይነት ሰላም - ከሌሎች ጋር ሰላም - ሊያድግና ሊበስጽግ የሕይወት ዘመን ይጠይቃል። በርግጥ፣ መንግሥተ ሰማይ እስክንደርስ ድረስ ፍፁም (ሙሉ) አይሆንም። ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚለውጥ አይደለም። እግዚአብሔር የርሱን ፍቅር በእኛ ውስጥ ለመትከል ይፈልጋል። ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ልንኖር እንችላለን።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። "የትዕዛዝ ፍፃሜ ግን ከንፁህ ልብ፣ ከበጎ ህሊና፣ ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው።" (1ጢሞ 1፥5) ፍፃሜአችሁ (ግባችሁ) ይህ ነው? እግዚአብሔር እንዲህ አይነቱን ፍቅር በልባችሁ ውስጥ እንዲተክልና በእርሱ ፍቅር መኖር እንድትችሉ ይረዳችሁ ዘንድ ጠይቁት።

## መውደድን መማር

ሌሎችን መውደድ አስፈላጊ ነገር ነው፣ ነገር ግን እንዴት ተግባራዊ ልናደርገው እንችላለን? እንደ ሰው ባህርይ ውስብስብ የሆነ ነገር የለም። እያንዳንዱን ሁኔታ ወይም እያንዳንዱን ግንኙነት የምናሟለበት ቀላልና ግልጽ የሆነ ቀመር የለም። ቤተ መጻሕፍትና





የየመጻሕፍት ቤት መደርደሪያች በምክር መጻሕፍት ተሞልተዋል - አንዳንዶች መልካም ምክር የያዙ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን አይደሉም። መጻሕፍቱ ከሌሎች ጋር እንዴት ተስማምተን እንደምንኖር የሚገልጹ ሲሆኑ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችም እንደዚሁ ግንኙነትን በተመለከተ የሚያስተላልፉት መልዕክት አይነቱና ብዛቱ ማስቂያ የለውም። ምንም እንኳ በዚህ ረገድ ብዙ መረጃዎች እንደ ጐርፍ የሚያጥለቀልቁን ቢሆንም፣ የምንኖረው ሁከትና ብጥብጥ በበዛባትና አለመግባባት በነገሰባት ምድር ነው። አንድ ሰው በጻፈልኝ ደብዳቤ፣ አሁን "በዐራተኛ የጋብቻ አማካሪያችን እየተመከርን ነው ያለነው" ካለ፣ በኋላ "ነገር ግን አሁንም መስማማት አልቻልንም" ብሎኛል።

የትኛውን ብንይዝ ይሻለናል? መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያነቡ ሰዎች ከሰው ልጅ ጋር የተያያዙ ብዙ አስደናቂ ታሪኮች ሲመለከቱ ሁልጊዜ ይገረማሉ። አንድ ሰው እንዲህ አለኝ፣ "መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበቤ በፊት፣ እንዲያው ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ እባባሎችን ብቻ የሚገልጽ ጽሑፍ የያዘ ነው ብዬ ገምቼ ነበር። ነገር ግን ብዙ እውነተኛ ባለታሪክ የሆኑ ሰዎችን አግኝቼበታለሁ። ልብ ወለድ ታሪክ ያልሆነ ከማንኛውም የሥነ - ፅሑፍ ሥራ የሚበልጥ መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ" ብሎኛል። መፅሐፍ ቅዱስ ማናቸውንም በሰው ልጆች ላይ እንደሚመጡ የሚታሰቡ እጣብቂኞችና በመካከላቸው የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች የሚያንፀባርቅ ነው።

ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ሌላኛው የምክር መጽሐፍ ወይም በማንም ሰው አረዳድ (እስተሳሰብ) የተጻፈ መፅሐፍ አይደለም፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ባለታሪኮች በስተጀርባ እግዚአብሔር ስላለ ነው። ልዩነቱ በዚህ ነው፣ እርሱ ስለፈጠረን፣ እርሱ ስለሚወደን፣ ስለእኛ ማንነት ሁሉ እርሱ ስለሚያውቅ ነው። ከእግዚአብሔር በተሻለ ከእያንዳንዳችን ጎን ሊሆን የሚችል እንዳለ ሊነግረን የሚችል ማነው? ጥበብን ከእግዚአብሔር ቃል፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ በተሻለ የት ልናገኝ እንችላለን? እግዚአብሔር ብቻውን "ድንቅ ምክር የሚመክር የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ የሚያወጣቸው እቅዶች ሁሉ ጥበብን የተሞሉ ናቸው

በወትርም ያለ ችግር ይከናወናሉ" (ኢሳ. 28፥29)። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ጥበብንና ትክክለኛ የሆነውን የኑሮ ዘዴ አስተማርኩህ፣ በቀናች ጎዳና መራሁህ" ይላል (ምሳ. 4፥11)

## በእግዚአብሔር መርህ መኖር

የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዴት እንደምንረዳና በተግባር እንደምናውለው ጥበቡና ምሪቱ እንደሚያስፈልገን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ነገር ግን እንዲያው በእያንዳንዱ ገጠመኛችን ሁሉ ይሔን አድርግ ይሔን አታድርግ እያለ መመሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ አይደለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥራዞች ያሉት መጽሐፍ በሆነ ነበር፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰውና እያንዳንዱ ገጠመኝ የተለያዩ ስለሆነ ነው።

ይልቁንም፣ መፅሐፍ ቅዱስ በግንኙነታችን ልንመራበት የሚገባንን ተከታታይ መርሆች ይሰጠናል። መርሆዎቹ ልክ በውሃ ዳርቻዎች እንዳሉ ብርሃናማ ቤቶች፣ ከአደጋ የሚያስጠነቅቁንና ወደ እረፍት ውሃ የሚመሩን ናቸው። በዚህ ምዕራፍ ቀሪ ክፍል፣ ከመርሆቹ ሰባቱን እንመለከታለን።

*የመጀመሪያው ይህ ነው፤ ግባችሁን (ፍጻሜአችሁን) ከሌሎች ጋር ሁሉ በሰላም አብሮ ለመኖር ተልሙ።* ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው "እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ በሰላም ኑሩ።" (ማር. 9፥50)

ጠበኛ፣ ጠብ ወዳድ ክርስቲያን የሚኖረው በመንፈስ ሳይሆን በሥጋው እየተመራ ነው። የራሳችን ባልነው መንገድ ሙጭጭ (ችክ) በምንልበትና ለሌሎች ግዴለሽ በምንሆንበት ጊዜ ግባችን ሰላም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" (ዕብ. 12፥14) ይላል።

ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም መኖር ይቻላል? እንዳለመታደል ሆኖ መልሱ አይቻልም ነው፣ ሌላው ቀርቶ የተፈለገውን ያህል የነጠረ ፍቅር የምናሳይ ቢሆን እንኳ አንዳንድ ሰዎች ያላቸውን የጠነከረ አቋም ሳያስለውጥ ይችላል። ሐዋርያው ጳውሎስ፣





"የሚቻላችሁ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉ" (ሮሜ 12፥18) በማለት ጽፏል። ጳውሎስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር እንዳለብን አጥብቆ አስገንዝቦናል። ነገር ግን ሁልጊዜ በሰላም ለመኖር እንደማይቻልም ጠንቅቆ ያውቃል። ባንድ ወቅት ወጣቱ ማርቆስ አብሯቸው ይጓዝ ወይም አይጓዝ በሚለው ውሳኔ ላይ ጳውሎስና በርናባስ አጥብቀው ተከራክረው ነበር፣ በመጨረሻም ሳይስማሙ ቀርተው ለየራሳቸው በተለያየ መንገድ ተጉዘዋል (የሐዋ 15፥36-41)። ዋናው ቁልፍ ነገር ስህተት ለመሥራታችን እግዚአብሔርን መጠየቅ፣ ከሆነም በንስሓ ይቅርታን መጠየቅና ድል እንድናደርግ እርዳታውን መፈለግ ነው።

## ወርቃማው ደንብ

*በስምምነትና በሰላም ለመኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው መመሪያ ይህ ነው፤ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ እንደምትፈልጉት እንዲሁ እናንተም አድርጉላቸው።* ይህ በጣም ቀላል ግን በጣም ወሳኝ መርህ "ወርቃማው ደንብ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ ከተናገረው የተወሰደ ነው፣ "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው፣ የሙሴና የነቢያትም ትምህርት የሚሉት ይህንኑ ነው" (ማቴ 7፥12)።

ይህንን ወርቃማ ደንብ በትክክል ብንለማመደው ሕይወታችን ምንኛ የተለየ በሆነ ነበር! ሰዎችን በንቀት ወይም እክብሮት በጐደለው ሁኔታ ሳይሆን በትህትናና በማክበር መቀበል ነበረብን። ለግላችን ዓላማ ከምናነሳሳቸው ይልቅ ለነርሱ መልካም የሆነ ነገር እንዲገጥማቸውና እንዲያገኙ በተመኘንላቸውና በረዳናቸው ነበር። የሕይወትን ምንነት በነሱ ቦታ ሆነን ባየን ነበር። ሰዎችን ጥሩ ህይወት እንዲኖሩ፣ የተሳካላቸው እንዲሆኑና ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ ከጎናቸው በቆምን ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወደ ክርስቶስ እናሳያቸው ነበር፣ ይህን ብናደርግ ማንንም ሰው ወደ ታላቁ ስጦታ ወደ ክርስቶስ አዳኝነት (ድነት) እናቀርባለን።

*ሶስተኛው መርህ ደግሞ የሚከተለው ነው፦ ለራሳችሁና ለጓደኞቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠላቶቻችሁም የምትጸልዩ ሁኑ።* ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ በሰበካቸው ስብከቶች ሁሉ አበክሮ ያወጀው፣ "ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህን ጥላ" እንደተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እንዲህ አላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩላቸው" (ማቴ 5፥43- 44) በማለት ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ ለሰቃዮቹ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" (ሉቃ 23፥24) ብሎ ፀለየ።

ስአንድ ሰው ልትጸልዩለትና ልትጠሉት አትችሉም። ሌላው ቀርቶ ጠላታችሁ የሚፈፅምባችሁን መጥፎ ተግባር እግዚአብሔር እንዲቆጣጠረው ስትፀልዩ፣ የጠላታችሁንም ልብ እንዲቀይረው ጭምር አብራችሁ ልትፀልዩ ይገባችኋል። የዘላለም ሕይወት ማግኘታችንን የምናረጋግጠው ለሌሎች በመፀለይ በምናደርገው አስተዋፅኦ ነው። ወርቃማውን ደንብ መፈፀማችንን በተግባር የምናሳይበት አንዱ መንገድ መፀለያችን ነው።

## ልናስወግዳቸው የሚገቡን ነገሮች

ከሰዎች ጋር በሰላምና በስምምነት አብሮ ለመኖር ግንኙነቱን የሚያጠናክሩ ሥራዎችን እንደመሥራት ሁሉ ግንኙነትን የሚጐዱ ነገሮችን ማስወገድን ይጠይቃል። *ይህ ወደ ዐራተኛው መርህ ይወስደናል፤ አንደበታችሁን ጠብቁ፣ በክፉ ፈንታ መልካም ለማድረግ ተጠቀሙ።* መዝሙረኛው፣ "እግዚአብሔር ሆይ ለአፌ ጠባቂ አኑር። በከንፈሮቼም በር ላይ ዘበኛ አቁም" (መዝ 141፥3) በማለት ፀልዮአል። ምን ያህል ትዳሮችና ግንኙነቶች ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ትችቶችና ንግግሮች ፈርሰዋል? በአስባልታችን፣ ሳናስተውል በተናገርናቸውና በቁጡ ንግግራችን ምን ያህ ግንኙነቶች ተበጥሰዋል? መጥፎ ከተናገርን በኋላ ልንመልሰው አንችልም፤ ይቅርታ መጠየቅም ያደረስነውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ ሊጠግነው አይችልም። ያዕቆብ ትክክል ነበር፤ "አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል። ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፣ በገሃነምም





ይቃጠላል" (ያዕ 3፥6)። እነዚህ ቃላት ጠንካራ ናቸው፤ ግን ትክክልና እውነት ናቸው።

አንደበታችን ለመልካም ሊያገለግል ይችላል። የኛ ግብ ይህ መሆን አለበት። አንዳንድ ጊዜም ከመናገር ይልቅ ዝም ማለት የበለጠ ጥሩ ነው (ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ዝም እንዳለው ማለት ነው) በተለይ የምንሰጠው ምላሽ ነገሮችን ወደ ከረረና ወደ ባሰ አለመግባባት የሚወስድ ሆኖ ሲገኝ ዝም ማለት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን ዓላማችን ሰዎችን ለመርዳት ሲሆን እግዚአብሔር ሰዎቹን እንድንጋፈጣቸው ወይም መመሪያ የሚሆን አስፈላጊ ነገር እንድንነግራቸው ያደርገናል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፣ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነፅ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ።" (ኤፌ 4፥29) ብሎናል።

## በቀልን ማስወገድ

አሳዛኙ ነገር፣ የሰው ዘር ታሪክ በበቀል ጥማት የተሞላ መሆኑ ነው። ጐሣዎች ወይም መንግሥታት በበቀል ባይነሳሱ ኖሮ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ጦርነቶች ባልተካሄዱ ነበር። ይህን ሁኔታ ወደ ግለሰቦች ስናመጣም ተመሳሳይ ነው። በቀል በቀላሉ ማለቂያ ወደ ሌለው የጥላቻና ብጥብጥ አዙሪት ውስጥ ይከታል።

*መጽሐፍ ቅዱስ ግን የተሰየ መመሪያ ይሰጠናል፤ በክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ* "ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ . . . ወንድሞቼ ሆይ፣ ቁጣን ለእግዚአብሔር ተው እንጂ ራሳችሁ አትበቀሉ ምክንያቱም የምበቀልና የበቀልንም ብድራት የምከፍል እኔ ነኝ ይላል እግዚአብሔር" (ሮሜ 12፥17፣19)።

አንድ ሰው ሕግን ጥሶ ጉዳት ቢያደርስብን ወደ ሕግ ፊት እንዲቀርብ የማድረግ መብት አለን፣ እንዲህ ማድረግ ለእኛም ሆነ ለህብረተሰቡ ደህንነት ጥሩና አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን የጎዱንን መልሰን እኛም በራሳችን ለመጉዳት ከተነሳን ሌላ ጉዳይ ነው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ዓይነት ወጥመድ ውስጥ መጠመድ የለበትም። አንድ ሰው በሚጐዳን ጊዜ ተፈጥሮአዊው ማንነታችን መልሶ ለማጥቃት ይፈልጋል - ብናደርግ ግን

የምናበላሸው የመታረቅ ዕድላች ንን ብቻ ሳይ ሆን ቁጣና ጥ ላቻ እንዲቆጣጠረን እንፈቅዳለን::

*ቀጣዩ ስድስተኛው መርህ ይህ ነው፦ በቀልን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የተበደላችሁትን የምትረሱ ሁኑ።* በቅርቡ አንዲት ሴት በጻፈችልኝ ረዘም ባለ ደብዳቤዋ የፈታችውን ባሏን እጅግ በጣም እንደምትጠላው ነግራኛለች። የደረሰባትን ጉዳት ብረዳውም በኋላ ላይ እንደጠቆመችኝ ከተፋቱ ከሃያ ዓመት በላይ ሆኖአቸዋል:: ያለፈ ነገር ምርኮኛ ሆና ለዓመታት በጥላቻና በበቀል ተሞልታ መኖርዋ ያሳዝናል:: ለአንዳንዶች ጥላቻ፣ ወይም ቂጣ የማንነታቸው መገለጫ ሆኖ ሕይወታቸውን በሙሉ አስቸጋሪና መራራ አድርጎት ይኖራሉ። ለመላቀቅ ቢፈልጉ እንኳን አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል::

ያለፈውን መለወጥ አንችልም፤ ነገር ግን ላለፉት ስህተቶቻችን የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቀነው ይቅር ብሎን እንደረሳው ሁሉ እኛስ አናደርግም? የቀድሞው ሁኔታችሁ ምርኮኛ እንዲያደርጋችሁ አትፍቀዱለት፣ ይልቁንም ቂጣችሁንና ቂማችሁን በመስቀሉ ስር ወስዳችሁ ጣሉት። ኢየሱስ፣ "እንግዲህ ልጁ ነፃ ካወጣችሁ በእርግጥ ነጻ ትወጣላችሁ" (ዮሐ. 8፥36) ብሏልና::

## የይቅርታ ኃይል

አንድ ሰው በጻፈልኝ ደብዳቤ፣ "የፈፀምኩት ተግባር በጣም የሚከብድ ነገር ነው ነገር ግን አሁን የሚሠማኝ ልክ አንድ ሺ ፓውንድ የሚመዝን ሸክም ከላዩ ላይ የተነሳልኝን ያህል ነው" ብሏል። *ይህ ሰው እየተናገረ ያለው የመጨረሻውን መርህ ነበር፣ ይኸውም የይቅርታ ኃይል ስለሚሠጠው ነፃነት ነው - የሚለውጠውን የይቅርታን ኃይል ተለማመዱ::*

በላምንት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው እንዲህ እያለ ይፅፍልኛል፣ "ይቅርታ ማድረግ አልችልም:: ምን ያህል እንደተጎዳሁ አታውቅም":: ምናልባት ይህ የራሳችሁን ተሞክሮ ያስተጋባላችሁ ይሆናል። ነገር ግን እንደ ይቅርታ ያለ ያለፈውን ነገር ከውስጣችን የሚነቅል ወይም ለእርቅ በር ከፋች ሌላ አንዳች





ነገር አይኖርም። የበደለን ሰው ስህተቱን ለመቀበል አሻፈረኝ የሚል ወይም ይቅርታችንን የሚያንቋሽሽ እንኳን ቢሆን ይቅርታ ከማድረግ ልንቆጠብ አይገባም።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን ግልፅ ነው፤ "እርስ በእርሳችሁ ታገሡ፣ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሠኘበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ:: ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር በሉ" (ቆላ. 3፥13):: የመጨረሻውን ሐረግ አስታውሳችኋል? እግዚአብሔር በነፃና ሙሉ በሙሉ በደላችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ይቅርታ አድርጎልናል፣ እኛም የበደሉንን በነፃና ሙሉ በሙሉ ይቅር እንድንላቸው መንገዱን አሳይቶናል። ምናልባት ከላይ የጠቀስኩላችሁ ዓይነት ሰው እጅግ የከበደ በደል ያደረሰባችሁን ሰው ይሆናል ይቅርታ የምታደርጉለት:: ነገር ግን በእግዚአብሔር እርዳታ ይቅርታ ልታደርጉ ትችላላችሁ - እናም አድርጉት።

ግንኙነታችሁ እንዲጠናከርላችሁ ምን ያሻችኋል? መራራ እስኪሆኑ ወይም እስኪቀዘቅዙ ድረስ አትጠብቋቸው:: በዚህ ፈንታ እንድታጠነክሩና በተግባር የምታውሉ መሆን እንድትችሉ ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ በፀሎት ለምኑት።

አታውቁም፣ ሕይወታችሁ ምንድነው? ለአንድ አፍታ ታይቶ በኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ እኮ" (ያዕቆ 4፥14)።

የህመም ስቃይ በራሱ ጠቃሚ የሆነ ሥራ አለው፣ እርግጥ ነው አደጋ እንዳለ ያነቃናል ወይም አንድ ችግር እንዳለ ያስጠነቅቀናል - አደጋውን ግን ቸል እንላለን። ሥቃዩ ሲቆይ ወይም ሲቀጥል፣ ሕይወታችንን በፍጥነት ይቆጣጠረዋል። አንድ ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር አስቸኳይና ጊዜ የማይሰጥ ውሳኔ የሚያስፈልገው አጣዳፊ ስራ ቢኖርበትና በዚያኑ ሰዓት የጥርስ ህመም ቢነሳበት፣ ሁሉን ነገር ትቶ ወደ ጥርስ ሐኪም ዘንድ መሄድን ያስባል።

ማንም ሰው በራሱ ፈቃድ አይሰቃይም ወይም በራሱ ሥቃይ አይደሰትም (ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት እርሱ መቀበሉን ባለመገንዘብ፣ በራሳቸው ላይ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ቅጣት የሚያደርሱ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩም)። ሥቃይና መከራ ወደ ሁላችንም ይመጣል፣ ትክክለኛው ጥያቄ ግን እንዴት ልንቋቋመው እንችላለን? የሚል ነው። እኔን የረዱኝን ሁለት አንኳር የሆኑ ደረጃዎች ልግለጽላችሁ።

*አንደኛ፣ የሥቃዩን አደጋዎች ተከላከሉ።* ማንኛውም ዓይነት ችግር በሚደርስብን ጊዜ፣ ትኩረታችንን ወደ ራሳችን እንመልሳለን - በተለይ እንዲህ የምናደርገው መጥፎ ስሜት በሚሰማን ጊዜ ነው። ይህ ዓይነት ሁኔታ በሚሆንበት ጊዜ፣ በአሳዛኝ ሁኔታ በስሜታችንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ አደጋ ሊፈጥሩ ለሚችሉ ሁኔታዎች በራችንን ከፈትን ማለት ነው። ብዙ ሕመምተኞች ለምሳሌ፣ ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡና ለሌሎች ስሜት የማይጠነቀቁ፣ ለመርዳት የሚሞክሩትንም እንኳን የሚገርፉ ይሆናሉ። ሌሎች ደግሞ በራስ ሀዘኔታ ወይም ምሬት የተያዙ ይሆናሉ። አሁንም አንዳንዶቹ ተስፋ በመቁረጥ ወይም እፎይታን በመፈለግ በአልኮል ሱሰኝነትና በአደንዛዥ ዕፅ ዘመናቸውን ይፈጽማሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በደረሰባቸው የህመም ስቃይ ምክንያት እግዚአብሔርን እያማረሩና እየወቀሱ ይኖራሉ። አንዲት ሴት በዓፈችልኝ ደብዳቤ፣ "እግዚአብሔር በእውነት የሚወደኝ ቢሆን ኖሮ፣ ይህ በእኔ ላይ ሊሆንብኝ አይገባም ነበር" ብላለች። ሊላውም "ያጠፋሁት ምን እንደሆነ አላውቅም፣ እግዚአብሔር ግን እየቀጣኝ





መሆን አለበት" በማለት ጽፎልኛል። ስሜታቸው ግልጽ ነው - ግን ሁለቱም ራሳቸውን ወደ ሞት አፋፍ እየመሩ ናቸው።

በአካላችን ህመም በሚሰማን ጊዜ ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ለማድረግ አዳጋች ነው። አብዛኞቻችን በበሽታ ወይም በሥቃይ ውስጥ ስንሆን መዝሙረኛውን እንመስላለን፣ "ለቅሶም እድሜዬን አሳጠረ፤ ከመከራዬ ብዛት የተነሳ ደከምኩ፣ አጥንቶቼም ደቀቁ" (መዝ 31፥10)። የሆነው ሆኖ፣ ንቁና እግዚአብሔር የሥቃዩን እንቅፋቶችና አደጋዎች እንድታሸንፉ እንዲረዳችሁ ለምኑት።

ይህንን ተግባራዊ ልናደርግበት የምንችልበት አንደኛው መንገድ ስለሌሎች ሰዎችና ስለፍላጎታቸው መሳካት መፀለይ ነው። ዝም ብላችሁ ለራሳችሁ ብቻ አትፀልዩ፤ ለሌሎች ደግሞ ፀልዩ! ወደ እግዚአብሔር ከሚጸልዩ በጸሎት ተዋጊ ከሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል በሕመም ወይም በአካለ ጉዶሎነት ምክንያት ብዙ መሥራት የማይችሉ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። መጸለይ ይችላሉ! በሕይወት ጉዞአችሁ ጥንት ታደርጉ የነበራችሁትን አሁን እንደ ቀድሞው ለማድረግ አቅም አይኖራችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን መጸለይ ትችላላችሁ። በህመም ውስጥ ወይም መጥፎ ስሜት በሚሰማችሁ ጊዜ ለመጸለይ ራስን መግዛትና ትዕግሥት ያስፈልጋል፤ ነገር ግን በኔ ልምምድ አካላዊ አቅማቸው የደከመ ሰዎች ከጸሎታቸው የተነሳ መንፈሳዊ ጥንካሬ አላቸው።

## የሥቃይን ትምህርቶች መማር

*ሁለተኛ፣ ከሥቃዩ መማር የሚገባችሁን እንዲያስተምራችሁ እግዚአብሔርን ለምኑት።* የሚያስደንቀው ዋናው ነገር፣ ሥቃይን እግዚአብሔር ለእኛ መልካም ነገር ለማድረግ የሚጠቀምበት መሆኑ ነው። ምናልባት እግዚአብሔር ችግሩ እንዲደርስብን ሊያደርግ ይችላል፣ ምክንያቱም ውጤቱ መልካም እንደሚሆን ስለሚያውቅ ነው። አንድ ሰው "እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ነገር ያደርጋል ብዬ አስቤ አላውቅም፣ የካንሰር ህመምተኛ ሆኜለሁ፣ ግን ደስተኛ ነኝ። እግዚአብሔር እኔን ወደርሱ ለመመለስ (ለማግኘት) ሲል የተጠቀመበት መንገድ ነው፣ ይህ እንዲሆን ሊሆን የሚችለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው ብዬ አስባለሁ" ብሎኛል። ባለፉት ቅርብ

ዓመታት ውስጥ ሁለት ጊዜ የመውደቅ አደጋ ደርሶብኛል። በመጀመሪያ ስወድቅ ወገቤን ተጐዳሁ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ስወድቅ ደግሞ ወገቤን በጽኑ የተጎዳሁበትና የወገብ አጥንቴ የተሰበረበት ነበር። ሁለቱም አደጋዎች የደረሱብኝ ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ በድንገት ነበር። በህመም ውስጥ ሆኜ ግን ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔርን ሀልውናና ዓላማውን መገንዘብ ችዬ ነበር። እግዚአብሔርም በበኩሉ አደጋዎቹ ያስከተሉትን የህመም ስሜት በመጠቀም በማንኛውም ሁኔታ በሱ ላይ እንድተማመንና ተገኘው እንድሆንለት ተጠቅሞባቸዋል።

ከሥቃይ የሚገኙ ትምህርቶች ምንድን ናቸው? በእርግጠኝነት እንደኛው ነገር ሕይወት የሚሰበርና አንድ ቀን የሚያበቃበት መሆኑ ነው። ይህንን ጤንነትና መልካም ስሜት በሚሰማን ጊዜ ሁሉ የምንረሳው ነው - ነገር ግን ምንም ያህል ጤናማ ብንሆን ወይም ዘመናዊ የህክምና ሳይንስ ምንም ያህል የረቀቀ ቢሆን፣ ሕይወታችን በጊዜው ያበቃል፣ እንሞታለን። ከሁሉም ነገር በላይ ግን፣ የህመም ስቃይ የሚያስገነዝበን የምድር ቆይታችን አጭር መሆኑንና ወደ ዘላለማዊነት ልንሄድ መቃረባችንን ነው።

መከራና ህመም ወደ እግዚአብሔር የበለጠ እንድንቀርብ ያደርጉናል። ጤናማ በሆንን ጊዜ፣ ለጊዜው በሚያስፈልገን ነገር የተጨናነቅንና የተጠመድን እንሆናለን፣ እግዚአብሔርንም በቀላሉ እንረሳዋለን። ነገር ግን ድንገተኛ አደጋ ወይም በሽታ ከመስመር ውጭ ሲያደርገን፣ በርግጥ የሚያስፈልገን ምን እንደሆነ ለማሳየት ጊዜ ይኖረናል። ከሁሉም ነገር በላይ፣ ከኢየሱስ ጋር ያለንን ግንኙነት እንድንፈትሽና ራሳችንንና የወደፊት ዘመናችንን በፍቅር እጆቹ ላይ አሳልፈን ለመስጠት ጊዜ ይኖረናል። በሰው ልጅ ታሪክ በመከራ ውስጥ ያለፉ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል እውነት መሆኑን ተገንዝበዋል፤ "እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ ወይም ባለማወላወል ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው" (መዝ 145፥18)። እንዲሁም በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እግዚአብሔር ሁልጊዜ መጠጊያ አምባችሁ ነው፣ ዘላለማዊው ክንዱም መደገፊያችሁ ነው።" (ዘዳ. 33፥27)





መከራ በሚመጣባችሁ ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ቀን በእግዚአብሔር እጅ እንዳላችሁ እመኑ፣ ደግሞም መከራውን ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ እንደሆነ አድርጋችሁ ተቀበሉ። በተጨማሪም፣ በተመስጦ ማድረግ ቢያቅታችሁ እንኳ፣ ከንፈሮቻችሁ በምስጋናና በፀሎት ይሞሉ፣ ለመፈወስ ፀልዩ፤ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ነው፣ ጣልቃ ሊገባና ሊፈውስን እርሱ ብርቱ ነው። ነገር ግን ከሁሉም በላይ የርሱ ፈቃድ በሕይወታችሁ እንዲከናወን ፀልዩ - የእግዚአብሔር ፈቃድ በጐና ትክክል ነው። እግዚአብሔር ከበሽታችሁ ባይፈውሳችሁ ለርሱ ያላችሁን ፍቅር ትቀንሱ ይሆን? ወይስ ምላሻችሁ የማያቋርጥ "የሥጋ መውጊያ" እንደተሰጠው እንደ ሐዋርያ ጳውሎስ ይሆንን? ነገር ግን ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ "እርሱ (እግዚአብሔር) " የኔ ኃ ይል የሚገለጠው በአንተ ደካማነት ስለሆነ ፀጋዬ ይበቃሃል" አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ ከምንጊዜም ይልቅ በደካማነቴ ልመካ እወዳለሁ" (2 ቆሮ 12፥9)።

ከሁሉም በላይ፣ መከራ በሚመጣበት ጊዜ፣ ከክርስቶስ የተነሣ የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ ስላለን እንደሰታለን። በምንም ሁኔታ ውስጥ ብታልፉ፣ አንድ ቀን ያበቃል፣ ለዘለዓለም ከክርስቶስ ጋር ትሆናላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፣ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና" (2ቆሮ 4፥17) ይለናል። የመንግሥተ ሰማይ የተስፋው ብርሃን የምድሩን መከራ ያደበዝዛል።

## ማጣትና ሐዘን

ሕይወትን ስለሚጎዱ አንዳንድ ነገሮች ተነጋግረናል፣ ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ በቀረው ክፍል፣ እኔና እናንተ ልንጋቋመው የተጠራንበትን በጣም ኃይለኛ ሕመም - ኀዘንን - በጥልቀት እንድንመለከተው እፈልጋለሁ።

በሕይወታችን የሚደርሰው አብዛኛው ጉዳት አንድ ነገር የሚያሳጣ ይሆናል። ጤንነትን ማጣት፣ ወዳጅነትን ማጣት፣ የገንዘብ ዋስትና ማጣት ወይም ውስጣዊ ሰላምን ማጣት፣ እንዲያውም ተስፋን ማጣት ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱን ነገር

እንደማልለማ ባወቅሁኝ ጊዜ አንድ ቶን የሚመዝን ጡብ የመታኝን ያህል ነበር የተሰማኝ" ብላኛለች።

የምንወዳቸው በሚሞቱበት ጊዜ፣ የመጀመሪያው ምላሻችን በከፍተኛ ሁኔታ መንቀጥቀጥና መደንዘዝ ነው። እንዴት እንደደነገጥኩና እንደደነዘዝኩ እስከ አሁን ድረስ የማስታውሰው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁ የቅርብ ጓደኞቼ ከነበሩት የጦር አውሮፕላን ኃይለት የነበረ ጓደኛዬ ጀርመን ውስጥ የሚያበረው አውሮፕላን ተመቶ መሞቱን በሰማሁ ጊዜ የነበረው ሁኔታ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ስሜታዊ በመሆን እንዳይሞቱ መከላከል ነበረብን ወይም በሚሞቱበት ጊዜ አጠገባቸው በነበርን በማለት የበደለኝነት ስሜት ሊሰማን ይችላል። ሐኪሞች ወይም ጤና ረዳቶች ለሞታቸው ምክንያት እንደሆኑ በማሰብ፣ ወይም የምንወደው ትቶን ስላለፈ፣ ወይም በእግዚአብሔር ላይ እንቆጣለን። ከእልዓዛር እህቶች አንዷ ወንድሟ በሞተ ጊዜ በኢየሱስ ላይ ስሞታዋን አሰምታለች፣ "ጌታ ሆይ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተ ነበር" (ዮሐ 1132)። ስለተሰማት የቅሬታ ስሜት ኢየሱስ አልገሠፃትም፤ ሐዘኗን ተረድቶ ነበርና ከጎኗ ሆነ እርሱ ለእኛም እንደዚሁ ያደርግልናል።

*ሁለተኛ፣ ሀዘናችሁን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጣሉት።* መዝሙረኛው፣ "ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፣ እርሱም ይደግፍሃል" (መዝ 55፥22) ይላል። "አንዳንድ ችግራችሁን ብቻ በጌታ ላይ ጣሉ" እንዳላለ አስተውሉ። ይልቁንም ሁሉንም ችግራችንን በርሱ ላይ እንድንጥል እግዚአብሔር የከበደንን ሀዘን ጭምር ማለት ነው። ከምንጊዜውም ይልቅ የከበደባችሁ ሀዘን የምትወዱት ስለሞተባችሁ ይሆናል። ለምን ብቻችሁን ትሸከሙታላችሁ? ለምን በእግዚአብሔር ላይ አትጥሉትም?

ይህን ለማድረግ የምንችለው ሁለት ታላላቅ እውነቶች በተገለጡልን ጊዜ ብቻ ነው። የእኛን የድካመት ጥልቀት እና የእግዚአብሔርን የፍቅሩን ጥልቀት ስናውቅ ነው። ሀዘናችሁን ለብቻችሁ አትሸከሙ። በዚህ ፈንታ፣ አፍቃሪ በሆነ ሰማያዊ አባታችሁ ላይ ጣሉት፣ ከእናንተም ላይ እንዲያነሳ ጠይቁት - እርሱም በርግጥ ያደርገዋል፣ ግን ቀስ በቀስ ያነሳዋል። አስተውሉ፤ እግዚአብሔር በምን ውስጥ እያለፋችሁ እንደሆነ ያውቃል፣ እርሱም





በእውነት "የምህረት አባትና የመጽናናት ሁሉ አምላክ በመከራችን ሁሉ ያጽናናል" (2ቆሮ 1፥3-4)።

*ሦስተኛ፣ በሐዘን መካከል (ውስጥ) ሆናችሁ የምታመሰግኑ ሁኑ።* ይህ የማይቻል ሊሆን ይችላል፤ እንዴት አድርገን ነው የምንወደውን በሞት አጥተን ልናመሰግን የምንችለው? በአንድ አቅጣጫ ስንመለከተው ይህ እውነትነት አለው፤ የምንወደውን ሰው በማጣታችን አመስጋኝ መሆን አንችልም፣ እግዚአብሔርም እንድንሆን አይጠብቀንም።

ነገር ግን በሐዘን ውስጥ እንኳ ሆነን፣ አመስጋኝ ልንሆን እንችላለን፣ ምስጋና ጉዳታችንን እንደሚያስታግሥልን ቅባት ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ፣ ምንም እንኳ የምንወደውን አጥተን ከልብ ብናዝንም፣ እግዚአብሔር ከዚህ ከምንወደው ሰው ጋር በአንድነትና በህብረት አብረን ለመኖር የሰጠንን ዓመታት በማስታወስና እርስ በርስ በብዙ ነገሮች ስንደጋገፍና ስንረዳዳ የኖርንበትን ጊዜ በማሰብ ልናመሰግነው እንችላለን። እግዚአብሔር አብራችሁ የነበራችሁባቸውን እነዚያን ጊዜዎች ማስታወስ ብቻ ሳይሆን፣ ለነዚያ ወቅቶች እግዚአብሔርን አመስግኑ። ለናንተ የተሰጡ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታዎች ነበሩና።

በተጨማሪም፣ እንወደው የነበረ በሞት የተለየ ሰው አሁን ከሕይወት መከራና ስብራት ባሻገር ለዘለዓለም በመንግስተ ሰማያት ዕርፍ ብኋል፣ ይህም በኢየሱስ አምኖ የዳነ ከሆነ ማለት ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ልናመሰግን እንችላለን። አንድ ቀን ከነዚህ በሞት ከተለዩ ትወዷቸው ከነበሩ ጋር እንደገና ተገናኝታችሁ፣ ባንድነት ለዘለዓለም እግዚአብሔርን በማመስገን ስለምታገለግሉ አመስግኑ። አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ስላለ ማመስገን ይገባል፤ እግዚአብሔር አይተዋችሁም፣ እግዚአብሔር እናንተን እዚህ ምድር ላይ እንድትቆዩ የፈለገበት የራሱ ዓላማ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር እግዚአብሔር አብን ዘወትር አመስግኑ" (ኤፌ 5፥20) ይለናል።

*በመጨረሻም፦ በሐዘን የተጎዱትን አጽናኑ።* በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች ሁሉ በልዩ ልዩ ምክንያት በሐዘን ወይም በልብ ስብራት ውስጥ ያሉ በመሆናቸው የእናንተን እርዳታና ማበረታታት ይፈልጋሉ። እናንተ ለእነሱ አስፈላጊዎች ናችሁ፣ እነሱም ለእናንተ አስፈላጊዎች ናቸው። ራሳችንን ለመርዳት ከምንችልባቸው ዋና

ዘዴዎች አንዱና ትልቁ ነገር ሌሎችን ሰዎች መርዳት ነው። ሐዘን ወደ ውስጣችን የሚገባ ነው፣ ርኅራኄና ደግነት ከውስጣችን የሚመነጭ ነው። ለዚህም ነው በሐዘን በምንጠቃበት ጊዜ እርዳታና ማበረታቻ የሚያስፈልገን። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እርስ በርሳችሁ በመተጋገዝ ከእናንተ እያንዳንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም" (ገላ 6፥2) ብሎ ይነግረናል።

ባዘናችሁ ጊዜ፣ የእናንተ እርዳታና አይዞህ ባይነት ወደሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዲመራችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት። ፀልዩላቸው፣ ጊዜአችሁን ከእነሱ ጋር አብራችሁ አሳልፉ፣ ችግራቸውን አድምጡላቸው፣ እርዱአቸው፣ አበረታቱአቸው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር አብራችሁ ተካፈሉ። ምናልባት በህመም ወይም በአንድ በሌላ ሸክም ወይም በልብ ስብራት ውስጥ ይሆናሉ፣ የናንተንም ድጋፍና ቸርነት የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ወይም እንደናንተው በተመሳሳይ የሐዘን ጉዳና ላይ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ምናልባት ለውን ለመርዳት አላሰባችሁም ይሆናል ብዬ እስባለሁ፤ ምናልባትም እናንተ ራሳችሁ ያለባችሁ ሸክም ከአቅማችን በላይ ነው ትሉ ይሆናል፣ በዚህም ምክንያት ከእናንተ አልፎ የሌሎችን ሸክም መቀበል የሚቻል ሆኖ አይታያችሁ ይሆናል። ነገር ግን ሸክምን መጋራት ማለት ሸክምን በግማሽ ማካፈል ማለት ነው፣ ሌሎችን ስታበረታቱ እግዚአብሔር ደግሞ እናንተን ያበረታታችኋል።

ቀደም ብለን እንዳየነው - እግዚአብሔር ለምን ቅይማት፣ መከራና ከፉ እንዲደርስብን እንደፈቀደ ሙሉ ለሙሉ መረዳትና ማወቅ በፍጹም አንችልም። አሁን አይደለም እንጂ አንድ ቀን ግን ሙሉ በሙሉ እንረዳዋለን። በሐዋርያ ጳውሎስ መልዕክት፣ "አሁን በመስተዋት እንደምናየው ዓይነት በድንግዝግዝ እናያለን፣ በዚያን ጊዜ ግን በግልጥ እናያለን" (1ቆሮ 13፥12) የሚል ይገኝበታል።

ነገር ግን አንድ ነገር እናውቃለን፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ኢየሱስን ወደ መምሰል እንድንመጣ ነው፤ እናም መከራና ችግር ኢየሱስን ወደ መምሰል የምንመጣበት ሂደት አካል ናቸው። አንድ ጓደኛዬ "መከራና ችግር እግዚአብሔር እኛን ለመቅረጽ የሚጠቀምበት መሮ ነው" ብሎኛል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ወንድሞቼ ሆይ! ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ በጣም ደስ ይበላችሁ። ምክንያቱም እምነታችሁ ሲፈተን በትዕግስት





ትጸናላችሁ። በትዕግስት መጽናታችሁ ምንም ሳይጎድልባችሁ ፍጹምና ሙሉ እንድትሆኑ የሚያበቃችሁ ይሁን" (ያዕ 1፥2-4) የሚለን።

በዚህ ሁኔታ በእምነት ጸንተን ስንኖር፤ "ሞትም ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላዕክትም ቢሆኑ፣ ባለስልጣኖችም ቢሆኑ፣ አሁን ያለውም ቢሆን፣ በኋላ የሚመጣውም ቢሆን፣ የሰማይ ኃይሎችም ቢሆኑ፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ከፍታም ቢሆን፣ ማንኛውም ፍጥረት ቢሆን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተገለጠልን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ እርግጠኛ ነን" (ሮሜ 8፥38-39) እምነት ዕውር አይደለም፣ ሀሳባዊ ምኞትም አይደለም። እምነት፣ ለክርስቲያኖች ተጨባጭ የሆነ እውነት ነው፤ ምክንያቱም በራሳችንና በአካባቢያችን ባሉት ሁኔታዎች ላይ ሳይሆን በኢየሱስ ላይ ያተኮረ ስለሆነ ነው።

በሐዘንና በመከራ ውስጥ ስትሆኑ፣ እምነታችሁን የምታደርጉት በኢየሱስ ላይ ነው?

የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው? ብለን ከመጠየቅ ይልቅ፣ በተቃራኒው "እስከመቼ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ክርስቲያን ሆኜ እዘልቀዋለሁ" ብለን እናማርራለን::

*የመጨረሻው ምክንያት፣ ነገር ግን፣ የችግሮች ሁሉ ቁንጮ የሆነው፣ የመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓታችን (ስነምግባራችን) መላላት ነው::* መጽሐፍ ቅዱሳችን ከመደርደሪያው አይወርድም፤ ጸሎታችን የይስሙላና የይድረስ ይድረስ ዓይነት ነው፤ የሞቀ የነበረው ክርስቲያናዊ ህብረትና ግንኙነታችን ይቀዘቅዝና በቤተ ክርስቲያናችን የምናደርገው ተሳትፎ በጣም ይቀንሳል፣ ለሌሎች የምንሰጠው አገልግሎት ይደበዝዛል:: መንፈሳዊ እድገታችን ባለበት የሚረግጥና የማያድግ ይሆናል፣ "ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ እደጉ" (2ጴጥ 3፥18) ወደተባለው አንደርስም:: ለራሳችን፣ "እግዚአብሔርን የምፈልገው ከሆነ ሁልጊዜ አለ ብለን እናስባለን፣ በተቃራኒው ደግሞ አንደገና መልሰን "ቁልቁለቱን መውረድ እችላለሁ" እንላለን::

አንድ ነገር አትዘንጉ፤ የማቀጣጠያ ነዳጅ ከሌለ እሳት እንደሚቀዘቅዝ ሁሉ እንዲሁ ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል፣ ጸሎትና ክርስቲያናዊ ህብረት እምነታችን ይዳከማል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሰይጣን በእኛ ላይ ድልን ያገኛል፣ ልክ ግልጽ በሆነ ኃጢአት ወይም የአሰማመን ችግር ውስጥ እንደከተተን ያህል ይቆጥራል:: እኛም በየዕለት ተግባሮቻችን በመጠመድ እምነታችን እንዲቀጭጭ መንገድ እንጠርግለታለን::

## መሠረታዊ መርህ

*መፍትሔው ምንድን ነው?* በመጀመሪያ ደረጃ፣ ችግሩን ለይቶ ማወቅ ነው:: የራሳችንን መንፈሳዊ ሁኔታ ዝቅ በማድረግና እግዚአብሔር እንደማያስብልን ድምዳሜ በመስጠት፣ "እኔ አንድ ተራ ክርስቲያን ነኝ" እንላለን::

ነገር ግን እንደዚህ ዓይነቱ እመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስን ወሳኝ መርህ እንዳናስተውል ይከልላል:: ኢየሱስ ሥልጣኑንና ፍቅሩን በሁለንተናዊ ኑሮአችን ውስጥ ሊያንሠራፋ ይፈልጋል:: ከሱ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ምንም ነገር ስለሌለ ሕይወታችንን ያጎደፈውን ኃጢአትና የሰይጣን አሠራር ከእኛ ላይ ፈጽሞ ሊያስወግደው ይፈልጋል::





በሳምንቱ ካሉን ሰባት ቀናት ውስጥ ሰድስቱን ለራሳችን ጉዳይ ተጠቅመን እግዚአብሔርን በአንዱ ቀን እንወስነዋለን:: ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ነፍሳችን እንጂ በዓለም ስላለው ጉዳያችን - ስለ ጊዜያችን፣ ገንዘባችን፣ ሥራችን ወይም ቤተሰባችን ግድ እንደማይለው እንደመድማለን:: በሌላ አነጋገር፣ ሕይወታችንን ለሁለት ክፍለን እግዚአብሔርን ባንድ ክፍል ገድበን ከሌሎች ጉዳዮቻችን እናስወጠዋለን::

ይህ ትልቅ ስህተት ነው:: ይህን እንድናደርግ ሰይጣን የሚፈልገው ነው:: ሰይጣን ለእግዚአብሔር በሳምንት አንድ ቀን ብቻ እንድንወስን ካግባባን ወይም ከሕይወታችን የተወሰነ ክፍል ብቻ እንድንተውለት ካደረገ ድል ተቀዳጅቷል ማለት ነው:: ነገር ግን አንድ ቀን ሰይጣን ድል ተመቶና የኢየሱስ ጌትነት በፍጥረት ሁሉ ላይ ይፋ ይሆናል:: እግዚአብሔርም ይህንን አሁኑኑ እንዲጀመር ይፈልጋል::

ኢየሱስ በእያንዳንዱ የሕይወታችሁ ጉዳይ እንዳይገባ ያገደው ምንድነው? በራሳችሁ ልታደርጉት (ልትቆጣጠሩት) በመፈለግ ነው? ወይስ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ሥልጣን እንዳለውና ሥልጣኑንም ለመዘርጋት እንደሚፈልግ ከቶ አልተረዳችሁም? ወይስ እርሱ በእናንተ ላይ ጌታ እንዳይሆን ያገደው ኃጢአት አለ? ምክንያታችሁ ምንም ይሁን ምን፣ ሁለተናችሁን ሙሉ ለሙሉ ለክርስቶስ እንድትሰጡና የሕይወታችሁን ክፍል ሁሉ እንዲቆጣጠረው አስረክቡት:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "ሁለንተናህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ:: በእርሱም ታመን እርሱም ይረዳሃል:: ታማኝነትህ እንደ ጠዋት ብርሃን እንዲወጣ በፍርድ የምታገኘው ነፃነት እንደቀትር ጸሐይ ደማቅ እንዲሆን ያደርግልሃል" (መዝ 37፥5-6)::

## የጊዜ ወጥመድ

ሁላችንም በቀን ውስጥ ተመሳሳይ የጊዜ መጠን (ደቂቃና ሰዓት) ያለን መሆኑ ግልጽ ነው፣ እውነትም ነው:: ዋናውና ትልቁ ጥያቄ፣ እንዴት እንጠቀማቸው? ነው::

በዚህ ዘመን አብዛኛው ህዝብ አንድም በስራ የተወጠረ ወይም ደግሞ በተቃራኒው የቦዘነ ነው:: የጊዜ አጠቃቀማችን የግርግር፣ ምንም ነገር በአግባቡ የማይሠራበት ወይም በጣም የተጨናነቀና ያቀድናቸውን ነገሮች ለመፈጸም የምንወጠርባቸው

እንደምንጠቀምበት ደግመን ደጋግመን ማሰብና እግዚአብሔር በሚፈልገው ቅድመ ተከተል ማስተካከል ማለት ይሆናል። እንዲሁም በጣም ባተሌ የሆንንበትን (ወይም የተጨናነቅንበትን) ሁኔታ መመርመር ያስፈልገናል። የምናደርገው በርግጥ አስፈላጊ ነው? ወይም የምናደርገው ዝም ብሎ የሌሎችን ቀልብ ለመሳብ ነው? ብለን ልንፈትሽ ይገባናል። ሁሉንም ነገር ልናደርግ አንችልም፣ አንዳንድ ሁኔታዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆኑ "እምቢ አልችልም" ልንል ይገባል።

*ሶስተኛ፣ ጊዜአችሁን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች መድቡ።* ማንም ክርስቲያን፣ "ለእግዚአብሔር ባተሌ ሆንኩ አይልም"፣ ነገር ግን (ካለመፀለይና መጽሐፍ ቅዱስ ካለማንበብ አልፎ) እንዴት ቀኑን ሙሉ ስለእግዚአብሔር ሳታስቡ ታሳልፋላችሁ? የናንተን እርዳታ ወይም ማበረታቻ የሚፈልግን ሰው ችላ ማለት እንዴት ይቻላችኋል?

ይህ ለምን ይሆናል? አንደኛው ምክንያት ለእግዚአብሔር ትርፍ ጊዜያችንን ልንሰጠው ስለምንፈልግ ነው። ነገር ግን ትርፍ ጊዜ ሳናገኝለት ቀኑ ያልቃል። በሌላ አባባል፣ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በአዕምሮአችን (በልባችን) ስንመዘግብ እግዚአብሔርን በዝርዝራችን መጨረሻ ላይ እናስቀምጠዋለን። መሆን ያለበት ግን ተቃራኒው ነው። ኢየሱስ፣ "እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ጽድቅና መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ሌላውም የቀረው ነገር ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ 6፥33) ብሏል።

*በመጨረሻም፣ ለራሳችሁ ፋታም ጊዜ ይኑራችሁ።* ሁላችንም ዕረፍትና መዝናናት እንፈልጋለን፣ እግዚአብሔር የሰራን በዚህ መልኩ ነው። አንዳንድ ሰዎች የዕረፍት ፈቃድ ሲወስዱ ወይም ለጥቂት ሰዓታት ከሥራ ሲለዩ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል፣ ነገር ግን እንዲህ ሊሆኑ አይገባም። በጣም በተጨናነቀ አገልግሎት ውስጥ ሳሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን፣ "እናንተ ብቻችሁን ወደ አንድ ገለልተኛ ሥፍራ ሒዱና ጥቂት ዕረፉ" (ማር 6፥31) ብሏቸዋል። ኢየሱስ ለማረፍ ጊዜ ያስፈልጋል ካለ እኛስ አያስፈልገንም? አንድ ሰው በቂ እንቅልፍ ካጣ ወይም በአግባቡ የማይመገብ ከሆነ በብዙ መልኩ ለሰይጣን ጥቃት የተጋለጠ ይሆናል።





## በሥራ ከኢየሱስ ጋር

ጊዜአችንን በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን አብዛኞዎቻችን በቀን ካለን ጊዜ ውስጥ የበለጠው የተያዘው በሥራ ነው። ይኼ እውነት የሆነው ተቀጥረው ስራ ሰርተው ደሞዝ በሚያገኙት ላይ ብቻ አይደለም፣ በቤት ውስጥ ሆነው በስራ ተጠምደው የሚውሉትንም ይጨምራል።

ብዙ ክርስቲያኖች፣ በየዕለት ሥራቸውና በእምነታቸው መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ጥቂት እንደሆነ አድርገው ይመለከታሉ፣ እንዲያውም የሚሠሩትን ሥራ (ሥራ መሥራትን) እንደ ሸክም ይመለከቱታል። በድፍረትም፣ እግዚአብሔር አዳምን ከኤደን ገነት በማባረር "በወዝህ ትበላለህ" አላለውምን? (ዘፍ 3፥19) ይላሉ። ነገር ግን ይህ ጠቅላላ እውነታውን የሚያሳይ አይደለም። ሥራ በራሱ ክፉ አይደለም፤ ከውድቀት በፊት እንኳ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በኤደን ገነት አኖረው። ይህንንም ያደረገው ሰው የእትክልቱን ቦታ እንዲያለማና እንዲንከባከበው ነው (ዘፍ 2፥15)። በተጨማሪም በመንግሥተ ሰማያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ዕረፍት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንድንሠራ ያዘጋጀልን ሥራ አለ (ራዕ 22፥3)።

ክርስቶስ በሕይወታችን እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ሥልጣኑን ለማስፈን እንደሚፈልግ ልብ በሉ። በሥራችንም ሊመራን ይፈልጋል። በየቀኑ በምትሠሩት ሥራ ላይ ኢየሱስ ጌታ ሆኖአል? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

*አንደኛ፣ ሥራችሁን እንደሸክም ከመመልከት ይልቅ በእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ኃላፊነትና አደራ እንደሆነ አድርጋችሁ ቁጠሩት።* ሥራችሁ ምንም ይሁን ችግር የለውም፣ ሥራችን ከክብር ጋር ሕጋዊ ቢሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። ምናልባት ሥራችን አድካሚና ትርጉም የለሽ ቢሆንብንም ከእግዚአብሔር እንደተሰጠን አንድ ጊዜ ካወቅን አመለካከታችን ይቀየራል። የመክብብ መጽሐፍ ፀሐፊ ይህንን እውነት፣ "እንግዲህ ለሰው የሚጠቅመው ነገር ቢኖር ደክሞ በመሥራት ያፈራውን ሁሉ በመብላትና በመጠጣት ራሱን ለማስደሰት መቻሉ ነው፣ ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ተረድቻለሁ" (መክ 2፥24) በማለት ጽፏል።

ስለ አንድ ሰው ለአንድ ዓይነት አገልግሎት ወይም ተልዕኮ በእግዚአብሔር "እንደተጠራ" አድርገን እንናገራለን፣ ነገር ግን ኢየሱስና ሌሎች በፈቃዱ ውስጥ መሆናቸውን ካወቃችሁ እናንተም ስለሥራው ተጠርታችኋል። ይህ ማለት ሥራው ከቶ አሰልቺ ወይም ከባድ ወይም አድካሚ አይሆንም ማለት ነው? በርግጥ አይደለም። ነገር ግን ሥራችንን እግዚአብሔር እንደሰጠን አንድ ነገር አድርገን ስናይ፣ እንዲያውም የድግግሞሽ ተግባራት እንኳን ቢሆኑ ዋጋ አላቸው።

*በተጨማሪም፣ በምትሠሩት ሥራ ታማኞች ሁኑ።* ኢየሱስ፣ በምድር የሕይወት ዘመኑ አብዛኛውን ጊዜ የኖረው፣ ማርያምና ዮሴፍ ከግብጽ ከተመለሱ በኋላ በተቀመጡበት በናዝሬት ነበር። ዮሴፍ አናጢ ነበር፣ ኢየሱስ የዮሴፍን ዱካ በመከተል አናጢ ሆኖ ነበር (ማር 6፥3)።

ኢየሱስ እንዴት ጥሩ አናጢ እንደነበር ልትገምቱ ትችላላችሁ? የዕቃ መደርደሪያ እንዲሠራላችሁ ካዘዛችሁት በሮቹን አልገጠመላችሁም? ወይም ደግሞ እንጨቱ የተሰጠነቀ ነበር? ወይም ሠርቶ ያስረከባችሁ ሁለት ወራት ዘግይቶ ነው? በርግጥ ኢየሱስ እንደዚህ አላደረገም። እኛስ በምንሰራው ሥራ ታማኝነትን እናጎድላለን?

ታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚነግሩን በሮማውያን አገዛዝ ስር ከነበሩ ህዝቦች መካከል ግማሽ ያህሉ ባሮች ነበሩ። (አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች የሮማ ውድቀት ምክንያት የሆነው ለዚህ ምግባረ ብልሹና አስከፊ ተቋም ድጋፍ በማድረግዋ ነው ይላሉ።) በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያን ባሮች በነበራቸው አነስተኛ የነፃነት ዕድል ውስጥ ሆነው በታማኝነት እንዲሠሩ ማስገንዘቢያ ተሰጥቷቸዋል፣ "አገልጋዮች ሆይ ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር ታዘዙ የምትታዘዙትም ሰውን ደስ ለማሰኘትና ለታይታ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስን በመፍራትና በልበ ቅንነት ይሁን" (ቆላ 3፥22)። አስሪዎቻቸውም (ጌቶቻቸው) እንደዚሁ በእውነትና በትህትና እንዲሆኑ ታዘዋል፣ "ጌቶች ሆይ! እናንተም በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ አገልጋዮቻችሁን በቅንነትና በእኩልነት አስተዳድሩአቸው" (ቆላ 4፡1)። ክፍለ ዘመኑ እንዳለቀ የሰው ልጅ ክቡር መሆኑ በወንጌል አማካይነት የተዘራው ዘር ከዘመናት በኋላ በመጨረሻ ፍሬ አፍርቶ የባሪነትን ሥርዓት አንገዳግዷል (በእርግጥ ከፍተኛ ትግልን የጠየቀ ነበር።) እናም ዛሬ





ማንኛውም ዓይነት የባርነት አገዛዝና ጥቃት እግዚአብሔርን እንደማጥቃት የሚቆጠር፣ የተጠላና የተወገዘ ነው። ምንም እንኳ በምድር ላይ በተለያዩ የዓለም ክፍሎችና አገዛዝ ውስጥ የምንኖር ቢሆንም ወሳኙ መርህ ግን አልተለወጠም። ሠራተኛ ወይም አሠሪ ብትሆኑ፣ በታማኝነትና ኃላፊነታችሁን በብቃት በመወጣት ሥሩ፣ እንደዚሁም የሚጠበቅባችሁን ትህትናና ቅንነት በሥራችሁ ሁሉ ላይ አሳዩ።

*በመጨረሻም፣ ሥራችሁን በሐቀኝነት ሥሩ።* በሥራቸው ላይ ችግር ካጋጠማቸው ክርስቲያኖች አልፎ አልፎ ደብዳቤ ይደርሰኛል። አሰሪዎቻቸው ሕገ ወጥ ወይም የማጭበርበር ሥራ እንዲሠሩ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊፈጽሙባቸው የጠየቋቸው፣ ወይም የማጭበርበር ወይም ሌላ ሕገወጥ ድርጊት ያጋጠማቸው ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ችግሮች በጣም ውስብስብና ፈታኞች ናቸው፣ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ የአተገባበር አቅጣጫ ለይቶ ለማወቅ ቀላል አይሆንም። ነገር ግን ምንም ዋጋ ቢያስከፍልም፣ ሥራቸውን በታማኝነትና በሐቀኝነት እንዲሠሩ እነግራቸዋለሁ። ከእግዚአብሔር ፈቃድና መስፈርት ጋር ድርድር ውስጥ እንዳይገቡ እመክራቸዋለሁ። እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር እንደሆነና እንደማይተዋቸው አሳስባቸዋለሁ። ከባድ ቢሆንም ከከፉ ይልቅ መልካም መሥራት እንደሚሻል አስታውሳቸዋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እናንተ ራሳችሁ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ። አሁን ግን በጌታ ብርሃን ስለሆናችሁ በብርሃን እንደሚኖሩ ሰዎች ኑሩ (ምክንያቱም የደግነት ሁሉ የጽድቅና የእውነት ፍሬ የሚገኘው ከብርሃን ነው) ስለዚህ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነ መርምሩ። ወደ ብርሃን አውጥታችሁ አጋልጡት እንጂ ፍሬ ቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ (ኤፌ 5፥8-11) ይላል። እነዚህ ቃላት ሁለተናችሁን፣ ሥራችሁንም ጨምሮ የሚመለከቱ ናቸው።

የሕይወታችሁ የዕለት ተዕለት የድግግሞሽ ተግባራት እምነታችሁን እንዲያላሉ አትፍቀዱላቸው፤ ነገር ግን በየቀኑ ሁለተናችሁን (ጊዜአችሁንና ሥራችሁን ጭምር) ለኢየሱስ አገዛዝ አስረክቡ። ከዚያም እምነታችሁና የፍቅር ግለታችሁ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር የሰጣችሁን "ነዳጅ" - የክርስቲያኖች ህብረት፣ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት "ነዳጅ" - በመጠቀም ኃይላችሁን አድሱ።

በጉባኤው ላይ መሳተፍ እንደማይገባኝ አጥብቀው ተቃወሙ:: የመጽሔትና የጋዜጣ አሳታሚዎችም በጉባኤው ላይ መሳተፌን በመቃወም አቋም ያዙ::

እኔ ግን አብዝቼ በፀለይኩ ቁጥር (መጽሐፍ ቅዱስን እየመረመርኩ፣ ጠቃሚ የሆነ ምክርንም ከወገኖች እየጠየቅሁ) ግብዣውን እንድቀበል እግዚአብሔር እየመራኝ እንደሆነ አመንኩ:: ውሳኔውን በአምንታ ሰቀበል የሰላም ጉባኤውን ሰካፈል ደግሞ በተመልካችነት መካፈል እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፣ በዚህ መልኩ ብሳተፍ ጉባኤው የሚያወጣውን አዋጅና መግለጫ የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ድምጽ ከመስጠት ውጪ ያደርገኛል፣ በጉባኤውም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰላም ምን እንደሚናገርና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ምን እንደሆነ ለመናገር እንደምችል አሰብኩ:: ሞስኮ በሚገኙ ሁለት ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ እንደምችል ተረዳሁ::

በመጨረሻም ለመሔድ ወሰንኩ:: ምንም እንኳ ጉዞአችን አሰመግባባትን የፈጠረ ቢሆንም ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድና አመራር ነበረው:: ወንጌልን በሞስኮ መስበክ ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ግዛት በሙሉ እግዚአብሔር የአገልግሎት በር በሰፊው ከፍቶልኛል:: ይህንን ቀደም ብዬ አላስተዋልኩትም ነበር:: ይህን ግብዣ ውድቅ ባደርገው ኖሮ አገልግሎታችን ባላደገ ነበር:: በተለይ በዚህ የአገልግሎት ጉዞ መንታ መንገድ አጋጥሞኝ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን መምረጥ ያሰብኝን መንገድ አሳይቶኛል::

## እግዚአብሔር ይጠነቀቅልናል?

በእርግጥ እግዚአብሔር ለምንሰጠው ውሳኔአችንና ምርጫችን ይጠነቀቅልናል? እግዚአብሔር ለሕይወታችን እቅድ - እና በትክክል የምናውቀው እቅድ - አለው? ወይስ እኛ እራሳችን በራሳችን ውሳኔ እንድናደርግ ይተወናል?

የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ግልጽ ነው፤ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉን ነገር ያውቃል፣ ደግሞም ለእኛ ምን እንደሚሻለንና እንደሚበጀን ያውቃል:: ከፊታችን ሊገጥመን የሚችለውን አደጋ ይመለከታል፣ የሚያጋጥመንንም ደስታ ያውቃል:: ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያውቀው መልካም የሆነውን ብቻ ሳይሆን መልካም ነገር እንዲሆንልንም ይፈልጋል:: ምክንያቱ በጣም ቀላል ነው፤ እግዚአብሔር ይወደናል::





ይህ ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ሰዎች ለሕይወታቸው መልካም እቅድ እንዳለው ለማመን ይቸገራሉ:: "እሱ በሥራ የተወጠረ ስለሆነ የኔ ጉዳይ ግድ ሊለው አይችልም" በማለት ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ:: ሌሎች ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ፈጽሞ አያስቡም፣ እራሳቸው ለራሳቸው እንዲወስኑ የተወላቸው አድርገው ያስባሉ:: አሁንም ሌሎች ደግሞ ሌላ ችግር ያለባቸው አሉ፤ እግዚአብሔር ጨካኝና አምባገነን እንደሆነና ሰዎችን ማስጨነቅ የሚፈልግ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ:: ለምንስ እንዲህ እንድንሆን ይፈርድብናል በማለት እንደነሱ አስተሳሰብ ጉስቁሎች እንድንሆን እስከሆነ ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለምን እንፈልጋለን? ብለው ያስባሉ::

ይሁን እንጂ፣ ለብዙዎቻችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳናውቅ መሰናክል የሚሆንብን አንዱና ትልቁ ችግር የራሳችንን ሕይወት በራሳችን ምርጫ ለመምራት ስለምንሮጥ ነው:: የኛ ችግር በልባችን ውስጥ ጦርነት መኖሩ ነው - ጦርነቱ በእግዚአብሔር ፈቃድና በራሳችን ፈቃድ መካከል የሚደረግ ነው::

እግዚአብሔርን የምንፈልገውና እንዲመራን የምንጠይቀው ለጥቅማችን ሊሆን ነው:: ከዚያም ያሰብነውን ነገር አግኝተነው ከጨበጥነው በኋላ እግዚአብሔር ለእሱ እንድናደርግለት የሚፈልገው ነገር እንዳለ ካሰብን ለማድረግ ፈቃደኛ አንሆንም:: አንዲት ሴት፣ "ላደርገው የምፈልገው ነገር ስህተት እንደሆነ አውቀዋለሁ፣ ነገር ግን ምንም ቢሆን አሁን አደርገዋለሁ:: እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል፣ ይቅርታ አያደርግልኝም?" በማለት ደብዳቤ ጽፋልኛለች::

እነዚህ ሀሳቦች በሙሉ መለኪያውን የሳቱና በመንፈሳዊ ረገድ እደገኛ ናቸው:: እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ለኛ ምን ያህል በጥልቀት እንደሚጠነቀቅልን የማያገናዝቡ ናቸው:: ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመግለጽ ከምፈልጋቸው እውነቶች መካከል አንዱና ዋናው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ነው:: እግዚአብሔር ባይወደን ኖሮ፣ በውሳኔአችን ምክንያት ስለሚገጥመን ችግር ግድ አይልም ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ይወደናል - ልዩ የሚያደርገውም ይህ ነው:: እርሱ ስለሚወደን፣ ፈቃዱ ለኛ ሁልጊዜ የተሻለ ስለሆነ፣ ሁልጊዜ መልካም ስለሆነ በፍጹም መተማመን ልንፈልገው እንችላለን:: ከሁሉም በላይ፣ እኛ የዘላለም ድነት እንድናገኝ ልጁን ወደ ዓለም በመላክ ስለ

ኃጢአታችን እንዲሞት አስከማድረግ ከወደደን እንዴት ስለ እኛ ስለ ነገአችን አይጠነቀቅልንም? እንዴት አይወደንም እንላለን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እግዚአብሔር ለአንድ ልጁ ሳይራራ ስለኛ አሳልፎ ከሰጠው፣ ከልጁ ጋር ሁሉን ነገር እንደሚሰጠን እርግጠኞች ነን" (ሮሜ 8፥32)::

አግዚአብሔር ይወዳችኋል፤ ስለሚወዳችሁም፣ ለሕይወታችሁ ዘላለማዊ ዕቅድ አለው:: ምንም ነገር ፈቃዱን እንዳትፈልጉ እንዲያደርጋችሁ አትፍቀዱለት::

## የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁለቱ ገጽታዎች (አቅጣጫዎች)

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አናውቃለን? የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ይህን ጥያቄ ሁልጊዜ በብዙ ክርስቲያኖች እንደሚጠየቁ ይነግሩኛል:: ጥያቄው የሚቀርብላቸው ከጥሩ ምክንያት ጋር ነበር:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ የበለጠ ሌላ የተሻለ ነገር ሊኖር ይችል ይሆን?

ከሁሉ አስቀድመን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለሁለት አቅጣጫ እንደሆነ በርግጠኝነት ልንገነዘብ ይገባናል:: *አንደኛ፣ እግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ወይም አጠቃላይ ብለን የምንጠራው ፈቃድ አለው፡፡* የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ ነው:: ይህን የአግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ ሞራላዊ (ከብረ ሀሊናዊ) ፈቃድ ብለን ልንጠራው አንችላለን፣ ምክንያቱም ይህ ፈቃድ ጉዳይ ያለው ከኛ ሥነ - ምግባራዊ ጠባይና ሞራል ጋር በመሆኑ ነው::

የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ፈቃዱ ከሰው ሰው የሚለዋወጥና የተለያየ አይደለም፤ በእኔ ላይ እንደሆነ እንዲሁ በናንተ ላይ ተመሳሳይ ነው:: ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁላችንም ሕይወታችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንድንሰጥና አምነን እንድንከተለው ነው:: እንደዚሁም የአግዚአብሔር ፈቃድ ኃጢአት ማድረግን እንድንተው ነው፤ እንድንዋሽ፣ ወይም እንድንሠርቅ ወይም ዝሙት እንድንፈጽም ወይም እንድንገድል ወይም እንድንመኝ ወይም ንፉጎች እንድንሆን ከቶ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: እነዚህ ነገሮች ሁላችንንም አይመለከቱምን? በእርግጥ ይመለከቱናል፣ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ የመጡት ከዐስርቱ ወርቃማ ትዕዛዛት ውስጥ ናቸው (በዘፀአት 20 እና በዘዳግም 5 ላይ ታገኙአቸዋላችሁ)::





የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ - ለሁሉ ሰው (እናንተንና እኔን ጨምሮ) የሆነ ፈቃዱን እንዴት እናውቃለን? ትክክለኛ መልስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን:: በእርግጥ፣ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበት አንዱ ምክንያት የእርሱን ፈቃድ እናውቅ ዘንድ ነው፤ "ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው፣ እርሱ እውነትን ለማስተማር፣ የተሳሳቱትን ለመገሰጽ፣ ስህተትን ለማረምና ለትክክለኛ ኑሮ የሚበጀውን መመሪያ ለመስጠት ይጠቅማል" (2ጢሞ 3፥16):: መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ወጣቶች ሕይወታቸውን በንጽሕና መጠበቅ የሚችሉት ትዕዛዛትህን በመፈጸም ነው" ይላል (መዝ 119፥9)::

እንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ልንከተለው የሚገባ ግልጽና ልዩ የሆነ መመሪያ ይሰጠናል:: መክፈል የሚገባንን ቀረጥ በማታለል አለመክፈል ስህተት ስለ መሆኑ እግዚአብሔርን መጠየቅ የለብንም፤ ምክንያቱም አርሱ አስቀድሞ፣ "ያለባችሁን ግዴታ ፈጽሙ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፤ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ክፈሉ" በማለት አዞናል:: ወይም ደግሞ ለትዳር አጋሮቻችን ታማኝ አለመሆን ስህተት ነው ወይስ አይደለም ብለን እግዚአብሔርን መጠየቅ ተገቢአችን አይደለም፣ ስለዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በጣም ግልጽ ነው፣ ስለዚህ ከዝሙት ራቁ (1ቆሮ 6፥18) ብሎናል:: አግዚአብሔር በፍጹም - ደግሞም በፍጹም - ቃሉን፣ መጽሐፍ ቅዱስን፣ የሚቃረን ነገር እንድታደርግ አይመራችሁም::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ልዩ መመሪያ ብቻ አይደለም የሚሰጠን:: እንድንመራበት ሞራላዊና መንፈሳዊ የሆኑ በጣም ጠቅለል ያሉ (አጠቃላይ) መመሪያዎችንም ጨምሮ ይሰጠናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ህጎች ሁሉ የሚበልጠው የትኛው እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ ሁለት መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ፣ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ፣ በፍጹም አሳብህም ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ" አለው (ሉቃስ 10፥27):: እነዚያን መመሪያዎች በትክክል የምንከተላቸው ቢሆን ኖሮ ምድራችን አሁን ካለችበት ሁኔታ የበለጠ እንዴት የተሻለች በሆነች ነበር!

"ለእግዚአብሔር ቃል ጭፍን ከሆንክ፣ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ጭፍን (ደንቆሮ) ትሆናለህ" የሚል አባባል

እንደሆነ አውቀናል ብለን እናስባለን፣ እግዚአብሔር ለኛ ያለው እቅድ ግን ሌላ ነው:: ይህ በናንተ ላይ እንዲሆን አትፍቀዱ፣ ማንኛውንም ውሳኔ ለእግዚአብሔር ስጡ:: ሲጀመር ብቻ ሳይሆን እስከመጨረሻው ሂደት ለርሱ ፍቀዱለት::

*ሁለተኛ፤ መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ።* ውሳኔና ምርጫ ለሚያስፈልገው ለማናቸውም ጉዳያችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ የሆነ መመሪያ አለው? እናንተ ላላችሁበት ሁኔታ የሚስማማ መመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ? እንደኔ ዓይነት ችግር ያጋጠመው ሰው ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ? ካለስ እንዴት ተወጣው? (አንዳንዶች ከፈፀሙት የስህተት ውሳኔ እንኳን ለመማር እንችላለን):: አስቀድመን ምን እንደተነጋገርን አስተውሉ፤ እግዚአብሔር ቃሉን (መጽሐፍ ቅዱስን) የሚቃረን ማናቸውንም ነገር እንድንፈጽም ከቶ አይመራንም::

*ሶስተኛው፤ በአካባቢያችሁ ያሉትን ሁኔታዎች እወቁ:* እግዚአብሔር የሚሠራው በእኛ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያችንም ይሠራል:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመራን በአካባቢያችን ባለው ሁኔታ አማካይነት ነው:: ለምሳሌ፤ እግዚአብሔር አንተን/ አንቺን ልዩ አድርጐ ፈጥሮአል፤ እርሱ ያላችሁን ችሎታና የችሎታችሁን ውስንነት እንድታውቁ ይፈልጋል:: እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድንሠራ ወይም እንድፈጽመው ለመፈፀም የምንችልበትን ችሎታና ብቃት ሳይሰጠን አያዘንም ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የርሱን ፈቃድ ስንፈልግ እግዚአብሔር የዕድሎችን በር በመክፈት ወይም በመዝጋት ይመራናል:: በተጨማሪ እግዚአብሔር ውሳኔ በምናደርግበት ጊዜ በጥበብና በዘዴ እንድናደርገው ይፈልጋል:: ውሳኔ ስናደርግ ውሳኔዎቹ ሊያመጡ የሚችሉትን ውጤት አስበናል (መዝነናል)? ያሉንን አማራጮችና ችሎታዎች ፈትሸን የትኛው አማራጭ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝልን እንደሚችል አይተናል?

*ዐራተኛ፤ አምላካዊ (በጐ) ምክር ፈልጉ፡፡* እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ልዩ የጥበብ ስጦታ ሰጥቷል፣ ስለዚህ ለመወሰን ስንቸገር፣ የነዚህን ሰዎች ምክር መፈለግ ይረዳል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "መልካምን ምክር ብትቀበል ሁሉ ነገር ይሳካልሃል:- ምክርን ባትቀበል ግን ምንም ነገር አይሳካልህም" (ምሳሌ 15፥22):: እነዚህ ሰዎች ሁኔታችሁን ተረድተው እንዲረዱአችሁ እግዚአብሔር





የሚጠቀምባቸው ቢሆንም፣ የሚሰጡንን ምክር በጥንቃቄ ልንመዝነው ይገባናል::

በዓመታት አገልግሎቴ በፈቃደኛነት ጥበባቸውንና ልምዳቸውን በማካፈል ላልተለዩኝና ለረዱኝ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አመሰግነዋለሁ:: የነዚህ ሰዎች ምክር እጅግ አስፈላጊ ሲሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመለየት ረገድ በብዙ ረድቶኛል::

*አምስተኛ፤ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ታመኑ፡፡* የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእውነትና በታማኝነት ስንፈልግ፣ እግዚአብሔር የፀና ውስጣዊ እምነት ወይም በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለብን ፍንጭ ይሰጠናል፣ ይገፋፋናልም:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ከመንገድ ወጥታችሁ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ብትባዝኑ ከበስተኋላችሁ፣ 'ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው፣ በዚህ ሂድ' የሚለውን ድምጽ ትሰማላችሁ" (ኢሳ 30፥21)::

የሚያበረታታው (የሚያደፋፍረው) ድምጽ የሚመጣው፣ ክርስቶስን ብናውቅ በውስጣችን ከሚኖረው ከቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: ኢየሱስ፣ "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ 16፥13) ብሏል:: ይህ የፀና ውስጣዊ እምነት ስሜት አይደለም፤ እግዚአብሔር እኛን የሚመራበት የተረጋጋ ሰላም የተሞላ እርግጠኛ መንገድ ነው::

መንፈስ ቅዱስ ተለይቶ (ብቻውን) አይሠራም:: ስለሆነም፣ የራሳችንን መሻት ከመንፈስ ቅዱስ ማበረታቻ ጋር እንዳናደበላልቅ (እንዳናወነባብድ) ልንጠበቅ ያስፈልጋል:: መጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፣ አካባቢያችንን መፈተሽ፣ እና አምላካዊ ምክር መፈለግ ያስፈልገናል:: እግዚአብሔር ወደ መጨረሻው ውሳኔ ወይም ግብ እንድንደርስ ሁልጊዜ በውስጣችን ያደፋፍረናል::

*በመጨረሻም፣ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሔር ታመኑ፡፡* እግዚአብሔር እንድትወስኑ ከመራችሁ በኋላ ወደኋላ አትበሉ:: ይልቁንም፣ በምሪቱ ታመኑ፣ ከፊታችሁ ቀድሞ እንደሚወጣ እመኑ - እርሱ ያደርጋል:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እንደመራን እርግጠኛ የምንሆነው ውሳኔ ካደረግን በኋላ ነው፤ ነገር ግን በእውነት የርሱን ፈቃድ የምንፈልግ ከሆነ፣ መንገዱ ግልጽ ባይሆን እንኳን እርሱ ሊመራን ተስፋ ሰጥቶናል::

ስለግል ሕይወቱ እግዚአብሔር ስላለው ፈቃድ በሺዎች የሚቆጠሩ ጥያቄዎች ያሉት የሚመስል የማውቀው ወጣት ነበረ። ስለጉዳዩ ከማንም ጋር ብዙ ሰዓታትን ይነጋገራል፤ ከሚገናኘው ሰው ሁሉ ምክር ይቀበላል፤ ብዙ ሰዓታትን በመናገር ያባክናል፣ ነገር ግን ከቶ ወደ ውሳኔ መድረስ አልቻለም።

ጊዜያችሁ እያለቀ እያያችሁ ከኋላ በመቀመጥ ዝም ብላችሁ ታላቅ መገለጥ (ራዕይ) ወደ እኛ ይመጣል ብላችሁ አትጠብቁ። ጊዜአችሁንም አታባክኑ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሔ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ባሰባችሁበት አቅጣጫ ጉዞአችሁን መጀመር የበለጠ ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ እየተጓዛችሁበት ያለው መንገድ እርሱ የማይፈልገው ሆኖ ቢዘጋና ሌላ መንገድ በሚከፍትበት ጊዜ በአመራሩ ታመኑበት። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን እንጂ በራስህ እውቀት አትደገፍ፣ በምታደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አስቀድመው፣ እርሱም በትክክለኛው መንገድ ይመራሃል" ይላል (ምሳሌ 3፥5-6)።

አስተውሉ፤ እግዚአብሔር ይወዳችኋል፣ ፈቃዱንም ታውቁ ዘንድ ይፈልጋል። ፈልጉ ... እወቁ ... እናም ፈጽሙ። የርሱ መንገድ ሁልጊዜም ተወዳዳሪ የለውም።





# ሃያ አምስት

## ስተሻለው ወይም ስከፋው

*ሰው ስባቱንና ስናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበረው ስስዚህ ነው፤ ሁስቱም ስንድ ይሆናስ*

(ዘፍ 2፥24)

ከመልካም ጋብቻ የበለጠ ደስታን የሚሰጥ እንደሌለ ሁሉ፤ መጥፎ ጋብቻ ከሚያመጣው ስቃይ የበለጠ የለም።

ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስመለከተው በወጣትነት ጊዜዬ ስለጋብቻ ትልቅ ስፍራ ሰጥቼ አስብ እንደነበረ አስታውሳለሁ፤ ነገር ግን ማግባት ማለት በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ ብዙም አላስብም ነበር።

አንድ ቀን አንድ ሰው በኮሌጅ የመጨረሻውን ዓመት ትምህርቴን ስማር እኖርበት ወደነበረው ቤት እየነዳ መጣ። በአቅራቢያችን የምትገኝ የአንዲት አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነበር። "በማኅበረ - ምዕመናኑ የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ እንድትሆንላቸው በማሰብ ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ" ብሎ ነገረኝ። በዚያ ዓመት ውስጥ በብዙ ቤተክርስቲያኖች እየተጋበዝኩ በመደበኛነት እየተገኘሁ እሰብክ ነበር፣ ከነርሱ አንዳንዶቹ ስብከት እዳምጠው እንደ ነበር አስባለሁ። ከቤተክርስቲያኒቱ ወገኖች ጋር ስለተፈለግኩበት ጉዳይ ከተነጋገርንበትና ከጸለይንበት በኋላ ግብዣቸውን ተቀበልኩ።

ይህን ውሳኔ ባስለፍኩበት ጊዜ ብቸኛው ችግሬ ልክ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅኩኝ (እንደተመረቅኩ) ከሩት ጋር ወዲያውኑ ለመጋባት ቃል መግባታችንን መርሳቴ ነበር - መጋቢ ለመሆን ጥሪውን ስቀበል ሩትን ማማከር ይገባኝ እንደነበር በጭራሽ አረስቼው ነበር። ውሳኔዬ እኔን እንደረበሸኝ እርሷንም ረበሻት።

ውሳኔው የጋራ እንጂ የግሌ ብቻ መሆን አልነበረበትም:: ወዲያውኑ እሷ እኔን ግዴለሽ እንደሆንኩ አድርጋ እንደቆጠረችኝ እንዳውቅ አደረገችኝ፣ በዚህ ምክንያት በመበሳጨቷም ልወቅሳት አልቻልኩም:: መማርና ማሰላሰል ጀመርኩ - ቀስ በቀስም መፍራት ጀመርኩ - ጋብቻ እንዲያው በቀላሉ የእርስ በርስ ግንኙነትን ወይም ወዳጅነትን በመመስረት ከመደሰት ያለፈ ነው:: ብዙ ብዙ ነገር በውስጡ አለ:: ከስድሳ ዓመታት ትዳር በኋላም አሁንም እየተማርኩ ነው::

## ጋብቻ:- የእግዚአብሔር ስጦታ ነው

*ጋብቻ ምንድን ነው? ከሁሉም በበለጠ ስለ ጋብቻ ልንረዳው የሚገባን አስፈላጊ እውነት፣ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ስጦታ መሆኑን ነው::* ጋብቻ በእግዚአብሔር የተሠራ ነው፣ በእኛ አይደለም:: ማኅበረሰብ የመሰረተው አይደለም፤ እግዚአብሔር የመሰረተው ነው:: ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ ከብዙ ዘመን በፊት እግዚአብሔር ወደ አዳም ተመለከተና እንዲህ አለ፣ "ሰው ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም፤ ስለዚህ ተስማሚና ረዳት ጓደኛ አፈጥርለታለሁ" (ዘፍ 2፥18)::

እግዚአብሔር ይህን እስካለበት ነጥብ ድረስ የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ "መልካም" ብሏል:: አሁን ግን አንድ ነገር - የአዳም የብቸኝነት ሁኔታ - መልካም እንዳልሆነ አሳወቀ:: ምንም እንኳ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ያልተገደበ ህብረትና ግንኙነት የነበረው ቢሆንም ያ በቂ አልነበረም:: አዳም ሕይወትን የሚጋራው ሌላ ሰው ያስፈልገው ነበር - ስለዚህ እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረለት:: የመጀመሪያው ሰርግ የተዘጋጀው በእግዚአብሔር በኤደን ገነት ውስጥ ነበር:: ጋብቻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ ጋብቻ የምንባረክበትና ፍጹም የምንሆንበት መንገድ ነው::

## ጋብቻ:- ለአብሮነት ነው

እግዚአብሔር ጋብቻን የሰጠን ለምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ምክንያቶችን ይሰጠናል:: ከነዚህ ዋንኛው፣ *እግዚአብሔር ጋብቻን የሰጠን አብሮ ለመሆን (ለአብሮነት) ነው::* እግዚአብሔር አዳምን የእንስሳት ሠራዊት ሁሉ ስም እንዲያወጣላቸውና እንዲቆጣጠራቸው ሲነግረው:- "ለአዳም ግን ተስማሚና ረዳት ጓደኛ ገና አልተገኘለትም ነበር" (ዘፍ 2፥20):: አዳም የተሠራው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፣ ልክ ፍቅር





የእግዚአብሔር ባሕርይ አካል እንደሆነ፣ ፍቅር የአዳምም ባሕርይ አካል ነበር:: እርሱ ሊወደው የሚገባው አንድ ሰው ያስፈልገው ነበር፣ በምላሹም እርሱን የሚወድ ሰው ይፈልግ ነበር:: ብቸኝነቱን የሚያርቅለትና ሙሉ የሚያደርገው አንድ ሰው ብቻ ነበር::

አንዳንድ ሰዎች "ሚስቴ/ባሌ ከሁሉ ይበልጥ ጓደኛዬ ናት/ ነው" በማለት ሲናገሩ ስሰማ ሁልጊዜ እበረታታለሁ:: ለብዙ ዓመታት እኔ በማደርገው ረጅም ጉዞ ምክንያት ከሩት ጋር ረጅም ቀናት ተለያይተን እንቆያለን፣ አንዳንድ ጊዜም በጣም ረዥምም ስሆን ጊዜ ለመቆየት ጉዞዬን ስጀምርና ልክ ቤቴን ለቅቄ የምሳፈርበትን ባቡር ወይም አውሮፕላን እንደያዝኩ አይኖቼ እንባ ያመነጫሉ:: አሁን በእርጅና እድሜያችን አንድ ላይ ሆነን፣ ትልቁ ደስታችን የሆነው አብረን መሆናችን ነው:: ቃላት ሳንለዋወጥ በጸጥታ ሆነን በተቀመጥንበት እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ አብረን ቴሌቪዥን በማየት፣ በህብረት ሆነን በመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል በመከፋፈል በአብሮነታችን እንደሰታለን:: አብሮ በመሆን የሚገኘውን የደስታ ጥልቀት ተገንዝበናል::

*እግዚአብሔር ጋብቻን የመሰረተበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በጋራ በመሆን እንድንረዳዳና እንድንበረታታ ነው::* ሔዋን ለአዳም "ተስማሚ" ወይም "በቂ" እንድትሆን ነበር:: ሔዋን ለአዳም ባሪያው ወይም አገልጋይ አልነበረችም:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን አደራ (የማስተዳደር ኃላፊነት)፣ "ብዙ ተባዙ ዘራችሁ ምድርን ይሙላ፣ ምድርም በቁጥጥራችሁ ሥር ትሁን" (ዘፍ 12፥8) ብሎ የሰጠውን በተሳካ ሁኔታ እንዲያሟላ የምታግዘው ረዳቱ ነበረች::

አዳም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን አደራ ብቻውን መወጣት አይችልም ነበር:: ለአዳም ሔዋን ታስፈልገው ነበር - ለሔዋንም አዳም ያስፈልጋት ነበር:: በመካከላቸው አንዳቸው በአንዳቸው ላይ የመበላለጥና የበታች ወይም የበላይ አልነበረም:: እርስ በርስ የሚፈላለጉና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ ነበሩ:: ባለትዳሮች ተለያይተው ሳይ በጣም አዝናለሁ:: የማይከባበሩና የሚናናቁ ጥንዶች ያሳዝኑኛል:: ባል ወይም ሚስት የትዳር አጋራቸውን ሲተቹ ወይም ሲሰድቡ ወይም ሲያንቋሽሹ መስማት አሳዛኝ ነው:: ለእርስ በርሳችን የማያቋርጥ መረዳዳትና ማበረታታት ያስፈልገናል::

የተመሠረተ ጋብቻ ከሰርግ ማግስት ጀምሮ ለመፍረስ የተዘጋጀ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እንድናፈቅር የማፍቀር ችሎታ የሰጠን እግዚአብሔር ብቻ ነው። የእውነተኛ ፍቅር ትርጉሙንም የሚያስተምረን እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## እውነተኛ ፍቅር

እውነተኛ ፍቅር ምንድነው? ቀደም ብለን ስለ እርስ በርስ ግንኙነት በሚያወራው ምዕራፍ እንደተመለከትነው፣ እውነተኛ ፍቅር በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ተግባር ነው። ይልቁንም ምርጥ ነው ብለን የምናስበውን ነገር ለራሳችን በማድረግ ፈንታ ለሌሎች ለማድረግ አስበንበት የምናደርገው ውሳኔ ነው። ለዚህም ነው በጋብቻ ውስጥ መስጠት የሚያስፈልገው። ወንዱና ሴቷ ሁለቱም አብረው እስከኖሩ ድረስ አንዱ ለሌላው መስጠት ማለት ነው።

እኔና ሩት በተጋባን ጊዜ፣ በቤተሰቦቻችንና በወዳጆቻችን ፊት ቆመን ለተጠየቅነው ሁሉ "እስማማለሁ" ብለናል። በነዚህ ቃላት በቀሪው ዘመናችን አንዳችን ለሌላው መስጠት እንዳለብን ቃል ኪዳን አድርገናል። ነገር ግን ኪዳን ስንገባ ቆመን የነበረው በጉባኤው ፊት ብቻ ሳይሆን የቆምነው በእግዚአብሔር ፊት ጭምር ነበረ፣ በሱ ፊት መሃላ ፈጽመናል። እርሱ አንድ አድርጎናል፣ ስለዚህ እርስ በርሳችን መዋደድ እንዳለብንና በሕይወት ዘመናችን ሁሉ አብረን በሕይወት ስንኖር ለርስ በርሳችን ታማኝ እንደምንሆን ለእግዚአብሔር ቃል ገብተናል። የፍቅራችን ኪዳን ከበድ ያለ የመስጠት ውሳኔ ሲሆን በእግዚአብሔር መገኘት ማህተም የታተመ ነበር። ከባለቤቴ ጋር ለዓመታት አብረን ስንኖር ድካምና ውጥረት በመንገዳችን ላይ ሲያጋጥሙን፣ ኢየሱስ፣ "እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው" (ማቴ 19፥6) ያለው ቃል ለርስ በርሳችን እውነተኛ እንድንሆን አድርጎናል።

## የፍቅር ስዕል

የኮሌጅ ተማሪ የሆነች አንዲት ወጣት በቅርቡ በጻፈችልኝ ደብዳቤዋ፣ "ለማግባት ያለኝ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ስለማወቁ እርግጠኛ አይደለሁም። ያደግኩት በፈረሰ ቤተሰብ ውስጥ ነው፣ እውነተኛ ፍቅር የሚባለውን ከቶ አይቼው አላውቅም። ለመሆኑ እውነተኛ ፍቅር የሚባል አለ? " በማለት ጠይቃኛለች።





አዎን አለ፣ እውነተኛ ፍቅር የሚባለው እውን አለ - ልናውቅም ልናገኝም የምንችለው በእግዚአብሔር ርዳታ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአታችንንና ራስ ወዳድነታችንን አስወግዶ በኛ ውስጥ የርሱን ፍቅር ሊተካ ይፈልጋል። የርሱ ፍቅር ለራሳችን ሳይሆን ለሌሎች ትኩረት እንድናደርግ የሚያደርግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፣ "እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ" (ፊልጵ 2፥4)።

እውነተኛ ፍቅር ማለት ይህ ነው፤ ኢየሱስ ለኛ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ፣ መስዋዕት እንደሆነ ማለት ነው፣ "ራሱን በትህትና ዝቅ አደረገ እስከ ሞት ድረስ የታዘዘ ሆነ" (ፊልጵ 2፥8) ፍቅር ማለት የራስን ፍላጐት ለሌላ መሠዋት ነው። ፍቅር ምን እንደሆነ ለማወቅ ትሻላችሁ? ኢየሱስን ተመልከቱ፣ በገዛ ፈቃዱ የመንግስተ ሰማያት ክብሩን ትቶ ኃጢአትና በደል በሰለጠነባት በዚህች ምድር ለመመላለስና ለሰው ሁሉ የሚሆን እጅግ ታላቅ የሆነ መስዋትነትን ለመክፈል የመጣውን - በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሞተልንን - ተመልከቱ፣ ስለዚህ እኛ ዳንን። በኛ ምትክ ራሱን አሳልፎ ሰጠ! ከራሱ ይልቅ እኛን አስበለጠን! እውነተኛ ፍቅር የሚሠራው እንዲህ ነው።

የሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን አሳልፎ የመስጠትን ፍቅር ምንነት ማብራሪያ - መጽሐፍ ቅዱስ አጋፔ ፍቅር ይለዋል - አብዛኛውን ጊዜ ጋብቻ በሚፈፀምበት ሠርግ ላይ ይጠቀሳል፣ ግን ወዲያውኑ ይረሳል። ነገር ግን በልባችንና በአዕምሮአችን ውስጥ መቀበር ያለበት ነው፣ "ፍቅር ታጋሽ ነው፣ ፍቅር ደግ ነው። ፍቅር አይመቀኝም፣ ፍቅር አይተበይም፣ ፍቅር አይኰራም። ፍቅር ስርዓተ ቢስ አይደለም፣ ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ አይደለም፣ ፍቅር አይበሳጭም፣ ፍቅር ቢበደልም በደልን አይቆጥርም። ፍቅር ሁሉን ችሎ ይታገሳል። ፍቅር በሁሉም ላይ ተስፋ ያደርጋል! ፍቅር በሁሉ ነገር ይፀናል፣ ፍቅር ሁልጊዜ ይኖራል እንጂ አይጠፋም (1ቆሮ 13፥4-5፣ 7-8)።

ይህ ለሚፀና ፍቅር ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጉዞ ካርታ ነው። ይህንን የጉዞ ካርታ ብንጠቀምበት ጋብቻችን (እናም ሕይወታችን) ምንኛ ልዩ በሆነ ነበር!

ከዓመታት በፊት አንድ ሰው በስዊዘርላንድ የተሠራ የእጅ ሰዓት ሰጠኝ:: ለዓመታት በትክክል ይቆጥር የነበረው ይህ ሰዓት አንድ ቀን መሥራቱን አቆመ:: ወደ ሰዓት ጠጋኝ ወሰድኩት፣ ከመረመረው በኋላ ጠጋኙ ራሱን በመነቅነቅ፣ "አዝናለሁ ይሄን ሰዓት ወደ ፋብሪካው መልስህ ላከው ሊያስተካክለው የሚችለው እርሱ (የሰራው ሰው) ብቻ ነው" በማለት መለሰልኝ:: የጋብቻ ነገርም እንዲሁ ነው:: እግዚአብሔር ጋብቻን መሠረተ፣ ለኛም ሰጠን፤ በዚህ ምክንያት ለጋብቻችን ዋስትና መመሪያውን መከተል ተገቢ አይደለምን? ደግሞስ በጋብቻችን ችግር ሲፈጠር ወደርሱ መምጣት የለብንም? እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለውን እቅድ ችላ ብንል፣ ቤታችን (ትዳራችን) ሁልጊዜ በአደጋ ውስጥ ነው:: መልካም ሥርዓት ያለው ቤተሰብ የሚመሠረተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሰረት ባደረገ መልካም ጋብቻ ላይ ነው:: በመልካም ጋብቻ ውስጥ ሶስት ሰዎች እንዳሉ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ:: እነሱም ባል፣ ሚስት እና እግዚአብሔር ናቸው:: ጋብቻችሁን ከአሁን ሰዓት ጀምሮ ለክርስቶስ (ሕይወታችሁንም ጨምሮ) በማስረከብ ጀምሩ::

ጋብቻችሁን ለእግዚአብሔር ማስረከብ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ነገር፣ በጋብቻ ተጣምሮ ለመኖር የፈጸሙትን ቃለ መሐላ የምር ማድረግ ነው፤ ቃለ መሃላ የገባችሁት ለእርስ በርስ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርም ጭምር ነው:: ይህ መሃላ ለእርስ በርስ ፍጹም ታማኝ መሆንን ይጨምራል:: በጣም የሚያሳዝነው ግን በምንዝርነት ምክንያት ጋብቻ እንደፈረሰ የሚገልጽ ዳብዳቤ ሳይደርሰኝ ያሳለፍኩት አንድም ቀን አለመኖሩ ነው::

ማህበረሰባችን ታማኝ አለመሆንን እንደ ቀላል ነገር ይቆጥራል - እግዚአብሔር ግን እንዲህ አይመለከትም፣ ምክንያቱም እርሱ የሚያስከትለውን ሥቃይና ጥፋት ስለሚያውቅ ነው:: ከዐስርቱ ትዕዛዛት አንዱ በግልጽ የሚያውጀው "አታመንዝር" ብሎ ነው (ዘፀ 20፥14):: በብሉይ ኪዳን ዘመን በሞት ያስቀጡ ከነበሩት ከባድ ወንጀሎች አንዱ ዝሙት ነበር:: ቀላል ነገር አልነበረም:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮ የጎደለው ነው:: እንዲህም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል" (ምሳሌ 6፡32) ብሎ ያስጠነቅቃል:: ለትዳራችሁ የገባችሁትን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ እስኪያቅታችሁ ድረስ የሚያደርግ ፈተና ወደ እናንተ እስኪመጣና እስኪሚጥላችሁ ድረስ አትጠብቁት፤ ይህንን ጉዳይ አስቀድማችሁ ወስኑ፣ በፍጹም መሰጠት ራሳችሁን ለታማኝነት አሁኑኑ አስረክቡ::





ከዚያ በኋላ ሰይጣን በናንተ ላይ ምንም ዓይነት ድል የሚያገኝበትን ክፍተት ያጣል::

ጋብቻን ለእግዚአብሔር ማስረከብ ማለት በተጨማሪ ከክርስቶስ ጋር ባላችሁ ግንኙነት በአንድነት ማደግ ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ባልና ሚስት ለየብቻቸው በመሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ አይደለም፣ ነገር ግን የተጋባን ከሆንን እንደ ባለትዳሮች በመንፈሳዊ ሕይወታችን በአንድነት እንድናድግ ነው:: በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር ለመጓዝ ከመማር የበለጠ በፀና አንድነት የሚያስተሳስር ነገር የለም - ባንድ ላይ መጸለይ፣ ባንድ ላይ ቃሉን ማንበብ፣ ባንድ ላይ ወደ ቤተክርስቲያን መሔድ፣ አብሮ ሕብረት ማድረግ:: በየዕለቱ ባንድነት ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረብ መንፈሳዊ ልምምድ (ሥነ ሥርዓት) ለደስተኛ ቤተሰብ የሚያስፈልግ ወሳኝ ርምጃ ነው::

በወከበ በተሞላ የጊዜ ሰሌዳ እየኖርን ይህ ነገር ሁልጊዜ ቀላል አይደለም:: ሰይጣን ሁልጊዜ "ይህ መቅደም አለበት" ብለን የምንሠራውን አንድ ነገር ያቀርብልናል:: ከዚህ በፊት አብራችሁ የመጸለይ ልምድ ከሌላችሁ፣ ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ሁልጊዜ ጥቂት ጊዜ ስጡና እግዚአብሔር ትመገቡት ዘንድ ስለሰጣችሁ ምግብ አመስግኑት:: ይህ የጀመራችሁት ጸሎት እየተመቻችሁ ሲመጣ፣ ሌሎች ጉዳዮቻችሁን ጨምሩና መጸለያችሁን ቀጥሉ:: በጋብቻችን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ ልጆቻችን በኛ ጥገኝነት ሥር እያሉ፣ ምግብ ከተመገብን በኋላ በምግብ ጠረጴዛችን ዙሪያ የቤተሰብ ጸሎት ጊዜ ነበረን:: አሁን ግን እኔና ሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል እናነብና ከመተኛታችን በፊት አብረን እንጸልያለን:: ዋናው ቁልፍ ነገር፣ በጊዜ ሠሌዳችሁ የሚስማማችሁን (አመቺ) ጊዜ ማድረግና በዚያ ጊዜ በፀሎት መቆየት መቻል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ "ስለዚህ አሁን በምታደርጉት ዐይነት አንዱ ሌላውን በማነጽ እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ" (1ተሰ 5፥11) ይላል::

## ሁለተኛ ርምጃ፣ ለጋብቻ ቅድሚያ ስጡ

*ከመጀመሪያው ቀጥሎ ሁለተኛው ደረጃ ራስን ለጋብቻ መስጠት (መሰጠት) ነው::*

በዚህ ዘመን ሁሉ ነገር ትኩረታችንን ለመሳብ ይጮኻል፤ ሥራ፣ መዝናኛ፣ ቤተክርስቲያን፣ ልጆች፣ ቴሌቪዥን፣ ገንዘብ፣

ማህበራዊ ግጼታዎችና የመሳሳሉት ይጮኻሉ። የጮሂዎች ዝርዝር ማስቂያ የሌለው ነው። ካልተጠነቀቅንለት (ካልጠበቅነው)፣ ጋብቻችን በነዚህ ነገሮች ይታፈናል። በቀላሉ የትዳር ጓደኛችንን በመውሰድ ይጀምራል፣ ክዚያ ቀጣዩ ማለያየት ነው። ነገር ግን ይህ በፍጹም የእግዚአብሔር እቅድ አይደለም።

እግዚአብሔርን መውደዳችንን ከምናሳይበት መንገድ አንዱ ፍቅራችንን ለትዳር ጓደኛችን በማሳየት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደና ራሱን ስለ እርስዋ አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ" (ኤፌ 5፥25) ይላል። ክርስቶስ ራሱን መስዋዕት አድርጐ የሰጠው ለህዝቡ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው፤ ባልም ለሚስቱ ካለው ፍቅር የተነሳ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ሊሰጣት ይገባዋል። ክርስቶስ ጋብቻን ሲመራና በፍቅሩ ሲሞላው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ (እንዲስማሙ) እና ባሎች ራሳቸውን እንደሚወዱ ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ የሚለው መመሪያ ቀላል ይሆናል፤ ክርስቶስን በሕይወቱ የሚያስቀድም ባል፣ ሚስቱን ይወዳል፣ ያከብራልም፤ አምባገነን አይሆንም።

ራስን ለጋብቻ መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? ከሁሉም ነገር በፊት ለጋብቻ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው፣ ለደህንነቱ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው። ይህም ማለት ማንኛውንም ማድረግ የምትፈልጉትን ነገር ማደደዝ ያለባችሁ በጋብቻችሁ ላይ የሚያስከትለውን ፈይዳ በማሰብ ነው። ይህም ማለት ጋብቻችሁ እንደ ማንኛውም ክዕለት እንቅስቃሴአችሁ እንደ አንዱ የሚታይ ሳይሆን ለሁሉም ነገር ዋንኛና ማዕከላዊ ሆኖ ሊታይ ይገባዋል ማለት ነው። ጋብቻችሁ እንደ ኃላፊነት እንጂ ልክ እንደ ልዩ መብት የሚታይ አይደለም ማለት ነው።

ጋብቻችሁ ለእናንተ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ለማጠናከር ምን እያደረጋችሁለት ነው? ጋብቻችሁ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ እንደሆነ ለእናንተም እንዲሁ ነው? እነዚህ እናንተው ብቻ የምትመልሷቸው ናቸው - ነገር ግን ችላ አትበሏቸው። ለጋብቻችሁ፣ ልክ እግዚአብሔር እንዳደረገው፣ ቅድሚያ ስጡ።

## ሦስተኛው ርምጃ ፍቅር እና አክብሮት

*ጠንካራ ጋብቻን ለመገንባት ሶስተኛው ደረጃ እርስ በርስ በፍቅርና አክብሮት በመስጠት መመላለስ ነው።*





እነዚህ የተለያዩ ሐሳቦች ይመስላሉ፤ ነገር ግን እውን የተቆራኙ ናቸው። ፍቅር ያለ አክብሮት ማለት አንድን ሰው ልክ ለማዳ እንስሳን እንደምንደባብሰው መደባበስ እንደማለት ነው። በአብሮነታቸው ብንደሰትም፣ ራሳችንን ከፍ አርገን በበታችነት ስሜት በመመልከት ምንም አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉበት ጠቃሚ ነገር እንደሌላቸው መናቅ ማለት ነው። አክብሮት ያለ ፍቅር ወደ ቀዘቀዘና ስኬታማ ወዳልሆነ ግንኙነት ይመራል።

የጋራ (የሁለቱ ወገን) ፍቅርና በአክብሮት መሆን ሁለቱም ለጠንካራ ጋብቻ አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ስለዚህ ባል ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደድ፣ ሚስትም ባልዋን ታክብር" (ኤፌ 5፥33) ይላል። ሐዋርያው ጴጥሮስም፣ "እናንተም ባሎች ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፣ ከእናንተ ይልቅ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑና ከእናንተም ጋር የሕይወትን ጸጋ ስለሚወርሱ አክብሩአቸው፣ በዚህ ዓይነት ለፀሎታችሁ መሰናክል የሚሆን ነገር አይኖርም" (1ጴጥ 3፥7) በማለት ጽፏል። ወንዶችና ሴቶች የተለያዩ ናቸው - እግዚአብሔርም የሠራን በዚህ መንገድ ነው - ባሎችና ሚስቶች እነዚህን ልዩነቶች ማወቅና መቀበል አለባቸው (በውስጣቸው ያለው ደስታ እንኳን ይለያል)። ነገር ግን አንዱ ከሌላው የተሻለ ነው ማለት አይደለም። ሁለቱም ባልና ሚስት በእግዚአብሔር ዐይን እኩል ናቸው፤ ሁለቱም በእሱ አምሳል ስለተፈጠሩ፣ በአስተሳሰብ፣ በሕሊና በልዩ መብትና በኃላፊነት እኩል ናቸው። በጋብቻ ውስጥ ለምንም ዓይነት አድሎ ሥፍራ የለውም።

በጋብቻ ውስጥ ለትዳር ጓደኛችን አክብሮት ከምናሳይበት አንዱና አስፈላጊው መንገድ የግንኙነትን ጥበብ በመማር ነው። ይህ ዝም ብሎ ከማውራት በላይ የሆነ ነገር ነው፤ ሀሳብን እንዴት ማድመጥ እንዳለብን መማርን ይጨምራል ሀሳብን እርስ በርስ ለመከፋፈል ፈቃደኝነትን ማሳየት ማለት ነው፤ ይህም የትዳር ጓደኛዬ ያቃወመኛል ወይም ይስቅብኛል የሚል ፍርሃት ገኖ በመጣል የሚሆን ነው። እርስ በርስ በስሜታዊነትም ሆነ አስተውሎት ባለው ደረጃ በምናደርገው ነገር መቀባበል ማለት ነው። በአጠቃላይ ይህ ጉዳይ ለእኛ ለወንዶች ከሴቶች ይልቅ ከባድ ፈተና ይሆንብናል፤ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንክረን መሥራት ይጠበቅብናል። ባለቤቴ ሩት ሁልጊዜ ችግር እያጋጠማት ወደ እኔ በመጣች ጊዜ፣ እሷ በትክክል የፈለገችውና ያጋጠማት ችግር፣ የእኔም ድርሻና ትብብር

የምታስረክቡበት ጊዜው አሁን ነው:: እግዚአብሔር ከእናንተ የበለጠ ስለ እናንተ ጋብቻ ያገባዋል፤ ክርስቲያን ከሆናችሁ፤ እንድታገቡ ፈቃዱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ ሕይወትን በጋራ አብራችሁ የምትኖሩአቸውን የትዳር ጓደኞች እንደመረጠላችሁ እርግጠኛ ሁኑ:: ስወደፊቱ ጋብቻችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ትጠይቃላችሁ? ለዚህ እጅግ አስፈላጊ ለሆነ ነገር ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስረክባችኋል? ካላስረከባችሁ አሁኑኑ አድርጉ::

ትክክለኛ ካልሆነ ሰው ወይም ትክክለኛ ባልሆነ ምክንያት በፍቅር አትውደቁ:: ስለ አካላዊ አቋምና ቁንጅና ትኩረታችንን ስንሰጥና ሰንሳብ፣ ውስጣዊ የሆነ ማንነትን ችላ እንላለን፣ የትዳር ጓደኛን እውን ማራኪ የሚያደርጉትን ዘላቂ ብቃቶችን አናያቸውም:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ቁንጅና ከንቱ ነው፣ ውበትም ይጠፋል እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን ልትመሰገን ይገባታል" ይላል (ምሳ 31፥30):: መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ እንዲህ ይላል "ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና የወርቅ ጉትቻን በማንጠልጠል ወይም የከበረ ልብስ በመልበስ በውጭ የሆነ ጌጥ አይሁንላችሁ" (1ኛ ጴጥ 3፥3-4)::

ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ይሁን፣ ግባችሁ በሁሉም ነገር - ጋብቻችሁን ጨምሮ - እግዚአብሔርን ለማክበር ይሁን::





# ሃያ ሰባት

## የኃላፊነት ቅብብሎሽ

*ልጆች ከእግዚአብሔር የሚገኙ ስጦታዎች ናቸው እውነተኛ በረከት ናቸው::*

. (መዝ. 127፥3)

የቤተሰብ ኃላፊነት ወላጆች የሆንን ሁሉ የምንጋፈጠው፣ ከፍተኛና አስፈላጊ ግዴታችን ሲሆን ማናችንም ብንሆን በትክክል የማንወጣው ነው::

እንደገና በሕይወት አንድ ብዬ ለመኖር ብችል፣ ካለኝ ጊዜ ውስጥ አነስተኛውን ለጉዞ፣ አብዛኛውን ደግሞ በቤቴ ውስጥ ከሩትና ከልጆቻችን ጋር ለማሳለፍ አደርግ ነበር:: ጉዞ በወንጌላዊ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊው ክፍል ነው (ምንም እንኳ ዘመናዊ የመገናኛ ዜዴዎች ግንኙነትን ቀላል ያደረጉት ቢሆንም)፣ ነገር ግን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው ቁጥራቸው የበዛ ጉዞዎቼ በእርግጥ አስፈላጊዎቼ ነበሩ ወይ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ::

ከቤተሰቦቼ ለረጅም ጊዜያት መለየት ለነርሱም ለኔም በጣም አስቸጋሪ ነገር ነበር:: በየጊዜው ስልክ እየደወልኩላቸው ላገኛቸው የምሞክር ቢሆንም (ከአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች የሚቻል ባይሆንም) ይህ ሙከራዬ አብሮ መሆንን የሚተካ አልነበረም:: ልጆቻችን እያደጉ ሳሉ አብዛኛውን ጊዜ ከጐናቸው ለመሆን አልቻልኩም:: ለነርሱም ዋናው ደጡት ነገር ቢኖር አባታቸው በእጠገባቸው አለመሆኑ ነበር::

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች የሚመክሩት የልጅን ጠባይ በደንብ ለመቅረጽ የመጀመሪያዎቹ የስድስት ወይም የስምንት ዓመታት ወቅት የበለጠ አመቺ እንደሆነ ነው:: ጥናቱ ብዙም አያስደንቀኝም፤ ምክንያቱም ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልጅን

እንዴት መኖር እንደሚገባው ብታሳየው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ከዚያ ፈቀቅ አይልም" (ምሳሌ 22፥6) በማለት አስቀምጦልናል::

በአንድ የበጋ ወራት በአውሮፓ ውስጥ ወንጌልን እየሰበክሁ ሳለሁ አንድ ጓደኛዬ በደግነት ስዊዘርላንድ የሚገኘውን ቤቱን እንድጠቀምበት አዋሰኝ:: ቤተሰቤም መጣና ተገናኘን:: መኪና እየነዳሁ ወደ ግቢው ስገባ የደስ ደስ ያለው ድክድክ የሚል ልጅ አየሁ:: ትንሹ ልጃችን ኔድ ነበር:: ብዙ ጊዜ ተለይቼአቸው ነበረና ተለወጠብኝና ዘንግቼው ነበር፤ እርሱም አልለየኝም ነበር:: እኔም ሆንኩ እሱ መዘንጋታችን ልቤን በሰላት እንደተወጋሁ ያህል ተሰማኝ::

እምሰቱን ልጆቻችንን የማሳደግ አብዛኛው ኃላፊነት በባለቤቴ በሩት ትከሻ ላይ ወድቆ ነበር - እኔ በወንጌላዊነት እንደተጠራሁ እርሷም ይህንን ልጆችን የማሳደግ ጥሪ ተቀብላለች:: አብሬአቸው በምሆንበት ጊዜ በተለየኋቸው ጊዜ ያልሠራሁትን ለማካካስ ማንኛውንም ነገር ለመሥራት እጥራለሁ፣ ነገር ግን ለማካካስ የማልችለው ልጆቻችንን ሲያድጉና ሲለወጡ ማየት ስለማልችል በዚያ የሚገኘውን ደስታ ነው::

በነዚያ ዓመታት የጠበቃቸውንና መልካም ወንዶችና ሴቶች ሆነው እንዲያድጉ ያደረጋቸውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: በዚህ ዙሪያ ዋጋ የከፈለችው ሩት ስለሆነች ባለውለታ ነች - ከሁሉም በላይ ደግሞ ለጌታ ምስጋና ይገባዋል::

## ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው

ልጆቻችንን የእኛ ልጆች ብለን እንጠራቸዋለን፣ ነገር ግን በርግጥ የእኛ ልጆች እንዳልሆኑ ሁልጊዜ እናውቃለን:: የእግዚአብሔር ሥጦታ ናቸው፣ ከእኛ ወጥተው የራሳቸውን ቤተሰብ እስኪመሠርቱ ድረስ በአደራ የተሰጡን ናቸው::

ልጆች ካሏችሁ፣ እነሱ ከእግዚአብሔር የተሰጧችሁ ስለሆነ ከቶ ችላ አትበሏቸው:: ኤሳው ወንድሙን ያዕቆብን ከብዙ ዓመታት መለያየት በኋላ ሲያገኘው "እነዚህ አብረውህ ያሉት እነማን ናቸው? ብሎ ጠየቀው:: ያዕቆብም ሲመልስ፣ ጌታዬ ሆይ! እነዚህ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠኝ ልጆች ናቸው" (ዘፍ 33፥5) አለ:: ነቢዩ ኢሳያስ ከቤተሰቡ ጋር የኖረው እግዚአብሔርን እጅግ በረሰ





ሕዝብ መካከል ነበር፣ እሱም በድፍረት፣ "እነሆ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች" በማለት አሳወቀ (ኢሳ 8፥18)::

ልጆቻችን የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፣ እግዚአብሔር እንዴት እንዳሳደግናቸው አንድ ቀን ይጠይቀናል:: ለክርስቲያን፣ የቤተሰብ ሕይወት አይመለከተኝም የሚባል አይደለም፤ የደቀመዝሙርነት አስፈላጊ አካል ነው::

እግዚአብሔር ጋብቻን እንደሰጠን፣ ቤተሰብን ደግሞ ሰጥቶናል:: ቤተሰቦችን እኛ አንፈጥርም፤ ቤተሰቦች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው ዕቅድ አካል ናቸው:: የቤተሰብ ሕይወት በአዳምና በሔዋን ተጀመረ፤ የመጀመሪያ ልጃቸው ሲወለድ፣ ሔዋን በመደነቅ፣ "በእግዚአብሔር እርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ" አለች (ዘፍ 4፥1):: ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፣ በቤተሰብ ውስጥ ሆኖ በብስለት እንዲያድግና የምድራዊ ወላጆችን ፍቅርና ሥርዓትን እንዲለማመድ የአባቱ (የእግዚአብሔር) ፈቃድ ነበር:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በማስጠንቀቅ የሚናገሩት ቤተሰቦች ስለሚፈርሱበት ጊዜ ነው፣ "ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸውን የሚወድዱ ይሆናሉ . . . ተሳዳቢዎች፣ ለገንዘብ የሚስገበገቡ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ ወለታ ቢሶች፣ ሃይማኖተ ቢሶች፣ ፍቅር የሌላቸው ይሆናሉ" (2ጢሞ 3፥2-3):: ቤተሰብ ሲፈርስ፣ ማኅበረሰብ ይፈረካከሳል:: አሁን እየኖርንበት ያለው በእነኚያ ቀኖች ውስጥ ነውን?

## ቤተሰብ ለምን?

እግዚአብሔር ልጆችን ሰጥቶናል፣ ግን ለምን? ዋናው ምክንያት ቀላል ነው፣ ነገር ግን አንዳንዴ ከአይናችን ይሰወራል፤ *እግዚአብሔር ልጆችን የሰጠን አዋቂ ሰው ሊደርገን እንድናዘጋጃቸው ነው::* ከጨቅላነት አንስቶ አድገው በመጨረሻው ቤታችንን ለቀው እስኪሔዱ ድረስ፣ ልጆቻችን ነፃ ወደ መሆን ያድጋሉ - ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ነው:: ምንም ነገር ጣልቃ ካልገባ፣ ሕይወት ሙሉ ክብ ይሆናል፤ ያሳደግናቸው ልጆች እነሱ ደግሞ በተራቸው ወላጆች ይሆናሉ፤ እናም የኃላፊነት ዱላ ቅብብሎሽ ወደሚቀጥለው ትውልድ ያልፋል:: "ባዶ ጐጆ" ለወላጆች የሚያም ቢሆንም፣ አስፈላጊ ነገር ነው::

ልጆች በአካላቸው፣ በአስተሳሰባቸውና በስሜታቸው ጐልማሳ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግብረገባዊና መንፈሳዊ መሰረት ከሌላቸው፣ ዘላቂ መረጋጋት ምን እንደሆነ ከቶ ሊረዱ አይችሉም። ኢየሱስ እንዲህ ዓይነቱን ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ በሰራ ሰው አመሳስሏል፣ "ዝናብ ዘነበ፣ ጐርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ቤቱም ወዲያውኑ ወደቀ አወዳደቁም እጅግ የከፋ ሆነ" (ማቴ 7፥27)። ልጆቻችን ክፉውን ከደጉ ሳይለዩ ካደጉ . . . በሐቀኝነት ለመኖር ፍላጐት አይኖራቸውም . . . በእግዚአብሔር እምነት አይኖራቸውም . . . ነፍሳቸው ትደኸያለች፣ እንዲሁም በሕይወታቸው የሚበልጠውን ነገር ይዘነጋሉ። "ከዚህ በኋላ ሁሉን ነገር እንደ እውሎ ነፋስ ጠራርገው ይሄዳሉ፣ ለነዚህ አመፀኞች አምላካቸው ጉልበታቸው ነው" (ዕን 1፥11) እንደተባለላቸው ይሆናሉ።

ግብረገባዊና መንፈሳዊ ባህርይ ባንድ ጊዜ የሚገኝ አይደለም፤ እንዲያውም፣ ስሜታዊና አዕምሯዊ እድገት ሊወስድ ከሚገባው ጊዜ በላይ ሊቆይ የሚችል ነው። ልጆቻቸው ለራሳቸው ስለወደፊት ሕይወት ራሳቸው እንዲያቅዱ የሚተውአቸውና ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለግብረገብነት እንደማያስተምሩዋቸው አንዳንድ ወላጆች አልፎ አልፎ ይነግሩኛል። ይህ በጣም ያሳዝነኛል፣ የማዝነው ወላጆቹ ኃላፊነታቸውን በመተዋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ምክንያት ወደፊት በልጆቻቸው ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ስለማውቅ ነው። እነዚህ ልጆች ልክ እንደ ወላጆቻቸው ካለ ምንም ግብረገብና መንፈሳዊ መሰረት ያድጋሉ።

ይህ ማለት ግን በልጆቻችን ላይ ዝም ብለን የግብረገብነትና የመንፈሳዊነት መርሃ ግብር እንጭንባቸዋለን ማለት አይደለም፤ ኮምፒዩተር አይደሉም፤ የራሳቸው ፈቃድ አላቸው፣ ባደጉም ጊዜ፣ ያስተማርናቸውን ሳይቀበሉት ይችላሉ። ከሕይወት ምስጢራት አንዱ ነገር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ሁለት ልጆች አንዳንዴ የሚመርጡት የሕይወት አቅጣጫ እጅግ የተለያየ መሆኑ ነው፤ አንዱ ክርስቶስን ሲከተል ሌላው ዐመፀኛና የተናቀ ይሆናል። ይህ የሚሆን ነገር ነው።

ልጆቻችንን ልክ እኛ እንደምናደርገው ልናደርጋቸው አንችልም - ነገር ግን ለግብረገባዊና መንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚሆን ትክክለኛና ምቹ ሁኔታን ልናመቻችላቸው እንችላለን። ጥሩውና መጥፎው ምን እንደሆነ እናስተምራቸዋለን - ወይስ ህሳቡን ከሚያዩት ፊልም እንዲቀስሙ እንተዋቸዋለን? በእኛ





ሕይወት ውስጥ ክርስቶስን ያዩታል? መጽሐፍ ቅዱስ፣ "አንተ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ልታስተምራቸው፣ እንዲሁም እንዴት መኖርና ማድረግ እንደሚገባቸውም ልትገልጥላቸው ይገባል" ይላል (ዘፀ 18፥20)። በተጨማሪም፣ "ለልጆቻችሁም (የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት) አስተምሩአቸው፣ በቤት በምትቀመጡበት ጊዜ፣ ወይም ስትሄዱ፣ ዕረፍት በምታደርጉበትም ሆነ በምትሠሩበት ጊዜ ሁሉ ስለነርሱ ተነጋገሩ" (ዘዳ 11፥19) ይላል።

## ጥበበኛ ወላጅ መሆን

ልጆቻችንን ከማሳደግ በላይ አስፈላጊ የሚሆን ነገር እንደሌለ ሁሉ እንደማሳደግ ፈታኝ ነገርም የለም። እያንዳንዱ ልጅ ይለያል . . . እያንዳንዱ ቤተሰብ ይለያል . . . እንደዚሁም እያንዳንዱ ቀን ይለያል። እንዴት አድርገን ነው መልካም ወላጆች የምንሆነው? እኔንና ሩትን የረዱንን አራት መመሪያዎች ልግለጽላችሁ።

*አንደኛ፣ ቤተሰባችሁን ለእግዚአብሔር አስረክቡ (አደራ መስጠት)*። ቤተሰብን ማሳደግ እጅግ ከባድ ነው - እናም በጣም አስፈላጊም ነው - ለብቻችን ልንፈጽመው የምንደፍረውም አይደለም። የእግዚአብሔር ጥበብና እርዳታ በየቀኑ ያስፈልገናል። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ባለቤቴን ሩትን ልጆቻችንን እንዴት እንዳሳደገቻቸው ጠየቃት፣ እርሷም ያለምንም ማወላወል "በጉልበቴ በመንበርከኬ!" ብላ መለሰችለት።

ቤተሰባችሁን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት (ማስረከብ) ማለት ምን ማለት ነው? *ቤተሰባችሁ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመስርቶ እንዲኖር ማድረግ ማለት ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ ልጅን የማቅኛ ዝርዝር የእጅ መጽሐፍ አይደለም፤ በሚያስፈልገን በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባን በትክክል አይነግረንም። ነገር ግን ልጆቻችንን የምናሳድግበትን መመሪያ ይሰጠናል፣ ሆኖም ችላ እንላቸዋለን። ለምሳሌ በቆላ 3፥20 "ወላጆች ሆይ፣ ተስፋ እንዳይቆርጡ ልጆቻችሁን በቁጣ አታስመርሩአቸው" ይላል። ይህን መመሪያ እየተከተልን ነው?

*ሌላው ቤተሰብን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት (ማስረከብ) ማለት ልጆችን ስለ እግዚአብሔር ማንነት ማስተማር ማለት ነው።* ልጆቻችን ልጆች በነበሩ ጊዜ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በቋሚነት (በአብዛኛው በመኝታ ጊዜ) እናነብላቸው ነበር።

በተጨማሪም ከመመገባቸው በፊት በፀሎት እንመራቸው ነበር:: አድገው ትልልቅ በሆኑ ጊዜ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔር ስለሰጠን ማዕድ የማመስገን ተራ ተረክበዋል:: ከልጆቻችን ጋር አብረን መጸለያችንና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘናቸው መሔዳችን እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ሥፍራ እንዲያውቁት ረድቶአቸዋል:: ከሁሉም በላይ፣ ሳናሰልስ እየጸለይንላቸው ሕይወታቸውን ለጌታ ኢየሱስ እንዲሰጡ እናበረታታቸው ነበር:: ልጆች የሚማሩት ከምንነግራቸው ብቻ ሳይሆን ከተግባራችንም ጭምር መሆኑን አስተውሉ::

ባለቤቴ ሩትና እኔ ሁልጊዜ ከቁርስ በኋላ በመመገቢያችን ጠረጴዛ ዙሪያ የቤተሰብ የጸሎት ጊዜ ነበረን:: ሁልጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠር ያለ ክፍል አንብበን (አንዳንዴም እያንዳንዱ ልጅ አንድ ጥቅስ እንዲያነብ አድርገን) ከተማርን በኋላ የጸሎት ጊዜ ይኖረናል:: የቤተሰብ የጸሎት ጊዜን አስደሳች አድርጉት፤ ለአጭር ጊዜም ይሁን:: አንድ ጊዜ ቤተሰባችንን ሊጎበኝ የመጣ ካህን የጸሎት ጊዜአችንን እንዲመራልን እድሉን ሰጠሁትና የካህኑ ጸሎት በጣም ረዘመ:: ወዲያውኑ ልጆቻችን መቁነጥነጥና መተራመስ ጀመሩ:: በመጨረሻም ታናሹ ልጃችን በጩኸት፣ "አባባ ይሔ በጣም ረዥም ነው!" ብሎ አምባረቀ::

## ጊዜ መስጠት

*ሁለተኛው መመሪያ ለቤተሰባችሁ ቅድሚያ መስጠት ነው::* አንዳንድ ወላጆች ይህን ማድረግ ያቅታቸዋል፤ ምክንያቱም ከቤተሰባቸው ይልቅ ለሥራቸውና ለማህበራዊ ኑሮአቸው ቅድሚያ ስለሚሰጡ ነው:: አንድ ጊዜ አንድ ባተሌ አባት "የሚፈልጉትን ሁሉ አደርግላቸዋለሁ፣ ኣላደርግም እንዴ?" ብሎኛል:: አባትነቱ የበለጠ የሚለማቸው በሚገዛላቸው ምርጥ አሻንጉሊት ሳይሆን አብሯቸው በመሆን የሚያሳልፈው ጊዜ ነው:: ልጆቻችን ልዩ እንደሆኑ እየተሰማቸው ማደግ ይኖርባቸዋል፣ ባተሌ ሆነን ለእነሱ ጊዜ የሌለን ከሆነ ግን ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም:: አንዳንድ ጊዜ ቆም ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል፣ "ልጆቼ የልጅነት ዘመናቸውን ማስታወስ ያለባቸው በምን ዓይነት መልኩ ነው? የልጅነት ጊዜ ትዝታቸው የሳቅና የደስታ ይሆንላቸው ይሆን? ወይስ በቂ ጊዜ ስላልሰጧቸው በቅሬታ ያዩኝ ይሆን? "





ልጆቻችን ከሌሎችም ማለትም በዝሪያ ከተያያዘው የቤተሰብ አካላት ብዙ ሊማሩ ይችላሉ:: ልጆቻችን ከተጠቀሙአቸው ትላልቅ ጥቅሞች አንዱ ከአያቶቻቸው በተለይ በአቅራቢያችን ይኖሩ ከነበሩት ከሩት ቤተሰቦች ጋር አብረው ያሳለፉት ጊዜ ነው:: አብዛኛው የደስታና የፈንጠዝያ ዘመን ትውስታቸው ከእነዚህ አያቶቻቸው ጋር ባሳለፉት ጊዜ ላይ የተመሰረተ ነው::

ብዙ ቤተሰቦች በችግር ውስጥ የሆኑበት አንዱ ምክንያት ቀደም ሲል የወላጆቹ ወላጆች (አያቶች) የፈፀሙትን ስህተት የአሁኖቹ ወላጆች በተራቸው በመድገማቸው ነው:: ነገር ግን እንዲህ መሆን አይገባውም:: ባንድ በሚነቀፍ ቤተሰብ ውስጥ ያደገና በየዘመዱ ቤት እየተንከራተተ የኖረ አንድ የማውቀው ሰው ነበር:: ይህ ሰው በጣም በሚጠነቀቅለት ባንድ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ በኩል ጌታን አገኘ:: በመጨረሻም ቤተሰብ መስርቶ ወላጅ ሲሆን፣ ከወላጆቹ በተሻለ ሁኔታ ቤተሰቡን ለማስተዳደር ቆርጦ ተነሳ፣ አደረገም:: እንዲህም አለኝ፣ "የቤተሰብህን ዓይነት መርጠህ መውሰድ አትችልም፣ ነገር ግን ለልጆችህ ምን ዓይነት ቤተሰብ መመሥረት እንዳሰብህ ልትመርጥላቸው ትችላለህ::" ብዙ ወላጆች የዚህ ሰው ዓይነት ጥበብ ቢሰጣቸው ምኞቴ ነው::

## በፍቅር መተሳሰር

*ሶስተኛው መመሪያ ይህ ነው፤ የቤተሰባችሁ ማዕከል ፍቅር ይሁን። ልጆቻችሁን ውደዱ፣ እንደምትወዷቸውም እንዲያውቁ አድርጉ:: እግዚአብሔር ይወዳቸዋል፣ እናንተም እንዲሁ አድርጉ* መፈቀርን የሚለማመዱ ልጆች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ለማመን ይቀላቸዋል::

ደግሞም አበረታቷቸው:: ባለቤቴ ሩት በግሏ በምታሳትመው የልጆች መጽሔት (ሀሳቦቿንና ጸሎቶቿን በምትጽፍበት ማለት ነው) ላይ አንድ ጊዜ፣ "የተከበርክ መጽሔት፣ እያንዳንዱን ልጅ የሚያበረታታ አንዳች ቃል ሳትናገር አንዲት ነጠላ ቀን እንኳን አትለፍ . . . 'ብዙ ሰዎች ከማንኛውም ምክንያት የበለጠ በማበረታታት ጉድለት የተነሣ ይወድቃሉና' በማለት አንዱ ጽፎልናል" በማለት ትፅፍ እንደነበር ትዝ ይለኛል::

ፍቅር ማለት ልጆች የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ መስጠት ማለት አይደለም:: ፍቅር ማለት አንዳንድ ጊዜ "አይደለም" ወይም

# ሃያ ስምንት

## ተፅዕኖ ማምጣት

*እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ::*

(ማቴ. 5÷14፤16)

እግዚአብሔር ልክ ሕይወታችንን ለክርስቶስ በሰጠንበት ቅጽበት ለምን ወደ መንግስተ ሰማያት አይወስደንም?

ከሁሉም በላይ፣ መንግስተ ሰማይ የመጨረሻው መኖሪያችን እስከሆነ ድረስ፣ እግዚአብሔር ወደዛው ቢወስደንና ከችግርና ከመከራ ወዲያውኑ ቢገላግለን የተሻለ አልነበረምን? ከዚያም ጭንቀት ወይም ኀዘን ወይም ሥቃይ አያገኘንም ነበር፣ ከመከራ ሸክሞቻችንና ፈተናዎቻችን በተወገዱልን ነበር:: *ሕይወታችንን ለክርስቶስ ባስረከብንበት ቅጽበት እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ያልወሰደን ግን ለምንድነው?*

ምክንያቱ ቀላል ነው፤ *እግዚአብሔር እዚህ ለኛ ሥራ አለው፡፡* መንግሥተ ሰማይ ግባችን ነው፤ እስከዚያ እስከ መጨረሻው ጊዜ እርሱ ወዳሰበት እስኪወስደን፣ እግዚአብሔር እዚህ የሚያቆየን በዓላማ ነው:: ምድር፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመግባት በፊት፣ ልክ እንደ መጠባበቂያ (መቆያ) ክፍል አይደለችም፣ ያለምንም ሥራ ተቀምጠን የመጨረሻው የመሔጃችን ሰዓት እስኪመጣ እጃችንን አጣጥፈን የምንቆይባት አይደለችም:: ምድር፣ የዘመናት ቲያትር (ታሪክ) የሚተውንባት መድረክ ናት:: ትዕይንቱ ክርስቶስ በኃጢአትና በሞት፣ በሰይጣንና በሲዖል ላይ ድልን የተቀዳጀበት ታሪክ ነው:: ማን የመሆናችን ጉዳይ ሳይሆን መለኮታዊ ድራማውን ለመጫወት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ልዩ ተግባር ያለን ነን::





### መለኮታዊ ዓላማ

እግዚአብሔር ለኛ የሰጠን ልዩ ተግባር ምንድን ነው? እዚህ ምድር የሚያቆየን ስምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ መልስ አለው፤ *በምድር ላይ እስካለን ድረስ፣ እግዚአብሔር ለኛ ያለው ዓላማ፣ ምንም ዓይነት ይሁን ምን በኑሮአችን ለርሱ ክብርና ምስጋና እንድንሰጠው (እንድናመጣለት) ነው::* መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ እግዚአብሔር፣ "ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን . . . ይህም የሆነው በመጀመሪያ በክርስቶስ ተስፋ ባደረግነው በእኛ ምክንያት ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና እንዲሆን ነው" (ኤፌ 1÷4፤12):: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ "ብዙ ፍሬ ስታፈሩ አባቴ ይከበራል፣ በዚህ ዓይነት የኔ ደቀመዛሙርት መሆናችሁን ታስረዳላችሁ" (ዮሐ 15÷8) አላቸው:: ግባችሁ፣ በምታደርጉት ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ነው?

ነገር ግን ይህ ብቻ ለመሠረታዊ ጥያቄአችን ሙሉ መልስ ሊሆን አይችልም:: እግዚአብሔር እዚህ እንድንቆይ ያደረገበት ምክንያት ምንድነው?

ይህን ጥያቄ ስመመለስ፣ እግዚአብሔር ራሳችንን ለክርስቶስ እንደሰጠን ወዲያውኑ ወደ መንግሥተ ሰማይ ቢወስደን ይህች ምድር ምን ልትመስል እንደምትችል ገምቱ:: የክርስቶስን የማዳን ኃይል ርኅራኄውንና ጽድቁን የሚናገር ባይኖር ኖሮ፣ (ያመኑት ያለ ቀሪ የሚሄዱ ቢሆን ኖሮ)፣ ይህች ዓለም ምን ዓይነት ትሆን ነበር? የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገልጽ ማንም በሌለበት፣ ስለክርስቶስ እንዴት አድርገው ሊሰሙ ወይም እምነታቸውን በርሱ ላይ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር? መልሱ ግልጽ ነው፤ ዓለማችን ዘላቂ በሆነ መንፈሳዊ ጨለማ፣ ለዘላለም በፍርሃት፣ በተስፋ ቢስነትና በክፋት ውስጥ እንድትኖር የተረገመች በሆነች ነበር::

ታዲያ እግዚአብሔር እዚህ የሚያቆየን ለምንድነው? የሚያቆይበት ምክንያት አለው፤ *ለዓለም የምሥራቹን ቃል እንድንናገር ያቆየናል:: የምሥራቹ ቃል የክርስቶስ ነው::* መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ህዝብ ናችሁ" (1ኛ ጴጥ 2፥9):: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ

የሰጠው ትዕዛዝ ከቶ አልተሻረም፤ "ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱና ለሰው ሁሉ ወንጌልን አስተምሩ" (ማር 16፥15)::

ይህ ማለት ሁላችንም ሰባኪዎች ወይም የወንጌል መልዕክተኞች ወይም ሚስዮናውያን እንሆናለን ማለት ነው? አይደለም - ለጥቂቶች ግን ነው:: ነገር ግን ሁላችንም የክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን ተጠርተናል፣ የርሱን ፍቅርና የሚለውጥ ኃይሉን ወደ ፈራረሰውና ወደ ተመሠቃቀለው ዓለም ልናመጣ ነው የተቀመጥነው::

## የአንድ ሰው ተፅዕኖ

"ዐመፅ በቸርነት ላይ" የሚል ታሪክ ለዘመናት አንባቢዎችንና ፊልም አፍቃሪዎችን ያስደነቀ ታሪክ ነበር:: ከዚያ በኋላ የሆነው ግን ከአስገራሚነቱ አልፎ በታዋቂነት ተርታ አልተፈረጀም::

ባንዳንድ ምክንያቶች አሁንም አከራካሪ የሆነ ሁኔታ በ1789 ተፈጽሞ ነበር፣ መርከብ ሠራተኞች የመርከቡ ካፒቴን ባሳየው የጭካኔ ተግባሩ ምክንያት ዐመፁበት:: ዊሊያም ብሊፍ የተባለው ይህ ካፒቴን ከዐመፁ ለማምለጥ ከጥቂት ሰዎች ጋር ሆኖ መርከቡን ጥሎ በጀልባ ሸሸ:: አማጺያኑ ግን በመርከቢቱ ላይ ቀሩ፣ በመጨረሻም ማንም የማይኖርባትና የተነጠለች፣ በሰላማዊ (ፖስፊክ) ውቅያኖስ በደቡባዊ ክፍል የምትገኝ፣ "ፒትካይርን ደሴት" አግኝተው ደረቅ መሬት ላይ ወረዱ:: ቁጥራቸው ሃያ አምስት ነበር፣ ከነርሱም ዘጠኙ እንግሊዛውያን መርከበኞች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስድስት ወንዶችና አሥር ሴቶች የታሂቲ ዜጎች ነበሩ:: ከመርከቧ ከወረዱ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ መርከቧን ፈጽመው አቃጠሏት፣ ከዚያም በደሴቲቱ ላይ በቋሚነት ሠፈሩ::

ነገር ግን ይህ ሙከራቸው ብዙም ሳይቆይ ትልቅ አደጋ ገጠመው:: አስቸጋሪ በሆኑ እንግሊዛውያን መርከበኞች እና በታሂታውያን መካከል ከፍተኛ ግጭት ተፈጠረ፣ አለመግባባታቸውም ተካሮ ወደ መገዳደል መራቸው:: አንዱ እንግሊዛዊ መርከበኛ ደግሞ ከዕፅዋት ጨምቆ የአልኮል መጠጥ ማዘጋጀት ጀምሮ "ሞቃታማ ገነት ናት" ያሏትን ደሴታቸውን የሰካሮች፣ የብልሹ ምግባርና የወራዳነት ሠፈር አደረገው:: ከአምስት የማይበልጡ ታሂቲዎችና አንድ እንግሊዛዊ መርከበኛ "ጆን አዳምስ" የተባለ ብቻ ተረፉ::





አንድ ቀን ጆን አዳምስ መርከቧን ሲያቃጥሏት ሳይቃጠል የተረፈና በመርከቧ ውስጥ ያገኘውን፣ ግን ለብዙ ጊዜ ረስቶት የነበረውን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንስቶ ማንበብ ጀመረ:: እግዚአብሔርም ቃሉን በመጠቀም ጆን አዳምስ ኃጢአተኛ እንደሆነ በማመን ንስሃ እንዲገባና በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምን መራው:: የጆን አዳምስ ሕይወት በአስደናቂ ሁኔታ ተለወጠ፣ ከዚያም ምንም ያህል ሳይቆይ ለስደተኛ ጓደኞቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያካፍላቸው ጀመር:: የተለወጠው የጆን አዳምስ ሕይወትና ያካፈላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት እነሱንም ለወጣቸው:: በ1808 ወደዚች እነጆን አዳምስ ወደሚኖሩባት ፒትካይርን ደሴት በመምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ የጎበኙት አሜሪካውያን መርከበኞች ነበሩ:: ጎብኚዎቹ ያገኙት ማኅበረሰብ እጅግ የበለፀገና ፍጹም ተስማምቶ የሚኖር፣ ወንጀል የሌለበት፣ እስር ቤት የሌለበት፣ የአልኮል መጠጥ የሌለበትና የሥነ ምግባር ጉድለት የማይታይበት ማህበረሰብ ነበር:: እግዚአብሔር የአንድን ሰው ምስክርነት ተጠቀመ፤ ግዛቱን በሙሉ ለመለወጥ የጆን አዳምስን ተፅዕኖ ተጠቀመ::

## ሁሉም ከእንቅብ በታች ናቸው

የጆን አዳምስን ሕይወት ያለው ምስክርነት ተላላፊ ነበረ፣ ከዚህ በጣም በተቃረነ መልኩ አንዲት ሴት የጻፈችልኝ ደብዳቤ እንዲህ የሚል ሀሳብ ነበረው:: ባለቤቷና እርስዋ ሃይማኖት የለሾችና "ወደ ቤተክርስቲያን በጭራሽ ሔደን አናውቅም፣ ምክንያቱም አብዛኞቹ ዘመዶቻችን ክርስቲያን እንደሆኑ ይነግሩናል፣ እንዲህ ነን እያሉ ግን ጋብዘውን አያውቁም ወይም የልደት ካርድ አይልኩልንም ወይም እንዲያውም ታምሜ በሆስፒታል ተኝቼ ሳለሁ እንኳን አልጎበኙኝም:: ይህን ለምን እንደሚያደርጉብን አንደኛዋ ዘመዴ ክርስቲያኖች ስላልሆንን እንደሆነ ነግራኛለች:: የክርስቲያኖች ተግባር ይህ ከሆነ፣ ከነርሱ ጋር ምንም ነገር ለማድረግ አልፈልግም" ይላል::

ወደ ክርስቶስ እንድትመለከት አጥብቄ አስገነዘብኳት፣ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ፍጹም ስለሆነና እርሱ ብቻ ከቶ የማያስቀይመን ስለሆነ ነው:: የሴትየዋ ደብዳቤ ግን አቀዝቅዞኛል፣ በተሰማት ጉዳይ ስለ ወሰነችው ውሳኔ ልጠቅሳት አልቻልኩም:: ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ የክርስቶስ ተከታይ ነን የሚሉ ሳይወዷት እንዴት ክርስቶስ ይወደኛል ብላ ልታምን ትችላለች? እነዚያ ዘመዶቿ እውን ክርስቲያኖች መሆናቸውን አላውቅም፤ ከሆኑ ግን እግዚአብሔር ለምን በዚህ ምድር እንዳስቀመጣቸው ፈጽሞ አልተረዱም::

መልክ ነው። እኛም ማድረግ የሚኖርብን እንዲሁ ነው። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "አንድ ጊዜ ክርስቶስ ለሁሉም መሞቱንና ሁሉም የእርሱ ሞት ተካፋዮች መሆናቸውን ስለተረዳን የክርስቶስ ፍቅር ለሥራ ይገፋፋናል . . . በሕይወት ያሉ ሁሉ ለነርሱ ለሞተውና ከሞትም ለተነሣው እንዲኖሩ እንጂ ከንግዲህ ወዲህ ለራሳቸው ሲሉ እንዳይኖሩ ክርስቶስ ለሁሉም ሞተ። ስለዚህ ካሁን ጀምሮ ማንንም ቢሆን በሥጋዊ አመለካከት ከንግዲህ አናይም፤ ከዚህ በፊት ክርስቶስን ያየነው በሥጋዊ አመለካከት ቢሆንም ከንግዲህ ወዲህ የምንመለከተው በዚህ ዓይነት አይደለም" (2ኛ ቆሮ 5፥14-16)።

ጳውሎስ ሁል ጊዜ በእንዲህ ዓይነት መንገድ አያስብም፤ አንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን ስለጠላ ለትንሽ ጥቅም ብዙ ይሮጥ ነበር። እግዚአብሔር ግን ልቡን ለወጠለትና ክርስቶስን ያላወቀ ሁሉ ያውቀት ዘንድ ሸክም ተቀበለ። የእግዚአብሔር ፍቅር መንፈሱን ሞላው፤ እግዚአብሔር ሰዎችን በሚያይበት መንገድ አየ፤ በሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳረፈ ተመለከተ። እርሱም አፈቀረ። ይህ በእናንተም ሕይወት እንዲሆንላችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

## የምሥራቹን ቃል መኖር

*ለክርስቶስ ተፅዕኖ ለማምጣት ሁለተኛው አስፈላጊ ነገር፣ በምንኖረው ሕይወት ወይም በምንኖርበት ሁኔታ ሁሉ የክርስቶስን ፍቅር ማሳየት ነው።*

የብዙዎቹ የጥንት ክርስቲያኖች ትልቁ ችግር ከማያምኑ ጋር ጋብቻ መፈፀማቸው ነበር። ከማያምኑ ጋር እንዴት ሊግባቡ ይችላሉ? ይልቁንም ከመጨቃጨቅ፣ በሚኖሩት ኑሮ ምሳሌ በመሆን ለማግባባትና ለማሸነፍ እንዲነሳሱ ሐዋርያ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጽፎላቸዋል፣ "እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ሆይ፣ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፣ በዚህ ዓይነት ገና በእግዚአብሔር ቃል የማያምኑ ባሎች ቢኖሩም በቃል ምስክርነት ብቻ ሳይሆን በሚስቶቻቸው የሕይወት ምስክርነት ሊመለሱ ይችላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ንፁህ የሆነውንና ሰው አክባሪ ሕይወታችሁን ሲመለከቱ ነው" (1ጴጥ 3፥1-2)። ሕይወታቸው የትዳር ጓደኞቻቸውን ወደ ክርስቶስ ሊያመለክት የሚችል ምስክርነት የሌለው ስብከት ነበር። በኛም ግንኙነት ተመሳሳይ መርህ ተግባራዊ ሊሆን ይገባዋል።





ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የርሱን ፍቅር ብዙ ግልጽ በሆኑ መንገዶች እንድናሳይ ይፈልጋል። በማንኛውም ጊዜ ኃጢአት ለጥፋት በቁጭት ሲወጣ፣ የሚለውጠውን የክርስቶስን ፍቅር ተግባራዊ ለማድረግ መለፈግ አለብን። ይህንን ዓለም ከቶ እንከንየለሽ ሥፍራ ልናደረገው አንችልም፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ክርስቶስ በክብርና በግርማ ተመልሶ ሲመጣ ብቻ ነው። እኛ ግን የተሻለ ስፍራ ልናደርገው ተጠርተናል፣ ጥሪአችን የሰዎችን ሥቃይ ለመቀነስ የቻልነውን ሁሉ በማድረግና ሰብአዊ በደሎችን በመዋጋት እንድንሠራ ነው። ከቁጥጥራቸው ውጭ በሆነ መንገድ የተቸገሩትን፣ የደኸዩትን፣ በበሽታ፣ በመንይምነት፣ በድርቅና በርሃብ፣ በአየር ንብረት መዛባት፣ በዘረኝነት፣ በሁከትና በጦርነት የተጐዱትን ሕዝቦች ሸክም ለመሸከም ከሰዎች ሁሉ ይልቅ፣ ክርስቲያኖች ኃላፊነት አለባቸው። ምናልባት እግዚአብሔር እነዚህን ችግሮች ለብቻችሁ ወይም ብዙ ሆናችሁ እንድትዋጉ ሊጠራችሁ ይችላል። ችግራቸውን ለመቀነስ እየሠሩ ያሉትን በክርስቶስ ስም ቢያንስ በጸሎታችሁና በገንዘባችሁ ልትደግፉአቸው ይገባል። ይህንን ካደረጋችሁ የክርስቶስን ርኅራኄ ለሌሎች ታሳያላችሁ፣ እንዲሁም ለወንጌል በር ታስከፍታላችሁ። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ በእውነት እላችኋለሁ፣ "የኔ ደቀመዝሙር በመሆኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውኃ እንኳ የሚሰጥ እውን ዋጋውን አያጣም" (ማቴ 10፥42)።

በምትኖሩት ሕይወት ሌሎች ክርስቶስን ያዩታል? አንዲት ሴት፣ "ጓደኛዬ ክርስቲያን ነኝ ትላለች፣ ግን ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው የባሰባት አሉባልተኛና ሐሜተኛ ናት። ክርስቲያኖች የሚያደርጉት እንዲህ ነው?" በማለት በመጠየቅ ጽፋልኛለች። ሌላው ሰው ደግሞ "የእህቴ ልጅ ክርስቲያን ነኝ ይለኛል፣ ነገር ግን ሁልጊዜ በሰዎች ላይ የሚያማርርና ስህተት የሚፈልግ ነው። ይህ ስህተት አይደለምን?" ብሎኛል። ሰዎች የሠራነውን ስህተት ነቅሰው ለማውጣት ፈጣን ናቸው - በዚህም ምክንያት ክርስቶስን ለመተው ሰበብ ያደርጋሉ፣ ወደኋላም ይመለሳሉ። አንድ እውነት የሆነ ጥንታዊ አባባል አለ፣ "ከምንለው ይልቅ የሆንነው የበለጠ ይናገራል።"

በኀ ምላሽ ሲሰጡ ሌሎች ለምን እምቢ እንዳሉ የምናውቀው እዚያ ነው። ግን አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ፀሎት በወንጌል አገልግሎት ውስጥ እጅግ ወሳኝ ድርሻ አለው፣ የወንጌል አገልግሎት አካልም ነው። አንዳንድ ጊዜ ለወንጌላዊነት አገልግሎት (ተልዕኮ) ዝግጅት የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ቅድመ ተከተሎችን እንድመዘግብላቸው ለሚጠይቁኝ ምላሼ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነው፤ "ጸሎት . . . ጸሎት እናም ብዙ ፀሎት ነው" እላቸዋለሁ። ሐዋርያ ጳውሎስ በቆላስይስ ለነበሩ ክርስቲያኖች፣ "እግዚአብሔር ለምሥራቹ ቃል በር እንዲከፍትልንና በእርሱ ምክንያት እኔ ታሥሬ የምገኝበትን የክርስቶስን ምስጢር ማብሰር እንድንችል ለኛም ፀልዩ" (ቆላ 4፥3) በማለት በጥብቅ አስገንዝቦአቸዋል።

በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋል። ለቤተሰባችሁ፣ ለጐረቤቶቻችሁ፣ አብረዋችሁ ለሚሠሩ፣ አብረዋችሁ ለሚማሩ ልትፀልዩላቸው ይገባል። ትፀልያላችሁ? እውነትን ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር የልባቸውን በር እንዲከፍትላቸው እግዚአብሔርን ትለምኑታላችሁ? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድትነግሩአቸው እግዚአብሔር እናንተን እንዲጠቀማችሁ ትጠይቁታላችሁ? በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር ከዓለም ዙሪያ ወደራሱ ለሚጠራቸው ሰዎች ልንፀልይላቸው ይገባናል። እግዚአብሔር ለተወሰኑ ሚሲዮናውያን ወይም ለአንድ አገር ወይም ጐሣ እንድትፀልዩ ሊያደርጋችሁ ይችላል። በዚህ በምድር ሕይወት እያላችሁ የምትፀልዩላቸውን በአካል ላትገናኙ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን የናንተ ጸሎት እነርሱን ወደ ዘላለም ድነት ለማምጣት ድርሻ እንደነበረው በመንግሥተ ሰማይ ትረዳላችሁ።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማደናቀፍ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ መንገድ፣ እኛ ለክርስቶስ ተዕዕኖ እንድናመጣ እግዚአብሔር እኛን ለመጠቀም እንደማይችል በማሳመን ነው። ይህ ግን እውነት አይደለም። ማንም በዙሪያችሁ ወዳሉ ሰዎች ሁሉ በወንጌል ሊደርስላቸው አይችልም። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10፥2 ያለው የኢየሱስ ቃል አሁንም እውነት ነው፤ "እንዲህም አላቸው፡ እነሆ መከሩ ብዙ ነው፣ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህ የመከሩ ጌታ ለመከሩ ሥራ ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት።" በናንተ እንዲጀምር ጠይቁት።





# ሃያ ዘጠኝ

## ሕይወት በየደረጃው

*እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፥ እስከሽበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ፣ እኔ ሠርቻለሁ፣ እኔም እነሣለሁ፣ እኔ እሸከማለሁ እኔም አድናለሁ።*

(ኢሳ 46፥4)

አንድን ውድድር እንዴት እንደምትጀምሩ ብቻ ሳይሆን፣ እንዴት እንደምትፈጽሙትም አስፈላጊነቱ እኩል ነው። የክርስትና ሕይወትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው።

አንድ ፕሮጀክት (ውጥን) ጀምራችሁ ሳትጨርሱት ትታችሁ ታውቃላችሁ? ብዙዎቻችን አድርገን እናውቃለን። የነበራችሁ ጉጉት ከጊዜ በኋላ ቀዝቅዞ ወይም ሰልችቶአችሁ ወይም ውጥኑ ከብዶአችሁ፣ በመጨረሻ ወደ ሌላ ነገር ሄዳችሁ ይሆናል።

የሕይወት ጉዞ ግን እንደዚህ አይደለም፤ ጉዞውን የምናቆምበትና ወደሌላ ሁኔታ የምንሄድበት አማራጭ የለም። የመፈፀም ወይም ያለመፈፀም ብሎ የምርጫ ነገር የለም። ጉዞው እስከኖርን ድረስ ይቀጥላል። ብቸኛው ጥያቄ ግን እንዴት አድርገን እንጨርሳለን ነው።

### ቁልቁል መውረድ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ በጣም አሳዛኝ ታሪኮች አንዱ፣ የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው የሳኦል ታሪክ ነው። ሳኦል የተመረጠና ተሰጥኦ ያለው ሰው ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ "ከርሱ ይልቅ መልካም ሰው አልነበረም" ይላል (1ሳሙ 9፥2)። የንግሥና ዘውድ ከጫነ በኋላ አንድ መሪ እንዲኖረው የሚፈለገውን ብቃት ሁሉ አሳየ፤ ትህትና፣ ጀግንነት፣ ግርማ ሞገስ፣ መልካም ባሕርይ፣ የማስተዳደር ብቃት መለያዎቹ ነበሩ። የእሥራኤል ከተማ እንደ ተከበበ መልዕክት በመጣ ጊዜ፣ "በሳኦል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደ (1ሳሙ 11፥6)፣ ሕዝቡ ሁሉ በዙሪያው ተሰበሰበ"

ሌሎች ደግሞ ያለጠባቂና ተንከባካቢ የቀሩ፣ የማይጠቅሙ እንደሆኑ ይሰማቸዋል ወይም ሰልቹ ይሆናሉ ወይም ድብርት ውስጥ ይገባሉ። እነዚህ ሁሉ ምላሾች በመንፈሳዊ ረገድ እኛን አደጋ ውስጥ ሊከቱን የሚችሉ ናቸው።

ለመሆኑ በዚህ የለውጥ ወቅት ምን ዓይነት አደጋዎች ናቸው ሊያሠጉን የሚችሉት? አንደኛው የጋብቻ አለመስማማት ነው። አንዲት ሴት በጻፈችልኝ ደብዳቤ "ለልጆቻችን ስንል አብረን ቆየን፣ አሁን ልጆቹ ሄደዋልና ከዚህ በኋላ አብረን ለመሆን የምንችልበት ምንም ምክንያት አይታየኝም" ብላለች። አንድ አባወራ ደግሞ "ልጆቻችን ከሄዱ ጀምሮ አንድ የሚያደርገን የጋራ የሆነ ነገር የለንም" በማለት ጽፎልኛል።

ችግሩን የሚያባብሰው ተጨማሪ ነገር ደግሞ የጉልማሳነት ዕድሜ፣ ልክ እንደማይፈለግ ባዶ ጐጆ ተደርጐ የሚታሰብ መሆኑ ነው። ሁሉም ሰው በዚህ "በዕድሜ ጠና የማለት ጠንቅ" ተብሎ በሚጠራው ችግር ውስጥ ያልፋል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የሚደርሱኝ ደብዳቤዎች በዚህ ችግር ውስጥ አያሌ ሰዎች መኖራቸውን ያረጋግጡልኛል። አንዲት ልቧ በዚህ ዓይነት ችግር የተሰበረ ሴት "ባሌ ጠባዩ ተለውጦብኛል፣ አሁን ልጁ ልትሆን ወደምትችል ወጣት ሴት ዘንድ ገብቷል፣ ከኔ ጋር ሲፋታ ይፈልጋል" በማለት ጽፋልኛለች። ሌላዋ ሴት ደግሞ "ባሌ በሥራው በጣም የተወጠረ ነው። ለኔ ምንም ትኩረት አይሰጥም። እኔ አሁን ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ጀምሬአለሁ። ምናልባት ይህንን እንደ ስህተት ልትቆጥር ትችላለህ፣ ነገር ግን እኔ ለመደሰት መብት የለኝም?" በማለት ጽፋልኛለች። እንደነዚህ ዓይነት ደብዳቤዎች ያሳስቡኛል፣ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት መንገዶች ደስታን ሊያመጡ በፍፁም የማይችሉና ደህንነት የሌላቸው መሆኑን አውቃለሁ።

የኋለኛው ደብዳቤ የሚጠቁመው ብዙውን ጊዜ በዚህ የሕይወት ደረጃ ወቅት ከበስተጀርባ እያደባ የሚመጣ ሌላ አደጋ መኖሩን ነው፤ *በሌሎች ነገሮች መጠመድ ነው። ጊዜ እያለፈ መሆኑን እንረዳለን፤* እናም የሚያስከፍለን ዋጋ ምንም ይሁን ምን የተሻለ ነው ያልነውን ነገር ለማድረግ እንወስናለን። አንዳንዶች (በሥራ እንደተዋጠው ባል) በሥራቸው የተዋጡ ይሆናሉ፤ ሌሎች ደግሞ እንደ ትንግርት ባሉ ወይም በሚያዝናኑ ፕሮግራሞች





(ልምምዶች) ራሳቸውን ያጠምዳሉ። አሁንም ሌሎች ደግሞ ስለ ገንዘብ ዋስትና ወይም በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሥፍራ ይጨነቃሉ፣ ወይም ደግሞ ዕድሜን ወደ ኋላ ለመመለስ ሲሉ ቅጥ ባጣ ሁኔታ ይመገባሉ ወይም ለመዋብ ብለው ቀዶ ጥገና ያደርጋሉ። ሕይወት ሚዛኑን የጠበቀ አይሆንም። በዚህ ሂደት እግዚአብሔርን ወደ ጠርዝ ይገፉታል ይልቁንም በሕይወታችን ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ ባለመርጋታችን፣ ክርስቶስን ቀስ በቀስ በጥላ ውስጥ እናስቀምጠዋለን። ይህ በእናንተ ላይ እንዲሆንባችሁ አትፍቀዱ።

## ከትውልድ ወደትውልድ

ከባዶ ጐጆ ጋር በጥብቅ የተያያዘ እያንዳንዱ ወላጅ የሚገጥመው ሌላው ጉዳይ *ከአዋቂ ልጆቻችን ጋር ያለን ግንኙነት* ነው።

ለዚህ ጥያቄ ቀለል ያለ መልስ የለም፤ ልጆቻችን ባላቸው ፍላጐትና በማንነታቸው (ሰብዕና) የተለያዩ ናቸው (ልክ እንደ እኛ)። ወላጆች እነዚህን አዋቂ ልጆቻቸውን በተመለከተ ብዙ ጥበብና ፀሎት ያስፈልጋቸዋል። ልጆችም እንደዚሁ ከወላጆቻቸው ጋር በተዛመደ መልኩ ከወላጆቻቸው የሚማሩት ብዙ ነገር አለ።

ማንኛውም ሁኔታ ልዩ ሆኖ ሳለ፣ ካደጉ ልጆቻችን ጋር ባለን ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ከሁለቱ ጽንፎች እንድንጠነቀቅ ይነግረናል። አንደኛ፣ ልጆቻችን አዋቂ ከሆኑ በኋላ ለመቆጣጠር የምናደርገውን ሙከራ ማስወገድ እንዳለብን ይነግረናል። አንዲት በቅርቡ ያገባች፣ "ወላጆቼ በኑሮአችን ውስጥ ባለማቋረጥ ጣልቃ እየገቡብን ነው፣ ጣልቃ እንዳይገቡብን ምን ልናደርግ እንችላለን?" በማለት ጽፋልኛለች።

ልጆች ራሳቸውን ሲችሉ (ጥገኝነትን ሲያቆሙ) ትልቅ የለውጥ ሽግግር ይሆናል። ከዚያ በኋላ በእኛ ሥልጣን ሥር አይደሉም። በተለይ ያህ ጉዳይ አንዴ ካገቡ እውነትነቱ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱሰ እንዲህ ይላል፣ "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል" (ዘፍ 2፥24) ከዚያ በኋላ የተለየ ቤተሰብ ይሆናሉ፣ እንደ ወላጆች እነሱን ለመቆጣጠርና በኑሮአቸው ውስጥ ያለብልሃት ጣልቃ ለመግባት መሞከራችንን ማስወገድ አለብን። ሳያገቡ የተቀመጡ ወይም በፍቺ ምክንያት በጉዳት ውስጥ ያለፉ ልጆች ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ይህ ማለት ግን ካገቡ በኋላ

እንረዳቸውም ወይም እንመክራቸውም ማለት አይደለም - በጭራሽ:: ነገር ግን እደረሬጋችን በጥበብ ይሁን::

ሌላው ጽንፍ ያደገ ልጆቻችንን ችላ ማለታችን ነው:: አንድ ሰው እንዲህ ብሎኛል፣ "ልጆቻችን ብዙ መከራ አሳይተውናል፣ ከዚህ በኋላ እስከመቼውም ባላያቸው ግድየለኝም::" ይህ ሰው የተናገራቸው ቃላት በጣም ሸካራ ነበሩ፣ በብዙ መታገሥ ተነጋግረን ስለ ልጆቹ እንዳልሆነ አረጋግጨአለሁ - ነገር ግን እንዳንድ ወላጆች ይህን ያደርጋሉ:: ሌሎች ደግሞ ዝም ብለው ከልጆቻቸው ይርቃሉ ወይም ይለያሉ:: እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ የቤተሰብን ቁርኝት ማላላት ብቻ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ረገድ ልናበረታታቸውና ልንረዳቸው የምንችልበትን ዕድል እናጣለን::

ይህ ሁኔታ በተለይ እውነትነቱ እየተገለጠ የሚመጣው ልጆቻችን የራሳቸው ልጆች በሚኖራቸው ጊዜ ነው:: አሥራ ዘጠኝ የልጅ ልጆቻችን (አሁን ደግሞ የልጅ ልጅ ልጃችን) ለኛ ለዓመታት ደስታን ሰጥተውናል፣ ይህን ሳስብ ልቤ ግንኙነታቸው በቦታ ርቀት ወይንም ደግሞ በፍቺ ምክንያት የተቋረጠባቸውን እያት ወላጆች ያሰባል:: የልጅ ልጆች ዝም ብሎ ልዩ መብት (ችሮታ) አይደሉም - ኃላፊነትን የሚጠይቁ ናቸው:: የልጅ ልጆቻችሁ ስለ እናንተ ምን ያስተውላሉ? አብራችሁ ያሳለፋችሁትን የደስታና የፈንጠዝያ ጊዜ ብቻ ነው የሚያስታውሱት? ወይንስ ለክርስቶስ ያላችሁን ፍቅርና ደስታችሁን ያስታውሳሉ?

እግዚአብሔር የልጅ ልጆች ቢሰጣችሁ ሳታቋርጡ ፀልዩላቸው:: እንዲሁም ለክርስቶስ መኖር ይችሉ ዘንድ የምትችሉትን ሁሉ በማድረግ አበረታቱአቸው:: ግንኙነታችሁንም አታቋርጡ፤ ለወላጆቻቸው ስትደውሉ እነሱንም አነጋግሩአቸው:: በበዓላት ቀናት ብቻ ሳይሆን በሌላ ጊዜም ካርድና ደብዳቤ ላኩላቸው (ወደ ኃላዬ መለስ ብዬ ሳስበው፣ ምነው እንደዚያ ለማድረግ ታማኝ በነበርኩ ብዬ እላለሁ::) ከሁሉም በላይ ምሳሌ ሁኑአቸው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለመጋቢዎች የጻፈው መልዕክት አያት ወላጆችንም የሚመለከት ነው:: "በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ" (ቲቶ 2፥7)::





## በወላጆቻችን ዕድሜ ስንሆን

ዕድሜ እየገፋ ሲመጣ፣ ሌላ ነገር ደግሞ ይገጥመናል፤ እሱም በሽምግልና ያሉ የወላጆቻችን ጉዳይ ነው:: በአንድ ወቅት እነሱ ለኛ ጥንቃቄ ያደርጉልን ይንከባከቡንም ነበር:: አሁን ደግሞ እኛ በተራችን እነሱን ልንከባከባቸው የሚገባ ይሆናል:: ከዐሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ እንዲህ ይላል፣ "አባትህንና እናትህን አክብር" (ዘፀ 20፥12) - ይህም እስከ ዕድሜ ልክ ነው:: ይህንን ትዕዛዝ ከምናከብርበት አንዱ መንገድ በእርጅናቸው ወቅት እንክብካቤና እርዳታ በማድረግ ነው:: ነገሩ ቀላል ላይሆን ይችላል:: ጥበብንና ትልቅ አዘኔታን የሚጠይቅ አስቸጋሪ ውሳኔ ያለበት ነው:: ወንድሜና እህቶቼ አሮጊት እናታችንን ከነበረችበት አሮጌ ቤት ወደ አፓርታማ "ይመቻታል" ብለው ሲያዛውሯት አስታውሳለሁ:: ከእኛ ጋር መሆንዋ ሁኔታዋን የተሻለ ያደርግላታል ብለን ነበር፣ ነገር ግን ወዲያውኑ የበለጠ ደስተኛ መሆን የምትችለው በራሷ አሮጌ ቤት ውስጥ መሆኑን ስለተረዳን ከምስጋና ጋር ወደ ቤቷ መልሰናት ልትረዳት የምትችል ሞግዚት አደረግንላት::

እግዚአብሔር በእርጅና ውስጥ ላሉ ወላጆቻችሁ ኃላፊነት ከሰጣችሁ፣ ለእነሱ ምርጥ የሆነው ምን እንደሆነ እሹ እንጂ ለእናንተ የበለጠ ምቹ የሆነውን አይደለም:: ግንኙነታችሁን አታቋርጡ! ብዙውን ጊዜ ደረጁ ሰዎችን የመኖሪያ ማዕከል በምጎበኝበት ወቅት ተንከባካቢዎቻቸው አንዳንድ በልጆቻቸው የተረሱትን ወላጆች ስላምታ እንዳቀርብላቸው ይጠይቁኛል:: "እንዲያው እንደምን ናችሁ ቢሉአቸው እንኳን በቂ ነበር፣ ቤተሰቦቻቸው በፍጹም አይጎበኙአቸውም" ይሉኛል:: ይህ ያሳዝናል! ወርቃማውን ትዕዛዝ (መመሪያ) ተግባራዊ ማድረግና መታዘዝ ካለብን ያረጁ ወላጆቻችንን መንከባከብን ይጨምራል::

## ጡረታ - አዲስ ጅማሬ

እግዚአብሔር እንድንሠራ ይፈልጋል (በቤታችንም ሆነ በሥራ ቦታ ማለት ነው)፣ ነገር ግን ጡረታ መውጣት ማለት ስህተት ነው ማለት አይደለም:: ሌዋውያን (እሥራኤልን በአምልኮ የመሩ) በአምሣ ዓመታቸው ጡረታ እንዲወጡ ታዘዋል (ዘኁ 8፥24-26)፣ ሙሴም ባረጀ ጊዜ በገላጣ መሬት ላይ ቆሞ "እኔ ዛሬ መቶ ሃያ ዓመት ሆኖኛል፣ ከዚህ በኋላ እወጣና እገባ ዘንድ አልችልም" በማለት አሳውቋል (ዘዳ 3፥12)::

የእርጅና ዕድሜ፣ ሰይጣን ከሕይወት ጉዞ ለመነጠል የመጨረሻ ዕድሉን የሚጠቀምበት ጊዜ ነው። እንደሚሞክርም እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ። ስለ ጤንነታችን ሁኔታ፣ ስለ ገንዘብ ችግር፣ ስለ ብቸኝነት፣ ወይም ስለ ሌሎች ስለተለያዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችን አንጨነቅም ማለት አንችልም። ራሳችንን መቻል ውልቅ ብሎ ሲወጣ ወይም እቅመቢስነታችን ሲባባስ ተስፋ መቁረጣችን የግድ ነው። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሐር ራሱ ትቶናል ብለን እንገረማለን።

ነገር ግን እግዚአብሔር አልተወንም። የኢየሱስ የተስፋ ቃል ልክ በሌሎች የዕድሜ ደረጃዎች እውነት እንደነበረ ሁሉ በእርጅና ዘመናችንም እውነት ነው፣ "እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ 28፥20) ብሎናል። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ በእግዚብሔር ዓይን፣ "ረዥም ዕድሜ የቅኖች ሽልማት ነው፣ ሽበትም የክብር ዘውድ ነው" (ምሳሌ 16፥31) ይላል። ባሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ከምንጊዜም በበለጠ ከእኔ ጋር እንደሆነ እንደሚሰማኝ በታማኝነት ልነግራችሁ እወዳለሁ። ይህ ለእናንተም እውነት ሊሆን ይችላል። ከዚህ በፊት መሥራት የምትችሉትን ነገር አሁን መሥራት አትችሉም - ነገር ግን አንድ ነገር መሥራት ትችላላችሁ። እግዚአብሔር አሁንም ሌሎችን ለመባረክ እናንተን ይጠቀማል። ይልቁንም፣ ብስጩ ወይም ቁጡ ከመሆን፣ በእርጅና ዘመናችሁ ክርስቶስን በሕይወታችሁ ማንፀባረቅ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ለምኑት።

የፀሎት ጊዜ መድቡ። አንድ ክርስቲያን ጓደኛዬ ከመሞቱ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ድምፁን እያወጣ መፀለይ እንዳቃተው ሲረዳ፣ በውስጡ በመቃተት መጸለዩን ቀጠለ፣ ይህም ሲያቅተው ከንፈሮቹን በማንቀሳቀስ ቀጠለ፣ ከንፈሮቹ ሲደክሙበት በፀጥታ ሆኖ በአዕምሮ መፀለዩን አላቆመም ነበር። ሌላው ጓደኛዬ ደግሞ የብዙ የወንጌል መልዕክተኞች ስም ዝርዝር ነበረው ለብዙ ዓመታትም ለነዚህ መልዕክተኞች ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ስማቸውን እየጠራ ይፀልይላቸው ነበር። በጣም አርጅቶ ሳለም ከነዚህ የወንጌል መልዕክተኞች አገልግሎት ጐን እንደሆነ ያውቅ ነበር።





## በጉዞ እቅጣጫው መዝለቅ

ራሳችንን ለእግዚአብሔር ስጥተን ከሆነ፣ የዕድሜአችን የመጨረሻ ዓመታት በጣም ስኬታማ የምንሆንባቸው ሲሆኑ ይችላሉ። ግን እንዴት ነው በአቅጣጫው መቀጠል የምንችለው?

*የመጀመሪያው ደረጃ፣ ሊገጥመን ለሚችል አደጋ ንቁ መሆን ነው።* ምናልባት "አስቀድሞ የተጠነቀቀ አስቀድሞ የታጠቀ ነው" የሚል ብሂል ሰምታችሁ ይሆናል። እናም እውነት ነው። መንፈሳዊ አደጋን መቋቋም የሚገባው ከመሆኑ (ከመድረሱ) በፊት ነው። ንጉስ ዳዊት በመካከለኛ የዕድሜ ዘመኑ ካጋጠመው ፈተና ራሱን ቢጠብቅ ኖሮ ሕይወቱ ምንኛ አስደሳችና ልዩ በሆነ ነበር። ይልቁንም፣ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ፣ በአመንዝራነት፣ በነፍስ ገዳይነት ምክንያት ሕይወቱ ቁልቁል ወረደበት፤ የልብ ስብራትም ደረሰበት (2ሳሙ 11-12)። ነገር ግን የሠራውን ኃጢአት ተናዞ ንስሃ ሲገባ እግዚአብሔር ምሕረት አደረገለት፤ ይሁን እንጂ ጥፋት ስለተፈፀመ ተሰሚነቱ ወይም ምሳሌነቱ እንደ ቀድሞው አልሆነለትም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከርሱ ነውና" ይላል (ምሳሌ 4፥23)።

*ሁለተኛ፣ ለክርስቶስ የገባችሁትን ቃል አጠንክሩ።* የእርጅና ዘመን ማዕበል ከሕይወት ጉዞ እቅጣጫ ሲያስወጣችሁ እስኪያስፈራራችሁ ድረስ አትጠብቁት። እምነታችሁን የምታጠነክሩበት ጊዜው አሁን ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት ከጠነከረ፣ የሰይጣንን ፈተና መከላከያችንም ጠንካራ ይሆናል። ሰይጣን ሁልጊዜ፣ አሁንም ቢሆን፣ ሊማርከን ይሞክራል፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንድንቋቋመው ይረዳናል። "ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ እንደሚሄድ" መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ምሳሌ 10፥9)።

*በተጨማሪ፣ ማንኛውንም ሁኔታ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትን ተማሩ፣ ስለውጤቱም በርሱ እመኑ።* በምንም ዓይነት ችግር ውስጥ ብትሆኑ ወይም ኑሮአችሁ የተረጋጋ ባይሆን እግዚአብሔር ለናንተ ያለው ፍቅር አይለወጥም። በርሱ ዘንድ ድንገተኛ (የማይታወቅ) ነገር የለም፣ እርሱ መልካሙን ሁሉ እንደሚያደርግ ሊታመን ይገባዋል። ይልቁንም፣ ፍራቻና ጭንቀት ሽባ እንዳያደርጉአችሁ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሐር አሳልፋችሁ መስጠትን ተማሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "ጌታ

እግዚአብሔር የዘላለም አምባ ነውና ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ" (ኢሳ 26፥4)::

*በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር በናንተና በሌሎች መካከል የመሠረተውን ግንኙነት አጠንክሩ::* ከትዳር አጋሮቻችሁ፣ ከልጆቻችሁ፣ ከጓደኞቻችሁና ከአማኞች ጋር ግንኙነታችሁን አጠንክሩ:: ከሰው ስንገለል ወይም ማንም አያስፈልገንም ብለን የምናስብ ከሆነ በሚያጋጥመን ፈተና የምንጐዳና የምናመቻምች እንሆናለን:: ሰይጣን በኢየሱስ ላይ የከረረ የጥቃት ሙከራ ያደረገው ብቻውን በሆነ ጊዜ ነበር (በምድረ በዳና በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ):: እንደ እግዚብሔር ሀሳብ የሆነ ግንኙነት ለሌሎች ኃላፊነት እንዲሰማንና ሕይወታችን በደስታ እንዲሞላ ያደርጋል:: እውነተኛ ደስተኛ የሆነ ክርስቲያንን ሰይጣን ሲያሸንፍ አላየሁም::

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሞት በተቃረበ ጊዜ፣ ምንም ነገር አልነበረውም:: በእምነቱ ምክንያት በሮም እስር ቤት ውስጥ ተጥሎ ሳለ በሰውነቱ ላይ የሚደርበው ካባ እንኳን አልነበረውም:: መጪውን ክረምት የሚቋቋምበት ምንም ልብስ አልነበረውም:: ወዳጆቹ ሁሉ ትተውት ወይንም ደግሞ ወደ ሌላ ሥፍራ ሔደው ነበር:: ሉቃስ ብቻ አብሮት ነበር:: በዓለም መስኪያ (ሚዛን) ሕይወቱ በውድቀት የተደመደመ ነበር::

በእግዚአብሔር መስኪያ ሲመዘን ግን በውድቀት አልተደመደመም:: ክርስቶስ ጳውሎስን ደቀመዝሙር እንዲሆን ጠራው:: ጳውሎስም ለጥሪው ታማኝ ነበረ:: ክርስቲያን ከሆነ በኋላ በመከራና በፈተና ያለፈበትን ወደ ኋላ መለስ ብሎ ከተመለከተ በኋላ በእርግጠኛነት፣ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፣ ኃይማኖቴን ጠብቄአለሁ" (2ኛ ጢሞ 4፥7) ለማለት በቅቷል::

ጳውሎስ ፍፃሜውን አሳመረ:: እናንተስ?





# ሰባሳ

## ያሸበረቀ ተስፋችን

*ዕንባን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ይጠርጋል:: ሞት ወይም ሀዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፤ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች ሥርዓት አልፏል::*

(ራዕይ 21፥4)

ሕይወት አስቸጋሪ ናት፤ እግዚአብሔር ግን መልካም ነው፤ መንግሥተ ሰማይም እውን ነው::

ማንም ሰው ቢሆን ስለመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ጥርጣሬ አይኖረውም:: እውነት ነው ሕይወት አስቸጋሪ ናት:: ይህን ምዕራፍ ስጽፍ አዕምሮዬ አብዛኛውን ጊዜ በአሜሪካ ደቡባዊ ክፍል የተነሳው ዐውሎ ንፋስ ባስከተለው የሞት አደጋና ጥፋት ተይዞ ነበር:: ከጥቂት ወራት በፊት ልክ ደቡባዊ እስያን እንዳወደመው እንደ "ሱናሚ" ነውጥ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከቤታቸው ተፈናቅለዋል፣ የት እንደሚደርሱ እንኳን ሳይወጥኑ በለበሷት ልብስ ብቻ ተሰደዋል:: አንድ በሺህዎች ጊዜ ሊባዛ የሚችል የአንድ ቤተሰብ ታሪክ ልሰ:: ይህ ቤተሰብ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በረግረጋማና ፍርስራሽ በሞላበት ወንዝ እየወደቀና እየተነሳ ከብዙ ጉዳትና ጉስቁልና በኋላ መጥቶ በአቅራቢያችን ያለች ቤተክርስቲያን የተቀበለችው ቤተሰብ ነበር:: ታሪኩ አሳዛኝ ነበር:: የኋላ ኋላ አደጋው የደረሰበት አካባቢ ተመልሶ የሚገነባ፣ "ካትሪና" የተባለው ዐውሎ ንፋስም ከትዝታችን የሚደበዝዝ ቢሆንም፣ ሕይወት ለአደጋው ሰለባዎች ግን አሁንም አስቸጋሪ ናት፣ በጣም አስቸጋሪ ናት::

ምናልባት አብዛኛዎቻችን እንደዚህ ዓይነት ከባድ አደጋ በፍጹም ደርሶብን አያውቅም - ነገር ግን እኛም ሕይወት አስቸጋሪ መሆኗን እናውቃለን:: አንዳንድ ጊዜ ሻከራነቷ ሳናስበው በድንገትና ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይመጣብናል፤ አንዳንድ ጊዜም የደረሰብን ችግር በአብዛኛው የሕይወት ዘመናችን አብሮን ያቆያል:: በዚህ መጽሐፍ አንዳንድ የልብ ስብራትና የትግል ሁኔታዎች

## ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር እንሆናለን

*እንደኛ፣ በመንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል::* መንግሥተ ሰማይ ብዙ ነገር ነው - ከሁሉም በላይ ዋናው ነገር የእግዚአብሔር መኖሪያ ሥፍራ መሆኑ ነው:: እግዚአብሔር የሚኖርበት ሥፍራ ነው! እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ መሆኑ እውነት ነው፤ ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ ከሁሉም ቦታ የበለጠ ነው:: ፍፁም ልዩ የሆነ ሥፍረታዊ መኖሪያ ሲሆን እግዚአብሔር በመሃሉ፣ ክርስቶስ በቀኙ በኩል ሆኖ አለ:: መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን" ይላል (1ተሰ 4፥17)::

ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም አብረን እንሆናለን! የሚለውን እስቲ አስቡት:: ከርሱ ጋር ስለምንሆን ከክፉ ሁሉ ፍጹም የተጠበቅን እንሆናለን:: ትካዜና ሥቃይ በፍፁም አያገኙንም - በፍፁም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ምንባቦች ውስጥ በጣም ስሜት የሚነካ ክፍል በዮሐንስ ራዕይ ከመጨረሻው ምዕራፍ በፊት የሚገኝ ነው፣ "ታላቅም ድምጽ ከሰማይ፣ እነሆ፣ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፣ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፣ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ" (ራዕ 21፥3-4)::

## በመጨረሻም ወደ ቤታችን እንገባለን

*ይህ ስለ መንግሥተ ሰማይ ወደ ሁለተኛው ታላቅ እውነት ይመራናል፣ በቤታችን እንሆናለን::* "ቤት" የሚለው ቃል ትርጉሙ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር ነው:: አንድ ወጣት፣ በልጅነት ዘመኑ የደረሰበትን ሁከትና ጉስቁልና እያስታወሰ "በጭራሽ ወደ ቤቴ አልመለስም" ብሎኛል:: እያይዞም፣ "ነገር ግን ለልጆቼ የተለየ እንዲሆንላቸው እፈልጋለሁ፣ እውነተኛ ቤት እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ" ብሎኛል:: ምንም እንኳን ዕድሉን ባያገኝም፣ ቤት የሰላምና የደስታ ቦታ መሆኑን ያውቅ ነበር::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ይህ ዓለም የእኛ የመጨረሻ ቤታችን እንዳልሆነ ይናገራል:: ነገር ግን አንድ መኖሪያ አለን፣ እርሱም





መንግሥተ ሰማይ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ "በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች" እንደሆንን ተጽፏል (ዕብ 11፥13):: እንዲሁም "አገራችን በሰማይ ነው" ተብሎናል (ፊልጵ 3፥20):: የልባችን ጩኸት ልክ ሐዋርያ ጳውሎስ እንደተናገረው ነው፣ "ከዚህ እንደ መኖሪያችን ከሆነው ሥጋችን ተለይተን ከጌታ ጋር መሆን እንመኛለን" (2ቆሮ 5፥8)::

በአካባቢዬ የሚታተም አንድ ጋዜጣ "በዜና ዕረፍት" ዐምዱ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ "ሟች እገሌ/ እገሊት ወደ ሰማያዊ ቤቱ/ቷ ሄደ/ች" እያለ ይጽፋል:: ይህን ዐምድ ሳይ ሁል ጊዜ "ሟች ክርስቲያን መሆን አለበት/አለባት" እላለሁ::

ቤት የደስታና የሰላም ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው:: ቤት የዕረፍትና የሚያስደስት ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው:: ቤት የፍቅርና የደህንነት ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ "ወደ ሰላም ይገባል፤ በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል" ይላል (ኢሳ 57፥2):: በክርስቶስ ሆነን ስንሞት፣ ከርሱ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ለዘለዓለም እንኖራለን::

አንዳንድ ሰዎች፣ "ደህና፣ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ የምፈልግ ለመሆኔ እርግጠኛ አይደለሁም:: በጣም አሰልቺ ይመስለኛል" ይሉኛል:: ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይ መሰልቸት የሚባል ነገር የለም፣ የእግዚአብሔርን የክብሩን ባለጠግነት ለማወቅ ዘላለምነትን እናገኛለን:: መጽሐፍ ቅዱስም፣ እግዚአብሔር የምንሠራውን ሥራ እንደሚሰጠን፣ እርሱን እንደምናገለግለው፣ ከርሱም ጋር እንደምንነግሥና ያለ ድካም እንደምናመልከው ይናገራል (ራዕ 22፥3፣5)::

## ለዘለዓለም እንለወጣለን

*በተጨማሪ፣ በመንግሥተ ሰማይ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደምንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል::* ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል እግዚአብሔር ያቀደው ዕቅድ አንድ ቀን ይጠናቀቃል፣ "የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን" (1ቆሮ 15፥51-52)::

ይመጣል አሉአቸው" (የሐዋ ሥራ 1፥11)። ኢየሱስም፣ "ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፣ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና" (ማቴ 24፥44) በማለት አስጠንቅቋል።

የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ከሌላው ተገቢ ከሆነው እውነታ ተለይቶ ሊታይ የሚችል አይደለም፣ ያም የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚኖር የተናገረው ቃል ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል። አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ አረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል" (ማቴ 25፥31-32)። የእግዚአብሔርን የድነት ነፃ ስጦታ የታቃወሙ ወደ "ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ" (ማቴ 25፥46) በማለት አስጠንቅቋል። ጳውሎስ በአቴንስ ለነበሩ አረማውያን ፈላስፎች፣ እግዚአብሔር "ቀን ቀጥሮአልና፣ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል" በማለት አሳውቆአቸዋል (የሐዋ ሥራ 17፥31) የእግዚአብሔር ፍርድ በተገለጸላቸው ጊዜ የሰጡት ምላሽ አሁን ባለንበትም ዘመን ብዙዎች ከሚሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ "የሙታንንም ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ አኩሌቶች አፌዙበት፣ አኩሌቶቹ ግን ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን አሉት" (የሐዋ ሥራ 17፥32)።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ብንንቅ በአደጋ ውስጥ መሆናችንን ያመለክታል። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ስለተፈፀመው ግፍና ክፋት ተጠያቂ በሆኑት ላይ ይፈርድባቸዋል። እግዚአብሔርን የናቁና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያዘጋጀውን ድነት ያንቋሸሹ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ በእነሱ ላይ ይሆናል። ልክ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፍርድ እውን እንደሆነ፣ የቅጣት ቦታውም መጽሐፍ ቅዱስ ገሃነም (ሲኦል) ብሎ የሚጠራው እውን ነው። በኢየሱስ ያመኑ ሁሉ የዘላለም መኖሪያቸው መንግሥተ ሰማይ (ገነት) እንደሆነ ሁሉ፣ በክርስቶስ በኩል የሚገኘውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የናቁ ሁሉ የመጨረሻ መድረሻቸው ሲኦል ነው። ይህ ከበድ ያለና ተገቢ የሆነ እውነት ነው። የአንድ ሴሚናሪዩም ፕሮፌሰር አንድ ጊዜ ለተማሪዎቹ፣ "ስለ ሲኦል ስትሰብኩ ካለ እንባ ባትሰብኩ ይሻላችኋል" ብሏቸዋል። አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች በሚጽፉልኝ ደብዳቤ





ሲኦልን በጉጉት እንደሚጠባበቁ ይነግሩኛል፣ ምክንያታቸው፣ "ሁሉም ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው እዚያ ስለሚገኙና ስለሚሆኑ ነው" ይላሉ። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል ፍፁም የተለየ ነው። ሲኦል ፍጹም የብቸኝነትና የተስፋ መቁረጥ ሥፍራ እንደሆነ ይነግረናል፣ "የጨለማ፣ የልቅሶና ጥርስ የማፋጨት ሥፍራ" እንደሆነ ይገልጽልናል (ማቴ 25፥30)። ከሁሉም በላይ፣ ሲኦል ከእግዚአብሔር መለየት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሲኦል ከተፃፉ ቃላት ወደ ሲዖል እንድንሄድ የሚያበረታታ አንድም ቃል የለም።

የምሥራቹ ቃል ወደ ሲኦል መሄድ እንደሌለብን የሚያሳስብ ነው! ክርስቶስ የማምለጫ መንገድ ሰጥቶናል - እናም ምክንያቱ እንዳየነው እርሱ በእኛ ፈንታ የሲኦልን (የገሃነምን) ሥቃይና ብቸኝነት ስለተቋቋመ ነው። የእግዚአብሔር ተስፋ እውነት ነው፤ "እንግዲህ፣ በክርስቶስ፣ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም" (ሮሜ 8፥1)። በዘለዓለማዊ ዕጣ ፈንታችሁ አትቆምሩበት። ነገር ግን ራሳችሁን ለክርስቶስ መስጠታችሁን ዛሬውኑ አረጋግጡ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዐት ጊዜ ስለሚፈጸሙ አንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች አይስማሙም - ዳሩ ግን፣ አንድ ነገር እርግጠኛ ነው፤ በዘመኑ ፍጻሜ፣ ክርስቶስ መንግሥቱን ሊመሠርት ዳግመኛ ይመጣል። አንድ ቀን እግዚአብሔር የገባው ተስፋ ቃል በርግጥ ይፈፀማል፤ "እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ!" (ራዕ 21፥5)። ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ በተደጋጋሚ ቃል ገብቷል። የሚመጣው የማይታወቅ ሆኖ አይደለም፣ የቤተልሔሙ ተራ ሰው ሆኖም አይደለም፣ በጨለማም አይደለም፤ የሚመጣው በክብርና በኃይል በዓለም ሁሉ ላይ በግልጽ ነው። ይህን መጽሐፍ ቅዱስ፣ "የተባረከው ተስፋችን - እርሱም የታላቁ አምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ" ብሎ ቢጠራ አያስገርምም (ቲቶ 2፥13)። እናቴ ባረጀች ጊዜ፣ ሁልጊዜ ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነቃ፣ "ይህ ቀን ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን ቢሆን ያስደንቀኛል?" ብላ ራስዋን ሳትጠይቅ ከቶ ከመኝታዋ አትነሳም ነበር። የሁላችንም የዘወትር ቋሚ ፀሎት በራዕይ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለው መሆን አለበት፤ "አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" (ራዕ 22፥20)።

## እስከዚያ ድረስ

*መንግሥተ ሰማይ እውን ነው - ነገር ግን ይኼ በአሁኑ* ሰዓት በክርስቲያኖች ላይ ምን ልዩነት ያመጣል? ክርስቲያኖች ስለ መንግሥተ ሰማይ ብቻ የሚያልሙ (የሚያስቡ) እንጂ በምድር ላይ የሚያስፈልገው መልካምነት የማያገናቸው ናቸው የሚባለው የጥንት ዘመን ቀልድ እውነት ነው? በርግጥ አይደለም - እውነቱ በተቃራኒው ነው።

*እንደኛ፣ መንግሥተ ሰማይ እውን ስለሆነ፣ ተስፋ ያለን ነን፤* ለወደፊቱ ተስፋ አለን፤ አሁን ላለንበት ኑሮአችንም ተስፋ አለን። በአሁኑ የምድር ኑሮአችን ምንም ይሁን ምን ቢገጥመን፣ ለዘለዓለም አብሮን እንደማይቀጥል እናውቃለን፣ ከፊት ለፊታችን የመንግሥተ ሰማይ ሰላምና ደስታ አለ። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ፣ "ሕይወት አስቸጋሪ ናት፣ እግዚአብሔር ግን መልካም ነው፤ መንግሥተ ሰማይም እውን ነው" ብዬአለሁ። ይህን ያልኩት እንደ ባልንጀራዬ የሆነ ሐኪም ወደርሱ ለሚመጡ ክርስቲያን ተካሚዎች የሚነግራቸውን ጠቅሼ ነው። ምክንያቱም በወቅታዊ ችግሮቻችን እንዴት በቀላሉ ልንጠመድ እንደምንችልና የእግዚአብሔርን የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ እንደምንረሳ ስሚያውቅ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስ፣ "በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ለዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ከሆነ፣ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የሚታዘንልን መሆናችን ነዋ!" ብሏል (1ቆሮ 15፥19)። ነገር ግን የኛ ተስፋ በዚህ ምድር ሕይወት ብቻ አያበቃም! በሕይወት ማዕበል መሃል ብንሆን፣ እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማይ ሊያወርሰን የገባልን ተስፋችን "እንደ ነፍስ መልሕቅ ነው፣ እርሱም እርግጥና ጽኑ ነው" (ዕብ 6፥19)።

*በተጨማሪ፣ መንግሥተ ሰማይ እውን ስለሆነ፣ የአሁኑ የምድር ኑሮአችን ትርጉምና ዓላማ አለው። የመክብብ መጽሐፍ* ጸሐፊ፣ ወደ እግዚአብሔር ከመመለሱ በፊት፣ "ሁሉም ነገር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው" በማለት ደምድሞ ነበር (መክ 1፥2)። ብዙዎች ዛሬም በተመሣሣይ መልኩ እንደዚሁ ዓይነት መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ። ነገር ግን ክርስቶስን ስናውቅ፣ ሕይወት ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ እንዳልሆነች እናውቃለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ሲያስቀምጠን (ሲያኖረን) የራሱ ምክንያት አለው። እያንዳንዱ የሚጨመርልን ቀን የእግዚአብሐር ስጦታ ነው፤ እንድንወደውና እንድናገለግለው የተሰጠን ተጨማሪ ዕድል ነው።





ይህን ሕይወት መንግሥተ ሰማይ አያቀለውም፤ ግን የበለጠ አስፈላጊ ያደርገዋል።

*ይህ መንግሥተ ሰማይ ወደሚያመጣው የመጨረሻ ልዩነት ይመራናል፤ መንግሥተ ሰማይ እውን ስለሆነ እያንዳንዱን ጊዜ ለኢየሱስ ክርስቶስ መኖር አለብን።* የምድር ኑሮአችን በጣም አጭር ነው፤ ማናችንም ብንሆን ለምን ያህል ጊዜ እንደምንኖር አናውቅም። እያንዳንዱን ቀን በምድር ላይ እንደ የመጨረሻው ቀናችን እንደሆነ በማሰብ እንኑር - አንድ ቀን የመጨረሻ መሆኑ አይቀርም። ሐዋርያ ጴጥሮስ፣ "እንግዲህ ሁሉ ነገር በዚህ ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ፣ ታዲያ እናንተ በቅድስናና በመንፈሳዊ ኑሮ መኖር እንዴት አይገባችሁም? እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት የምትጠባበቁና በቶሎም እንዲመጣ የምትሠሩ ሁኑ። በዚያ ቀን ሰማይ በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል፣ ፍጥረትም በእሳት ግለት ይቀልጣል" (2ጴጥ 3፥11-12)። ለክርስቶስ መኖር ከፈለጋችሁ፣ ጊዜው አሁን ነው።

*ግባችሁ መንግሥተ ሰማይ ነው? ወደዚያ ለመሄድ በናፍቆት* እየተጠባበቃችሁ ነው? እኔ እየናፈቅሁ ነኝ፣ ለእናንተም እፀልያለሁ። እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀው የወደፊት ሕይወት ምንኛ አስደናቂና የከበረ ነው!

የዚህ ዓለም ሸክምና መከራው ከዚህ ሕይወት እንዳያደናቅፋችሁ ወይም ተስፋ እንዳያስቆርጣችሁ ተጠንቀቁ። ነገር ግን ዓይናችሁ እግዚአብሔር በጉዞ መጨረሻ ላይ ሊሰጥ በገባው ተስፋ (እርሱም መንግሥተ ሰማይ ነው) ላይ የፀና ይሁን።

> "ስለዚህም አንታክትም፣ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው" (2ቆሮ 4፥16-18)።

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስላለን ተስፋ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን!

## የቢሊግራሃም

## የመጨረሻ መልዕክት

አንድ ቀን የሕይወት ጉዞአችሁ ያበቃል፤ ወደ ዘለዓለማዊነትም ትሸጋገራላችሁ፡፡ ነገር ግን የሕይወት ጉዞአችሁ ፍፃሜ ምን ዓይነት ይሆን? በሕይወታችሁ ፍፃሜ፣ የተጓዛችሁት በስህተት መንገድ ላይ እንደሆነና ዕድሉ እንዳመለጠ በመገንዘብ በሀዘንና በፀፀት መለስ ብላችሁ ትመለከቱ ይሆን? ወይስ ምናልባት የተጓዛችሁት መንገድ ትክክለኛ መንገድ ሆኖ፤ ነገር ግን ባጋጠማችሁ በዚህ ዓለም ፈተናና ችግር ተተብትባችሁ ወደኋላ እንዲያስቀራችሁና ወደሙሉ ብቃት እንዳትደርሱ ሆናችሁ ይሆን? ይልቁንም፣ ፀሎቴ በሕይወታችሁ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንድትሆኑ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ የጉዞአችሁ ፍፃሜ በደስታ የሚጠናቀቅ እንዲሆን እፀልያለሁ፡፡ የእግዚብሔርን ሀልውና በሁሉም አቅጣጫ እንድታውቁና በኑሮአችሁ መሃል የሚያጋጥማችሁ ጥልቅ በሆነ ችግር ውስጥ ስታልፉ በርሱ እንድትበረቱ ፀሎቴ ነው፡፡

አንተ እና እኔ አሁን አብረን ለመቀመጥና ለመነጋገር ብንችል ኖሮ፣ እስካሁን ስላደረከው ጉዞ በሰማሁ ነበር፡፡ ጉዞህ በየትኛው መንገድ ነው? እግዚአብሔር ባዘጋጀልህ በትክክለኛው መንገድ ነው? ወይስ አሁንም ኢየሱስ "ሰፊው መንገድ" ብሎ በገለፀው - የሚያባብልና ቀላል የሆነ ግን በመጨረሻ ባዶነትን፣ ሀዘንና ሞትን የሚያተርፍ መንገድ - ላይ ነህ?

የትኛውን መንገድ እንደምትከተሉ ለመወሰን ሰዓቱ አሁን ነው፡፡ እስካሁን ከቶ ያልወሰናችሁ ከሆነ፣ ዛሬ ወደ ክርስቶስ እንድትመለሱና በእምነት ወደ ሕይወታችሁ እንዲመጣ እንድትፈቅዱለት አጥብቄ እሳስባችኋለሁ፡፡ ማንም ብትሆኑ፣ ምንም አድርጋችሁ ቢሆን፣ እግዚአብሔር አሁንም ይወዳችኋል፣ ወደ አዲስ የሕይወት መንገድ መምጣት እንድትችሉ፣ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞቷል፣ ተነሥቷልም፡፡ የርሱ መንገድ ይኼ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ተስፋ ለናንተም ነው፣ "በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ 3፥16)፡፡ ዛሬውኑ ራሳችሁን ለክርስቶስ ስጡ፡፡





ከዚያም፣ ግባችሁ በየዕለቱ እርሱን መከተል ይሁን፡፡ በዚህ መጽሐፍ እንደተመለከትነው እግዚአብሐር በሕይወታችን በሚደርሱ ችግሮችና መከራዎች አማካይነት ራሳችንን እንድንፈትሽና ጉዞአችንን በድል እንድንፈጽም ሁሉን ነገር ሰጥቶናል፡፡ ሕይወታችሁን አታበላሹት፣ ከእግዚአብሔር ዕቅድ በወረደ ነገር ራሳችሁን አታጠላልፉ፡፡

አንድ ቀን የምድር ሕይወት ያበቃል፡፡ ያንን ቀን እኔ እናፍቃለሁ፤ ምክንያቱም ከዚህ ሕይወት በኋላ ያለው መንግሥተ ሰማይ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ እናንተም እንድትናፍቁ እፀልያለሁ፡፡ ነገር ግን እስከዚያ ቀን፣ እግዚአብሔር ወደርሱ እስከሚጠራችሁ ደረስ፣ ግባችሁን ለክርስቶስ ለመኖር አድርጉ፡፡

"ይህን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ፣ እንዲያስተምራችሁና በዚህ አስተማማኝ ባልሆነ ዓለም በእምነት እንድትኖሩ እንዲያደርጋችሁ እሻለሁ።"

ቢሊ ግራሃም



ቢሊ ግራሃም፣ ታዋቂ ፀሐፊ፣ ሰባኪና በታሪክ ከተዘገቡት ከማናቸውም የበለጠ ለብዙ ሰዎች ፊት ለፊት ወንጌልን የሰበኩ ወንጌላዊ ናቸው፣ በዚህ አገልግሎታቸው በዓለም ላይ ወደ ሁሉም አህጉራት ሄደው አገልግለዋል። አነሳሳሽና ቀስቃሽ የሆኑ ሥራዎቻቸው (ለምሳሌ መላዕክት፣ የደስታ ምስጢር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ተስፋ ለተጨነቀ ልብ፣ ዳግመኛ መወለድ) በሚሊዮኖች ተነበዋል።

ይህን ጉዞ የምትጓዙት ለአንዴ ብቻ ነው። ጉዞአችሁ ምን ዓይነት ይሆን?

ቢሊ ግራሃም

በዚህ በሚጠናቀቅ የሕይወት ጉዞ፣ እግዚአብሔር ለናንተ ያለው እቅድ ምን እንደሆነ እንድትፈልጉ ቢሊ ግራሃም ይጋብዟችኋል። በሕይወት ጉዞአችሁ በየትኛውም ደረጃ ላይ - በጅማሬ፣ በጉልምሳነት ወይም በማጠናቀቂያው ጫፍ - ብትሆኑ ሕይወት የተለያየ የመጓዣ መንገድ እንደምታቀርብላችሁ ተምራችኋል። በጉዞአችሁ ውሳኔ የሚጠይቁ መንታና መስቀለኛ መንገዶች ያጋጥሙአችኋል፣ በሕይወታችሁ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ውሳኔ የሚሹ ይሆናሉ። ትክክለኛውን ጎዳና የምትመርጡት እንዴት ነው? በጉዞአችሁ ከሚያጋጥሙአችሁ አይቀሬ ከሆኑ እንቅፋቶችና ስርጓጉጦች የምታፈገፍጉትስ እንዴት ነው?

ቢሊ ግራሃም፣ ብቻችንን አይደለንምና የምሥራች ይሉናል። እግዚአብሔር ለኛ ጎዳናውን ማጠፍ ብቻ ሳይሆን በመንገዳችን በሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ሊረዳንና ወደ ግቡ (ወደ ቤታችን) እንድንደርስ ሊመራን አብሮን ለመሆን ይፈልጋል።

ታዋቂው ፀሐፊና ወንጌላዊ፣ በዚህ መጽሐፋቸው በርኅራኄና በፍፁም ግልጽነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ከተጓዙ ሰዎች ብቻ የሚገኝ ግንዛቤ እየሰጡን ደረጃ በደረጃ ይመሩናል። እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ዓላማና ኢየሱስ የሠራልንን እንማራለን። ፈተናዎችን አፍራሽ ልማዶችንና የሕይወት ቅይማቶችን (መከፋቶችን) እንዴት እንደምናስተናግዳቸው እንገነዘባለን። እንዲሁም ትክክለኛ ውሳኔ በማድረግ፣ ጋብቻችንን ለማጠናከር፣ እና በጉዞአችን ለሚገጥመን ህመም፣ ሥቃይና ሀዘን፣ በፀሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበትን ተሞክሯዊ ምክር ይሰጠናል።

ይህ የቢሊ ግራሃም ሥራ፣ በብዙ በግል ሕይወታቸው ልምዶች የተሞላ መጽሐፍ ሲሆን፣ የሚልቀውን ለሚፈልግ ለማንም፣ ጥበብ፣ ማበረታቻ፣ ተስፋና መነሳሳት ይሰጣል . . .

የማይደገም ጉዞ።

Printed by Africa Printing P.L.C

ዋጋ ብር 35.00